# መጽሐፈ መዝሙር

## መግቢያ

### አሰያየሙ

"መዝሙራት" እንዲሁም "መጽሐፈ መዝሙር" የሚሉት ስያሜዎች የተወሰዱት ከሰኘቱዋጊንት (ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ከተመለሰው ትርጉም) ላይ ሲሆን፣ እነዚህ ስያሜዎች በመጀመሪያ የአውታር መሣሪያዎችን (እንደ ክራር፣ መሰንቆና በገና የመሳሰሉትን) ቀጥሎም በልዩ ልዩ መሣሪያ ታጅበው የሚ ዘመሩትን መዝሙሮች ያመለክቱ ነበር:: ምንም እንኳ በመጽሐፈ መዝሙር ውስጥ የምናገኛቸው መዝ ሙሮች በአብዛኛው "ቴፊሎትም" (ጸሎቶች) ቢሆኑም፣ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው በዕብራውያን ልማድ ግን "ቴሒሊም" ("ውዳሴዎች"፤ የ145 ርእስ ማብ ይመ) የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል:: በመጽሐፉ ውስጥ ከተካተቱት ስብስቦች አንዱ "የእሴይ ልጅ የዳዊት ጸሎት" (72፥20) የሚል ርእስ የተሰጠው በዚህ ምክን ያት ነው::

### የመጽሐፉ አሰባሰብ፣ አቀነባበርና የተጻፈበት ጊዜ

መጽሐፈ መዝሙር የስብስቦች ስብስብ ከመሆኑም በላይ አሁን ባለው ደረጃ ሊዘጋጅ የቻለው በብዙ ምእተ ዓመታት ሂደት ውስጥ ነው :: መጽሐፉ አሁን ያለውን የመጨረሻ ገጽታ የያዘው ከምርኮ በኋላ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያገለግሉ በነበሩ ሹማምት ሲሆን፣ ይህም የሆነው በሦስተኛው ምእተ ዓመት ዓ.ቅ.ክ. ገደማ ነው:: መጽሐፉ የጸሎት መጽሐፍ (ማለትም የጸሎት፣ የውዳሴና የሃይማኖት መመሪያ መጽሐፍ) በመሆን በሁለተኛው (በዘሩባቤልና በሄሮድስ ዘመን) ቤተ መቅደስና በምኵራቦች ውስጥ ያገለግል ነበር:: በመጀመሪያው ምእተ ዓመት ላይ "መጽሐፈ መዝሙር ወይም የመዝሙር መጽሐፍ" በመባል ይታወቅ ነበር (ሉቃ20፥44፤ ሐሥ1፥20):: በዚያን ዘመን መዝሙራት የሚለው መጠ ሪያ በአይሁድ የብሉይ ኪዳን ቀኖና ውስጥ "ጽሑፎች" የሚል ርእስ የተሰጠውን ክፍል ይወክል ነበር:: ይህ መጽሐፍ በዚህ መልክ ተሰብስቦ ከመዘጋጀቱ በፊት በርካታ ስብስቦች ነበሩ:: እርግጥ መዝሙራቱ መሰብሰብና መዘጋጀት የጀመሩት በመጀመሪያው (የሰለሞን) ቤተ መቅደስ (ወይም በዳዊት ዘመን) በመጀመሪያ ዎቹ ዓመታት ላይ ሳይሆን አይቀርም፤ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ሥርዐተ ቅዳሴ መልክና ቅርጽ እየያዘ የመጣውም በዚያን ጊዜ ነበር:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ "የዳዊት ጸሎቶች" የሚለው መጠሪያ የተለመደ ሆነ:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዲካተቱ ከተደረጉት ሌሎች ስብስቦች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፤ (1) የቆሬ ልጆች መዝሙር (መዝ42-49፤84-85፤87-88)፤(2) የአሳፍ መዝሙር (መዝ50፤73-83) እንዲሁም (3) የመዓርግ መዝሙር (መዝ120-134)::

መጽሐፉ በየጊዜው ከተሰበሰቡ መዝሙሮች የተዘጋጀ መሆኑን የሚጠቁሙ ሌሎች ማስረጃዎች አሉ:: መዝ1-41 (ክፍል አንድ) "ያህዌ" (እግዚአብሔር) የሚለውን ስመ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ሲጠ ቀም፣ መዝ42-72 (ክፍል ሁለት) ደግሞ "ኤሎሂም" ("እግዚአብሔር /አምላክ") የሚለውን ብዙ ጊዜ ይጠቀ ማል:: ይሁን እንጂ በክፍል ሁለት ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሶ የምናገኘው ስመ እግዚአብሔር ("ኤሎ ሂም") በክፍል አንድ ውስጥ ተጠቅሶ ከምናገኘው ("ያህዌ") ለምን እንደ ተለየ የተገለጸ ነገር የለም፤ የሆነ ሆኖ ሁለቱም ስሞች በእስራኤል ንጉሥ መንግሥ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ የታወቁ መሆናቸውን መናገር ይቻላል:: ከዚህ በተጨማሪ መዝ93-100 ከእስራኤል ታሪክና እምነት ጋር ተያይዞ የተሰበሰበ ይመስላል (በ9፥31፤96፥10፤97፥1፤99፥1 ላይ "እግዚአብሔር ነገሠ" የሚለውን ይመ):: በተመሳሳይ ርእስ ዙሪያ የተጕዳኙ ሌሎች መዝሙሮችም አሉ፤ እነርሱም መዝ111-118 ("የግብፃውያን ሃሌል")፣ መዝ 138-145 (በየመዝሙሮቹ ርእስ ላይ "የዳዊት" የሚል ቃል ተጠቅሶአል) እንዲሁም መዝ 146-150 (እግዚአብሔርን አመስግኑ የሚል ሐረግ ብዙ ጊዜ ተጠቅሶአል) ናቸው:: "ታላቁ ሃሌል" (መዝ120-136) በመባል የሚታወቀው ክፍል ዕውቅና ይኑረው ወይም አይኑረው ምንም የሚታወቅ ነገር የለም:: (የሚጠ ሩበትን ስም ከክርስቲያኖች ሥርዐተ ቅዳሴ የወሰዱት ሰባቱ "የንስሓ መዝሙሮች" በአይሁድ የመዝሙ ራት ስብስብ ውስጥ እንደ አንድ ክፍል ተደርገው አይታዩም፤ የመዝ6 መግቢያን ይመ)::

መጽሐፈ መዝሙር 150 መዝሙሮችን ይዟል፤ ይህም የሆነው በልዩ ልዩ አርታዕያን ከተዘጋጀ በኋላ ነው:: የሰብዓ ሊቃናት ትርጕምና የዕብራይስጡ ቅጅ፣ መጽሐፉ 150 መዝሙሮች እንዳሉት ቢ ያመ ለክቱም ወደዚህ ቍጥር የሚደርሱት ግን በተለያየ መንገድ ነው:: ቍጥሩ ሲሰላ የሰብዓ ሉቃናት ትርጕም አንድ ተጨማሪ መዝሙር አለው (ሆኖም መዝ151 ብሎ በግልጽ አይጠቅስም)፤ እንዲሁም መዝ9-10 እና መዝ114-11 አንድ መዝሙር ሲያደርጋቸው፣ መዝ116 እና መዝ147ን እያንዳንዳ ቸውን ሁለት መዝሙሮች ያደርጋቸዋል:: እዚህ ላይ አንድ የሚያስደንቅ ነገር ይታያል፤ ይኸውም የሰብዓ ሊቃናቱ ትርጕምና የዕብራይስጡ ቅጅ መዝ 42-43 እንደ ሁለት መዝሙሮች አድርገው ይወስዷቸ ዋል፤ በመሠረቱ ግን አንድ መዝሙር ናቸው::

መጽሐፈ መዝሙር በአምስት መጻሕፍት ይከፈላል (መዝ1-41፤42-72፤73-89፤90-106፤107-150)፤ እያንዳንዱ መጽሐፍ የሚያበቃው በቃለ ውዳሴ ነው (41፥13፤ 72፥18-19፤ 89፥52፤ 106፥48፤150 ይመ):: ቀደም ሲል እንደ ተመለከተው፣ የመጀመሪያዎቹ ሁለት መጻሕፍት ቅድመ ምርኮ ሳይሆኑ አይቀርም:: የተቀረው መዝሙር በሦስት መጻሕፍት የተከፈለውና በድምሩ አምስት መጻሕፍት እንዲሆኑ የተደረ

ገው ምናልባት ከአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ጋር እንዲመሳሰል ለማድረግ ነው:: ከእነዚህ ክፍፍሎች (በመዝ106 እና 107 መካከል) ውስጥ አንዱ ቢያንስ በንሲብ የተደረገ ነው (የመዝ 107 መግቢያ ይመ):: መጽሐፉ በአምስት ከመከፈሉ በስተቀር እንደ አንድ መጽሐፍ ሊታይ ስለሚችል፣ የራሱ መግቢያና (መዝ 1-2) መደምደሚያ (መዝ146-150) አለው:: በመዝሙሩ ውስጥ የሚገኙት ማብራሪያዎች መዝሙሩ በዚህ መልክ ሊከፈል ስለቻለበት ምክንያት ተጨማሪ ሐሳብ ይሰጣሉ::

**ጸሓፊውና አርእስቶቹ**

ከ150 መዝሙራቱ መካከል ርእስ የሌለው መዝ34 ብቻ ነው (በሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ላይ ደግሞ መዝ17 ብቻ ነው):: እነዚህ በተለምዶ "ባለቤት /ወላጅ የለሽ መዝሙራት" በመባል የሚታወቁት በአብዛኛው የሚገኙት ከመጽሐፍ 3-5 ባሉት ክፍል ነው፤ የሚገኙትም ቾምቾም ብለው ነው (መዝ91፤ 93፤97፤99፤104፤107፤111፤119፤135፤137፤146፤150):: በመጽሐፍ 1 እና 2 ውስጥ ርእስ የሌላቸው መዝ12፤10፤33፤43፤71 ናቸው፤ እርግጥ መዝ 10 እና 43 ተከታይ መዝሙሮች ናቸው:: የርእሶቹ ይዘት ቢለያይም በጥቅሉ ግን ከዚህ እንደሚከተለው ሊመደቡ ይችላሉ፤ እነዚህም (1) ጸሓፊ፣ (2) የሰብሳቢው (የአካቢው) ስም፣ (3) የመዝሙሩ ዐይነት፣ (4) የሙዚቃ (የዜማ) ምልክቶች፣ (5) ሥርዐተ ቅዳሴዎች፣ (6) የመዝሙራቱ ዐላማ ናቸው:: ለዝርዝር ማብራሪያ በየመዝሙሮቹ መግቢያ ላይ የሚገኙትን ርእሶች ይመ::

መጽሐፉን በጥልቀት ለማጥናት የሞከሩ ሰዎች በርእሶቹ ጥንታዊነትና ተዓማኒነት ላይ አልተስማሙም:: ብዙዎቹ ርእሶች ቅድመ ምርኮ በመሆናቸው፣ የሰብዓ ሊቃናት ተርጓሚዎች እንኳ ትርጒማቸውን በውል ሊያውቁት አልቻሉም:: ከዚህም በላይ የጸሓፊውን ስምና ርእስ ከጽሑፉ ጋር አያይዞ ማቅረብ በጥንት ዘመን የተለመደ ነበር:: በሌላ በኩል ደግሞ በሰብዓ ሊቃናቱ ትርጒምና በዕብራይስጡ ቅጆች መካከል የተደረጉ ንጽጽሮች እንደሚያሳዩት፣ በርእሶቹ መካከል ልዩነት አለ:: የምሁራኑ ውይይት የሚያተኩረው ከፍ ሲል በተጠቀሱት በተራ ቍጥር 1 እና 6 ላይ ነው::

መዝሙራቱ የተደረሰብትን ጊዜ የሚያመለክቱት ርእሶች የተጻፉት ከ1ኛና 2ኛ ሳሙኤል መጻሕፍት ላይ እንደተወሰዱ ተደርገው ነው:: በተጨማሪም ርእሶቹ ከመዝሙራቱ ይዘት ጋር አይጣጣሙም:: ይህም አንድ ጥርጥጣሬ አስከትሏል፤ ይኸውም ለመዝሙራቱ ርእስ የተሰጣቸው ከሰዎች ሕይወት ታሪክ ጋር ለማስማማት ታስቦ ነው:: ይሁንና የምልክቶቹ ቍጥር ውሱን የሆነው ለምንድን ነው? የመዝሙራቱስ ርእስ ከይዘቱ ጋር ያልተጣጣመው ለምንድን ነው? ውይይቱ በሁለቱም አቅጣጫ ይሄዳል::

የመዝሙሩን ጸሓፊም በተመለከተ የተለያዩ አስተያየቶች ተሰጥተዋል:: ምልክቶቹም ቢሆኑ አከራካሪ ናቸው:: ምክንያቱም ይህን ለመግለጽ የገቡት ሐረጎች በሙሉ ጥቅል እንጂ ዝርዝር ሐሳብ የላቸውም:: ስሞቹ የሚያመለክቱት መዝሙራቱ የተሰበሰቡት በተወሰኑ ሰዎች መሆናቸውን ነው ("የአሳፍ"ወይም "የቆሬ ልጆች"):: የመዝሙሩ ጸሓፊ ዳዊት ነው የሚለው አመለካከት ብዙ ችግር ባያኖርበትም፣ መጽሐፉ በአንድ ወቅት ዝነኛ ዘማሪና ሙዚቀኛ የነበረውን ሰው መዝሙሮች ይዟል:: መዝሙሮቹ ስለ ዳዊት ወይም ከዳዊት ቤት ስለሚወጡት ንጉሦች ያትታሉ::ይሁንና የትኞቹ መዝሙሮች በዳዊት እንደ ተጻፉ በትክክል መናገር አይቻልም:: በዳዊት እንደ ተጻፉ የሚነገርላቸው መዝሙሮችም ቢሆኑ ከዳዊት በኋላ ስላለው ዘመን የሚያወሱ ናቸው (ለምሳሌ የመዝ30 ርእስ፤ የመዝ69 መግቢያንና የመዝ122 ርእስ ይመ):: ከዚህ በተጨማሪ በርእሶቹ ላይ ገብቶ የምናገኘው "ዳዊት" የሚለው ስም ከእርሱ ቤት የሚወጡትን ነገሥታት ያመለክታል::

"ሴላ" የሚለው ቃል የሚገኘው በ39 መዝሙሮች ላይ ነው:: ከሁለቱ በስተቀር (መዝ 140፤143፤ ሁለቱም በዳዊት የተጻፉ ናቸው) የተቀሩት በሙሉ የሚገኙት በመጽሐፍ 1-3 ላይ ነው:: ይህ ቃል በዕንባቆም 3 ላይ ይገኛል:: የቃሉን ትርጒም በተመለከተ ብዙ አስተያየቶች ቢኖሩም፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ምንም የሚታወቅ ነገር የለም:: ምናልባት የሥርዐተ ቅዳሴ ምልክት ሊሆን ይችላል:: ባንጻሩም ቃሉ በዕብራይስጡ ቅጂ ላይ ስለ መገኘቱ አጠያያቂ ነው::

**የመዝሙራቱ ዐይነት**

የመዝሙራቱ ርእሶች በጥንት ጊዜ የነበረውን የአከፋፈል ሥርዐት እንድናስተውል ይረዱናል:: እነዚህም፣ (1) ሚዝሞር ("መዝሙር")፤ (2) ሺጋዩን (የመዝ7 ርእስ ማብ ይመ)፤ (3) ሚክታም (የመዝ 16 ርእስ ማብ ይመ)፤ (4) ሺር ("ዝማሬ")፤ (5) ማስኪል (የመዝ32 ማብ ይመ)፤ (6) ቴፊላህ ("ጸሎት")፤ (7) ቴሂላህ ("ምስጋና")፤ (8) ሌሃዝኪር ("በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰብ የሚቀርብ ምስጋና")፤ (9) ሌቶዳህ ("ውዳሴ" ወይም "ምስጋና")፤ (10) ሌላሜድ ("ትምህርት")፤ (11) ሺር የዲዶት ("የፍቅር መዝሙር" ማለት በሠርግ ላይ የሚዘመር) ናቸው:: የእነዚህ ስያሜዎች ትርጒም ግን በትክክል አይታወቅም::

የመዝሙራቱን ይዘት በዝርዝር ያጠኑ ሰዎች መዝሙራቱን በተለያዩ ፈርጆች ለመመደብ ተገደዋል፤ ይህም መዝሙራቱን አመቺ በሆነ መንገድ ለማጥናት በር ከፍቷል:: ዋና ዋናዎቹ የመዝሙሮች ዐይነት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤ (1) የግለ ሰቦች ጸሎት (መዝ3፤7-8)፤ (2) እግዚአብሔር ማዳኑን ያሳያቸው ግለ ሰቦች /ያቀረቡት ምስጋና (መዝ30፤34)፤ (3) የኅብረተ ሰቡ ጸሎት (መዝ12፤44፤79)፤ (4) እግዚአብሔር ማዳኑን ያሳያቸው ኅብረተ ሰቦች ያቀረቡት ምስጋና (መዝ66፤75)፤ (5) በእግዚአብሔር የሚታመን ሰው የተናገረው ቃል (መዝ11፤16፤52)፤ (6) የእግዚአብሔርን ታላቅነትና በጎነት ለመወደስ

የቀረበ መዝሙር (መዝ8፤19፤29፤65)፤ (7) እግዚአብሔር በመላው ዓለም መንገሡን የሚያውጅ መዝሙር (መዝ47፤93-99)፤ (8) የእግዚአብሔር ከተማ የጽን መዝሙር (መዝ46፤48፤76፤ 84፤የ22፤126፤129፤137)፤ (9) እግዚአብሔር ስለ ቀባው ንጉሥ የቀረበ ንጉሣዊ መዝሙር (መዝ2፤18፤20፤ 45፤72፤89፤110)፤ (10) የተሳላሚዎች መዝሙር (መዝ120-134)፤ (11) የቅዳሴ መዝሙር (መዝ15፤24፤68)፤ (12) የትምህርት መዝሙር (1፤34፤37፤73፤112፤119፤128፤133)።

ይህ አፈራረጅ ራሱ ተወራራሽ ነው። ለምሳሌ "የግለ ሰቦች ጸሎት" የተባለው የንጉሡን ጸሎት ወይም የኅብረተ ሰቡን ጸሎት ሊያካትት ይችላል። ይሁንና ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን መዝሙሮች ጐን ለጐን ማጥናት የራሱ የሆነ ጠቀሜታ አለው። መዝሙራቱ የሚዘመሩበት ቀን አላቸው የሚለው አመለካከት ግን ይሄን ያህል አሳማኝ አይደለም። በዚህ ረገድ የተሰጠውን ማብራሪያ በየመዝሙራቱ መግቢያ ላይ ይመ።

ከእነዚህ መዝሙሮች ውስጥ የጸሎት መዝሙሮች (በግለ ሰቦችም ሆነ በኅብረተ ሰቡ የቀረቡት) እጅግ ውስብስብ ናቸው። መዝሙረኛው አቤቱታውን ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው በተለያዩ ቋንቋዎች ነው፤ (1) ወደ እግዚአብሔር በመጮኽ፤ "እግዚአብሔር ሆይ"፣ "አምላኬ ሆይ"፣ "አድኜ"፤ (2) አቤቱታውን በመደርደር፤ "ተነሥ"፣ "መልስልኝ"፣ "እርዳኝ"፣ "ታደገኝ"፤ (3) ጭንቀቱን በመግለጽ፤ "ብዙዎች ተነሥተውብኛል"፣ "ክፉዎች አሳደውኛል"፣ "ተጨንቄአለሁ"፤ (4) በእግዚአብሔር ላይ ያለውን ጥያቄ በመናገር፤ "ስለ ምን ተውኸኝ"፣ "ፊትህን ከእኔ የምትሰውረው እስከ መቼ ነው"፤ (5) ይግባኙን በማስታወቅ፤ "ከእኔ አትራቅ"፣ "ፍረድልኝ"፤ (6) እግዚአብሔር ልመናውን እንዲያደምጥ በማድረግ፤ "መሸሸጊያዬ አንተ ነህ"፣ "ስለ ስምህ ብለህ"፤ (7) በባላጋራዎቹ ላይ ክሱን በማቅረብ፤ "በአፋቸው እውነት የለም"፣ "ጨካኝ ሰዎች ነፍሴን ተመኙ"፤ (8) እግዚአብሔር ጠላቶቹን እንዲበቀልለት በመለመን፤ "ይዋረዱ"፤ (9) ንጽሕናውን በማስታወቅ፤ "በጽድቅ ተመላለስሁ"፣ "ያለ ምክንያት ጠሉኝ"፤ (10) ኀጢአቱን በመናዘዝ፤ "አንተን በድያለሁ"፣ "በደሌን እናዘዛለሁ" (11) እምነቱን በመግለጽ፤ "አንተ ጋሻዬ ነህ"፣ "አንተ ትመልስልኛለህ"፤ (12) እግዚአብሔር የሚታደገው ከሆነ ምስጋና ለማቅረብ ቃል በመግባት፤ "ስለ ኀይልህ እዘምራለሁ"፣ "ከንፈሮቼ ያመስግኑሃል"፤ (13) ውዳሴ በማቅረብ፤ "እግዚአብሔርን ከእኔ ጋር ከፍ ከፍ አድርጉ"፣ "እግዚአብሔርን አመስግኑ"፤ (14) የሚያመሰግንበትን ምክንያት በመግለጽ፤ "ታድገኸኛልና"፣ "እግዚአብሔር የምስኪኖችን ጸሎት ይሰማል"።

ምንም እንኳ በሚቀርቡት ጸሎቶች ሁሉ ውስጥ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ይታያሉ ለማለት ባያስደፍርም፣ ሁሉም ግን የአቤቱታ ጸሎቶች አካል ናቸው። በጥቅሉ የሚያሳዩን የፍርድ ቤት ገጽታን ነው። መዝሙረኛው አቤቱታውን በሰማያዊው ንጉሥ ዳኛ ፊት ያቀርባል። ክፉዎች ጠላቶች ሲያስጨንቁት፣ ያለበትን ሁኔታ በማስታወቅ ንጽሕናውን ይናገራል፤ ከዚያም እግዚአብሔር ጠላቶቹን እንዲበታትንለትና ቅን ፍርዱንም እንዲሰጠው ይለምናል። በእግዚአብሔር እጅ መከራ ሲደርስበት (እግዚአብሔር ባላጋራው ሲሆን)፣ ኀጢአቱን ይናዘዛል፤ ምሕረትም ይጠይቃል። በጸሎቶቹ ውስጥ የተጠቀሱትን የተለያዩ ንግግሮችና የፍርድ ውሳኔዎች ልብ ብሎ መመልከት ተደራስያን መዝሙሩን ይበልጥ እንዲረዱ ያግዛቸዋል።

### ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ

ምንም እንኳ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ጸሎቶች ቢገኙም፣ መዝሙሩ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የተጻፈው ግን በግጥም መልክ ነው፤ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ ጸሎቶች ሁሉ የተጻፉት በግጥም መልክ አይደለም (1ነገ8፥23-53፤ ዕዝ9፥6-15፤ ነህ9፥5-37፤ ዳን9፥4-19 ይመ)። ወይም ደግሞ የውዳሴ ቃሎች ሁሉ የተጻፉት በግጥም መልክ አይደለም (1ነገ8፥15-21 ይመ)። መዝሙራቱ ልብ የሚነኩ፣ ምስል የሚከስቱና ሐሳብ የሚጨብጡ ናቸው። በምስል፣ በተነጻጻሪ ዘይቤና በተለዋጭ ዘይቤ የተሞሉ ናቸው። በተመሳሳይ ድምፅ የሚጨረሱ ወይም የሚጀምሩ ስንኞችን ማግኘት የተለመደ ነው። ቃልን ወይም ሐሳብን መድገምና ተመሳሳይ ትርጕም ያላቸውን ቃላት አንዱን በአንዱ ላይ መከመር ሌላው ባሕርያቱ ናቸው። ቁልፍ ቃላት በጸሎቱ ወይም በመዝሙሩ ውስጥ የሚገኙትን ዐበይት ጭብጦች የሚያጎለምሱ ናቸው። እያንዳንዱ መዝሙር የተቀነበበው በመግቢያውና በመደምደሚያው ላይ በሚገኙ ተመሳሳይ ቃላት ነው።

የዕብራይስጥ ግጥሞች ቤት አይመቱም። የግጥሞቹ ዐቢይ ባሕርይ ጉድኝት ነው። የግጥሙ ስንኞች ሁለት (አንዳንድ ጊዜ ሦስት) እኩኩል (ተመጣጣኝ) ክፍል አላቸው። ሁለተኛው ክፍል የመጀመሪያውን ክፍል በተመሳሳይ ጉድኝት የሚያስተገባ ወይም በተቃርኖ ጉድኝት የሚያነጻጽር ነው። እነዚህ ጉድኝቶች ጥቅል እንጂ በሁለቱ መሠረታዊ ስንኞች ውቅር ውስጥ ባለቅኔው ሊያሳይ የሞከራቸውን ልዩ የአገላለጽ ስልቶች ሙሉ በሙሉ የሚገልጹ አይደሉም። ይሁንና አንባቢው ልዩነቶቹን ለማወቅ እንዲችል ይረዱታል።

የዕብራይስጡ ግጥም ስንኞች (ወይም የስንኝ ክፍሎች) የሚጀምሩትና የሚጨርሱት የት እንደ ሆነ በትክክል መለየት አይቻልም። የሰብዓ ሊቃናቱ ትርጕም እንኳ ስንኞቹን የሚጀምረውና የሚጨርሰው ከዕብራይስጡ በተለየ መንገድ ነው። እንግዲህ ዘመናዊ ትርጕሞች ቢለያዩ የሚያስደንቅ አይደለም።

ከዚህ ጋር የሚያያዘው ችግር የዕብራውያን ባለ ቅኔዎች የአጻጻፍ ዘዬ በጣም አጭርና አንድ ወይም ሁለት ቃላትን በመግደፍ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው። የቃላቱን አገባብና ዝምድና የምናው

ቀው ከዐውደ ንባቡ ነው:: ከአንድ በላይ አማራጮች ሲኖሩ፣ ተርጓሚው አሻሚ ነገር ውስጥ ይወድ ቃል:: የትኛው ቃል ወይም ሐረግ ከየትኛው ስንኝ (ክፍል) ጋር ተያይዞ መነበብ እንዳለበት በትክክል አያውቅም::

የዕብራይስጥ ግጥሞች የአንጓ ውቅር ሌላው አከራካሪ ጉዳይ ነው:: በመዝ42-43፤57 ላይ እንደ ሚታየው የግጥሙ አንጓዎች ተለይተው የሚታወቁት በተደጋጋሚ ተጠቅሰው በሚገኙት አዝማቾች ነው:: በመዝ110 ላይ ሁለት እኩኩል (ተመጣጣኝ) አንጓዎች የተከፈሉት በየመግቢያዎቹ ላይ በሚገኙት ንግሮች ነው (የመዝ132 መግቢያን ይመ)፤ መዝ119 ደግሞ ለእያንዳንዱ የዕብራይስጥ ፊደሎች ስምንት ስንኞችን ሰጥቷል:: በአብዛኛው ግን እንዲህ ዐይነት የመለያ ምልክቶች አልሰጡም:: ይህ ትርጒም (አመት) የግጥሞቹን አንቀጽ ("አንጓ" ያልናቸውን) ለመለየት ክፍት ቦታዎችን ትቶአል:: እንዲህ የተደረገው በብዙ ጥናት በመሆኑ፣ አንባቢው እንዲከተላቸው እንመክራለን:: ይሁንና አንዳንድ ጊዜ የአ ንቀጾቹ (የአንጓዎቹ) አከፋፈል አጠያያቂ ይሆናል፤ በዚህ ጊዜ አጠያያቂ የሆነው ነገር በማጥኛ ጽሑፉ ውስጥ ተብራርቷል::

1) ጸሐፊዎቹ መዝሙራቱን በሚጽፉበት ጊዜ በአእምሮአቸው አንድ አጠቃላይ ሐሳብ ይዘው እንዲጽፉ መዝሙሮቹን በጥንቃቄ በማጥናት ማወቅ ይቻላል:: ይህ አባባል እውነት መሆኑን የምና ውቀው፣ ባለ ቅኔው መዝሙሮቹን ሲጽፍ እያንዳንዱ የዕብራይስጥ ፊደሎች አንድ አንጓ (በመዝ 111-112) ወይም አንድ ስንኝ (በመዝ25፤34፤145) ወይም ሁለት ስንኝ (በመዝ 37) ወይም ስምንት ስንኝ (በመዝ 119) በመስጠት የተለየ የአጻጻፍ ዘዴ መጠቀሙን ስናስተውል ነው:: በተጨማሪም መዝ33፤38፤103፤ እያንዳንዳቸው 22 ስንኝ አላቸው፤ ይህም ከዕብራይስጡ የፊደል ገበታ ጋር ለማመ ሳሰል የተደረገ እንደ ሆነ ምንም ጥርጥር የለውም (በሰቆቃወ ኤርምያስ መግቢያ ላይ "ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ" የሚለውን ይመ):: የጥንት ሰዎች አንድን ነገር በቃላቸው ለመያዝ የሚሞክሩት በዚህ ዐይ ነት ዘዴ መሆኑን ታሪካቸው ይመሰክራል:: ፊደሎቹ ውስብስብ የሆኑ ነገሮችን በቀላሉ ለማስታወስ የሚረዱ ምልክቶች ናቸው::

ሌሎች የአጻጻፍ ዘዴዎችም ጥቅም ላይ ውለዋል:: ከእነዚህም ውስጥ አንዱ "እኩኩል" የሚባለው ነው:: ይህም ማለት ለእያንዳንዱ አንጓ የሚሰጡት ስንኞች በቍጥር እኩል ናቸው (ለምሳሌ መዝ12፤41 ይመ):: በዚህ ዐይነት የሚጻፉ መዝሙሮች (1) መግቢያና መደምደሚያ፣ (2) ዐቢይ ሐሳብ አላቸው:: የአጻጻፍ ዘዴዎቹን ይበልጥ የምናደንቀው በጥልቀት ስናጠናቸው ነው::

**ትምህርተ መለኮቱ**

መጽሐፈ መዝሙር በአብዛኛው የጸሎትና የውዳሴ መጽሐፍ ነው:: ለእግዚአብሔር የሚናገረው በጸሎት ነው፤ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርበው ደግሞ በምስጋና ነው:: ምንም እንኳ አልፎ አልፎ የጽድ ቅን መንገድ የሚያስተምር መጽሐፍ ቢሆንም፣ ስለ "ምስጢራት" የሚያስተምር መጽሐፍ ግን አይደ ለም:: እንግዲህ ትምህርተ መለኮቱ ረቂቅ ወይም በሥርዐት የተዋቀረ ሳይሆን፣ በንስሐና በምስጋና የተ ቀረጸ ነው::

መጽሐፈ መዝሙር የብዙ ልዩ ልዩ መዝሙሮች ስብስብ ነው፤ የተጻፈውም ለተለያየ ዐላማና በብዙ ምእተ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው:: በመሆኑም ስለ ትምህርተ መለኮቱ ስንነጋገር ዐቢይ የሆኑትን ብቻ ለመምረጥ እንገደዳለን:: ይህም ሆኖ ሙሉ ማብራሪያ መስጠት አይቻልም:: እያንዳንዱ መዝሙር የራሱ የሆነ ትምህርተ መለኮት አለው፤ በሌላ አነጋገር በመጽሐፉ ውስጥ እያደገ የሚሄድ አንድ ወጥ ሐሳብ የለም::

2) የመዝሙሩ አርታዕያን ይህን መዝሙር የጻፉት ያገኙትን ነገር ሁሉ መሠረት በማድረግ አይደለም:: በጽሑፉ ውስጥ በየዘመኑ የተሰሙ ድምፆች እንደሚመጡ ያውቃሉ፤ ይሁንና አንዱም ከነቢ ያቱና ከሕጉ ድምፅ አይወጻደሩም::

የመዝሙሩ የሕይወት፣ የታሪክና የፍጥረት ማእከል እግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር የሰማይና የምድር ንጉሥ በመሆኑ፣ ፍጥረት ሁሉ ለእርሱ ይገዛል:: ሁሉን የፈጠረና ሁሉን የሚኖር እርሱ ነው:: ፍጥረታት የክብሩ መጐናጸፊያ ናቸው:: እርሱ ስላዘዛቸው በሥርዐት ይኖራሉ:: እርሱ ስለሚጠብቃቸው ከመበተን፣ ከመታወክና ከመጥፋት ድነዋል:: እርሱ ልዑል ስለ ሆነ የሚገዙትም ሆነ የሚመሩት በእርሱ ዐላማ ነው:: እርሱም ስለሚገዛቸውና ስለሚመራቸው በሥርዐት ይንቀሳቀሳሉ:: ሥነ ፍጥረትና ታሪክ የምንለው ነገር ሁሉ አንድ ጌታ አላቸው፤ በእርሱ ትእዛዝ በአንድነት ይነቀሳቀሳሉ:: የታላቁ ንጉሥ ክብር የተገለጠውም በሥነ ፍጥረቱ ነው:: እግዚአብሔር መልካም (ጠቢብ፣ጻድቅ፣ታማኝ፣ ቸር፣ መሐሪ) ነው፤ በመሆኑም ልንታመንበት ይገባል:: ደግሞም እግዚአብሔር ታላቅ (በዕውቀቱ፣ በሐሳቡ፣ በሥራው) ነው፤ በመሆኑም ልንሰግድለት ይገባል:: ቅዱስ አምላክ መሆኑን ያሳየው በመልካምነቱና በጌት ነቱ ነው:: ንጉሥ፣ የሥነ ፍጥረት ጌታና ልዑል በመሆኑ፣ የሚቃወሙትን፣ የሚክዱትንና የሚንቁትን ኀይሎች ከቶ አይታገሥም:: ሕዝቦችን ሊገዛ ይመጣል፤ ያን ጊዜ ሰዎች ሁሉ ይሰግዱለታል:: የመዝሙረ ኛው ተስፋ ይህ እንደ ሆነ መገመት አያዳግትም:: መንግሥቱም ትመጣለች:: ተቃዋሚዎቹን ይበቀላል፤ ፍጥረትን ከዐመፀኝነት ያነጻል፤ ይህም የታሪክ መደምደሚያ ይሆናል::

እግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ የሚደገፍበት ታላቅ ንጉሥ በመሆኑ፣ በሰው እጅ በተሠሩ ሌሎች አማ ልክት የሚታመኑትንና በራሳቸው ነገር የሚመኩትን ትዕቢተኞች ይቃወማል:: እንደዚህ ዐይነት ሰዎች የዚህን ዓለም ሀብት፣ ክብርና ዝና ለማግኘት ሲሉ የማይፈነቅሉት ድንጋይ፣ የማይመሱት ጉድጓድ

የለም፤ ደግሞም ሕግ የለሾችና በዝባዦች ናቸው:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ዐይነቱ "ትዕቢት" የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው:: ትዕቢተኞች የበለጸጉ ቢመስላቸውም፣ መጨረሻቸው ግን ሞት ነው:: እግዚአብሔር የሚወደው በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ እርሱን ተስፋ የሚያደርጉ ትሑታንን ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔርን መፍራት፣ በእርሱ መታመንና ለእርሱ መታዘዝ የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው (111፥10):: በመጨረሻም ትሑታን ምድርን ይወርሳሉ፤ የእግዚአብሔርን ፊት እንዳያዩ ሞት እንኳ ሊከለክላቸው አይችልም::

መዝሙረኛው ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንግሥቱ እንዲሁም ስለ እግዚአብሔር ሰዎች ያለው የወደፊት ተስፋ አንዳንድ ጊዜ ጥቅል ቢሆንም ጽኑ ነው:: መዝሙሩን ከጻፉት ሰዎች መካከል ዘመንን ከሁለት ቦታ ከፍለው (ክፉ የሆነውን የአሁኑን ዘመንና የሚመጣውን የጽድቅና የሰላም ዘመን) የተመለከቱ የሉም:: እንዲህ ያለው አመለካከት ብቅ ማለት የጀመረው በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ዘመን መካከል በተጻፉ ሥነ ጽሑፎች ውስጥ ነው:: ይህም ቀደም ሲል በነቢዩ ዳንኤልና (12፥2-3) በኢሳይያስ (65፥17-25፤ 66፥22-24) ትንቢት ተመልክቶአል:: ይህ አመለካከት ይበልጥ ተስፋፍቶ የተነገረው በኢየሱስና በሐዋርያት ነው::

እግዚአብሔር ታላቅ ንጉሥ በመሆኑ፣ በሰዎች መካከል ፍትሕን ማስፈን የሚችል እርሱ ብቻ ነው (ራሳችን ብንበቀል ግን ድትጊቱ እንደ "ትዕቢት" ይቈጠራል):: ሰዎች ሲበደሉና ሲጨቈኑ አቤቱታቸውን ሊሰማ የሚችል እውነተኛ ዳኛ እርሱ ብቻ ነው:: ምድራዊ ዳኞች ከጥቅም የተነሣ ወይም ከኀይል የተነሣ ወይም ከፍርሃትና ከሙስና የተነሣ ትክክለኛ ዳኝነት መስጠት አይችሉም:: እግዚአብሔር ግን ለተጨቈኑና ለተበደሉ ሁሉ ታማኝና ብርቱ ጠበቃ ነው:: እርሱ ሐሳብንና ልብን ሁሉ መመርመር የሚችል ነው:: በእርሱ ዘንድ አንዳች የተሰወረ ነገር የለም:: የሐሰት ምስክር ፍርዱን ሊያጣምም አይችልም:: ወደ እርሱ የሚቀርቡትን አቤቱታዎች ሁሉ ያደምጣል:: መልካምና ታማኝ ዳኛ በመሆኑ፣ የተጨቈኑትንና የተበደሉትን ነጻ ያወጣል፤ ጠላቶቻቸውንም ሁሉ ድል ያደርጋል:: መዝሙረኛው "እኔ ምስኪንና ድኻ ነኝ" ስለዚህ ታደገኝ፤ ከዚህ ሁሉ "ነጻ የማታወጣኝ ለምንድን ነው? ዝም የምትለው እስከ መቼ ነው?" በማለት ወደ እግዚአብሔር የሚጮኸው በዚህ ምክንያት ነው::

እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ ታላቅ ንጉሥ በመሆኑ፣ በዓለም ካሉት ሕዝቦች መካከል እስራኤልን የራሱ ሕዝብና "ርስቱ" አድርጎ መረጠ:: በታላቅ ክንዱም በዓለም ካሉት ኀያላን እጅ ነጻ አወጣቸው:: የሚኖሩበት ምድር (ከአሕዛብ መንግሥታት የወሰደውን) ሰጣቸው:: ከእነርሱ ጋር በቃል ኪዳን በመተሳሰር የተዋጁ ሕዝብ አደረጋቸው:: የሕዝቡም ዕድል ፋንታ በዚሁ ቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተ እንዲሆን አደረገ:: ስለ እርሱ የሚመሰክረውን የቃሉን መገለጥ ሰጣቸው:: በቃሉም አማካይነት ተስፋውን ገለጠላቸው፤ ፈቃዱንም አወጀ:: በተደረገው ቃል ኪዳን መሠረት እስራኤል ለሰማይ አምላኳ በመታመን በአሕዛብ መካከል መኖር ይጠበቅበታል:: በጥበቃው ማረፍ፣ የገባለትን ቃል ተስፋ ማድረግ፣ እንደ ፈቃዱ መኖርና እርሱን ብቻ ማምለክ ይኖርበታል:: ለእግዚአብሔር የሚገባውን ውዳሴ ለዓለም ሁሉ መዘመር አለበት:: ይህም አሕዛብን በወንጌል ለመድረስ መንገድ ከፋች ይሆን ዘንድ የተሰጣት ጸጋ ነው::

እግዚአብሔር ታላቅ ንጉሥና የእስራኤል የኪዳን አምላክ በመሆኑ፣ በምድር የእርሱ መንግሥት እንደራሴ እንዲሆን ዳዊትን መረጠ:: ዳዊትም በዚህ ሥልጣኑ የታልቁ ንጉሥ አስተዳደር አባል በመሆን የጌታ አገልጋይ ነበር:: ጌታም ራሱ በስሙ የሚያስተዳድር የቤተ መንግሥቱ ልጅ አድርጎ ዳዊትን ቀባው፤ አሳደገውም:: በእርሱም አማካይነት እግዚአብሔር ሕዝቡን በተስፋቱ ምድር በሰላም አስቀመጠ:: ሕዝቡን የሚገዳደረውን ጠላት ዝም አሰኘ:: የዳዊትንም ሥርወ መንግሥት ለማጽናት ቃል ገባ:: በምድር ያለው የእግዚአብሔር መንግሥት ከዳዊት ሥርወ መንግሥት ጋር የተያያዘ እንዲሆን አደረገ:: በዚህች ክፉ ዓለም የእስራኤል ሰላምና ተስፋ በዚህ መንግሥት ብርታትና ጽናት ላይ የተመሠረተ ነው:: ከዳዊት ግንድ የሆኑት ነገሥታት በምድር ላይ የእግዚአብሔር ተወካዮች ስለ ሆኑ "በቀኜ ተቀመጥ" (110፥1) የሚለው ቃል የነገሥታቱ ሥልጣን ዓለም አቀፋዊ መሆኑን (መዝ 2) ያመለክታል::

እንግዲህ በጌታ የተቀባው የጌታ ባሪያ ከአንድ ጠረፍ ንጉሥ ይበልጣል:: በእግዚአብሔር ጽድቅ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲመራ የተሾመ ነው:: የተጨቈኑትን ነጻ እንዲያወጣ፣ ደህ አደጉንና መበለቲቱን እንዲታደግ፣ ክፋትን እንዲያስወግድና የምድር ሕዝቦችን በሰላሙና በብልጽግናው እንዲባርክ ተቀብቶአል:: በእግዚአብሔር ፊት ስለ ሕዝቡ የሚማልድ፣ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ የሚጠብቅና ሕዝቦች ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ የሚጮኽ ድምፅ ነው:: ንጉሥ ብቻ ሳይሆን ካህን (መዝ110 እና ማብ ይመ) የተባለውም ለዚህ ሳይሆን አይቀርም::

ታላቅ ንጉሥና የእስራኤል የኪዳን አምላክ በመሆኑ፣ እግዚአብሔር ዳዊትንና ሥርወ መንግሥቱን የራሱ እንደራሴ አድርጎ እንደመረጠ ሁሉ፣ የዳዊት ከተማ የሆነችውንም ኢየሩሳሌምን በምድር የዙፋኑ መቀመጫና መናገሻው እንድትሆን መርጧታል:: ስለዚህ ኢየሩሳሌም (ጽዮን) በምድር የእግዚአብሔር መንግሥት ዋና ከተማ (ምሳሌ) ሆነች:: በኢየሩሳሌም ባለው ቤተ መንግሥቱ ማለትም በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ በሕዝቡ መካከል ተቀመጠ:: በዚያም ሕዝቡ ወደ እርሱ መጸለይ፣ እርሱን መወደስ፣ ኀይሉንና ክብሩን ማየት ይችላሉ:: እግዚአብሔርም በዚያ ድነትን ያውጃል፤ በረከትን ያፈሳል፤ ፍርድንም ይሰጣል::

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው በጎነትና ታማኝነት "በትልቁ ንጉሥ ከተማ" (መዝ48፥2) በኢየሩሳሌም በሚገኘው ቤተ መቅደሱ በሕዝቡ መካከል ለመገኘት በገባው ቃል ተገልጾአል:: እግዚአብሔር

በጎነቱንና ታማኝነቱን ይበልጥ የሚገልጠው ግን ለትሑታንና ለልበ ንጹሐን፣ በእርሱ ለሚታመኑና እርሱንም ለሚያከብሩ ነው:: በደለኝነት ተሰምቶአቸው ባዘኑ ቍጥር የኪዳናቸውን አምላክ ምስክርነት እንዲህ እያሉ ያስታውሳሉ፤ "እግዚአብሔር እግዚአብሔር፣ ርኅሩኅና ቸር ለምሕረት፣ ለቍጣ የዘገየ፣ ፍቅሩና ታማኝነቱ የበዛ፣ ፍቅሩን ለሺዎች የሚጠብቅ፣ ክፋትን፣ ዐመፅንና ኀጢአትን ይቅር የሚል፣ በደለኛውን ግን ሳይቀጣ ዝም ብሎ አይተውም፤ በአባቶች ኀጢአት ልጆችንና የልጅ ልጆችን እስከ ሦስት አራት ትውልድ ይቀጣል" (ዘፀ34፥6-7):: እንግዲህ ሊፈሩትና ሊያከብሩት የሚችሉት በዚህ ዐይነት ብቻ ነው (መዝ 130፥3-4 ይመ)::

በመዝሙር መጽሐፍ ከተነሡት መሠረታዊ የትምህርተ መለኮት ነጥቦች መካከል የመጀመሪያው እግዚአብሔር የነገሥታት ንጉሥ መሆኑ ነው:: እግዚአብሔርም ታላቅነቱንና በጎነቱን በዚህ መጽሐፍ ገልጾአል:: መጽሐፉ የሰው ልጅ ራሱን፣ ፍጥረትን በፍጥረትና በታሪክ ውስጥ ያለውን ክስተት ሊመጣ ያለውንም ነገር እንዲያጤን ያሳስባል:: ፍጡር ራሱ የእግዚአብሔር መንግሥት አባልና ተገዥ ነው:: ሰው በምድር ላይ እግዚአብሔርን እየፈራና ተስፋ እያደረገው የሚኖር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የእግ ዚአብሔር እንደራሴ ነው:: ይህን እውነት መካድ የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው፤ ዓለምን እያጥለቀለቀ ያለውም ከዚሁ ክህደት የወጣ ክፋት ነው::

እግዚአብሔር ቃሉን ከመስጠቱ ጋር እስራኤልን መምረጡ በኋላም ዳዊትንና ጽዮንን መምረጡ የእግዚአብሔር የጽድቅ መንግሥት በክፋት ወደ ተሞላች ዐመፀኛ ዓለም በአዲስ መልክ መግባቱን ያመለክታል፤ ይህም ጻድቃንን ከክፉዎች ከመለየቱም ሌላ በጥልቀት ሲታይ እስራኤልን እንኳ የሚ ይምር መለኪያ ነው:: በመጨረሻም ጽድቅ ያሸንፋል፤ ትዕቢተኛው ይዋረዳል፤ ክፋትም ይወድቃል:: ትሑታንም ምድርን ይወርሳሉ፤ በጽድቅና በሰላም የተሞላች የእግዚአብሔር መንግሥት ትገለጣለች:: በመጽሐፉ ውስጥ የተመለከቱት እነዚህ ዐበይት ሥነ መለኮታዊ ጉዳዮች ሃይማኖትንና ሥነ ምግባርን የሚያንጸባርቁ ናቸው::

እዚህ ላይ መነሣት ያለበት ጥያቄ "የመዝሙር መጽሐፍ ስለ ክርስቶስ ይናገራልን?" የሚለው ይሆናል:: አዎ! መጽሐፉ ስለ ክርስቶስ ይናገራል፤ ነገር ግን ነቢያት ከሚጠቀሙበት መንገድ ይለያል:: የቀረበው ልዩ በሆነ መልክ ነው:: መዝሙር ትንቢት ስላልሆነ ከትንቢት መጻሕፍት እንደ አንዱ ሆኖ አልተጠቀሰም::

መዝሙራት በዳዊት ዙፋን ስለ ተቀመጡት ነገሥታት የተናገሩት በወቅቱ ዘውድ የጫኑትን (መዝ2፤72፤110፤ አንዳንዶች መዝ110 የተለየ መሆኑን ቢናገሩም) ወይም በሥልጣን ላይ የነበሩትን ነገሥታት (መዝ 45) ለማመልከት ነው:: ዳዊት በእግዚአብሔር በመቀባቱ የተሰጠው ክብር፣ እግዚአብሔርም በዳዊት ሥርወ መንግሥቱ አማካይነት ሊሠራ ያለው ሁሉ በዚህ መጽሐፍ ተነግሮአል:: ወደፊት ሊመጡ ስላሉ የዳዊት ልጆችም ተነግሮአል:: በተለይ በምርኮ ጊዜና ከምርኮ በኋላ ማንም በእስራኤል ባልነገሠበት ወቅት እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር የገባው ቃል ኪዳን በእርሱ እንደሚፈጸም ነቢያት ስለ ተነበዩለት የዳዊት ልጅ ለእስራኤል ሕዝብ ገልጾአል:: የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትም እነዚህን መዝሙራት የሚመሰክሩ አድርገው ጠቅሰዋቸዋል:: በእርግጥ በመዝሙራት ውስጥ ያለው ቃል ኪዳን በክርስቶስ ተፈ ጽሞአል::

የመዝሙር መጽሐፍ ስለ ጻድቃን መከራ ብዙ ይናገራል:: ጻድቃን የዋሃንና ንጹሐን ናቸው፤ በእግዚአብሔር የሚታመኑና በመከራ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የሚጮኹ (መዝ22፤69) አሁን ባለጨ ናቂ ዓለም ውስጥ እየተሰቃዩ ያሉት ቅዱሳን ድምፆች ናቸው:: የእግዚአብሔርን ቅዱሳን የሚረዱ ናቸው::

በመዝሙረ ዳዊት ያለው ጩኸት የቅዱሳን ጩኸት ነው፤ ይህም በእስራኤል የጸሎት መዝገብ የተጻፈ ነው:: ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደ ዓለም የመጣው በእግዚአብሔር ባሪያዎች ምሳሌ ራሱን አዋርዶ ነው:: የእግዚአብሔር ጻድቅ አገልጋይ ሆነላቸው፤ በክፉ ሰዎች የሚፈጸምባቸውን መከራ ስለ እነርሱ ተቀበለ፤ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ጸሎቶችም ልዩ በሆነ መልክ የእርሱ ሆኑ:: በጸሎቱ የተገለጸው መከራና ነጻነትም በእርሱ ተፈጽሞአል፤ መስቀላቸውን ተሸክመው እርሱን የሚከተሉትም በዚህ ጸሎት ይጠቀ ማሉ::

እንደዚሁም መጽሐፉ በእግዚአብሔር ማደሪያና በከተማው ስላለው የቃል ኪዳን ሕዝብ በማተት በመጨረሻ ስለ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ያመላክታል:: መዝሙረ ዳዊት የእግዚአብሔር ሕዝብ ጽኑ የጸሎት መዝገብም እንጂ የሁለተኛው ቤተ መቅደስ የጸሎት መጽሐፍ ብቻ አይደለም:: አሁን ግን በመሲሑ የመጀመሪያ ምጽአት በተጀመረውና በዳግም ምጽአቱ ፍጻሜ በሚያገኘው ታላቅ ቤዛነት አንጻር አገልግሎት ላይ መዋል አለበት::

# አንደኛ መጽሐፍ
## ከመዝሙር 1-41
## መዝሙር 1
### ሁለቱ መንገዶች

1በክፉዎች ምክር የማይሄድ፣
 በኀጢአተኞች መንገድ የማይቆም፣
በፌዘኞችም ወንበር የማይቀመጥ፣
 ሰው ብፁዕ ነው::
2ነገር ግን ደስ የሚሰኘው *በእግዚአ
 ብሔር* ሕግ ነው፤
 ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያሰላስለዋል::
3እርሱም በወራጅ ውሃ ዳር እንደ ተተከለች፣
 ፍሬዋን በየወቅቱ እንደምትሰጥ፣
ቅጠሏም እንደማይጠወልግ ዛፍ ነው፤
 የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል::
4ክፉዎች ግን እንዲህ አይደሉም፤
 ነገር ግን ነፋስ ጠራርጎ እንደሚወስደው፣
 ገለባ ናቸው::
5ስለዚህ ክፉዎች በፍርድ ፊት፣
 ኀጢአተኞችም በጻድቃን ማኅበር
 መቆም አይችሉም፤
6*እግዚአብሔር* የጻድቃንን መንገድ
 ይጠብቃልና፤
 የክፉዎች መንገድ ግን ትጠፋለች::

## መዝሙር 2
### መሲሓዊ ትዕይንት

1ሕዝቦች ለምን ያሤራሉ?[u]

1፥1 ዘፍ49፥6፤ዘዳ 33፥29፤ኢዮ11፥3፤ 21፥16፤ መዝ10፥2-11፤26፥4-9፤37፥38፤ 40፥4፤51፥13፤89፥15 ፤104፥35፤128፥4፤ምሳ 1፥22፤ኢሳ 28፥14፤ ሆሴ7፥5

1፥2 ዘፍ24፥63፤ መዝ 19፥7፤112፥1፤ 119፥1:16:35፤ሕዝ 11፥20፤18፥17፤ሮሜ 7፥22

1፥3 ዘፍ39፥3፤ዘኍ 24፥6፤ኢዮ14፥9፤መዝ 46፥4፤52፥8፤65፥9፤9 2፥12:14፤128፥3፤ኢሳ 1፥30፤33፥21፤64፥6፤ ኤር 11፥16፤31፥9፤ ሕዝ17፥5፤47፥12፤ዘካ 4፥3

1፥4 ኢዮ13፥25፤ ኢሳ 40፥24፤ኤር 13፥24 1፥5 ኢዮ19፥29፤ መዝ5፥5፤26፥12፤35፥18 ፤82፥1፤89፥5፤107፥32፤111፥1፤149፥1
1፥6 ዘሌ26፥38፤ መዝ9፥6፤37፥18፤121፥5፤145፥20፤ናሆ1፥7
2፥1 መዝ21፥11፤ 83፥5፤ምሳ24፥2

[u]1 ዕብራይስጡ እንዲሁ ሲሆን ሰብዓ ሊቃናት ግን *ይቈጣሉ* ይላል::

*መዝሙር 1፤* የዚህ ምዕራፍ ጸሓፊ ማን እንደ ሆነ፣ መች እንደ ጻፈው በውል አይታወቅም:: ይህ ከእግዚአብሔር የሆነው ጥበብ የሁለቱን "መንገዶች" ማለትም "የኀጢአተኞችን መንገድ" (ቍ1) እና "የጻድቃንን መንገድ" (ቍ6) የመጨረሻ እድል ፈንታ ይወስናል:: ቍ34፥19-22፤ 37 እንዲሁም በመጽሐፈ ምሳሌ መግቢያ ላይ "የጥበብ ጽሑፍ" የሚለውን ክፍል ይመ:: ይህ መዝሙር የመጽሐፉ መግቢያ እንደ መሆኑ አንባቢን እንደሚከተለው ያሳስባል፤ (1) መዝሙሩ (የተለያዩ ስያሜዎችን በመጠቀም) እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ የሚመለከታቸው ሰዎች እግዚአብሔር ወደ ራሱ ያቀረባቸው፣ ደኅንነቱንና በረከቱንም የሰጣቸው በመሆኑ፣ ጽድቅ ዐይነተኛ መለያቸው (መታወቂያቸው) ሊሆን ይገባል፤ በደለኞች ግን ከእነርሱ ጋር ዕጣ ፈንታ የላቸውም (ቍ5፤ መዝ15፤24 ይመ)፤ (2) በመዝሙሩ ላይ የሚታየው የጽሞና ሐሳብ እግዚአብሔር ለሕይወት ይበጅ ዘንድ ለሰጠው መመሪያ ቀና የሆነ መልስ ነው፤ ይህ ጌታ የሰጠው የሕይወት መመሪያም ወደ ፍጹም በረከት ይመራል::

*1፥1፤* ይህ ንባብ ከኀጢአተኞች ጋር መተባበርንና የክፉ ሥራቸውም ተባባሪ መሆንን አስመልክቶ ደረጃ በደረጃ ይናገራል፤ ብፁዕ፣ ጌታን የሚፈሩና ፈቃዱን የሚፈጽሙ ሰዎች የሚያገኙትን ደስታ ያመለክታል (94፥12፤ 112፥1፤ 119፥1-2፤ 128፥1፤ ምሳ29፥18 ይመ፤ ከመዝ41፥1፤106፥3፤ ከምሳ14፥21፤ ከኢሳ56፥2 ጋር ያነጻጽሩ)፤ እነርሱም እግዚአብሔርን መታመኛ ያደረጉ ናቸው (40፥4፤ 84፥5-12፤ 144፥15፤ 146፥5፤ ምሳ16፥20፤ ኢሳ30፥18፤ ኤር17፥7 ይመ፤ ከመዝ2፥12፤ 34፥8 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ባርኮአቸዋል (በተለይ 41፥1-3፤ 144፥12-14፤ እንዲሁም ማቴ5፥3-12 ይመ):: መዝሙረኛው አንድ መንፈሳዊ ሰው ሊያገኘው በሚችለው ባርኮት በመጀመር፣ ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ እግዚአብሔርን በምድርና በሰማይ ባለው መቅደሱ እንዲያመሰግኑት በማሳሰብ ነገሩን ያጠቃልላል (መዝ150):: *የማይሄድ፤* በልማዳቸው መሠረት አብሮ ያልተጓዘ ማለት ነው:: *ምክር፤* በዚህ አገባቡ በሚገባ የታሰበበት ሐሳብ ወይም ምክር ማለት ነው (ምሳ 1፥10-19 ይመ):: *የማይቆም፤* ለክፉዎች ሐሳብ ራሱን ያልሰጠ ማለት ነው:: *ኀጢአተኞች፤* ቍ5 ይመ፤ ክፉ ሥራን የዘወትር ተግባር ያደረጉ፣ በደልንም መፈጸም እንደ ዋና የሕይወት ዘይቤ ያደረጉ ማለት ነው:: *የማይቀመጥ፤* በዚያ ላይ ልቡን ያላሳረፈ ማለት ነው:: *ፌዘኞች፤* በእግዚአብሔር ስም የሚያፌዙ፣ ሕጉንም ሁሉ በግልጽ የሚቃወሙ ናቸው::

1፥2 *ሕጉንም ... ያሰላስለዋል፤* በክፉዎች መንገድ ከመሄድ ይልቅ፣ ለሕይወቱ መመሪያ የሚሆነውን የእግዚአብሔርን ሕግ፣ ተግቶ ይፈልጋል ማለት ነው:: *በቀንና በሌሊት፤* ኢያ 1፥8 ይመ::

1፥3 *እንደማይጠወልግ ዛፍ፤* ኤር17፥8 ይመ:: አንድ ጻድቅ ሰው ምን ያህል የተባረከ እንደ ሆነ የሚያሳይ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው:: እንዲህ ያለ ዛፍ የነፋስን ኀይል ይቋቋማል፤ ጊዜውን ጠብቆ በማደጉም ሰውን፣ እንስሳትንና እፅዋትን በፍሬውና በጥላው ያገለግላል::

1፥4 *ነፋስ ጠራርጎ እንደሚወስደው ገለባ፤* ክፉዎች ምን ያህል የተረገሙና ከንቱም እንደ ሆኑ የሚያሳይ ዘይቤ ነው፤ መዝሙረኛው ይህን ዘይቤ በዚህ ቦታ የተጠቀመው፣ በመከር ወቅት የሚደረገውን ነገር ከክፉ ሰዎች ጋር ለማነጻጸር እንዲጠቅመን በማሰብ ነው:: በከብቶች እግር የተረገጠው አዝመራ በመንሽ ወደ ሰማይ ይበተናል:: እንዲህ የሚደረገው ፍሬውን ከገለባው ለመለየት ነው:: ፍሬው ወደ መሬት ተመልሶ ሲወድቅ ገለባው ግን ወደ ሰማይ እንደ ተበተነ ይቀራል:: ክፉዎችም ልክ እንዲሁ ናቸው፤ እንደ ገለባም ምንም የማይጠቅሙ ናቸው (የሩት 1፥22 ማብ ይመ)::

1፥5 *በፍርድ ፊት ... መቆም አይችሉም፤* እግዚአብሔር በሚፈርድበት ጊዜ ቍጣውን ሊቋቋሙ አይችሉም (76፥7፤ 130፥3፤ ዕዝ9፥15፤ ሚል3፥2፤ ማቴ25፥31-46፤ ራእ6፥17 ይመ):: *በጻድቃን፤* የእግዚአብሔርን ሰዎች ለማመልከት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከተጠቀሱት በርካታ መጠሪያዎች ውስጥ አንዱ ነው:: ይህ መጠሪያ ሰዎቹ እግዚአብሔርን እንደሚያከብሩትና ሕይወታቸውንም እንደ ፈቃዱ እንደሚመሩ ያሳያል:: እነዚህ ሰዎች በማንኛውም ማኅበራዊ ግንኙነትና ግንኙነቱ የሚጠይቀውን ግዴታ ተግባራዊ ያደርጋሉ፤ ይህንም ሲያደርጉ ኀይልና ሥልጣን ለሌሎች በረከት እንዲሆን እንጂ ሌሎችን ባሪያ የሚያደርግ መሆን እንደሌለበት በማስተዋል ነው:: *ማኅበር፤* በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ሕዝቦች ናቸው (ይህንንም በ22፥25፤26፥12፤ 35፥18፤ 40፥9-10፤ 111፥1፤ 149፥1 ላይ መመልከት ይቻላል፤ እንዲሁም መዝ15፥24 ይመ)::

1፥6 *መንገድ ... መንገድ፤* ሁለት ዐይነት ሰዎች (ክፉዎችና ጻድቃን) እንዳሉ ሁሉ ሁለት ዐይነት መንገዶችም አሉ (የክፉዎች መንገድና የጻድቃን መንገድ):: ከሁለት አንዱን የሚመርጡ፣ የመጨረሻ ዕድል ፈንታቸውም በምርጫቸው ላይ የተመሠረተ ነው::

*መዝሙር 2፤* ይህን ምዕራፍ የጻፈው ማን እንደሆነና የተጻፈውም መቼ እንደ ሆነ በውል አይታወቅም (በሐሥ4፥25 ላይ ጴጥሮስና ዮሐንስ የዚህ መዝሙር ደራሲ ዳዊት እንደ ሆነ አመልክተዋል፤ ይህም ሊሆን የቻለው በአይሁድ ልማድ መሠረት የመዝሙረ ዳዊት ጸሓፊ ዳዊት እንደ ሆነ ስለሚታመን ነው):: ይህ መዝሙር የቤተ መንግሥት መዝሙር ሲሆን በመጀመሪያ የተደረሰውም፣ ጌታ ከዳዊት ቤት ጋር ቃል ኪዳን በገባው መሠረት ከዳዊት ዘር የሚወጡ ነገሥታት በሚነግሡበት ሰዓት እንዲዘመር ታስቦ ነው (2ሳሙ7 ይመ):: ውሎ ሲያድር በዳዊት ቤት ላይ የፍርድ ቃል ከተነገረ በኋላና እግዚአብሔርም አንድ ቀን ከዳዊት ዘር በሚወጣው ታላቅ ልጅ በኩል ሕዝቡን እንደሚቤዠው ይፋ ከሆነ በኋላ ይህ መዝሙር መሢሐዊ መዝሙር መሆን ጀመረ:: ከዚህም በተጨማሪ የእግዚአቤሔርን ጌትነትና በእርሱም የተቀባውን መሲሕ የሚቀበሉ እንዲሁም "እግዚአብሔርን መጠጊያቸው የሚያደርጉ" (ቍ12) ምን ያህል የተባረኩ መሆናቸውን ያሳያል (የቍ 1፥1 ማብ ይመ):: ይህ መዝሙር ክርስቶስን የዳዊት ኀያል ልጅና እግዚአብሔር የቀባው መሢሕ አድርጎ በሚያመለክትበት ረገድ፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል::

2፥1-12 *ነገሥታት ስለምን ያጒረመርማሉ?* ይህ መዝሙር ጉልህ የሆኑ አራት መሠረታዊ ነገሮችን ይዞ ይገኛል፤ (1) የዓለም ሕዝቦችና መሪዎች እግዚአብሔር በቀባው ላይ የተነሡ መሆናቸውን በማመልከት፣ መዝሙረኛው ይጀምራል (1፥3ይመ፤ ከሐሥ4፥25-27 ጋር ያነጻጽሩ):: ይህ መዝሙር የዓለም ሕዝቦች በእግዚአብሔርና በሕጉ በቤዛውና በመሢሑ እንዲሁም ለሕይወት መመሪያ ይሆን ዘንድ በገለጠው ቃል ላይ በዐመፀኝነት መነሳታቸውን የሚያሳይ አሳዛኝ ገጽታ ይተርካል:: በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት አዲስ ኪዳንን የጻፉ አገልጋዮችም፣ ዓለም ከክርስቶስ፣ ከምእመ

ሰዎችስ ለምን ከንቱ ነገር ያውጠ
ነጥናሉ?
2 የምድር ነገሥታት ተነሡ፤
ገዦችም *በእግዚአብሔርና* በመሢሑ^
ላይ፣
ሊመክሩ ተሰበሰቡ፤
3 “ሰንሰለታቸውን እንበጥስ፣
የእግር ብረታቸውንም አውልቀን
እንጣል” አሉ።

4 በሰማይ ዙፋን ላይ የተቀመጠው
ይሥቃል፤
ጌታም ይሣለቅባቸዋል።
5 ከዚያም በቍጣው ይናገራቸዋል፤
በመዓቱም ያስደነግጣቸዋል፤
6 ደግሞም፣ “እኔ ግን በተቀደሰው
ተራራዬ፣
በጽዮን ላይ የራሴን ንጉሥ ሾምሁ”
ይላል።

7 *የእግዚአብሔርን* ሕግ ዐውጃለሁ፤
እርሱም እንዲህ አለኝ፤ “አንተ ልጄ ነህ፤
እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ፤*
8 ለምነኝ፤
*መንግሥታትን* ርስት አድርጌ፣
የምድርንም ዳርቻ ግዛት እንዲሆንህ
እሰጥሃለሁ።
9 አንተም በብረት በትር ትቀጠቅጣቸዋለህ፤~
እንደ ሸክላ ዕቃ ታደቃቸዋለህ።”

10 ስለዚህ እናንት ነገሥታት ልብ በሉ፤
እናንት የምድር ገዦችም፣
ተጠንቀቁ።
11 *እግዚአብሔርን* በፍርሃት አገልግሉት፤
ለእርሱ መራድም ደስ ያሰኛችሁ።
12 እንዳይቈጣና በመንገድ እንዳትጠፉ፣
ዝቅ ብላችሁ ልጁን ሳሙት፤
ቍጣው ፈጥኖ ይነዳልና።
እርሱን መጠጊያ የሚያደርጉ ሁሉ
የተባረኩ ናቸው።

## መዝሙር 3

### የመከራ ተቀባዩ የጧት ጸሎት

*ዳዊት ከልጁ ከአቤሴሎም በሸሸ ጊዜ የዘመረው መዝሙር*

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጠላቶቼ ምንኛ በዙ!

2፥2 1ሳሙ9፥16፤ መዝ48፥4፤ዮሐ1፥41፤ ሐሥ4፥25-26
2፥3 2ሳሙ3፥34፤ ኢዮ36፥8
2፥4 መዝ37፥13፤ ምሳ1፥26፤ኢሳ 37፥16፤40፥22፤66፥1
2፥5 መዝ6፥1፤21፥9 ፤27፥9፤38፥1፤79፥6፤9 0፥7፤110፥5
2፥6 ዘፀ15፥17፤2ነገ 19፥31፤መዝ9፥11፤10 ፥16፤24፥10፤48፥2፡11 ፤78፥68፤110፥2፤ 133፥3
2፥7 2ሳሙ7፥14፤ ማቴ3፥17፤4፥31፤ሐሥ 13፥33፤ዕብ1፥5፤5፥5
2፥8 ኢዮ22፥26፤ መዝ22፥27፤67፥7፤ ማቴ21፥38፤ራእ2፥26
2፥9 ዘፍ49፥10፤ዘፀ 15፥6፤ኢሳ30፥14፤ ኤር19፥10፤ራእ2፥27 ፤12፥5፤19፥15
2፥10 መዝ141፥6፤ ምሳ8፥15፤27፥11፤ አሞ2፥3
2፥11 1ዜና16፥30፤ መዝ9፥2፤35፥9፤103፥ 11፤104፥34፤ኢሳ 61፥10
2፥12 ቍ7፤ዘዳ9፥8፤ መዝ5፥11፤34፥8፤64፥10፤84፥12፤ራእ6፥16
3፥1 ርዕስ 2ሳሙ 15፥14

^2 ወይም *የተቀባው*
*7 ወይም ... *አባትህ ሆንሁ*
~9 ወይም *በብረት ዘንግ ትሰባብራቸዋለህ*

ናን፣ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጸው እውነት ጋር ተጻራሪ መሆኑን ገልጸዋል (ዮሐ15፥19፤ኤፌ6፥12)። (2) ዓለም እግዚአብሔርን ደግሞ ፈቃዱን ለመቃወም በመነሳቷ እግዚአብሔር በትዝብት ዐይን ይመለከታታል፤ ሐሳቧም ከንቱ መሆኑን እየተመለከተ ያፌዝባታል፤ (4-6) የሰው ዐመፅ የሚያበቃበት ወቅት እየቀረበ መሆኑንና እግዚአብሔርም አንድ ቀን መንግሥቱን በዚህ ምድር እንደሚያጸና ተመልክቶአል (ሮሜ1፥18፤ 1ተሰ5፥1-11፤ 2ተሰ2፥8፤ ራእ19፥11-21)። (3) እግዚአብሔር አብ የተወደደ ልጁን እንደሚልክ (ቍ7-9)፣ ይህም ልጅ የሕዝቦች ርስት እንደሆነና (ሐሥ13፥33፤ ዕብ1፥5፤ 5፥5 ይመ፤ ከማቴ3፥17፤ 17፥5፤ ከ2ጴጥ1፥17 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ተቃዋሚዎቹንም ድል እንደሚያደርግ ተስፋ ሰጥቶአል። ይህም ተስፋ እውን የሚሆነው ክርስቶስ በመጨረሻው ዘመን ወደ ምድር ተመልሶ ሲመጣና የእግዚአብሔርንም ጠላቶች ድል ሲነሣ ነው (ራእ12፥5፤ 19፥15 ይመ)። (4) መንፈስ ቅዱስ በመዝሙረኛው በማደር አስፈሪ የሆነው የፍርድ ቀን ከመድረሱ በፊት፣ የሰው ዘር በእግዚአብሔር ፊት ልብ ገዝቶ፣ መጠጊያውን እርሱን ብቻ እንዲያደርግ ያሳስባል (ቍ10-12፤ ከዕብ3፥7-9 ጋር ያነጻጽሩ)።

*2፥1-3፤ ሕዝቦች ያምፃሉ፤* በጥንት ቅርብ ምሥራቅ፣ አንድ ንጉሥ ዘውድ በሚደፋበት ወቅት ከዚህ ቀደም ለነበረው ንጉሥ ጸጥ ለጥ ብለው ይገዙ የነበሩ ሕዝቦችና ነገሥታት ለዐመፅ ይነሳሱ ነበር። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንደምናየው አዲስ የተቀባው ንጉሥ የነገሥታት ንጉሥ ተደርጎ ተቈጥሮአል።

*2፥1-2፤* በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ ንባብ በእንዴት ያለ መንገድ እንደ ዋለ ለመረዳት ሐሥ4፥25-28 ይመ።

2፥1 *ለምን?* መልስ አዘል ጥያቄ ሲሆን፣ ይኸውም፣ “እንዴት ቢደፍሩ ነው?” እንደ ማለት ነው።

2፥2 *በእግዚአብሔርና ... በመሢሑ፤* ጌታ በቀባው ላይ ማመፅ ማለት በቀቢው ላይ ማመፅ ማለት ነው። *በመሢሑ፤* የቍ 6-7 ማብ ይመ። ይህ መዝሙር በቀጥታ የሚመለከተው ከዳዊት ቤት የሚወጣውን ንጉሥ ሲሆን፣ ይህም በመጨረሻ በክርስቶስ ተፈጽሞአል። “መሢሕ” የሚለው የአማርኛ ቃል “የተቀባ” ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጕሙም “በእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ሥራ የተቀባ” እንደ ማለት ነው (የማቴ1፥17 ማብ ይመ)።

*2፥4-6፤ ጌታ በዐመፀኞች ላይ ይስቃል፤* እግዚአብሔር የዓለምን ኀያላን ዐመፀኞች ማኅበር እየተመለከተና የፌዝም ሳቅ እየሳቀ በቅድስቲቷ ከተማ በጽዮን የዳዊትን ሥርወ መንግሥት የመሠረተው እርሱ ራሱ እንደ ሆነ ይፋ ያደርጋል። 2፥4፤ 59፥8 ይመ።

2፥5 *በቍጣው ... በመዓቱም፤* የእግዚአብሔር ቍጣ ሁል ጊዜ የሚያሳየው እርሱ ጻድቅ አምላክ መሆኑን ነው (7፥11፤ እንዲሁም የ4፥1 ማብ ይመ)።

2፥6 *በተቀደሰው ተራራዬ፤* የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የሚገኝበት ቦታ ነው (2ዜና 33፥15 ይመ)፤ እንዲሁም 3፥4፤ 15፥1፤ 43፥3 (“ቅዱስ ተራራ”)፣ 46፥4 (“ቅዱስ ተራራ”) የተባለውን ይመ።

*2፥7-9፤* በጌታ የተቀባው መሲሕ የጌታን የንግሥ ዐዋጅ ያስታውቃል። አዲስ ኪዳን ይህንን ክፍል ለጌታ ትንሣኤ እንዴት እንዳዋለው ሐሥ13፥33 ይመ፤ እንዲሁም ጌታ ከመላእክት እንዴት እንደሚበልጥና ዕብ1፥5፣ ሊቀ ካህናትም ሆኖ እንዴት እንደ ተሾመ ደግሞ ዕብ5፥5 ይመ።

2፥7 *ልጄ ... ወለድሁህ፤* በጥንቱ መካከለኛው ምሥራቅ በአንድ ንጉሠ ነገሥትና በሥሩ በሚገኙት ነገሥታት መካከል ያለው ግንኙነት የሚገለጸው፣ “ጌታ” እና “አገልጋይ” በሚል መጠሪያ ብቻ ሳይሆን፣ “አባት” እና “ልጅ” በሚለው ጥምር ነበር። ይህ አገላለጽ እዚህ ላይ ውሎ መገኘቱም ጌታ መንፈስ ቅዱስ በተለመደው አባባል ይህን የአባትና የልጅ ግንኙነት መግለጹን ያመለክታል። ከዳዊት ዘር የሚወጣው ንጉሥ “አገልጋይ” እንዲሁም “ልጁ” ነው (2ሳሙ7፥5፡14)።

2፥8 *ርስት ... እሰጥሃለሁ፤* የተስፋዪቱ ምድር የጌታ ርስት እንደ ሆነች ሁሉ ይህም ለአንተ ግዛት ይሆንልሃል ማለት ነው (ዘፀ15፥17፤ እንዲሁም ኢሱ22፥19፤ መዝ28፥9፤ 79፥1፤ 82፥8 ይመ)። *የምድርንም ዳርቻ፤* ጌታ የቀባው ንጉሥ የሚቀበለው ግዛት፣ በመጨረሻ እስከ እግዚአብሔር ግዛት ድረስ ይዘልቃል።

*2፥9፤* በራእይ 12፥5፤ 19፥15 መሠረት ይህ ቃል ተፈጻሚ የሚሆነው ክርስቶስ በድል አድራጊነት ሲገዛ ነው፤ በራእ2፥26-27 ላይ ጌታ ኢየሱስ አሕዛብን ከሥሩ አድርጎ ሲገዛ ለእርሱ ታማኝ በመሆን እስከ መጨረሻው የቆሙትን የመንግሥት ተካፋይ አድርጎ እንደሚሾማቸው በግልጽ ተናግሮአል። *እንደ ሸክላ ዕቃ ታደቃቸዋለህ፤* ኤር19፥11 ይመ።

*2፥10-12፤* በዐመፀኛ ነገሥታት ማስጠንቀቂያ ሲሰጣቸው በዚህ ቦታ ይታያል።

2፥11 *ደስ ያሰኛችሁ፤* ጌታ ንጉሥ መሆኑን በደስታ ዐውጁ። *በመንቀጥቀጥ፤* በፍርሀትና በአክብሮት ማለት ነው።

2፥12 *በመንገድ እንዳትጠፉ፤* 1፥6 እና ማብ ይመ። *ሳሙት፤* ተገዥ መሆንን የሚያሳይ ምልክት ነው (1ሳሙ10፥1፤ 1ነገ19፥18፤ ሆሴ13፥2፤ እንዲሁም የዘፍ41፥40 ማብ ይመ)። በጥንት የአሦር ግዛት ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ለአንድ የአሦር ንጉሥ ተገዥ መሆናቸውን የሚያሳዩት እግሩንም በመሳም ነበር። *እርሱን፤* ጌታን ማለት ነው። *የተባረኩ ናቸው፤* 1፥1 እና ማብ ይመ።

*መዝሙር 3፤* ምንም እንኳን መዝሙረኛው በብዙ ጠላቶች የተከበበ ቢሆንም ጸሎቱን ግን ለጌታ ማቅረቡን አልተወም ነበር።

ስንቱስ በእኔ ላይ ተነሣ!
2ብዙዎች ነፍሴን፣ “እግዚአብሔር
አይታደግሽም” አሏት። ሴላ[ሠ]
3እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን ዙሪያዬን
የምትከልል ጋሻ ነህ፤
ክብሬና፣ ራሴንም ቀና ቀና የምታደርግ
አንተ ነህ።[ሬ]
4ወደ እግዚአብሔር ድምፄን ከፍ
አድርጌ እጮኻለሁ፤
እርሱም ከተቀደሰ ተራራው
ይመልስልኛል። ሴላ
5እተኛለሁ፤ አንቀላፋለሁ፤
እግዚአብሔር ደግፎ ይዞኛልና
እነቃለሁ።
6በየአቅጣጫው የከበበኝን፣
አእላፍ ሕዝብ አልፈራም።
7እግዚአብሔር ሆይ ተነሥ!
አምላኬ ሆይ፤ ታደገኝ፤
የጠላቶቼን ሁሉ መንጋጋ ትመታለህ፤
የክፉዎችንም ጥርስ ትሰባብራለህ።
8ማዳን የእግዚአብሔር ነው፤
በረከትህ በሕዝብህ ላይ ይሁን። ሴላ

3፥2 መዝ22፥8፤ 71፥11፤ኢሳ36፥15፤ 37፥20
3፥3 ዘፍ15፥1፤መዝ 27፥6
3፥4 ኢዮ30፥20፤ መዝ2፥6
3፥5 ዘሌ26፥6፤መዝ 17፥15፤139፥18
3፥6 ኢዮ11፥15፤ መዝ23፥4፤27፥3፤ 118፥11
3፥7 2ዜና6፥41፤ኢዮ 16፥10፤29፥17፤መዝ6 ፥4፤7፥1፤57፥4፤59፥1፤ 109፥21፤119፥153፤ ምሳ30፥14፤ኢሳ25፥9 ፤33፥22፤35፥4፤36፥ 15፤37፥20፤ኤር 42፥11፤ሰቆ3፥16፤ ማቴ6፥13
3፥8 ዘኍ6፥23፤መዝ 27፥1፤29፥11፤37፥39 ፤62፥1፤129፥8፤ኢሳ 43፥3:11፤44፥6:8፤45 ፥21፤ሆሴ13፥4፤ዮና2፥ 9፤ራእ7፥10

## መዝሙር 4

### የሠርክ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች የሚዜም የዳዊት መዝሙር*

1የጽድቄ አምላክ ሆይ፤
በጠራሁህ ጊዜ መልስልኝ፤
ከጭንቀቴ አሳርፈኝ፤
ማረኝ፤ ጸሎቴንም ስማ።

4፥1 ዘፍ32፥7፤መሳ2፥15፤መዝ13፥3፤17፥6፤30፥10፤ 54፥2፤69፥16፤84፥8፤86፥7፤88፥2፤102፥2

ሠ2 በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ በተደጋጋሚ የሚገኝ ሲሆን የቃሉ ትርጉም በትክክል አይታወቅም፤ የሙዚቃ ምልክት ሳይሆን አይቀርም

ሬ3 ወይም *እግዚአብሔር ... ወደ ላይ የምታነሣ ክብሬ ሆይ*

*መዝሙር* 3 እና 4 የእግዚአብሔርን ክብርና (ቍ3፤ 4፥2 እንዲሁም የሁለቱን ቍጥሮች የጽሑፉን ማብ ይመ) የመዝሙረኛውን የሌሊት እንቅልፍ የሚያወሱ በመሆናቸው የእርስ በርስ ትስስር አላቸው (ቍ5፤ 4፥8)። በቍ5 ላይ ዳዊት ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነሣ በሰላም እንደሚነሣ በእርግጠኝነት ይናገራል፤ ምክንያቱም ሌሊት ተኝቶ ሳለ እግዚአብሔር ይጠብቀዋል። በ4፥8 ላይ እግዚአብሔር ሌሊቱን ሙሉ ጥበቃ ስለሚያደርግለት ወደ መኝታው የሚሄደው በእርጋታ መንፈስ እንደ ሆነ ይናገራል። ገና ከመግቢያው ላይ የመዝሙረኛው ጸሎት ጠዋት በደኅና ከመነሣቱና ሌሊት ደግሞ በሰላም ከመተኛቱ ጋር ጐን ለጐን ተያይዞ በመቅረቡ እግዚአብሔር በእርሱ የሚታመኑትን ሁሉ ቀንና ሌሊት እንደ ሚንከባከባቸው መዝሙረኛው ያረጋግጣል፤ ይህንን የሚመስሉ ጸሎቶች በዚህ የመዝሙር መጽሐፍ ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠቅሰዋል።

3 ርእስ *በሸሸ ጊዜ፤* 2ሳሙ 15፥13-17፥22 ይመ። ዳዊት በእንዴት ያለ አስቸጋሪ ሕይወት ውስጥ እንዳለፈ በ13 መዝሙሮቹ ውስጥ ተመልክቶአል (3፤7፤18፤34፤51-52፤ 54፤56-57፤59-60፤63፤142)፤ ከመዝ142 በስተቀር ሁሉም በአንደኛውና በሁለተኛው መጽሐፍ ላይ ይገኛሉ፤ “ደራሲ እና ርእስ” የሚለውን ወይም ንዑስ ርእስ ይመ።

*3፥1-2፤* የዳዊትን ፍላጎት የሚያሳይ ሲሆን በብዙ ጠላቶች መከበቡን ያመለክታል።

*3፥2፤* 22፥7-8፤ 71፥10-11 ይመ። *መዝሙረኛው* ከፉጨቋኞቻቸው በእግዚአብሔርና በአገልጋዮቹ ላይ ምን ያህል እንደሚሳለቁ ለማሳየት ሲል ሁኔታውን በተደጋጋሚ ይጠቅሳል (የ1፥1 ማብ ይመ)። *ሴላ፤* የጽሑፉን ማብ፤ እንዲሁም በመግቢያው ላይ “ደራሲ እና ርእስ” የሚለውን ወይም ንዑስ ርእሱን ይመ።

*3፥3-4፤* ጸሎቱን ችላ በማይለው አምላክ ላይ ዳዊት ምን ያህል እንደሚታመን ያመለክታል።

3፥3 *ጋሻ፤* በጥንት እስራኤላውያን ዘንድ ንጉሥ እንደ መጠጊያ ወይም እንደ ጋሻ ተደርጎ ይቈጠራል (በ7፥10፤ 47፥9፤ 59፥11፤ 84፥9፤ 89፥18፤ ዘፍ15 ላይ የጽሑፉን ማብ ይመ)። ጌታም የሕዝቡ ጋሻ እንደ ሆነ በብዙ ቦታዎች ላይ ተጠቅሶአል (84፥11፤ 91፥4፤ 115፥9-11፤ ዘዳ33፥29፤ ምሳ30፥5)፤ እግዚአብሔርን ጋሻ ማድረግ የተለመደ መሆኑንም መዝሙረኛው በሰፊው አውስቶአል (18፥2:30፤28፥7፤ 33፥20፤ 119፥114፤144፥2 ይመ)። *ክብሬ፤* መዝሙረኛው፣ ጌታ ጠባቂውና የሚያስፈልገውንም ሁሉ የሚያዘጋጅለት በመሆኑ በእርሱ ሐሤት አደረገ (የ2፥11 ማብ ይመ)፤ አማራጭ ትርጕሙን ይመ። *ራሴንም ቀና ቀና የምታደርግልኝ፤* በጠላቶቼ ላይ ድልን ትሰጠኛለህ ማለቱ ነው (110፥7 ይመ)።

3፥4 *ከተቀደሰ ተራራው፤* የእግዚአብሔር ማደሪያ ቦታ ነው፤ በሰማይ ማደሪያ እንዳለው ሁሉ በምድርም እንዲሁ ማደሪያ አለው (የ2፥6 ማብ ይመ)።

*3፥5-6፤* የዳዊት ዋስትና እግዚአብሔር ነው፤ ምክንያቱም እርሱ ቀንም ሆነ ሌሊት ይጠብቀዋል።

*3፥5፤* በራሱ ትጉ መሆን ቢያቅተው እንኳን ዘወትር ትጉ የሆነው አምላክ ይጠብቀዋል (4፥8 ይመ)።

*3፥7-8፤* የዳዊት ጸሎት ነው።

3፥7 *ተነሥ ... ታደገኝ፤* አብዛኛውን ጊዜ በዕብራይስጥ ፈሊጣዊ ንግግር ውስጥ ትእዛዛዊ አንቀጾች በመጀመሪያ ላይ የሚመጡት አንድ ሰው ፈጥኖ እንዲነሣ ጥሪ ለማድረግ ሲፈልግ ነው (በዘፀ 12፥31 ላይ “ተነሡ” በዘዳ2፥13፤ በመሳ7፥9 “ተነሡ” የሚለውን ይመ)። በግጥሙ ውስጥ እንደሚታየው በፈሊጣዊ ንግግሩ ውስጥ ያሉት ሁለት ትእዛዛዊ አንቀጾች በሁለቱም ስንኞች ላይ ተበትነው ይታያል። ስለዚህ የመዝሙረኛው ጸሎት “ተነሣ ደግሞም ታደገኝ” የሚል ይሆናል። *እግዚአብሔር ... አምላኬ፤* ይኸውም የእኔ አምላክ እግዚአብሔር እንደ ማለት ነው፤ ሁለቱ የመለኮት ስሞችም፣ በሁለቱም ስንኞች ላይ እንደዚሁ ተበትነው ይገኛሉ። *መንጋጋ ትመታለህ፤* ምናልባት ጠላቶቹን ከዱር አራዊት ጋር ለማመሳሰል የተጠቀመበት ሊሆን ይችላል (የ7፥2 ማብ ይመ)።

3፥8 *ማዳን የእግዚአብሔር ነው፤* በመዝሙረኛው ጸሎት ውስጥ አንድ የማይታጣ ባሕርይ ቢኖር መዝሙረኛው መቼም ይሁን መች ጸሎቱ የተሰማ ወይም የሚሰማ መሆኑን በሙሉ ልብ ማመኑ ነው (ይኸውም በ6፥8-10፤ 7፥10-17፤ 10፥16-18፤ 12፥7፤ 13፥5-6 ላይና በሌላም ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል፤ የ12፥5-6 ማብ ይመ)፤ በዚህ ቦታ እንደሚታየው የዳዊት ጽኑ እምነት፣ ለእግዚአብሔር ሰዎች ቋሚ ምስክር ነው። *በረከትህ በሕዝብህ ላይ ይሁን፤* 25፥22፤ 28፥8-9፤ 51፥18 ይመ። መዝሙረኛው የሕዝብ መሪ እንደ መሆኑ መጠን፣ በኀያሉ ንጉሥ በእግዚአብሔር ፊት ቆመ።

*መዝሙር 4፤* መከራ ደርሶ ነበርና (ምናልባት ድርቅ ሊሆን ይችላል) ብዙዎች የተሻለ ይሆንልናል በሚል እምነት ጌታን በማመን ፈንታ የከነዓናውያንን አማልክት ተከትለው ስለነበር ከዚያ ታላቅ ቍጣ ለማምለጥ ሲባል የቀረበ ጸሎት ሳይሆን አይቀርም፤ በም3 ላይ የቀረበውን መግቢያ ይመ።

4 ርእስ፤ ዕን3፥19 ይመ። *ለመዘምራን አለቃ፤* ምናልባት ይህ መዝሙር ዳዊት በደረሳቸውና የእስራኤልም የመዘምራን አለቆች ባሰባሰቧቸው መዝሙሮች ላይ እንዲጨመር የታሰበ መዝሙር ሳይሆን አይቀርም። ምክንያቱም በጥንት እስራኤላውያን ዘንድ መዝሙሮችን ማሰባሰብ የቆየ ልማድ ነበር። መዝሙሮች ደግሞ የእግዚአብሔርን አባትነትና ተንከባካቢነት በጥሞና ለማሰላሰል ይረዳሉ ተብሎም ይታመን ነበር። ምንም እንኳን ይህ መዝሙር በአንደኛ መደብ ተባዕት ነጠላ ቍጥር የተነገረ ቢሆንም በማኅበር ግን ይዘመር ነበር። *በበገናዎች፤* የመዝ6፤ 54-55፤ 61፤ 67፤ 76 ርእሱን ይመ። ይህ የቅዳሴ ምልክት ሲሆን፣ ሌዋውያኑ መዝሙሩን በከራርና በዋሽንት መዘመር እንዳለባቸው ያመለክታል (1ዜና23፥5፤ 25፥1:3:6 ይመ፤ ከመዝ 33፥2፤ 43፥4፤ 71፥22 ጋር ያነጻጽሩ፤ የመዝ39እና 42 ማብ ርእሶችን ይመ)።

*4፥1፤* መዝሙረኛው ልቡን በእግዚአብሔር ፊት አፍስሶ አል። *የጽድቄ፤* በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ (እንዲሁም በብዙ ብሉይ ኪዳን ክፍሎች ውስጥ) እግዚአብሔር “ጻድቅ” ነው ሲባል

2ሰዎች ሆይ፤ እስከ መቼ ድረስ ክብሬን
ዝቅ[ሀ] ታደርጋላችሁ?
እስከ መቼስ ድረስ ከንቱ ነገርን
ትወዳላችሁ?
ሐሰትንስ[ለ] ትሻላችሁ? ሴላ
3እግዚአብሔር ጻድቁን ለራሱ እንደ ለየ
ዕወቁ፤
እግዚአብሔር ወደ እርሱ በተጣራሁ ጊዜ
ይሰማኛል።
4ስትቈጡ ኀጢአት አትሥሩ፤
በአልጋችሁም ላይ ሳላችሁ፣
ልባችሁን መርምሩ፤ ጸጥም በሉ። ሴላ
5የጽድቅን መሥዋዕት አቅርቡ፤
በእግዚአብሔርም ታመኑ።
6ብዙዎች፣ "አንዳች በጎ ነገር ማን
ያሳየናል? ይላሉ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ የፊትህ ብርሃን
በላያችን ይብራ።
7ስንዴና አዲስ የወይን ጠጅ በብዛት
ባመረቱ ጊዜ ከሚያገኙት ደስታ ይልቅ፣
አንተ ልቤን በታላቅ ሐሤት ሞልተኸዋል።
8በሰላም እተኛለሁ፤ እንቀላፋለሁም፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ያለ ሥጋት
የምታሳድረኝ አንተ ብቻ ነህና።

## መዝሙር 5

### የጧት ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በዋሽንት የሚዘመር፣ የዳዊት መዝሙር*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ቃሌን አድምጥ፤
መቃተቴንም ቸል አትበል።
2ንጉሤና አምላኬ ሆይ፤
ወደ አንተ እጸልያለሁና፣
ድረስልኝ ብዬ ስጮህ ስማኝ።
3እግዚአብሔር ሆይ፤ በማለዳ ድምፄን
ትሰማለህ፤
በማለዳ ልመናዬን በፊትህ አቀርባለሁ፤
ፈቃድህንም በጥሞና እጠባበቃለሁ፤
4አንተ በክፋት ደስ የምትሰኝ አምላክ
አይደለህም፤
ክፉም ከአንተ ጋር አያድርም።
5እብሪተኞች በፊትህ መቆም አይችሉም፤
ክፉ አድራጊዎችንም ሁሉ ጠላህ።
6ሐሰት የሚናገሩትን ታጠፋቸዋለህ፤
ደም የተጠሙትንና አታላዮችን፣
እግዚአብሔር ይጸየፋቸዋል።
7እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት
ወደ ቤትህ እገባለሁ፤
አንተንም በመፍራት፣
ወደ ተቀደሰው መቅደስህ እሰግዳለሁ።
8እግዚአብሔር ሆይ፤ ከጠላቶቼ የተነሣ፣
በጽድቅህ ምራኝ፤
መንገድህንም በፊቴ አቅናልኝ።

4፥2 ዘፀ16፥7፤መሳ 2፥17፤1ሳሙ4፥21፤2ነገ19፥26፤ኢዮ8፥22፤መዝ31፥6፤35፥26፤40፥4፤ኤር13፥25፤16፥9፤አሞ2፥4
4፥3 መዝ6፥8፤12፥1፤30፥4፤31፥23፤79፥2፤ሚክ7፥2፡7፤1ጢሞ4፥7፤2ጴጥ3፥11
4፥4 መዝ63፥6፤ዳን 2፥28፤ኤፌ4፥26
4፥5 መዝ31፥6፤115፥9፤ምሳ3፥5፤28፥26፤ኢሳ26፥4፤ዮሐ 14፥1
4፥6 ዘኍ6፥25
4፥7 ዘፍ27፥28፤ዘዳ 28፥51፤ኢሳ9፥3፤35፥10፤65፥14፡18፤ሐሥ 14፥17
4፥8 ዘሌ26፥6፤ዘኍ 6፥26፤ዘዳ33፥28፤ኢዮ 11፥18፤ኤር 32፥37
5፥1 1ነገ8፥29፤መዝ 17፥1፤38፥9፤40፥1፤1 16፥2፤ኢሳ35፥10፤ 51፥11፤ዳን9፥18
5፥2 ኢዮ19፥7፤24፥ 12፤36፥5፤መዝ44፥4፤ 68፥24፤84፥3
5፥3 መዝ62፥1፤ 119፥81፤130፥5፤ኢሳ 28፥19፤50፥4፤ኤር21 ፥12፤ሕዝ46፥13፤ዕን 2፥1፤ሰፎ3፥5፤ሮሜ 8፥19
5፥4 መዝ1፥5፤11፥5 ፤104፥35፤ምሳ2፥22
5፥5 2ነገ19፥32፤ መዝ1፥5፤45፥7፤73፥3 ፤75፥4፤101፥3፤119፥ 104፤ምሳ8፥13፤ኢሳ 33፥19፤37፥33
5፥6 ምሳ19፥22፤ ዮሐ8፥44፤ሐሥ5፥3፤ራእ21፥8
5፥7 ዘዳ13፥4፤2ሳሙ 12፥16፤1ነገ8፥48፤ መዝ138፥2፤ኤር44፥10፤ዳን6፥26
5፥8 1ነገ8፥36፤መዝ 23፥3፤31፥1፤71፥2፤85፥13፤89፥16፤ምሳ8፥20፤ዮሐ1፥23

[ሀ]2 ወይም *ወደ ራሳችሁ*
[ለ]2 ወይም *የሐሰት አማልክት*

በሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ታማኝ ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር ታማኝነቱን ለሕዝቡ የሚያሳየው በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ነው። የተጨቈኑት ካሣ የሚያገኙት፣ የተራቡትም ቸርነት የሚቀበሉት ከእርሱ ነው። *አሳርፈኝ፤* "ዘና ያለ ቦታ ስጠኝ" እንደ ማለት ነው (18፥19 እና ማብ ይመ)።

*4፥2-3፤* ዳዊት ከእርሱ አምላክ ከድተው ወደ ባእድ አማልክት የሄዱትን ሰዎች ክፉኛ ይወቅሳቸዋል፤ ጌታም ጸሎቱን እንደሚሰማና መልስም እንደሚሰጠው ያረጋግጥላቸዋል።

4፥2 *እስከ መቼ፤* በመግቢያው ላይ "ትምህርተ መለኮት" የሚለውን ክፍል ይመ፤ እንዲሁም የ6፥3 ማብ ይመ። *ክብሬን፤* ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ልዩ ኅብረት የክብሩ መሠረት ሆኖለታል፤ ምናልባትም በዚህ ቦታ የሚናገረው ስለ እግዚአብሔር ክብር ሊሆን ይችላል። የዚህን ጽሑፍ ማብ፣ የ3፥3 ማብ ይመ)። *ሴላ፤* የጽሑፉን ማብ፤ በ3፥2 ላይ ይመ፤ እንዲሁም በመግቢያው ላይ "ደራሲና ርእስ" የሚለውን ይመ።

4፥3 *ጻድቁን፤* "ሃሳድ" ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የተተረጐመ ሲሆን በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ 26 ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል፤ ይህ ቃል ብዙ ጊዜ "ጻድቃን" ተብሎ ተተርጕሞአል፤ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከሚጠሩበት ስም መካከል አንዱ ሲሆን፣ ሕይወታቸውን ለእርሱ አሳልፈው የሰጡና ለእርሱም ታማኝ ሆነው መገኘት እንዳለባቸው ያሳስባል።

*4፥4-5፤* ዝም ብሎ ከመበሳጨትና ከመጨነቅ ይልቅ፣ ወደ ጌታ መመልከት ተገቢ መሆኑን ያስገነዝባል (ይህ ንባብ በቍጣና በጭንቀት የምትርዱት ለምንድን ነው ተብሎ ሊተረጐም ይችላል)።

4፥4 *ስትቈጡ ኀጢአት አትሥሩ፤* ጳውሎስ እነዚህኑ ቃላት ለየት ባለ ዐውደ ምንባብ ውስጥ ተጠቅሞባቸዋል (ኤፌ 4፥26 ይመ)።

*4፥6፤* አስተማማኝ የሆነ ነገር በሌለበት ወቅት፣ ዳዊት የጌታን ባርኮት በጸሎት ተማጸነ፤ "ማን" የሚለው ቃል ከአማልክት መካከል "ችሎታ ያለው ማን ነው?" ማለት ነው። *የፊትህ ብርሃን በላያችን ይብራ፤* የ13፥1 ማብ ይመ፤ በጥንት እስራኤላውያን ዘንድ የተለመደ የልመና ቃል ነው፤ ሰዎች የእግዚአብሔርን በረከት ማግኘት ሲፈልጉ "የፊትህ ብርሃን በላያችን ይብራ" ይላሉ፤ ይህ አባባል ከአሮን የቡራኬ ንግግር የተወረሰ ነው (ዘኍ6፥25-26 ይመ)።

*4፥7-8፤* የዳዊትን ልበ ሙሉነት ያመለክታል (3፥8 ማብ ይመ)።

4፥7 *ልቤን፤* በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "ልብ" የሰዎች መንፈስ እምብርት ወይም ማእከል ነው፤ ሐሳብና ፍላጎት ሁሉ የሚመነጩት ከልብ ነው፤ በሌላ ቦታ ልብ "የሕይወት ምንጭ" ተብሎ ተገልጾአል (ምሳ4፥23)።

*4፥8፤* 3፥5-6 ይመ። *በሰላም፤* ያለ አንዳች ጭንቀት ማለት ነው።

*መዝሙር 5፤* ይህ የጧት ጸሎት ምናልባት የጧት መሥዋዕት በሚቀርብበት ሰዓት የቀረበ ጸሎት ሳይሆን አይቀርም፤ ጸሎቱም የቀረበው መዝሙረኛው ብዙ ጠላቶች በተነሱበት ወቅት ነው፤ ስለዚህ ታዳጊውን ፍለጋ መዝሙረኛው ጮኸ።

5 ርእስ *የመዘምራን አለቃ፤* የመዝ 4 የርእስ ማብ ይመ። *በዋሽንት፤* በዕብራይስጥ ይህ ቃል ተጠቅሶ የሚገኘው በዚህ ቦታ ብቻ ነው፤ የቃሉም ፍቺ በትክክል አይታወቅም።

*5፥1-3፤* መዝሙረኛው የልቡን ሸክም ሁሉ አንድ በአንድ ይናገራል። ምክንያቱም ጸሎቱን የሚሰማው አምላክ እንዳለ ፍጹም እርግጠኛ ነው። ጸሎቱንም የሚያደርሰው በትእዛዝ አንቀጾች ነው፤ "አጽም" እያለ ለጥንት ሰዎች የተለመደ አነጋገር ነው።

5፥2 *ንጉሤና፤* በመግቢያው ላይ "ትምህርተ መለኮት" የሚለውን ይመ።

*5፥4-6፤* የእግዚአብሔር ጽድቅ በምድር ላይ እንዲሰፍን የቀረበ ልመና ነው።

5፥5 *እብሪተኞች፤* የ31፥23 ማብ ይመ።

*5፥7-8፤* መዝሙረኛው ልመናውን የሚያቀርበው ፍጹም ትሑት በሆነ ልብ ነው (ቍ7)፤ ለልመናው መታመኛም ያደረገው የእግዚአብሔርን ምሕረትና (ቍ7) ጽድቅ ነው (ቍ8)።

5፥7 *በምሕረትህ ብዛት፤* የ6፥4 ማብ ይመ።

5፥8 *በጽድቅህ፤* የ4፥1 ማብ ይመ። *መንገድህን ... አቅናልኝ፤* የምትመራኝ መንገድ ቀና፣ ደልዳላና ለስላሳ ሆኖ ከመሰናክልና ከፈተና ነጻ ይሁንልኝ ማለት ነው። መዝሙረኛው

[9]በንግግራቸው ውስጥ እውነት የለም፤
ልባቸው የጥፋት ጕሬ ነው፤
ጕሮሮአቸው የተከፈተ መቃብር ነው፤
በምላሳቸውም ይሸነግላሉ።
[10]አምላክ ሆይ፤ የእጃቸውን ስጣቸው!
ተንኰላቸው መውደቂያቸው ይሁን፤
ከኀጢአታቸው ብዛት የተነሣ
አስወግዳቸው፣
በአንተ ላይ ዐምፀዋልና።
[11]አንተን መጠጊያ የሚያደርጉ ሁሉ ግን
ደስ ይበላቸው፤
ዘላለም በደስታ ይዘምሩ፤
ስምህን የሚወዱ በአንተ ደስ
እንዲላቸው፣
ተከላካይ ሁንላቸው።
[12]እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ጻድቃንን
ትባርካቸዋለህ፤
በሞገስህም እንደ ጋሻ ትከልላቸዋለህ።

5፥9 መዝ12፥2፤ 28፥3፤36፥3፤ምሳ15፥4፤ኤር5፥16፤9፥8፤ሉቃ11፥44፤ሮሜ3፥13
5፥10 መዝ78፥40፤ 106፥7፤107፥11፤ሰቆ1፥5፤3፥42
5፥11 ኢዮ22፥19፤ መዝ33፥1፤69፥36፤81፥1፤90፥14፤92፥4፤95፥1፤119፥132፤145፥7
5፥12 ዘፍ15፥1፤ መዝ32፥7፤112፥2
6፥1 መዝ2፥5
6፥2 ዘኍ12፥13፤ መዝ4፥1፤22፥14፤26፥11፤31፥10፤32፥3፤38፥3፤42፥10፤61፥2፤77፥3፤102፥3፤142፥3፤ኢሳ40፥31፤ኤር3፥12፤8፥18፤12፥15፤31፥20፤ሕዝ21፥7
6፥3 1ሳሙ1፥14፤ 1ነገ18፥21፤ኢዮ7፥11፤መዝ4፥2፤31፥7፤38፥8፤55፥4፤89፥46፤ኢሳ 6፥11፤ኤር4፥14፤ዕን 1፥2፤ዘካ1፥12፤ዮሐ 12፥27፤ሮሜ9፥2፤ 2ቆሮ2፥4

## መዝሙር 6
## በጭንቅ ጊዜ የቀረበ ጸሎት

ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች የሚዘመር፤ የዳዊት መዝሙር በሸሚኒት*

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ በቍጣህ አትገሥጸኝ፤
በመዓትህም አትቅጣኝ።
[2]እግዚአብሔር ሆይ፤ ዐቅመ ቢስ ነኝና
ማረኝ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ዐጥንቶቼ
ተናግተዋልና ፈውሰኝ።
[3]ነፍሴ እጅግ ታውካለች፤
እስከ መቼ፤ አንተ እግዚአብሔር ሆይ፤
ይህ እስከ መቼ ድረስ ይሆናል?

*የ6 መግቢያ ርእስ ሲሆን በሙዚቃ ውስጥ የሚጠቀሙበት ቃል ሳይሆን አይቀርም።

እግዚአብሔር በዚህ ዐይነት መንገድ እንዲመራውና ጠላቶቹም በእርሱ ላይ እንዳይሳለቁ ይለምናል (25፥4፤ 27፥11፤ 139፥24፤ 143፥8-10 ይመ)። *ምራኝ፤* አንድ የበግ እረኛ በጎቹን እንደሚመራ ማለቱ ነው (23፥3 ይመ)።

*5፥9-10፤* ምላሽ የሚፈልግ ክስ ነው (በመዝሙረኛው ጸሎት ውስጥ የተለመደ አነጋገር ነው)።

5፥9 *በንግግራቸው ውስጥ፤* እንደ መዝሙረኛው ባሉ ሰዎች ላይ ዘወትር የሚወረወር ክፉ መሣሪያ ቢኖር አንደበት ነው (በዚህ በሚያስደንቅ ሁኔታ ነገሩን ለማየት መዝ 12 እንዲሁም የ10፥7 ማብ ይመ)። ክፉ አንደበት ልክ እንደ ሰይፍ እንደ ሆነ መዝሙረኞቹ ከሕይወት ልምድ ያውቁታል (57፥4፤ 64፥3-4 ይመ)። አንደበታቸውን ለክፉ ነገር የሚያውሉትን እግዚአብሔር እንዲቀጣቸው በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠይቆአል፤ ምክንያቱም መዝሙረኛው ትክክለኛ ፍርድ የሚገኘው ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ እንደ ሆነ ያውቃል። *ልባቸው፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *ጕሮሮአቸው ... መቃብር፤* የ49፥14 ማብ ይመ። *በምላሳቸውም ይሸነግላሉ፤* አንድን ንጉሥ ከመንበረ ሥልጣኑ ለማውረድ በሚደረገው ሤራ ውስጥ ሽፍጥና ሐሰት ትልቅ ቦታ አለው፤ በዚህ ንጉሥ ላይ የተደረገውም ይሄው ነው፤ መዝ 17፤25፤27-28፤31፤35፤41፤52፤54-57፤59፤63-64፤71፤86፤109፤140-141 ይመ። ብዙውን ጊዜ እንዲህ ያሉ ዘመቻዎች በአንድ ንጉሥ ላይ የሚደረጉት ንጉሡ በጣም በሚያዝንበትና እግዚአብሔርም የተወው በሚመስለው ጊዜ ነው (ይኸውም በመዝ 25፤35፤ 41፤ 75፤ 86፤109 ላይ እንዳለው ሁኔታ ማለት ነው)። እንዲህ ከሆነ ደግሞ፣ እግዚአብሔር ተለይቶታል ተብሎ ስለሚገመት ሕዝብን ለመምራት ብቃት የለውም (በመሆኑም የሕዝቡን ደኅንነት በሚያስተማምን ሁኔታ ሊጠብቅ አይችልም፤ 1ሳሙ8፥20፤ 11፥12፤ 12፥12፤ 25፥28፤ 2ሳሙ3፥18፤ 7፥9-11 ይመ)፤ በየትኛውም አጋጣሚ ለጠላት ጥቃት በቀላሉ የተጋለጠ ነው (3፥2፤ 22፥7-8፤ 71፥11 ይመ)። እንዲሁም የ86፥17 ማብ ይመ፤ ጳውሎስ ይህንን ጥቅስ በሮሜ 3፥13 ላይ በእንዴት ያለ መንገድ እንደ ተጠቀመበት ይመ።

*5፥10፤* በዚህ መዝሙር ውስጥ እንዲህ ያሉ ከባድ "የርግማን ቃላት" መኖራቸው ብዙ ሰዎችን በእጅጉ አሳስቦአል። አንዳንዶቹ እንዲያውም ኢየሱስ በመስቀል ላይ የፈጸመውን ምሳሌነትና (ሉቃ23፥34) "ቀኝ ጉንጭህን ለሚመታ፣ ግራ ጉንጭህን አዙርለት" እንዲሁም "ስደትና መከራ ለሚያደርሱባችሁ ጸልዩላቸው" (ማቴ5፥39-44) በማለት የተናገረውን በመጥቀስ መቋጫ የሌለው ክርክር ውስጥ ሊገቡ ችለዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እነዚህ "ርግማን መሰል ቃላት" በእርግጥ ርግማን አይደሉም፤ ይልቁንም በመዘምራኑ ላይ የደረሰውን በደል እግዚአብሔር እንዲመለከትና ዳኝነትም እንዲሰጥበት የሚማጠኑ ናቸው (28፥4 ይመ)፤ በምድር እንኳ ፍትሕ ይሰጥ የለ (ዘዳ25፥1-3 ይመ)። መዘምራኑ አንድ በደል የደረሰበት ሰው በደሉን በገዛ እጁ መበቀል እንደሌለበት በሚገባ ያውቃሉ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር "በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ" (ዘዳ32፥35፤ ምሳ 20፥22) በማለት ተናግሮአል። ስለዚህ ጉዳያቸውን ለመለኮታዊው ዳኛ አቀረቡ (ኤር15፥15 ይመ)። *አስወግዳቸው፤* ከፊትህ አስወግዳቸው ማለት ነው፤ እንዲሁም ከሆነ የበረከትና የሕይወት ምንጭ ከሆነው ይራቁ ማለት ነው (ዘፍ3፥23ይመ)። *በአንተ ላይ ዐምፀዋልና፤* በመዝሙረኛው ላይ ማሤር ማለት በእግዚአብሔር ላይ ማሤር ማለት ነው፤ እናም መዝሙረኛውን መቃወም፣ እግዚአብሔርን መቃወም ነው።

*5፥11፤* ቅዱሳንም በምልጃው ውስጥ ይታቀፉ ዘንድ መዝሙረኛው የጸሎቱን ክልል ሰፋ አድርጎ ይጸልያል። *ስምህን፤* የእግዚአብሔር ስም የባሕርዩ ደግሞም የማንነቱ መገለጫ ነው (የዘፀ 3፥14-15፤ 34፥6-7 ማብ ይመ)። የእግዚአብሔር ስም ከእግዚአብሔር የተለየ ሕልውና በራሱ የለውም፤ ስሙ ሁልጊዜ የማንነቱ መገለጫ ነው፤ ሕዝቡም ማንነቱን የሚያውቀው በስሙ በኩል ነው። ስለዚህ የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ፣ ስሙ በሕዝቡ መካከል የሚያድርበት ምድራዊ ማደሪያ ነው (74፥7፤ ዘዳ12፥5፡ 11፤ 2ሳሙ7፥13ይመ)፤ ሕዝቡም ስሙን በመጥራት ጸሎት ማድረግ ይችላሉ (79፥6፤ 80፥18፤ 99፥6፤ 105፥1፤ 116፥4፡13፡17 ይመ)። የጌታ ስም ሕዝቡን ይጠብቃል (20፥1፤ ምሳ18፥10 ይመ)፤ ጌታም ሕዝቡን የሚያድነው በስሙ ነው (54፥1 ይመ)፤ ማዳኑም ስሙ ቅርብ መሆኑን ይመሰክራል (52፥9 ይመ)፤ በዚህም ምክንያት ቅዱሳኑ በስሙ ይታመናሉ (20፥7፤ 33፥21)፤ በስሙም ተስፋ ያደርጋሉ (52፥9)፤ ለስሙም ምስጋና ያቀርባሉ (7፥17፤ 9፥2፤ 18፥49)፤ በስሙም ሐሤት ያደርጋሉ (89፥16)። እግዚአብሔር መወደድና መፈራት እንደሚገባው ሁሉ፣ ስሙም ሲወደድና ሲፈራ ታይቶአል (ፍቅር 69፥36፤ 119፥132፤ መፈራት 61፥5፤ 86፥11፤ 102፥15)።

*5፥12፤* የ3፥8 ማብ ይመ። *ጻድቃንን፤* የ1፥5 ማብ ይመ።

6፤ ይህ መዝሙር በጽኑ ሕመም ጊዜ የቀረበ ጸሎት ነው። መዝሙሩ የአካልና የመንፈስ ስብራት የደረሰበትን ሰው ሁኔታ የሚያንጸባርቅ ነው። ይህ መዝሙር በጥንት ቤተ ክርስቲያን የቅዳሴ ሥርዐት ውስጥ ከሰባቱ የንስሓ መዝሙሮች ጋር ተደምሮ ይቈጠር ነበር (ሌሎቹ የንስሓ መዝሙሮች 32፤38፤51፤102፤130፤143 ናቸው)።

6 *ርእስ፤* የመዝሙር 4 ርእስ ማብ ይመ። *በበገናዎች፤* በመዝሙር 12 እና በ1ዜና 15፥21 ርእስ ላይ ይገኛል፤ ምናልባት ባለስምንት አውታር የሙዚቃ መሣሪያዎችን ሳያመለክት አይቀርም (የጽሑፉን ማብ ይመ)።

*6፥1-3፤* እግዚአብሔር ምሕረቱን ያወርድ ዘንድ የቀረበ ጸሎት ነው፤ ምንም እንኳን በኀጢአቱ ምክንያት ሊገሥጸው ሕመም ቢልክበትም (32፥3-5፤ 38፥1-8፡17-18)፣ መዝሙረኛው ግን እግዚአብሔር በቍጣው እንዳይመጣና በኀጢአቱም እንዳያጠፋው ልመና ያቀርባል፤ እንዲያ ባይሆንማ ኖሮ ሞት ወዲያውኑ በመጣ ነበር (ቍ5፤ እንዲሁም 130፥3 ይመ)።

*6፥1፤* መዝሙር 38 የሚጀምረውም ልክ እንዲሁ ነው። *በቍጣህ ... በመዓትህም፤* የ2፥5 ማብ ይመ። *አትገሥጸኝ ... አትቅጣኝ፤* 39፥11 እንዲሁም የ3፥7 ማብ ይመ።

6፥2 *ዐጥንቶቼ፤* የሰው አካል ውስጠኛ ክፍል እንደ መሆናቸው መጠን፣ ሁለንተናን ይወክላሉ።

6፥3 *ነፍሴ፤* ይህ ቃል በሥጋና በመንፈስ ወይም በመዝሙረኛው "ውስጣዊ አካልና ውጫዊ አካል" መካከል ልዩነት መኖሩን ከቶ አያሳይም፤ ቃሉ ሁልጊዜ የሚያመለክተው ጠቅላላ

4 እግዚአብሔር ሆይ፤ ተመለስና ሕይወቴን
ታደጋት፤
ስለ ጽኑ ፍቅርህም አድነኝ፤
5 በሞት የሚያስታውስህ የለምና፤
በሲኦልስ[a] ማን ያመሰግንሃል?

6 ከመቃተቴ የተነሣ ዝያለሁ፤
ሌሊቱን ሁሉ በልቅሶ ዐልጋዬን አርሳለሁ፤
መኝታዬንም በእንባዬ አሾቃለሁ።
7 ዐይኖቼ በሐዘን ብዛት ደክመዋል፤
ከጠላቶቼም ሁሉ የተነሣ ማየት
ተስኖአቸዋል።

8 እናንተ ክፉ አድራጊዎች ሁሉ፤ ከእኔ
ራቁ፤
እግዚአብሔር የልቅሶዬን ድምፅ
ሰምቶአልና።
9 እግዚአብሔር ልመናዬን አድምጦአል፤
እግዚአብሔር ጸሎቴን ይቀበላል።
10 ጠላቶቼ ሁሉ ያፍራሉ፤ እጅግ
ይደነግጣሉ፤
በመጡበት ይመለሳሉ፤ ድንገትም
ይዋረዳሉ።

## መዝሙር 7
## በስደት ጊዜ የጻድቁ ሰው ጸሎት

*ዳዊት በብንያማዊው በኩዝ ምክንያት ለእግዚአብሔር የዘመረው መዝሙር*

1 እግዚአብሔር ስምላኬ ሆይ፤ አንተ
መሸሸጊያዬ ነህ፤
ከሚያሳድዱኝ ሁሉ አድነኝ፤ ታደገኝም፤
2 አለበለዚያ እንደ አንበሳ ይዘነጣጥሉኛል፤
የሚያድነኝ በሌለበትም ይበጫጭቁኛል።
3 እግዚአብሔር ስምላኬ ሆይ፤ ይህን አድርጌ
ከሆነ፣
በደልም በእጄ ከተገኘ፣
4 በጎ ለዋለልኝ ክፉ መልሼ ብሆን፣
ጠላቴንም በከንቱ ዘርፌ ከሆነ፣

6፥4 መዝ13፥5፤25፥
16፤31፥2:16፤69፥16፤
71፥2፤77፥8፤85፥7፤8
6፥16፤88፥2፤102፥2፤
119፥41:132፤ኢሳ
54፥8:10
6፥5 መዝ30፥9፤88፥
10-12፤115፥17፤መክ
9፥10፤ኢሳ38፥18
6፥6 መሳ8፥5፤ኢዮ
3፥24፤7፥3፤16፥16፤2
3፥2፤መዝ12፥5፤77፥3
፤102፥5፤ሰቆ1፥8:11:2
1:22፤ሉቃ7፥38፤ሐሥ
20፥19
6፥7 ኢዮ16፥8፤መዝ
31፥9፤69፥3፤119፥82
፤ኢሳ38፥14
6፥8 መዝ5፥5፤119፥
115፤139፥19፤ማቴ
7፥23
6፥9 መዝ28፥6፤
116፥1
6፥10 2ነገ19፥26፤
መዝ40፥14
7 ርዕስ ዕን3፥1
7፥1 መዝ2፥12፤3፥7
፤11፥1፤31፥1:15፤119፥86:157:161 7፥2 ዘፍ49፥9፤መዝ3፥2፤
71፥11፤ራእ4፥7 7፥3 ኢሳ59፥3 7፥4 መዝ35፥7:19 ፤ምሳ24፥28

[a]5 ወይም *በመቃብር*

አቋምን ሲሆን መዝሙረኛው ሕያውና የሚያስብም መሆኑን ያመለክታል። ዕብራውያን "ዐጥንት" እና "ነፍስ" ሲሉ ሁለት የተለያየ ነገር መናገራቸው አይደለም፤ በጥንት ምሥራቃውያን ዘንድ በሁለቱ ቃላት መካከል መሠረታዊ ልዩነት የለም፤ ጸሓፊው ራሱን ለመግለጽ የተጠቀመበት ሁለት ዐይነት መንገድ ነው (31፥9፤ 63፥1)። *ይህ እስከ መቼ ድረስ?* በመግቢያው ላይ፣ "ትምህርተ መለኮት" የሚለውን ይመ፤ በመዝሙረኛው ጸሎት ውስጥ እንዲህ ያለውን አቤቱታና ጩኸት መስማት በጣም የተለመደ ነው (አብዛኛውን ጊዜ "እስከ መቼ?" ወይም "መቼ?" ወይም "ስለምን?" የሚሉ አቤቱታዎችን እናገኛለን)። ይህ አቤቱታ መዝሙረኛው ከሥቃዩ ገና አለመገላገሉንና በመካከላቸውም ያለውን ግንኙነት መሠረት በማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር ሙግት መግጠሙንም ያሳያል (የ4፥1 ማብ ይመ)።

*6፥4-5፤* ከሞት ለመዳን የቀረበ ልባዊ ጸሎት ነው።

6፥4 *ስለ ጽኑ ፍቅርህም፤* የዕብራይስጡ ቃል ወዳጅ መሆኑን ያመለክታል። የእግዚአብሔርን ጽኑ ፍቅር፣ ቸርነትና ምሕረት መሠረት አድርጎ ልመና ማቅረብ በብሉይ ኪዳን የተለመደ ነው፤ ይህ የልመና ቃል ጌታ ለእስራኤል (ዘጸ7፥9:12)፣ እንዲሁም ለዳዊ ትና ለቤቱም የገባውን ቃል ኪዳን የሚያሳይ ነው (89፥24: 28: 33፤ 2ሳሙ7፥15፤ ኢሳ55፥3 ይመ)።

*6፥5፤* መዝሙረኛው ለእግዚአብሔር ማቅረብ የሚገባው ምስጋና በመጓደል ላይ መሆኑን ያሳስባል፤ ከዚያም አልፎ ሕያዋን እንጂ ሙታን ምሕረቱንም ሆነ ታዳጊነቱን ሊያስታውሱ እንደማይችሉ በግልጽ ይናገራል። እስራኤላውያን ሞትን የሚረዱት እንደሚያዩት ነው፤ ምክንያቱም ሞት የሕይወት ተቃራኒ ነው። ምንም እንኳ ስለ ትንሣኤ ያላቸው አመለካከት ገና ያልዳበረ ቢሆንም መሠረታዊ እሳቤው ግን ከአመለካከታቸው ውስጥ ጨርሶ አልጠፋም። ሆኖም ቅዱሳን በሞት ከተለዩ በኋላ ምን ሁኔታ እንደሚገጥማቸው ግልጽ የሆነ አመለካከት የላቸውም። የብሉይ ኪዳን ጸሓፊዎች፣ ሰው የተፈጠረው ለሕይወት እንጂ ለሞት እንዳልሆነ በሚገባ ያውቃሉ፤ የእግዚአብሔርም ፈቃድ ሕዝቡ በሕይወት እንዲኖርና እግዚአብሔርም በሞት ላይ ሥልጣን እንዳለው ያውቃሉ፤ ከዚህ በተጨማሪ ሞት በማንኛውም ሰው ላይ ሊደርስ እንደሚችልና ይህንንም በጸጋ መቀበል ተገቢ ምሆኑን ያውቃሉ፤ ምክንያቱም ቅዱሳን ጊዜው ደርሶ በሞት ሲለዩ በእግዚአብሔር ክንድ ላይ ያርፋሉ (ዘፍ15፥15፤ 25፥8፤ 47፥30፤ 49፥33፤1ነገ2፥2 ይመ)። ሞት በሕይወት የሚገኙትን ሰዎች ከሚመጣው ክፉት (2ነገ22፥20፤ ኢሳ57፥1-2 ይመ) የሚገላግል በመሆኑ በጻድቃን ዘንድ እንደ በረከት ሊታይ ይችላል። ከዚህም በላይ የጻድቃን ሞት ከክፉዎች ሞት እጅግ የተሻለ ነው (ዘኍ 22፥10 ይመ)፤ ሞት ለጻድቃን የነገር ሁሉ መጨረሻ አይደለም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለጻድቃን ያዘጋጀላቸው ብዙ ነገር አለ (በተለይ 16፥9-11፤ 17፥15፤ 49፥14-15፤ 73፥24፤ እንዲሁም የዘፍ5፥24 ማብ ይመ)። መዝሙረኛው ከእግዚአብሔር ጋር ሙግት የገጠመው በሕይወት ለመኖር ሲል ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም እግዚአብሔር ምስጋናን የሚያገኘው ከሕያዋን በመሆኑ ነው።

*6፥6-7፤* መዝሙረኛው ሕመሙ ስለ በረታበትና ጠላቶቹም ስላየሉበት በሌሊት ያቀረበው ጸሎት ነው።

6፥6 *ከመቃተቴ የተነሣ ዝያለሁ፤* የግጥሙ ዐቢይ ሐሳብ ነው፤ በመሆኑም የመዝሙረኛውን ጽኑ ስብራት አጉልቶ ያሳያል፤ የመዝሙሩን ኀይለ ቃል በመዝሙሩ መካከል ላይ ማምጣት በመጽሐፈ መዝሙር ውስጥ በተደጋጋሚ የታየ ስልት ነው (የ8፥4፤ 21፥7፤ 23፥4፤ 34፥8-14፤ 42፥8፤ 47፥5-6፤ 48፥8፤ 54፥4፤ 71፥14፤ 74፥12፤ 76፥7፤ 82፥50፤ 86፥9፤ 92፥8፤ 97፥7፤ 113፥5፤ 138፥4-5፤ 141፥5 ማብ ይመ፤ እንዲሁም በመግቢያው ላይ "ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ" የሚለውን ይመ)።

6፥7 *ዐይኖቼ ደክመዋል ... ማየት ተስኖአቸዋል፤* በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንደሚታየው ዐይን የሚደክመው በዐቅም ማነስ (38፥10፤ 1ሳሙ14፥27:29፤ እንዲሁም የጽሑፉን ማብ ይመ፤ ኤር14፥6 ይመ)፣ በሐዘን (ብዙውን ጊዜ ሐዘን ከመከራ ጋር የተያያዘ ነው 31፥9፤ 88፥9፤ ኢዮ17፥7፤ ሰቆ2፥11) እና ተስፋ እውን ሳይሆን ሲቀር ነው (69፥3፤ 119፥82:123፤ ዘዳ28፥32፤ ኢሳ 38፥14 ይመ)። *ከጠላቶቼም ሁሉ፤* የ5፥9 ማብ ይመ።

*6፥8-10፤* አስተማማኝና ብሩህ የሆነም ተስፋ መኖሩን የሚያመለክት የመደምደሚያ ቃል ነው።

*6፥10፤* መዝሙረኛው ወደ ዙፋኑ ሲመለስ ጠላቶቹ ይዋረዳሉ።

*መዝሙር 7፤* ጠላቶች በተነሡ ጊዜ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት የሚቀርብ አቤቱታ ነው።

7 ርእስ *መዝሙር፤* የጽሑፉን ማብ ይመ። ቃሉ የሚገኘው በዚህ ቦታ ብቻ ነው (የቃሉን የብዙ ቍጥር አጠቃቀም አስመልክቶ ዕን3፥1 ይመ)። *ኩዝ፤* በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማንነቱ በየትም ቦታ አልተገለጸም፤ ነገር ግን ከብንያም ወገን በመሆኑ የሳኦል ደጋፊ ሳይሆን አልቀረም፤ በዚህም ምክንያት ነው ርእሱ ይህን መዝሙር ሳኦል ዳዊትን ለማጥፋት ከነበረው ቍርጠኛ ሐሳብ ጋር ያዛመደው። በመግቢያው ላይ "ጸሓፊውና አርእስቶቹ" የሚለውን ወይም ንዑስ ርእሱን ይመ።

*7፥1-2፤* በዳዊት አቤቱታ ላይ የተመሠረተ የመጀመሪያ ማጠቃለያ ሐሳብ ነው።

7፥1 *መሸሸጊያዬ፤* ራሳቸውን በታማኝነት ለእግዚአብሔር የሰጡ ሰዎች እግዚአብሔርን መሸሸጊያቸውና መታመኛቸው በማድረግ ያሉባትን ሁኔታ ለእርሱ ማስረከብ ይችላሉ። ፍትሕ ሲረገጥና አስከፊ ሁኔታ ሲያጋጥም፣ ራሳችንን በእግዚአብሔር ጥበቃ ሥር ማድረግና በፊቱም ያለንን ታማኝነትና ጽድቅ መሠረት በማድረግም ልመናችንን ማቅረብ እንችላለን (ቍ3-5:8)።

7፥2 *እንደ አንበሳ፤* ዳዊት በግ ጠባቂ በነበረበት ወቅት አንበሶች ይተናኮሉት ነበር (1ሳሙ17፥34-35 ይመ)። በመጽሐፈ መዝሙር ውስጥ የጠላትን ትንኮሳ ከዱር አራዊት በተለይም ከአንበሳ ጋር ማዛመድ የተለመደ ይትበሀል ነው (10፥9፤17፥12፤ 22፥12-13:16:20-21፤35፥17፤57፥4፤58፥6፤124፥6 ይመ)።

*7፥3-5፤* ዳዊት ንጹሕ መሆኑን በግልጽ ይናገራል፤ ጠላት እንዲነሣበት ያደረገው ምንም ነገር የለም።

7፥5 *ይያዘኝ፤* "እኔን" ሲል "ክብሬን" እንደ ማለት ሲሆን

5 ጠላቴ አሳዶ ይያዘኝ፤
ሕይወቴን ከምድር ይቀላቅል፤
ክብሬንም ከዐፈር ይደባልቅ:: ሴላ
6 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ በመዓትህ ተነሥ፤
በቍጣ በተነሡብኝ ላይ ተነሥ፤
አምላኬ ሆይ፤ ንቃ፤ ትእዛዝም አስተላልፍ!
7 የሕዝቦች ጉባኤ ይክበብህ፤
አንተም ከላይ ሆነህ ግዛቸው፤
8 *እግዚአብሔር* በሕዝቦች ላይ ይፈርዳል::
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እንደ ጽድቁ
ፍረድልኝ፤
ልዑል ሆይ፤ እንደ ቅን አካሄዴ
መልስልኝ::
9 ልብንና ኵላሊትን የምትመረምር፣
ጻድቅ አምላክ ሆይ፤
የክፉዎችን ዐመፅ አጥፋ፤
ጻድቁን ግን አጽና::
10 ጋሻዬ† ልዑል አምላክ ነው፤
እርሱ ልበ ቅኖችን ያድናቸዋል::
11 እግዚአብሔር ጻድቅ ዳኛ ነው፤
ቍጣውንም በየዕለቱ የሚገልጥ አምላክ
ነው::
12 ሰው በንስሓ የማይመለስ ከሆነ ግን፣
ሰይፉን‡ ይስላል፤
ቀስቱን ይገትራል::
13 የሚገድሉ ጦር ዕቃዎቹን አሰናድቶአል፤
የሚንበለበሉትን ፍላጻዎቹንም
አዘጋጅቶአል::
14 ክፋትን እያማጠ ያለ ሰው፣
ቅጥፈትን አርግዞ፣ ሐሰትን ይወልዳል::
15 ጕድጓድ ምሶ ዐፈሩን የሚያወጣ፣
ባዘጋጀው ጕድጓድ ራሱ ይገባበታል::
16 ተንኰሉ ወደ ራሱ ይመለሳል፤
ዐመፃውም በገዛ እናቱ ላይ ይወርዳል::
17 ስለ ጽድቁ *ለእግዚአብሔር* ምስጋና
አቀርባለሁ፤
የልዑል *እግዚአብሔርን* ስም በመዝሙር
እወድሳለሁ::

## መዝሙር 8

### የፈጣሪ ግርማ በፍጥረቱ ላይ

*ለመዘምራን አለቃ፣ በዋሽንት የሚዜም፤ የዳዊት መዝሙር*

1 *እግዚአብሔር* አምላካችን ሆይ፤
ስምህ በምድር ሁሉ ላይ ምንኛ
ግርማዊ ነው!
ክብርህ ከሰማያት በላይ፣
ከፍ ከፍ ብሎአል::
2 ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ ሕፃናት አፍ፣
ምስጋናን¹ አዘጋጀህ፤
ከጠላትህ የተነሣ፤
ባላንጣንና ቂመኛን ጸጥ ታሰኝ ዘንድ::

7፥5 ዘፀ15፥9፤2ሳሙ22፥43፤2ነገ9፥33፤ ኢዮ7፥21፤ኢሳ10፥6፤ሰቆ3፥16
7፥6 2ዜና6፥41፤ መዝ35፥23፤44፥23፤ 138፥7
7፥7 መዝ68፥18
7፥8 ዘፍ3፥5፤20፥5 ፤ዘኍ24፥16፤1ሳሙ2 6፥23፤1ዜና16፥33፤ መዝ18፥20፤ማር5፥7
7፥9 1ዜና28፥9፤መዝ 26፥2፤37፥23፤40፥2፤ ኤር11፥20፤ራእ2፥23
7፥10 ኢዮ33፥3፤መዝ3፥3
7፥11 ዘፍ18፥25፤ ዘዳ 9፥8፤መዝ9፥8፤ 67፥4፤75፥2፤96፥13፤ 98፥9፤ኢሳ11፥4፤ኤር 11፥20
7፥12 ዘዳ32፥41፤ 2ሳሙ22፥35፤መዝ21 ፥12፤ኢሳ5፥28፤ 13፥18፤ሕዝ3፥19
7፥13 መዝ11፥2፤ 18፥14፤64፥3
7፥14 ኢሳ59፥4፤ያዕ 1፥15
7፥15 ኢዮ4፥8፤መዝ 35፥7፡8፤40፥2፤94፥13 ፤ምሳ26፥27
7፥17 ዘፍ14፥18፤ 2ዜና31፥2፤መዝ5፥8፤ ሮሜ15፥11፤ዕብ2፥12
8፥1 ዘፀ15፥11፤1ዜና 16፥10፤መዝ57፥5፤ 8፥5፤113፥4፤148፥13፤ዕን3፥3፤ሉቃ2፥9
8፥2 መዝ143፥12፤ ማቴ21፥16

†10 *ወይም የኔ ልዑል*
‡12 *ወይም ሰው ንስሓ ካልገባ፣ እግዚአብሔር ሰይፉን ...*
¹2 *ወይም ብርታትን*

የአንድን ሰው ሁለንተና የማመልከቻ ዘዴ ነው (16፥19፤30፥12፤ 57፥8፤108፥1 እና ማብ ይመ)::

*7፥6-9፤* የምድር ሁሉ ጌታ የሆነው በሕዝቦች ላይ እንዲፈርድ፣ በተለይ ደግሞ ለዳዊት አቤቱታ ብያኔ እንዲሰጥ የሚማጠን አቤቱታ ነው::

7፥6 *በመዓትህ፤* ቍ11እና የ2፥5 ማብ ይመ:: *ተነሥ ... ተነሥ፤* የ3፥7 ማብ ይመ:: *ንቃ፤* ክፉት እየተንሰራፋ ሲሄድ፣ የተገፉ ሰዎችም በከንቱ ሲጮኹ (ወደ በኣል በከንቱ እንደ ጮኹ ሁሉ 1ነገ18፥27) ጌታ አያንቀላፋም (121፥4 ይመ):: መዘምራኑ አቤቱታቸውን የገለጹበት ቋንቋ ምን ያህል እንደተጨነቁ በግልጽ ያሳያል፤ በእግዚአብሔርም ዝምታ ትዕግሥት ያጡ ይመስላል፤ ምክንያቱም እንዲያ ያለ ችግር ውስጥ ገብተው ሳለ ዝም ብሎአቸዋል (80፥2፤ እንዲሁም 78፥65፤ ኢሳ51፥9 ይመ)::

7፥8 *ጽድቁ፤* ቍ3-5 ይመ::

7፥9 *ልብንና ኵላሊትን፤* ልብንና አሳብን ማለት ነው፤ በእስራኤላውያን ዘንድ እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ አላቸው፤ ይኸውም ልብ የሰውን ውስጠኛና ለባዊት ክፍል ያመለክታል (የ4፥7 ማብ ይመ):: "ልብንና ኵላሊትን መፈተን" እግዚአብሔር የሰውን ድብቅ ሐሳብና ምኞት አንድም ሳይቀር መመርመር የሚችል አምላክ መሆኑን የሚያመለክት አገላለጽ ነው (ኤር11፥20፤ 17፥10፤ 20፥12 ይመ):: *ጻድቅ፤* የ4፥1 ማብ ይመ:: *ጻድቁን፤* የ1፥5 ማብ ይመ::

*7፥10-13፤* ዳዊት እምነት ያለውና ጸሎቱም የሚሰማለት መሆኑን ያመለክታል (3፥8 ማብ ይመ)::

7፥10 *ጋሻዬ፤* የ3፥3 ማብ ይመ:: *ልበ ቅኖችን፤* የ4፥7 ማብ ይመ::

7፥11 *በየዕለቱ፤* የእግዚአብሔር ሙሉ ፍርድ አንድ ቀን የሚገለጥ ቢሆንም፣ ነገሩን በአንድ ቀን ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም፤ መዝሙረኛው የሚማጠነው ፍርድህ አንድ ቀን ይገለጥ እያለ ሳይሆን፣ ዛሬውኑ ይታይ እያለ ነው::

*7፥14-16፤* በእግዚአብሔር ግዛት ውስጥ፣ "ክፉት አያዋጣም" በሚለው የተለመደ ጥበባዊ አባባል ዳዊት ራሱን ያጽናናል::

*7፥17፤* ምስጋና ለማቅረብ የተገባ መሐላ ነው:: በመጽሐፈ መዝሙር ውስጥ የሚገኙ ጸሎቶች፣ በተስፋ የተሞሉና እንዲህ ያለ መሐላ የያዙ ናቸው:: ይህም የእስራኤላውያንን ሃይማኖታዊ አሳቤ የሚያንጸባርቅና ምስጋና ሁልጊዜ ትድግናን ተከትሎ መምጣት እንዳለበት የሚያሳይ ነው፤ እግዚአብሔር እውነተኛ ምስጋናን እንዲቀበል ካስፈለገ ሕዝቡን መታደግ አለበት:: እንዲህ ያለው ምስጋና፣ ከምስጋና ቍርባን ጋር በመሆን በቤተ መቅደስ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ለእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ይሠዋ ነበር (50፥14-15፡23፤ እንዲሁም የ9፥1 ማብ ይመ):: *ልዑል፤* የዘፍ14፥19 ማብ ይመ:: *የእግዚአብሔር ስም፤* የ5፥11 ማብ ይመ::

*መዝሙር 8፤* እግዚአብሔር እንዴት ያለ ኀያል ፈጣሪና ልዕልናውም እንዴት ያለ ገናና መሆኑን የሚያወሳ መዝሙር ነው (ከቍ1 እና 9 እንደምንረዳው የመዝሙረኛው ውዳሴ ያተኰረው በእግዚአብሔር ጌትነት ላይ ነው፤ እንዲሁም የ9፥1 ማብ ይመ) ዘፍጥረት ም1 (በተለይም ቍ26-28) እግዚአብሔር እንዴት ያለ ብርቱ ፈጣሪ እንደ ሆነ በግልጽ ያሳያል፤ ዳዊት ግን ይህንን የተናገረው ከራሱ ልምድ ተነሥቶ ነው (ይህንን የተናገረው ምናልባት አያሌ የሰማይ ብርሃናት ከአድማስ እስከ አድማስ ተዘርግተውና አስደናቂ ብርሃናቸውንም ቀንና ሌሊት ሲረጩ ተመልክቶ ሊሆን ይችላል፤ ዳዊት እንዲህ ያለውን ትንግርት ያስተዋለው ከዕለት ተዕለት ተግባሩ ተለይቶና አእምሮውም በጥልቅ ምርምር ውስጥ በነበረበት ሰዓት ነው):: ዳዊት በሁለት ሁኔታዎች እጅግ ተደንቆአል፤ (1) የእግዚአብሔር ክብር በሰማይ ላይ ፈስሰው በሚታዩት ከከዋክብት መገለጹና፣ (2) እግዚአብሔር በሚያስደንቅ ሁኔታ ራሱን በሰው ደረጃ ማስገኘቱ፣ እንደ ኢምንት የሚቈጠረውን ሰው ማስታወሱና ለእርሱም ታላቅ ሞገስን መስጠቱ እንዲሁም የፍጥረት ሁሉ የበላይ አዛዥ እንዲሆን መፍቀዱ ናቸው::

8፥1ሀ *ስምህ፤* የ5፥11 ማብ ይመ::

*8፥1ለ-2፤* ክብሩ በሰማያት ሁሉ የተዘረጋው ልዑል አምላክ፣ በእርሱ ላይ የተሰለፉትን የጨለማ ኀይላት ለማሳፈር ሲል ከሕፃናት ምስጋናን ለመቀበል ወሰነ (ይህንን ንባብ አዲስ ኪዳን በእንዴት ያለ መንገድ እንደ ተጠቀመበት ለማስተዋል ማቴ21፥16 ይመ)::

8፥2 *ቂመኛን፤* 44፥16 ይመ፤ አድብቶ የሚበቀል ሰው ማለት ነው (ይህ ግን በ9፥12 ላይ እንደ ተመለከተው ዐይነት አይደለም)::

*8፥3-5፤* የእግዚአብሔር እጅ ሥራ የሆነው ይህ እጅግ

3የጣቶችህን ሥራ፣
ስማያትህን ስመለከት፣
በስፍራቸው ያኖርሃቸውን፣
ጨረቃንና ከዋክብትን ሳይ፣
4በሐሳብህ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው
ምንድን ነው?
ትጠነቀቅለትም ዘንድ የሰው ልጅ
ምንድን ነው?
5ከመላእክት በጥቂት አሳነስኸው፤
የክብርንና የሞገስን ዘውድ አቀዳጀኸው።
6በእጆችህ ሥራ ላይ ሾምኸው፤
ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛህለት፤
7በጎችንና ላሞችን ሁሉ፣
የዱር አራዊትንም፣
8የሰማይ ወፎችንና፣
የባሕር ዓሦችን፣
በባሕር ውስጥ የሚርመሰመሱትንም
ሁሉ አስገዛህለት።
9እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፤
ስምህ በምድር ሁሉ ላይ ምንኛ
ግርማዊ ነው!

8፥3 ዘፍ1፥16፤15፥5፤ዘፀ8፥19፤ዘዳ10፥14፤1ዜና16፥26፤ 2ዜና2፥12፤መዝ102፥25፤1ቆሮ15፥41
8፥4 1ዜና29፥14
8፥5 ዘፍ1፥26፤መዝ21፥5፤103፥4
8፥6 ዘፍ1፥28፤1ነገ5፥3፤ኢዮ10፥3፤መዝ19፥1፤102፥25፤145፥10፤ኢሳ26፥12፤29፥23፤45፥11፤1ቆሮ15፥25:27፤ኤፌ1፥22፤ዕብ1፥10፤2፥6-8
8፥7 ዘፍ2፥19፤13፥5፤26፥14
8፥8 ዘፍ1፥26
8፥9 ቍ1
9፥1 ዘዳ4፥34፤መዝ86፥12፤111፥1፤119፥2:10:145፤138፥1

## መዝሙር 9'

### በክፉ ላይ ፍርድ

*ለመዘምራን አለቃ፤ በሙትላቤን ቅኝት፤ የዳዊት መዝሙር*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ በፍጹም ልቤ
አመሰግንሃለሁ፤
ስለ ድንቅ ሥራዎችህም ሁሉ እናገራለሁ።

'ምዕ9 መዝ9 እና 10 በመጀመሪያው የጥንት ቅጅ ላይ አንዳንዶቹ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆህያት የሚጀምሩ እንዲሁም ጅማሬው ወይም መጨረሻው ትርጕም አዘል የሆነ አንድ ወጥ ግጥም ነበር። በሰብዓ ሊቃናት ውስጥ ሁለቱም አንድ መዝሙር ናቸው።

ግዙፍና ውብ ዓለም (19፥1-6፤ 104፥19-23 ይመ)፣ ጥልቅ አድናቆትን በመፍጠር እግዚአብሔር ኢምንት ለሆነውና ዛሬ ታይቶ ነገ ለሚጠፋው ሰው ምን ያህል ቸርነት እንዳደረገ ሐሳብን ከምርመራ ላይ ያውላል (144፥3-4 ይመ)። (እግዚአብሔር ሰውን ከቁም ነገር በመቍጠሩ ኢዮብ ያሰማውን ቅሬታ በኢዮ7፥17-21 ላይ ይመ)።

*8፥3፤* የዘፀ8፥19 ማብ ይመ።

*8፥4-6፤* ዕብ2፥6-8 ከሰብዓ ሊቃናት ትርጕም (ብሉይ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ ከዕብራይስጥ ቋንቋ ወደ ግሪክ ቋንቋ በግብፅ እስክንድርያ እንደተተረጐመ ይታወቃል፤ ይህ መጠሪያ የሚያገለግለው ለዚህ ትርጕም ሲሆን፣ በእንግሊዝኛ ይህ ትርጕም ስፕቱዋጀንት ይባላል) ላይ በመጥቀስ ይህንን ንባብ ሰዎችን ሁሉ ለወከለውና የሰዎችንም መጨረሻ ሙሉ በሙሉ እውን ላደረገው ሥጋ ለለበሰው ለእግዚአብሔር ልጅ ለኢየሱስ ክርስቶስ አውሎታል። እንግዲህ የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ ስለ ክርስቶስ በሚመሠክርበት ወቅት ትንቢታዊነት የሌላቸውን ቃላት ሥነ-ፍጻሜያዊ አንድምታ እንዲኖራቸው አድርጓል ማለት ነው። ጳውሎስም በ1ቆሮ15፥27 ላይ ቍ6ን በተመሳሳይ መልክ ተጠቅሞበት ይገኛል (እንዲሁም ኤፌ1፥22 ይመ)።

8፥4 *በሐሳብህ፣ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ፤* በቀጥታ ሲተረጐም ጕዳዬ የምትለው ማለት ነው (የዘፍ8፥1 ማብ ይመ)። *የሰው ልጅ፤* ብዙውን ጊዜ "ሰው" የሚለውን ግጥማዊ ዘይቤ የሚተካ ነው (80፥17፤ 144፥3፤ እንዲሁም የሕዝ2፥1 ማብ ይመ)። *ምንድን ነው?* በቍ1እና 9 ላይ ይህ ሐረግ የተመለሰበት የዕብራይስጡ ቃል "እንዴት?" ይለዋል፤ የመዝሙሩም ማእከላዊ ሐሳብ የሚጀምረው ከዚሁ ነው (የ6፥6 ማብ ይመ)።

8፥5 *ከመላእክት፤* እግዚአብሔርን ሰማያዊ በሆነው ዙፋኑ ዙሪያ የሚያጅቡ ወይም የሚከቡ ታላላቅ ሰማያዊ ፍጥረታት ናቸው (ለምሳሌ በኢሳ6፥2 እንደ ተመለከተው ዐይነት ነው)፤ ይሁን እንጂ የጽሑፉን ማስታወሻ መመልከት ይጠቅማል።

*8፥6-8፤* ዘፍ1፥26-27 ይመ። ሰው ገዥ እንደ ሆነ እሙን ነው፤ ይህም "የክብሩና የሞገሱ" (ቍ5) አንደኛው ገጽታ ነው። ሰው የተፈጠረውም ለገዥነት ነው (ጳውሎስና የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ ከዚህ ንባብ ውስጥ እንዴት ያለ ሥነ-ፍጻሜያዊ አንድምታን መዘው እንዳወጡ ለማየት ቍ4-6 ይመ)።ይህ የሰው አገዛዝ ግን ፍጹምና ነፃ አይደለም። ሰው የሚገዛው ከእግዚአብሔር ጋር በመተባበርና ከእግዚአብሔርም ፍጹም አገዛዝ ሥር በመሆን ነው። በመሠረቱ ይህ ኀላፊነት ስጦታ እንጂ መብት አይደለም።

*8፥9፤* የቍ10 ሐሳብ ቃል በቃል ተደግሞ ይገኛል (የቍ1 ማብ ይመ)።

***መዝሙር 9፤*** አንዳንድ ጊዜ መዝሙር 9እና10 እንደ አንድ መዝሙር ይታዩ (ወይም በአገልግሎት ላይ ይውሉ) ነበር የሚለው ሐሳብ የተገኘው ከሰብዓ ሊቃናት ትርጕም (የግሪክ ብሉይ ኪዳን ትርጕም፤ የጽሑፉን ማብ ይመ) ነው። መዝሙሮቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲደረሱ እንደ አንድ መዝሙር ተደርገው ይደረሱ ወይም አይደረሱ ምንም የሚታወቅ ነገር የለም፤ በርካታ ፍንጮች የሚጠቁሙት ግን አንድ መዝሙር መሆናቸውን ነው። ከመዝሙር 3እስከ 32 ባሉት መዝሙሮች ውስጥ ንዑስ ርእስ የሌለው፣ መዝሙር 10 ብቻ ነው፤ የዕብራይስጡ ቅጂ እነዚህ ሁለት መዝሙሮች ማለትም መዝሙር 9እና 10 ያልተሟላ ዕዝለ ቃል መዋቅር እንዳላቸው ያመለክታል፤ በመዝሙር 9 መጀመሪያ ላይና በመዝሙር 10 መጨረሻ መስመር አካባቢ፣ የእያንዳንዱ ስንኝ መነሻ ቀለም (ፊደል) ወይም የጥንድ ስንኞች መነሻ ቀለም የዕብራይስጡን የፊደል ገበታ ቅደም ተከተል የያዘ ነው። መዝሙር 9 በአብዛኛው እግዚአብሔር ሕዝቡን ከክፉ መንግሥታት በመታደጉ ምክንያት ለስሙ የቀረበ (በንጉሡ) ምስጋና ነው፤ (እስራኤል በቀጥታ ድል ያደረገቻቸው መንግሥታት ባይኖሩም እግዚአብሔር ግን በራሱ መንገድ አጥፍቶአቸዋል፤ ይህ የምስጋና መዝሙር መቼ እንደ ተደረሰ በትክክል አይታወቅም)። መዝሙሩ በየመሀሉ፣ እግዚአብሔር እብሪተኛ በሆኑ ሕዝቦች ላይ በጽድቅ መፍረዱን እንዲቀጥል የሚያሳስብ አጫጭር ጸሎቶችን ይዞአል። መዝሙር10 በአብዛኛው፣ እግዚአብሔር ክፉና ኀጢአተኛ እንዲሁም ስግብግብና ትዕቢተኛ በሆኑ ሰዎች ላይ በጽድቅ እንዲፈርድ የሚማጠን መዝሙር ነው። እነዚህ ሰዎች "በደካሞች" (ቍ2) ላይ የተረማመዱና በእስራኤልም ላይ የተዘባነኑ ናቸው (ቍ2-11 የሁለቱንም ወገኖች ማንነት ገላልጦ የሚያሳይ ነው)። እነዚህን ሁለት መዝሙሮች እንደ አንድ መዝሙር አጣምሮ ማየት "ከቶ የማይታሰብ ነገር" ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም በቅዱሳን ማኅበረሰብ ላይ ከውስጥ ወይም ከውጭ የተነሱ "ክፉዎች" (9፥5፤ 10፥4) በእውነተኛዪቱ እስራኤል ህልውና ላይ ስጋት ማሳደራቸው በሁለቱም መዝሙሮች ውስጥ ታይቶአል። እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ስለ አደረገው ትድግና፣ ምስጋና ማቅረብ በመዝሙረኛው መጽሐፍ ውስጥ ጉልህ ስፍራ አለው (3፥3-4:8 እንዲሁም 40፥1-5 ይመ)፤ በጥንት ቅርብ ምሥራቃውያን ጸሎትም ውስጥ ተመሳሳይ ነገር አለ። እንዲህ ያለው ምስጋና የመዝሙረኛውን የተስፋ መሠረት የሚያንጸባርቅና የመዝሙረኛውም ጸሎት የሚሰማ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፤ ከዚህም በቀር የእግዚአብሔር ክንድ በሕዝቡ (ወይም በአገልጋዮቹ) መካከል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲገለጥ የሚያነሳሳም ነው። ስለ ጸሎት የተሰጡ ሌሎች ረጅም መቅድሞችን በመዝሙር 40፤ 44፤ 89 ላይ ይመ። እንደ መዝሙር 42-43 ሁሉ መዝሙር 9 እና 10ም ምናልባት ለተለየ የቅዳሴ ሥርዐት አጠቃቀም የተመደቡ ሳይሆን አይቀርም (የመዝሙር 42-43 መግቢያ ይመ)።

*መዝሙር 9* ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝሙር 4 ርእስን ማብ ይመ።

*9፥1-2፤* የምስጋና ዐዋጅ መጀመሪያ ነው።

9፥1 ***ልቤ፤*** የ4፥7 ማብ ይመ። ***እናገራለሁ፤*** በቍ14 ላይ ይህ ቃል ከዕብራይስጡ የተመለሰው "በገሃድ እንድናገር (እንዳውጅ)" ተብሎ ነው። በመዝሙረኛው መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምስጋናዎች፣ በመዝሙረኛውና በጌታ መካከል ብቻ የሚታወቁ ግላዊ ጕዳዮች አይደሉም፤ መዝሙሮቹ በአብዛኛው በአደባባይ (በቤተ መቅደስ) የተዘመሩና የእግዚአብሔርን ቅዱስ አሠራር እንዲሁም ማዳኑንና ቸርነቱን የሚያወድሱ ናቸው። መዝሙረኛው በምስጋናው ውስጥ የእግዚአብሔርን ክቡር ባሕርያት ወይም መልካም ተግባራት እየጠቀሰ (የ4፥1 ማብ ይመ) ለጉባኤው አንድ በአንድ ያስታውቃል (ይህን በተመለከተ 22፥22-31፤ 56፥12-13፤ 61፥8፤ 65፥1፤ 69፥30-33 ይመ)። ዝማሬውን ወይም ውዳሴውን የሚሰሙ ሁሉ እነርሱም በአንድነት ምስጋና እንዲያቀርቡና በእግዚአብሔርም ታላቅነት፣ ቸርነትና መልካምነት ሁሉ ሐሴት እንዲያደርጉ ጥሪ ይቀርብላቸዋል። በመጽሐፈ መዝ

2በአንተ ደስ ይለኛል፤ ሐሤትም
አደርጋለሁ፤
ልዑል ሆይ፤ ስምህን በመዝሙር
እወድሳለሁ።
3ጠላቶቼ ወደ ኋላ በተመለሱ ጊዜ፣
ተሰነካክለው ከፊትህ ይጠፋሉ፤
4ፍርዴም ጉዳዬም በአንተ እጅ ናቸውና፤
ቅን ፍርድ እየሰጠህ በዙፋንህ ላይ
ተቀምጠሃል።
5ሕዝቦችን ገሠጽህ፤ ክፉዎችንም አጠፋህ፤
ስማቸውንም እስከ ወዲያኛው
ደመሰስህ።
6ጠላቶች ለዘላለም ጠፉ፤
ከተሞቻቸውንም ገለባበጥሃቸው፤
መታሰቢያቸውም ተደምስሶአል።
7እግዚአብሔር ግን ለዘላለም በዙፋኑ ላይ
ነው፤
መንበሩንም ለፍርድ አጽንቶአል።
8ዓለምን በጽድቅ ይዳኛል፤
ሕዝቦችንም በፍትሕ ይገዛል።
9እግዚአብሔር ለተጨቈኑት አምባ ነው፤
በመከራም ጊዜ መጠጊያ ይሆናቸዋል።
10ስምህን የሚያውቁ ይታመኑብሃል፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ የሚሹህን
አትተዋቸውምና።
11በጽዮን ለሚኖር ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤
ሥራውንም በሕዝቦች መካከል
በግልጽ አውሩ፤
12ደም ተበቃዩ አስቦአቸዋልና፤
የጭቍኖችንም ጩኸት አልዘነጋም።
13እግዚአብሔር ሆይ፤ ጠላቶቼ
የሚያደርሱብኝን መከራ ተመልከት፤
አይተህም ራራልኝ፤ ከሞት ደጅም
አንሥተህ መልሰኝ፤
14ይህን ስታደርግልኝ፣ በጽዮን ሴት ልጅ
ደጅ፣
ምስጋናህን አውጃለሁ፤
በማዳንህም ሐሤት አደርጋለሁ።
15አሕዛብ በቈፈሩት ጕድጓድ ገቡ፤
እግራቸውም ራሳቸው በስውር
ባስቀመጡት ወጥመድ ተያዘ።
16እግዚአብሔር በትክክለኛ ፍርዱ የታወቀ
ነው፤
ክፉዎችም በእጃቸው ሥራ ተጠመዱ።
ሒጋዮን[ሀ] ሴላ
17ክፉዎች ተመልሰው ወደ ሲኦል[ለ]
ይወርዳሉ፤
እግዚአብሔርን የሚዘነጉ ሕዝቦችም ሁሉ
እንደዚሁ።
18ችግረኞች ግን መቼም ቢሆን አይረሱም፤
የድኾችም ተስፋ ለዘላለም መና ሆኖ
አይቀርም።

9፥2 2ዜና31፥2፤ ኢዮ22፥19፤መዝ14፥7፤31፥7፤70፥4፤92፥1፤97፥8፤126፥3፤ምሳ23፥15፤ኢሳ25፥9፤ኤር30፥19፤ኢል2፥21፤ሶፎ3፥14፤ማቴ5፥12፤ራእ19፥7
9፥4 1ነገ8፥45፤ኢዮ16፥21፤መዝ7፥11፤11፥4፤47፥8፤67፥4፤98፥9፤ኢሳ6፥1፤1ጴጥ2፥23
9፥5 ዘዳ20፥7፤37፥10፤1ዜና16፥21፤ኢዮ18፥17፤መዝ59፥5፤105፥14፤ኢሳ26፥14፤66፥15
9፥6 ዘጸ29፥28፤መዝ34፥16፤109፥15፤መክ9፥5፤ኢሳ14፥22፤26፥14፤ኤር2፥3፤46፥1-51:58፤ሶፎ2፥8-10
9፥7 1ዜና16፥31፤መዝ11፥4፤47፥8፤93፥2፤ኢሳ6፥1፤66፥1፤ራእ19፥6
9፥8 ቍ4፤መዝ7፥11፤11፥7፤45፥6፤72፥2
9፥9 ዘጸ33፥27፤2ሳሙ22፥3፤መዝ10፥18፤32፥7፤74፥21፤121፥7
9፥10 ዘፍ28፥15፤ዘጸ4፥31፤መዝ22፥1፤37፥25፤70፥4፤71፥11፤91፥14፤ኢሳ49፥14፤ኤር15፥18፤ዕብ13፥5
9፥11 መዝ2፥6፤7፥17፤18፥49፤44፥11፤57፥9፤105፥1፤106፥27፤ኢሳ24፥13፤ሕዝ20፥23፤1ጢሞ3፥16
9፥12 ቍ18፤2ሳሙ 4፥11፤መዝ10፥17፤22፥24፤72፥4፤ኢሳ 49፥13
9፥13 ዘኍ10፥9፤ኢዮ17፥16፤መዝ3፥7፤6፥2፤18፥3፤41፥4፤51፥1፤86፥3:16፤119፥132፤ማቴ16፥18 9፥14 2ነገ19፥21፤መዝ13፥5፤35፥9፤50፥23፤51፥12:15፤ኢሳ1፥8፤10፥32፤37፥22፤62፥11፤ኤር4፥31፤6፥2፤ሰቆ1፥6፤ሚክ1፥13 ፤ሶፎ3፥14፤ዘካ2፥10፤ማቴ21፥5፤ዮሐ12፥15፤1ጴጥ2፥9 9፥15 ኢዮ4፥8፤መዝ 35፥7:8፤57፥6 9፥16 ምሳ5፥22
9፥17 ዘኍ16፥30፤ ኢዮ8፥13፤ምሳ5፥5 9፥18 ቍ12፤መዝ25፥3፤39፥7፤71፥5፤74፥19፤ምሳ23፥18፤ኤር14፥8

[ሀ]16 ወይም *በተመሥጦ ማሰብ* [ለ]17 ወይም *መቃብር*

ሙር ውስጥ ይህ ዐይነቱ የምስጋና ገጽታ፣ በአዲስ ኪዳን ይፈጸማል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው የወንጌል ትምህርት ገና ከወዲሁ በብሉይ ኪዳን መነገሩን የሚያሳይ እንደ ሆነ ብዙዎች ያምኑበታል። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ እስራኤላውያን ከግብፅ ሲወጡ እንደ ሆነው ዐይነት ወይም በምድረ በዳ ሲቅበዘበዙ እንደ ሆነው ዐይነት ወይም ወደ ተስፋዪቱ ምድር ሲገቡ እንደ ሆነው ዐይነት በታምራት የታጀበ ነው። አንዳንድ ጊዜ ግን እንዲህ አይሆንም። ሆኖም የእግዚአብሔር ማዳን ግን ሁልጊዜ ሉዓላዊነቱና ጌትነቱ የሚታይበት ነው፤ የጊዜና የሁኔታዎችም ባለቤት መሆኑ የሚገለጥበት ነው፤ በዚህ መዝሙር ውስጥ የቀረበው ምስጋና ከጠላቶች መደምሰስ ጋር የተያያዘ ነው።

9፥2:10 *ስምህን፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

9፥2 *ልዑል ሆይ፤* የዘፍ14፥19 ማብ ይመ።

*9፥3-6፤* እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እንዳልነበሩ በማድረግ በዳዊት እና በእስራኤል ላይ የተፈጸመውን በደል ተበቅሎአል።

9፥4 *በዙፋንህ፤* የቍ7 ማብ ይመ።

9፥5 *ስማቸውንም ... ደመሰስህ፤* በፓፒረስ ሸምልሎች ወይም ጥቅልሎች ላይ ከተዘረዘሩት ስሞች መካከል ፍቆ እንደ ማጥፋት ዐይነት ነው (ዘኍ5፥23፤ እንዲሁም ዘጸ9፥14፤ 25፥19፤ 29፥20፤ 2ነገ14፥27 ይመ)፤ የፓፒረስ ሸምልሎች ወይም ጥቅልሎች ፓፒረስ ከሚባል ተክል ላይ ከሚወሰድ ቅርፊት ወይም ልጣጭ የሚዘጋጁ ሲሆን የጥንት ግብፃውያን፣ ግሪካውያንና ሮማውያን ለመጻፊያ የሚጠቀሙበት መሣሪያ ነው፤ የፓፒረስ ተክል ቁመቱ ከ3-12 ጫማ የሚያደርስና በአብዛኛው የሚገኘው በናይል ወንዝ ዳርቻ ላይ ነው።

*9፥7-10፤* ለእግዚአብሔር የጽድቅ አገዛዝ የቀረበ ምስጋና ሲሆን (የ4፥1 ማብ ይመ)፣ ይህም ልባቸውን ወደ ጌታ ለሚያቀኑ ሰዎች እምነትን የሚፈጥር ነው (የቍ1 ማብ ይመ)።

*9፥8፤* ሐሥ17፥31 ይመ።

*9፥10-11፤* እግዚአብሔር ትክክለኛ ዳኛ እንደሆነ ሁሉ ርኅሩኅ መጠጊያም ነው፤ ቀደም ባሉት ቍጥሮች ላይ "ዳኛ" እንደ ነበር ተጠቅሶአል፤ አሁን ደግሞ "መጠጊያ ወይም አምባና መሸሸጊያ" እንደሆነ ተጠቅሶአል፤ እነዚህ ሁለት ተምሳሌቶች የእርስ በርስ ዝምድና አላቸው፤ አንዱ አምላክ ዳኛና ዐምባ ነውና።

*9፥11-12፤* እግዚአብሔርን ስለ ጻድቅ ፍርዱ ያመሰግኑት ዘንድ በቤተ መቅደስ ለተሰበሰቡት የቀረበ ጥሪ ነው።

9፥11 *በጽዮን ለሚኖር፤* የእግዚአብሔር ሰማያዊ ዙፋን (የቍ7 ማብ ይመ) በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስም ውስጥ ተመሳሳይ ተግባር አለው፤ ዓለምንም የሚገዛው ከዚሁ ማዕከል ነው (2፥6፤ 3፥4 እና ማብ 20፥2 ይመ)። እግዚአብሔር ጽዮንን የዙፋኑ መንበር ስለማድረጉ መዝ132፥13 ይመ።

9፥12 *ደም ተበቃዩ፤* ዘዳ32፥41:43 ይመ።

*9፥13-14፤* ዳዊት፣ እግዚአብሔር የመለሰለትን ጸሎት እያስታወሰ ሳይሆን አይቀርም (በቍ12 ላይ "የተጨነቁትን ሰዎች ጩኸት" ይላልና)።

9፥13 *ከሞት ደጅም፤* ኢዮ17፥16 እና ማብ ይመ።

9፥14 *በጽዮን ልጅ፤* ኢየሩሳሌምንና መሪዎቹን ለመግለጽ ጸሐፊው የተጠቀመበት ሰውኛ አባባል ወይም ዘይቤ ነው። *ደጅ፤* ዳዊት "ወደ ሞት ደጆች" እስኪጣል ድረስ ጠላቶቹ አጥቅተውት ስለ ነበር (ቍ13)፣ የእግዚአብሔርን ትድግና "በጽዮን ልጆች ደጅ" ማመስገን እንዲችል ልመናን አቀረበ (የቍ1 ማብ ይመ)። *አውጃለሁ፤* የቍ1፤ 7፥17 ማብ ይመ።

*9፥15-18፤* በእግዚአብሔር አገዛዝ ሥር ሌሎችን ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ የሚያጠቁ ሁሉ፣ በራሳቸው ላይ ጥፋትን ይጋብዛሉ (7፥14-16 እና ማብ ይመ)፤ የመጨረሻ ዕጣ ፈንታቸ ውም የሞት ሞት ነው፤ ጥቃት የደረሰባቸው ("ችግረኞች" ቍ18) ግን በጌታ ያላቸው እምነት ከንቱና መና ሆኖ አይቀርም።

9፥17 *የሚዘነጉ፤* ጕዳዩ የማይሉ ወይም ከነመኖሩ የሚረሱ ማለት ነው።

9፥18 *ችግረኞች ... የድኾችም፤* በዚህ መዝሙር ውስጥ ዳዊትና እስራኤል በእግዚአብሔር ከሚታሰቡት ውስጥ ተቈጥረዋል። *አይረሱም፤* እግዚአብሔርን ጕዳዩ ያላሉ ሁሉ እነርሱም በፈንታቸው የተረሱ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔር ችግረኞችንና ድኾችን ግን ምንጊዜም አይረሳቸውም (ቍ12 ይመ)።

19 እግዚአብሔር ሆይ ተነሥ፤ ሰውም
አያይል፤
አሕዛብም በፊትህ ይፈረድባቸው::
20 እግዚአብሔር ሆይ፤ ድንጋጤ
አምጣባቸው፤
ሕዝቦች ሰው ከመሆን እንደማያልፉ
ይወቁ:: ሴላ

## መዝሙር 10[ሀ]

### ለፍትሕ የቀረበ ልመና

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ ለምን እንዲህ ርቀህ
ቆምህ?
በመከራ ጊዜስ ለምን ድምፅህን አጠፋህ?
2 ክፉዎች የተጨነቀውን በእብሪት
ያሳድዳሉ፤
በወጠኑት ተንኰል ይጠመዱ::
3 ክፉ ሰው በልቡ ምኞት ይኵራራል፤
ስግብግቡን ይባርካል፤ እግዚአብሔርንም
ይዳፈራል::
4 ክፉ ሰው ከትዕቢቱ የተነሣ እግዚአብሔርን
አይፈልግም፤
በሐሳቡም ሁሉ ስፍራ የለም፤
5 መንገዱ ዘወትር የተሳካ ነው፤
ዕቡይ፣ ከሕግህም የራቀ ነው::
በመሆኑም በጠላቶቹ ላይ ያፌዛል::
6 በልቡም፣ "ከስፍራዬ የሚነቀንቀኝ የለም፤
ከትውልድ እስከ ትውልድም መከራ
አያገኘኝም" ይላል::
7 አፉ መርገምን፣ ቅጥፈትንና ግፍን
የተሞላ ነው፤
ሸንገላና ክፋት ከምላሱ ሥር ይገኛሉ::
8 በየመንደሩ ሥርቻ ያደፍጣል፤
ንጹሐንን በሰዋራ ስፍራ ይገድላል::
ዐይኖቹንም በምስኪኖች ላይ
ያንከባልላል::
9 በደኑ ውስጥ እንዳለ አንበሳ በስውር
ያደባል፤
ረዳት የሌለውን ለመያዝ ያሸምቃል፤
ድኻውንም አፈፍ አድርጎ በወጥመዱ
ይጐትታል::
10 ምስኪኑም ይደቅቃል፤ አንገቱን ይደፋል፤
ያልታደለውም በክንዱ ሥር ይወድቃል::
11 በልቡም፣ "እግዚአብሔር ረስቶአል፤
ፊቱን ሸፍኖአል፤ ፈጽሞም አያይም"
ይላል::
12 እግዚአብሔር ሆይ ተነሥ፤ አምላክ ሆይ፤
ክንድህን አንሣ፤
ረዳት የሌላቸውንም አትርሳ::
13 ክፉ ሰው በእግዚአብሔር ላይ ለምን ክፉ
ይናገራል?
በልቡስ፣ "ስለ ሥራዬ አይጠይቀኝም"
ለምን ይላል?
14 አንተ ግን መከራንና ሐዘንን ታያለህ፤
በእጅህም ዋጋ ለመክፈል ትመለከታለህ፤
ምስኪኑም ራሱን በአንተ ላይ ይጥላል፤
ለድኻ አደግም ረዳቱ አንተ ነህ::

9፥19 2ዜና14፥11፤ መዝ3፥7፤110፥6፤ኢሳ 2፥4፤ኢል3፥12
9፥20 ዘፍ35፥5፤መዝ 31፥13፤62፥9፤ኢሳ 13፥8፤31፥3፤ሕ28፥2 ፤ሉቃ21፥26
10፥1 መዝ13፥1፤ 22፥1:11፤35፥22፤38፥ 21፤71፥12
10፥2 ቍ9፤ኢዮ 20፥19
10፥3 ኢዮ1፥5፤መዝ 49፥6፤94፥4፤ኤር 48፥30
10፥4 መዝ36፥1
10፥5 መዝ18፥27፤ 101፥5፤ምሳ6፥17፤ ኢሳ13፥11፤ኤር 48፥29
10፥6 ራእ18፥7
10፥7 ኢዮ20፥12፤ መዝ73፥8፤119፥134፤ መክ4፥1፤ኢሳ30፥12 ፤ሮሜ3፥14
10፥8 መዝ37፥32፤ 59፥3፤71፥10፤ምሳ1፥ 11፤ኤር5፥26፤ሆሴ6፥ 9፤ሚክ7፥2
10፥9 ቍ2፤ኢዮ 18፥8
10፥10 ኢዮ9፥17
10፥11 ኢዮ22፥13: 14፤መዝ42፥9፤77፥9
10፥12 መዝ3፥7፤ 9፥12፤17፥7፤20፥6፤1 06፥26፤ኢሳ26፥11 ፤ሚክ5፥9
10፥13 ቍ3፤ኢዮ 31፥14
10፥14 ቍ7፤ዘዳ 33፥29፤መዝ22፥11፤3

[ሀ]ምዕ10 መዝ9 እና 10 በመጀመሪያው የጥንት ቅጅ ላይ አንዳው ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆሄያት የሚጀምሩ እንዲሁም ጅማሬው ወይም መጨረሻው ትርጒም አዘል የሆነ አንድ ወጥ ግጥም ነበር፤ በሰብዓ ሊቃናት ውስጥ ሁለቱ አንድ መዝሙር ናቸው::

*9፥19-20፤* በምስጋናው ቃል መደምደሚያ ላይ የቀረበ ጸሎት ነው፤ በጸሎቱ ላይ እንደሚከተለው መዝሙረኛው፣ እግዚአብሔር በአሕዛብና በመንግሥታት ላይ ለዘላለም እንዲገዛ፣ "እርሱንም በዘነጉት ላይ" (ቍ17) ክንዱን እንዲያነሣና አሕዛብ ሰብዓዊ ፍጡራን እንጂ አማልክት እንዳልሆኑና የእስራኤልንም አምላክ መቋቋም የማይችሉ መሆናቸውን እንዲያውቁ ይጠይቃል (10፥18 ይመ)::

9፥19 *ተነሥ፤* የ3፥7 ማብ ይመ::

*መዝሙር 10፤* ከጨካኞችና ከክፉዎች እጅ ለማምለጥና ለመዳን የቀረበ ጸሎት ሲሆን፣ ይህ መዝሙር በብሉይ ኪዳን ላይ ለዘመናት ስለ "ክፉዎች" የሰፈረውን ሥዕላዊ መግለጫ የያዘ ነው፤ የመዝ 9 መግቢያን ይመ::

*10፥1፤* የ6፥3 ማብ ይመ:: እንዲሁም በመግቢያው ላይ "ትምህርተ መለኮት" የሚለውን ይመ::

*10፥2-11፤* በጨቋኞች ላይ የቀረበ ክስ ነው (የ5፥9-10 ማብ ይመ):: የዕብራይስጡ ቅጅ እንደሚያመለክተው ይህ ክስ የቀረበው በአጠቃላይ በጨቋኞች ሁሉ ላይ ነው:: እነዚህ ጨቋኞች በትዕቢት የተወጠሩ በመሆናቸው (ቍ2-5 ይመ፤ ሀብት በሀብት እስከ ሆኑ ድረስ ለምን በትዕቢት አይነፉ፤ አይ ወጠሩ ቍ5)፣ እግዚአብሔርን አቃለዋል (ቍ3-4:13 በተለይ ደግሞ በቍ6:11 እና 13 ላይ የሰፈረውን የእብሪት ንግግር ይመ)፤ እግዚአብሔርንም ሆነ (ቍ4)፣ ሕጉን (ቍ5) ከምንም አልቈጠሩም፤ ደግሞም ሌሎች ሰዎችን ያለ አንዳች በደላቸው በማሠቃየትና ቁም ስቅላቸውን በማሳየት በቃኝን ለማያውቀው ከርሳቸው የሚ ሆነውን ምግብ ከዚህም ከዚያም ያግበሰብሳሉ::

10፥2 *ክፉዎች ... ያሳድዳሉ፤* መዘምራኑ ብዙውን ጊዜ ምስል የሚከስቱ የአነጋገር ዘይቤዎችን ሲጠቀሙ ይታያል፤ በዚህ ቦታ የተጠቀሙት፣ አንድ አዳኝ ለአደን ሲወጣ የሚያደርገውን ነገር ነው (ቍ8-9 ይመ)::

10፥3 *በልቡ፤* የ4፥7 ማብ ይመ::

*10፥4፤* ክፉ ሰው ድርጊቱን ሁሉ የሚመለከት አምላክ እንዳለ ልብ አይልም (የቍ11 ማብ እንዲሁም 14፥1፤ 36፥1፤ 53፥1 ይመ)::

*10፥6፤* ቍ11:13 እና የ3፥2 ማብ ይመ:: *በልቡም፤* በቀጥታ ሲተረጐም "ለራሱም" እንደ ማለት ነው (እንዲሁም በቍ11 እና 13 ላይ ተመልክቶአል)፤ የ4፥7 ማብ ይመ:: *የሚነቀንቀኝ የለም፤* የተደላደለ ኑሮዬን የሚያናውጥ ወይም ሰላሜን የሚያደፈርስ የለም ማለቱ ነው::

10፥7 *መርገምን፣ ቅጥፈትንና ግፍን፤* በእስራኤላውያን የቀን ተቀን ኑሮ ውስጥ እነዚህ ሦስት ቃላት የምላስ ዐይነተኛ መሣሪያዎች ናቸው፤ እስራኤላውያን ምላስን እንደ መሣሪያ ይጠቀሙበታል (የ5፥9 ማብ ይመ):: *መርገምን፤* በጥንት ቅርብ ምሥራቅ ሰዎች አስተሳሰብ አንድ ሰው ላይ የርግማን ቃልን መናገር ማለት በዚያ ሰው ላይ የአማልክት ቍጣ ይገለጥ (ወይም የአማልክት መዓት ይዝነብ) ማለት ነው፤ "እንዲህና እንዲያ" ይድረስብህ በማለት የሚናገሩት አያሌ የርግማን ዐይነቶች አሏቸው:: *ቅጥፈትንና፤* አንድ ሰውን ለመጕዳት ሲባል በዚያ ሰው ላይ የሚነገር የሐሰት ቃልና የስድብ ቃል ነው (ለምሳሌ 1ነገ21፥8-15 ይመ)::

*10፥9፤* የ7፥2 ማብ ይመ::

*10፥11፤* የ3፥2 ማብ ይመ:: ክፉዎች በእብሪት እንዴት እንደሚናገሩ (17፥10 ይመ)፣ በተለይም እግዚአብሔር ክፉ ሥራዬን አያይም፣ ክፉ ተግባሬንም ሥራዬ ብሎ አይከታተልም በማለት እንዴት እንደሚዘባነኑ መዝሙረኞቹ ነገሩን በተደጋጋሚ አውስተውታል (ቍ13፤ 12፥4፤ 42፥3:10፤ 59፥7፤ 64፥5፤ 71፥11፤ 73፥11፤ 94፥7፤ 115፥2፤ እንዲሁም ኢሳ29፥15፤ ሕዝ8፥12 ይመ)::

*10፥12-15፤* እግዚአብሔር የክፉዎችን ሥራ እንዲመለከትና የሥራቸውንም እንዲሰጣቸው የቀረበ ጸሎት ነው::

10፥12 *ተነሥ፤* የ3፥7 ማብ ይመ:: *ረዳት የሌላቸውን፤* በጨቋኞቻቸው ምሕረት ስር ያሉትን ማለት ነው (ቍ9 ይመ):: *አትርሳ፤* 9፥18 ይመ::

10፥13 *ለምን? ... ለምን?* የ6፥3 ማብ ይመ::

*10፥14፤* የእግዚአብሔር ጽድቅ አገዛዝ ይሰፍን ዘንድ የቀረበ ልመና ነው (5፥4-6 ይመ)::

15የክፉውንና የበደለኛውን ክንድ ስበር፤
የእጁንም ስጠው፤
ምንም እስከማይገኝ ድረስ።
16እግዚአብሔር ከዘላለም እስከ ዘላለም
ንጉሥ ነው፤
ሕዝቦችም ከምድሩ ይጠፋሉ።
17እግዚአብሔር ሆይ፤ የተገፉትን ምኞት
ትሰማለህ፤
ልባቸውን ታበረታለህ፤ ጆሮህንም ወደ
እነርሱ ባል ታደርጋለህ፤
18ከዐፈር የተፈጠረ ሰው ከእንግዲህ
እንዳያስጨንቃቸው፣
አንተ ለድኻ አደጉና ለተገፋው
ትሟገታለህ።

## መዝሙር 11

## የጻድቃን ትምክህት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1*በእግዚአብሔር ታምኛለሁ፤*
*ታዲያ ነፍሴን፣ "እንደ ወፍ ወደ*
*ተራራ ብረሪ"*
*ለምን ትሏታላችሁ?*
2ደግሞም ለምን እንዲህ ትሉኛላችሁ?
"ክፉዎች፣ እነሆ፣ ቀስታቸውን ገትረዋል፤
የቅኑን ሰው ልብ በጨለማ ለመንደፍ፣
ፍላጻቸውን በአውታሩ ላይ ደግነዋል።
3መሠረቱ ከተናደ፣
ጻድቅ ምን ማድረግ ይችላል?"[ኀ]
4እግዚአብሔር በተቀደሰ መቅደሱ አለ፤
የእግዚአብሔር ዙፋን በሰማይ ነው።
ዐይኖቹ ሰዎችን ይመለከታሉ፤
ቅንድቦቹም የሰው ልጆችን ይመረምራሉ።
5እግዚአብሔር ጻድቁንና ኀጥኡን
ይመረምራል፤[መ]
ዐመፃን የሚወዱትን ግን፣
ነፍሱ ትጠላቸዋለች።
6እርሱ በክፉዎች ላይ የእሳት ፍምና
ዲን ያዘንባል፤
የጽዋቸውም ዕጣ ፈንታ፣
የሚለበልብ ዐውሎ ነፋስ ነው።
7እግዚአብሔር ጻድቅ ነውና፤
የጽድቅ ሥራም ይወዳል፤
ቅኖችም ፊቱን ያያሉ።

## መዝሙር 12

## ከክፉ ዐለም ለመዳን የቀረበ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በስምንተኛው ቅኝት የሚዘመር፤ የዳዊት መዝሙር።*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ደግ ሰው የለምና
አንተው ድረስልኝ!

[ኀ]3 ወይም *ጻድቁ ምን እያደረገ ነው?*
[መ]5 ወይም *ጻድቁ እግዚአብሔር ኀጥኡን ይመረምራል*

7፥5
10፥15 ኢዮ31፥22
10፥16 ዘዳ15፥18፤ዘጸ8፥20
10፥17 ዘዳ22፥23፤ መዝ9፥12
10፥18 ዘጸ24፥17፤ መዝ9፥9፤146፥9
11፥1 ዘፍ14፥10፤ መዝ7፥1፤50፥11
11፥2 2ሳሙ22፥35፤ኢዮ33፥3፤መዝ 7፥10፡13፤10፥8፤58፥7
11፥3 መዝ18፥15፤ 82፥5፤ኢሳ24፥18
11፥4 1ነገ8፥48፤2ዜና 6፥18፤መዝ9፥7፤18፥6፤27፥4፤33፥18፤66፥7፤ ምሳ15፥3፤ዮና2፥7፤ሚ ክ1፥2፤ዕን2፥20፤ማቴ 5፥34፤23፥22፤ራእ4፥2
11፥5 ዘዳ7፥13፤ኢዮ 23፥10፤28፥28፤መዝ5፥5፤45፥7፤ኢሳ1፥14
11፥6 ዘፍ19፥24፤ 41፥6፤ኢዮ1፥19፤ራእ 9፥17
11፥7 2ዜና12፥6፤ ዕዝ9፥15፤ኢዮ1፥1፤ መዝ9፥8፤17፥15፤33፥5፤99፥4፤140፥13፤ኢሳ 28፥17፤30፥18፤56፥1፤61፥8፤ኤር 9፥24፤ሉቃ23፥50፤2 ጢሞ4፥8
12፥1 ኢሳ57፥1፤

10፥15 *ክንድ ስበር፤* የመጨቈኛ ኀይላቸውን ዐመድ አድርግ ማለት ነው። *የእጁን ስጠው፤* በቅን ፍርድህ ትዕቢቱን ልክ አስገባ ማለት ነው።

*10፥16-18፤* መዝሙረኛው በጌታ የጽድቅ አገዛዝ ያለውን እምነት ያመለክታል (የ3፥8 ማብ ይመ)። ይህ ንባብ ስለ ሕዝቦች ዕጣ ፈንታ የሚናገር በመሆኑና (ቍ16)፣ ትዕቢተኛውም አንድ ቀን ልክ የሚገባ መሆኑን በማሳየቱ (ቍ18 ይመ)፣ ከመዝሙር 9 ጋር ዐይነተኛ ተዛምዶ እንዳለው ያመለክታል። ይህ ስንኝ የመዝሙር 10 መደምደሚያ እንደ መሆኑ፣ የእግዚአብሔር ቅን አገዛዝ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ እንደሚንሰራፋ ያለውን እምነት ይገልጻል፤ ከዚህም በቀር እግዚአብሔር በቅን ፍርዱ ክፉ ጨቋኞችን ልክ እንደሚያስገባና ለአምላክነቱም ተገቢውን ቦታ ያል ሰጡትን ሕዝቦች (ቍ16 ይመ) በፍርዱ እንደሚያበጥራቸው ያስገነዝባል። እግዚአብሔር በእብሪተኞች ፊት ማንነቱን የሚያሳየው በዚህ መንገድ ነው።

10፥18 *ከዐፈር የተፈጠረ፤* አምላክ ባለመሆኑ መቼም ቢሆን የሚያስፈራ አይደለም (49፥12፡20፤ 56፥4፡11፤62፥9፤ 78፥39፤ 103፥14-16፤ 118፥6፡8-9፤144፥4፤ ኢሳ31፥3፤ ኤር17፥5 ይመ)።

*መዝሙር 11፤* በክፉት የተሞሉ ጠላቶች ቀኝ እጅ ያገኙ በሚመስልበት ወቅት በእግዚአብሔር የጽድቅ አገዛዝ መታመንን የሚገልጽ ጸሎት ወይም ኑዛዜ ነው።

11 ርእስ *ለመዘመራን አለቃ፤* የመዝ 4 የርእስ ማብ ይመ።

*11፥1-3፤* ዳዊት በዙሪያው ከበው ለሚያስፈራሩት ሰዎች በጌታ ላይ (በዐምባው ላይ) ያለው እምነት የማይናወጥ መሆኑን መሰከረ። እነዚህ ሰዎች የጠላትን ኀይልና ሽንገላ በማየት (በጨለማ ለመንደፍ ደግነዋል፤ ቍ2) መሠረቱ ተናግቶአልና (ቍ3) ያለው ዕድል ወደ ተራሮች መሸሽ ነው ይላሉ። እርሱ ግን የፍርሀት ምክራቸውን ሁሉ መና ያደርገዋል።

*11፥2፤* እነዚህ ቀስትና ወስፈንጠር የያዙት ሰዎች በእርግጥ ቀስተኞች ይሁኑ ወይም በሐሰት ከሳሾች በግልጽ አይታወቅም (57፥4፤ 64፥4፤ እንዲሁም የ5፥9 ማብ ይመ)። *ልብ፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

11፥3 *መሠረቱ፤* የዓለም ሥርዐት ማለት ነው (82፥5 ይመ)። ሽሽትን እንደ መፍትሄ አድርገው ለሚያቀርቡ ሰዎች የክፉ ኀይል እያየለና እየበረታ መምጣት፣ መልካምና በጎ የሆነው ነገር ክፉና እኩይ በሆነው ነገር ላይ ድልን ይቀዳጃል ብለው እንዳያስቡ ያደረጋቸው ይመስላል። *ጻድቅ፤* የ1፥5 ማብ ይመ።

*11፥4-7፤* ፍርሀት ለገባቸው መልስ የሚሆን ነው፤ ጌታ አሁንም ከቶ በማይናወጥ ሰማያዊ ዙፋኑ ላይ አለ፤ ይህ ጻድቅ ጌታ (ቍ7 ይመ)፣ እርሱ ባለበት እነርሱም ይሆኑ ዘንድ ጻድቃንን ይመረምራል (ቍ7 ይመ)፤ በክፉዎች ላይ ግን የማያባራ ፍርድ ያወርዳል (ቍ6)።

11፥4 *እግዚአብሔር በተቀደሰ መቅደሱ አለ፤* ቃል በቃል በዕን2፥20 ላይ ተጠቅሶ ይገኛል፤ በዚህ ቦታ የሚያመለክተው ግን ሰማያዊ ዙፋኑን ነው።

*11፥6፤* ምናልባት በሰዶምና በገሞራ ላይ የወረደውን የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚያስታውስ ሊሆን ይችላል (ራእ 14፥10፤ 20፥10፤ 21፥8 ይመ)። *ዕጣ ፈንታ፤* በቀጥታ ሲተረጐም "ጽዋቸውም" ማለት ነው (75፥8 እንዲሁም የ16፥5 ማብ ይመ)።

11፥7 *ጻድቅ፤* የ4፥1 ማብ ይመ። *ቅኖችም፤* ፈሪዎች ተስፋ ያስቈረጧቸው ማለት ነው (ቍ2 ይመ)። *ፊቱን ያያሉ፤* በዕብራይስጥ ቋንቋ "የንጉሥ ፊት አየ" የሚለው አገላለጽ በንጉሥ ፊት ለመቅረብ ዕድል አገኘ ማለት ነው (ዘፍ43፥3፡5፤ 44፥23፡26፤ 2ሳሙ3፥13 "ወደ ፊቴ ግባ" 14፥24፡28፡32)። አንዳንድ ጊዜ በንጉሡ ፊት የሚያገለግሉትን ያመለክታል (2ነገ25፥19 "የንጉሡ አማካሪዎች"፤ በመጽሐፈ አስቴር ላይም 1፥14፣ "ወደ ንጉሡ ፊት ለመግባት ልዩ ፈቃድ ያላቸው")። በዚህ ቦታ ዳዊት ወደ ሰማያዊ ንጉሡ ዘንድ ለመግባት ልዩ መብት እንዳለው ይናገራል፤ ይህ አባባል በቤተ መቅደሱ ውስጥ (በእግዚአብሔር ምድራዊ ቤተ መንግሥት ውስጥ) ያለውን ነፃነት እንደሚያመለክት ምንም ጥርጥር የለውም፤ ሆኖም በሰማያዊ ዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ፊት ያለውንም ነፃነት ሊያመለክት ይችላል። ደግሞም አንድ ቀን ወደ ሰማይ ዙፋኑ ፊት መግባት የሚቻል መሆኑንም ሊያመለክት ይችላል (16፥11፤ 17፥15፤ እንዲሁም 23፥6፤ 140፥13 ይመ)። እስራኤልን የከበቧት አረማውያን እንኳ ሰው ከሞት በኋላ ህልውናው ሊቀጥል ይችላል የሚል እምነት አላቸው፤ ይህ ህልውና ምንነቱ በሚገባ በማይታወቅ የሙታን ዓለም ውስጥ የሚሆን ነው (ኢሳ14፥9-17 ይመ)።

*መዝሙር 12፤* ሰዎች ሁሉ እምነት የለሽና ምላስም ሁሉ ሐሰተኛ በሆነበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ርዳታ ለማግኘት የቀረበ ጸሎት ነው (ሚክ7፥1-7 ይመ)።

12 ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ 4 የርእስ ማብ ይመ። *በስምንተኛው ቅኝት፤* የመዝ 6 የርእስ ማብ ይመ።

*12፥1-2፤* የጭንቀትን መንሥኤ ለመግለጽ የቀረበ አቤቱታ ነው።

12፥1 *ደግ ሰው፤* የ4፥3 ማብ ይመ። *ታማኝ፤* በአካሄዱ

ከሰዎችም መካከል አንድ ታማኝ
አይገኝም።
2እርስ በርሳቸው ውሸት ይነጋገራሉ፤
በሽንገላ ከንፈርና በሁለት ልብ
ይናገራሉ፤
3ሽንጋዩን ከንፈር ሁሉ፣
ነገር የምታበዛውንም ምላስ እግዚ
አብሔር ያጥፋ!
4እነዚህም፣ "በአንደበታችን እንረታለን፤
ከንፈራችን የእኛ ነው፤[o] ጌታችንስ
ማነው?"
የሚሉ ናቸው።
5እግዚአብሔር፣ "ስለ ድኾች መከራ፣
ስለ ችግረኞችም ጩኸት፣
አሁን እነሣለሁ፤
በናፈቁትም ሰላም አኖራቸዋለሁ"
ይላል።
6የእግዚአብሔር ቃል የጠራ ቃል ነው፤
ሰባት ጊዜ እንደ ተጣራ፣
በምድር ላይ በከውር እንደ ተፈተነ
ብር ነው።
7እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ትጠብቀናለህ፤
ከዚህም ትውልድ ለዘላለም
ትከልለናለህ።
8በሰዎች ዘንድ ክፋት ከፍ ከፍ ባለ ጊዜ፣
ዐመፀኞች በየአቅጣጫው በዛቻ ይዞራሉ።

ሚክ7፥2
12፥2 መዝ5፥6፡9፤ 34፥13፤141፥3፤ምሳ6፥19፤12፥17፤13፥3፤ ኢሳ32፥7፤ሮሜ16፥18
12፥3 መዝ73፥9፤ ምሳ 26፥28፤28፥23፤ ዳን7፥8፤ያዕ3፥5፤ራእ 13፥5
12፥4 ምሳ18፥21፤ ያዕ3፥6
12፥5 መዝ3፥7፤6፥6፤34፥6፤35፥10፤44፥24፤62፥10፤72፥14፤73፥8፤መክ4፥1፤5፥8፤ ኢሳ3፥15፤5፥7፤ 30፥12፤59፥13፤ሐሥ 7፥34
12፥6 2ሳሙ22፥31፤ኢዮ23፥10፤28፥1፤መዝ18፥30፤119፥140፤ኢሳ48፥10፤ዘካ 13፥9
12፥7 መዝ16፥1፤27፥5፤37፥28፤ዮሐ 17፥12
12፥8 መዝ55፥10-11
13፥1 ዘዳ31፥17፤ መዝ6፥3፤22፥24፤ 42፥9፤ኢሳ8፥17፤ 54፥9፤ ሰቆ5፥20
13፥2 መዝ42፥4፤ 55፥2፤94፥3፤139፥23፤ኢሳ33፥18፤ዳን7፥28
13፥3 ዕዝ9፥8፤መዝ 4፥1፤9፥12፤25፥18፤31፥7፤35፥23፤59፥4፤

## መዝሙር 13

### በአምላኩ የታመነ ሰው አቤቱታ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር።*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ እስከ መቼ ድረስ
ለዘላለሙ ትረሳኛለህ?
ፊትህንስ ከእኔ የምትሰውረው እስከ
መቼ ድረስ ነው?
2ከሐሳቤ ጋር የምሟገተው፣
ልቤም ቀኑን ሙሉ የሚያዝነው እስከ
መቼ ነው?
ጠላቴስ በእኔ ላይ የሚያይለው እስከ
መቼ ድረስ ነው?
3እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ተመልከት፤
ስማኝም፤
የሞት እንቅልፍ እንዳልተኛ ዐይኖቼን
አብራ፤
4በዚህም ጠላቴ፣ "አሸነፍሁት" እንዳይል፣
ባላጋራዎቼም በውድቀቴ ደስ
እንዳይላቸው ርዳኝ።
5እኔ ግን በጽናት ፍቅርህ እታመናለሁ፤
ልቤም በማዳንህ ደስ ይለዋል።
6ቸርነቱ በዝቶልኛልና፣
ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ።

6፥5፤80፥14፤90፥5፤107፥41፤119፥50፡153፤ኤር51፥39 13፥4 1ነገ 19፥2፤መዝ25፥2፤38፥16፤118፥13 13፥5 ኢዮ33፥26፤መዝ6፥4፤ 9፥14፤ኢሳ 25፥9፤33፥2 13፥6 ዘፀ15፥1፤መዝ 7፥17

[o]4 ወይም *ከንፈራችን ግረኛ ምላጫችን ነው*

ሁሉ ፍጹምና ቀጥተኛ የሆነና በዚህም ጸንቶ የሚኖር ማለት ነው።

*12፥2፤* 5፥9 እና ማብ ይመ።

*12፥3-4፤* ጸሎት ነው።

12፥3 *ነገር የምታበዛውንም፤* የ10፥2-11 ማብ ይመ። *ያጥፋ፤* ወደ ፍጻሜ ያምጣ ማለት ነው (አባባሉ አካልን ቈራርጦ ከመጣል ጋር ምንም ዝምድና የለውም)።

*12፥4፤* የ3፥2፤10፥11 ማብ ይመ።

*12፥5-6፤* ከጌታ የመጣ የማረጋገጫ ቃል ነው፤ በመጽሐፈ መዝሙር ውስጥ፣ ከጸሎት በኋላ እንዲህ ያለው የማረጋገጫ ቃል የሚነገረው ምናልባት በካህናት በኩል (1ሳሙ1፥17) ወይም በነቢያት በኩል ነው (51፥8 እና ማብ እንዲሁም 2ሳሙ12፥13 ይመ)። የእግዚአብሔር የጽድቅ አገዛዝ ምንጊዜም እንደማይጠፋ ልብ ማለት ያሻል (የ4፥1 ማብ ይመ)።

12፥5 *አሁን እነሣለሁ፤* ኢሳ33፥10 ይመ።

12፥6 *የእግዚአብሔር ቃል፤* ጕራቸውን ከሚነዙት ጠላቶች ቃል ጋር ተነጻጽሮአል፤ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ነጠረ ብር እጅግ ውብ ነው። *ሰባት ጊዜ፤* የአንድን ነገር ፍጹምነትና ሙሉነት የሚያሳይ ነው፤ በዚህ ቦታ ግን የንጥረቱን ጥራት ወይም የነጠረውን ነገር ንጹሕነት ያመለክታል። *በከውር እንደ ተፈተነ፤* የዘዳ4፥20 ማብ ይመ።

*12፥7-8፤* በመደምደሚያ ላይ የተገለጸ የመታመኛ ቃል ነው (የ3፥8 ማብ ይመ)።

*12፥8፤* ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ክፉዎች ቀኝ እጅ ያገኙ ቢመስላቸውም፣ ዳዊት ግን በዚህ ሁሉ ውስጥ በጌታው ታምኖአል (ቍ1-4 ይመ)።

*መዝሙር 13፤* ዳዊት ለሞት ከሚያደርስ ሕመም (ቍ3 ይመ) ይድን ዘንድ ለጌታ ያቀረበው ጸሎት ነው፤ ከሕመሙ ባይድን ግን፣ ጠላቶቹ የሚፈልጉትን ያገኛሉ፤ የዳዊት ጩኸት እንዲህ እንዳይሆን ነው፤ የመዝሙር 6 መግቢያን ይመ።

13ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝሙር 4 ርእስ ማብ ይመ።

*13፥1-2፤* ለረጅም ጊዜ ከቆየ ሕመም የተነሣ የቀረበ አቤቱታ ነው።

13፥1 *እስከ መቼ?* የ6፥3 ማብ ይመ፤ እንዲሁም በመግቢያው ላይ "ትምህርተ መለኮት" የሚለውን ይመ። *ትረሳኛለህ፤* ችላ የምትለኝ ማለት ነው። *ፊትህንስ ከእኔ የምትሰውረው፤* ከመረሳት ጋር በአንዴት ያለ መንገድ እንደ ተጣመረ 44፥24 ይመ። መዝሙረኞቹ ርዳታን በሚሹበት ጊዜ እግዚአብሔር ፊቱን ለምን እንደሚሰውርባቸው ይጠይቃሉ (30፥7፤ 44፥24፤ 88፥14 ይመ)፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንዲህ እንዳያደርግ ይማጠናሉ (27፥9፤ 69፥17፤ 102፥2፤ 143፥7 ይመ)። ጌታ ፊቱን ሲሰውር ግን በእርሱ ላይ የሚታመኑት ተስፋ ይቈርጣሉ (30፥7፤ 104፥29 ይመ)። የጌታ ፊት በአንድ ሰው ላይ ሲያበራ ደግሞ በረከቱና ትድግናው እውን ይሆናል (4፥6 እና ማብ 31፥16፤ 67፥1፤ 80፥3፡7፡19፤ 119፥135 ይመ)።

13፥2 *ልቤም፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

*13፥3-4፤* ከሞት ይታደገው ዘንድ የቀረበ አቤቱታ ነው።

13፥3 *ዐይኖቼን አብራ፤* ወደ ቀድሞ ቦታዬ መልሰኝ ማለት ነው (የ6፥7 ማብ ይመ)።

*13፥4፤* የ3፥2፤ 5፥9 ማብ ይመ። *በወድቀቴ፤* መሞትን ያመለክታል (ይኸውም በ18፥38፤ 82፥7፤ 106፥26፤ በመሳ5፥27፤ በ2ሳሙ1፥19፤ በኢዮ18፥12 ላይ እንደ ተመለከተው ዐይነት ነው)።

*13፥5-6፤* በመደምደሚያ ላይ የቀረበ የመታመኛ ቃል ነው (የ3፥8 ማብ ይመ)።

13፥5 *በጽናት ፍቅርህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ። *ልቤም፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *ደስ ይለዋል፤* ደስታን የሚያገኘው ዳዊት እንጂ ጠላቶቹ አይደሉም።

*13፥6፤* የ7፥17 ማብ ይመ።

*መዝሙር 14፤* የክፉ ሰዎችን የማይረባ አስተሳሰብ የሚያመለክት ምስክርነት ነው። ይህ መዝሙር ከመዝሙር 10 እና 12 ጋር በብዙ መንገድ ይዛመዳል፤ ጻድቅ የሆነው ጌታ አሁንም በዙፋኑ ላይ ነው በማለቱ ከመዝሙር 12 ጋር የሚያዘምደው ነገር አለ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ስላገኙ ሰዎች የሚገልጽ በመሆኑ ደግሞ ከመዝሙር 15 ጋር የሚያነጻጽረው ነገር አለ። መዝሙር 53 በአንዳንድ ረገድ ሲታይ የዚህ መዝሙር ክላሽ ነው ማለት ይቻላል፤ በሌላ አነጋገር መዝሙር 53 ከመዝሙር 14 ተመልሶ ወይም ተከልሶ እንደ ገና በአዲስ መልክ የቀረበ መዝሙር ነው።

14ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝሙር 4 የርእስ ማብ ይመ።

*14፥1-3፤* የክፉ ሰዎችን ማንነት የሚገልጽ ነው። ጳውሎስ እነዚህን ጥቅሶች በተለየ ዐውደ ንባብ ውስጥ እንዴት ባለ መልክ እንደ ተጠቀመበት ሮሜ3፥10-12 ይመ።

## መዝሙር 14

### አምላክ የለሽ ሰዎች

14፥1-7 ተጓ ምብ-መዝ53፥1-6

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር።

1ሞኝ[a] በልቡ፣
"እግዚአብሔር የለም" ይላል።
ብልሹዎች ናቸው፤ ተግባራቸውም
ጸያፍ ነው፤
በጎ ነገር የሚሠራ አንድም የለም።

2የሚያስተውል፣ እግዚአብሔርን የሚፈልግ
መኖሩን ለማየት፣
*እግዚአብሔር* ከሰማይ
ወደ ሰው ልጆች ተመለከተ።
3ሁሉም ከመንገድ ወጥተዋል፤
በአንድ ላይም ብልሹ ሆነዋል፤
አንድ እንኳ፣
መልካም የሚያደርግ የለም።

4*የእግዚአብሔርን* ስም የማይጠሩት፣
ሕዝቤን እንደ እንጀራ የሚበሉት፣
ክፉ አድራጊዎች ሁሉ ዕውቀት
የላቸውምን?
5ባሉበት ድንጋጤ ውጦአቸዋል፤
እግዚአብሔር በጻድቃን መካከል ይገኛልና።
6እናንተ የድኾችን ዕቅድ ለማፋለስ
ትሻላችሁ፤
*እግዚአብሔር* ግን መጠጊያቸው ነው።
7ምነው እስራኤልን የሚያድን ከጽዮን በወጣ!
*እግዚአብሔር* የሕዝቡን ምርኮ
በሚመልስበት ጊዜ፣
ያዕቆብ ደስ ይበለው፤ እስራኤልም
ሐሤት ያድርግ።

## መዝሙር 15

### የእግዚአብሔር ቤተኛ

የዳዊት መዝሙር

1*እግዚአብሔር* ሆይ፤ በድንኳንህ ውስጥ
ማን ያድራል?
በተቀደሰው ኰረብታህስ ማን መኖር
ይችላል?

2አካሄዱ ንጹሕ የሆነ፣
ጽድቅን የሚያደርግ፤
ከልቡ እውነትን የሚናገር፤
3በምላሱ የማይሸነግል፤
በባልንጀራው ላይ ክፉ የማይሠራ፤
ወዳጁን የማያማ፤
4ነውረኛ በፊቱ የተናቀ፤
*እግዚአብሔርን* የሚፈሩትን ግን የሚያከብር፤
ዋጋ የሚያስከፍለውም ቢሆን፣
ቃለ መሐላውን የሚጠብቅ፤
5ገንዘቡን በአራጣ የማያበድር፣
በንጹሐን ላይ ጕቦ የማይቀበል፤

እነዚህን የሚያደርግ፣
ከቶ አይናወጥም።

14፥1 መዝ10፥4
14፥2 ዕዝ6፥21፤ኢዮ41፥34፤መዝ85፥11፤92፥6፤102፥19፤ሰቆ3፥50
14፥3 1ሳሙ8፥3፤1ነገ8፥46፤መዝ143፥2፤መክ7፥20፤ሮሜ3፥10-12፤1ጢሞ5፥15፤2ጴጥ2፥7
14፥4 መዝ27፥2፤79፥6፤82፥5፤ኢሳ64፥7፤65፥1፤ኤር4፥22፤10፥25፤ሆሴ7፥7፤ሚክ3፥3
14፥6 2ሳሙ22፥3
14፥7 ዘዳ30፥3፤መዝ 2፥6፤ኤር48፥47
15፥1 ዘፀ15፥17፤25፥8፤29፥46፤2ዜና22፥19፤መዝ20፥2፤23፥6፤27፥4፤61፥4፤78፥69፤150፥1
15፥2 ዘፍ6፥9፤መዝ18፥32፤ምሳ16፥13፤ኢሳ45፥19፤ኤር7፥28፤9፥5፤ዘካ8፥3፡16፤ሮሜ9፥1፤ኤፌ1፥4፤4፥25፤1ተሰ 3፥13፤ቲቶ1፥6
15፥3 ዘሌ19፥16
15፥4 ዘዳ23፥21፤ኢሱ9፥18፤ኢዮ19፥9፤ማቴ5፥33፤ሐሥ28፥10
15፥5 ዘፀ18፥21፤22፥25፤1ሳሙ8፥3፤ኢዮ29፥18፤መዝ21፥7፤112፥6፤ሐሥ2፥25፤24፥26፤ዕብ 12፥28፤2ጴጥ1፥10

[a] 1 በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ሞኝ ወይም ተላላ ተብለው የተተረጐሙት የዕብራይስጥ ቃላት ግብረ ገባዊ ንቅዘትን የሚያመለክቱ ናቸው።

*14፥1፤* "የአላዋቂነትን" ጠባይ ወይም ማንነት ለመግለጽ የቀረበ አይደለም፤ ከዚህ በላይ ያለውን ግብና አግራጭ ትርጕሙን ይመ። *በልቡ፤* የ4፥7 ግብ ይመ። *እግዚአብሔር የለም፤* ክህደት ማለት እንዲህ ያለው ነው (10፥4፡ 6፡11፡ 13፤ 36፥1፤ እንዲሁም የ10፥4 ግብ ይመ)። *ይላል፤* የ3፥2 ግብ ይመ። *በጎ ነገር የሚሠራ አንድም የለም፤* በአጠቃላይ ሲታይ የሰው ዘር ነቅዞአል፣ ከትክክለኛውም መንገድ ወጥቶአል፤ በዚህ ቦታ ቃሉ የተነገረው እግዚአብሔርን ከምንም ለማይቈጥሩና በጻድቃንም ማኅበር ላይ ጉዳት ለማድረስ ወደ ኋላ ለማይመለሱ ሰዎች ነው (ቍ4-5 ይመ)፤ ይኸውም በ9፥19-20፤ 10፥2-11፡13፡ 18፤ 12፥1-4፡7-8 ላይ እንደ ተመለከተው ነው (መዝሙር 11 የሚገልጸውም ይህንኑ ሁኔታ ነው)። በሌላ ቦታ መዝሙረኞቹ ራሳቸውን ያመሳሰሉት በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ካልሆኑ ሰዎች ጋር ነው (130፥3፤ 143፥2፤ እንዲሁም 1ነገ 8፥46፤ ኢዮ 9፥2፤ መክ7፥20 ይመ)።

14፥2 *እግዚአብሔር፤* አላዋቂ ከሆነው ሰው ጋር በአጽንዖት ተነጻጽሮአል (ቍ1)። *እግዚአብሔርን የሚፈልግ፤* እግዚአብሔርን ከልብ የሚፈልጉ ሰዎች እንዳሉ በመዝሙር 15 ላይ ተገልጸዋል።

14፥3 *ከመንገድ ወጥተዋል፤* ከእግዚአብሔርና በጎ ከሆነው ነገር ማለት ነው።

*14፥4-6፤* የክፉ ሰው ቂልነት ምን እንደሚመስል በዚህ ቦታ በሚገባ ተብራርቶአል።

14፥4 *የሚበሉት ... ዕውቀት የላቸውምን?* በአዲስ አገላለጽ የቀረበ የክፉ ሰዎች ባሕርይ ነው፤ በእጃቸው ክፉ ሥራ እንጂ በጌታ አይተማመኑም (10፥2-4 ይመ)።

*14፥5፤* እግዚአብሔር የጻድቃን ጠበቃና መጠጊያ አምባ ሆኖ ጻድቃንን እንዴት እንደሚንከባከባቸው እያዩ እንኳን አይግሩም። *በጻድቃን፤* የ1፥5 ግብ ይመ።

14፥6 *የድኾችን፤* የእግዚአብሔር ሰዎች በፍትህ መጓደል ምክንያት ምን ያህል እንደ ተበደሉ ያመለክታል። *መጠጊያ፤* የ4፥1 ግብ ይመ።

*14፥7፤* መዝሙረኛው እስራኤል ከጠላቶቿ መዳፍ ነፃ የምትወጣበትን ቀን በናፍቆት ይጠባበቃል፤ ይህም የሚሆነው እግዚአብሔር ስለደካሞች ሲል በበቀል ሲገለጥ ነው፤ ይህ ሁኔታ እንዴት ባለ መልክ ተስፋፍቶ እንደ ተገለጸ ለመገንዘብ 10፥16-18 እና ግብ ይመ። *ጽዮን፤* የ9፥11 ግብ ይመ። *ያዕቆብ ... እስራኤል፤* ተመሳሳይ ስሞች ናቸው (ዘፍ32፥28 ይመ)።

*መዝሙር 15፤* ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለመግባት ለሚፈልጉ ሁሉ የተሰጠ መመሪያ ነው (24፥3-6፤ ኢሳ 33፥14-16 ይመ)፤ እንዲሁም የመዝሙር 14 መግቢያን ይመ።

15፥1 *ያድራል ... መኖር ይችላል፤* እንደ ካህን በመሆን ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር እንግዳ በመሆን በቅዱስ ማደሪያው ውስጥ መኖር ማለት ነው (23፥6፤ 27፥4-6፤ 61፥4፤ 84፥10፤ 2ሳሙ 12፥20 ይመ)። *በተቀደሰው ኰረብታህስ፤* የ2፥6 ግብ ይመ።

*15፥2-5፤* መሥዋዕት ወይም የመንጻት ሥርዐት ሳይሆን (በጥንት ቅርብ ምሥራቃውያን ሃይማኖታዊ ልምምድ ውስጥ ይደረግ እንደ ነበረው)፣ ምግባራዊ ቅድስና ነው ወደ እግዚአብሔርና ወደ እስራኤልም አምላክ ፊት ለመግባት የሚያበቃው (በመጀመሪያ የተሰጠውን ኪዳናዊ ሕግ ለማጤን ዘፀ20፥1-17፤ እንዲሁም ኢሳ1፥10-17፤ 33፥14-16፤ 58፥6-10፤ ኤር7፥2-7፤ ሕዝ18፥5-9፤ ሆሴ6፥6፤ አሞ5፥14-15፡21-24፤ ሚክ6፥6-8፤ ዘካ7፥9-10፤ 8፥16-17 ይመ)።

15፥2 *አካሄዱ ንጹሕ የሆነ፤* ዘፍ17፥1 እና ግብ ይመ። *ጽድቅን የሚያደርግ፤* የ1፥5 ግብ ይመ። *ጽድቅን፤* የ1፥5 ግብ ይመ። *ከልቡ፤* የ4፥7 ግብ ይመ።

15፥3 *በምላሱ፤* የ5፥9 ግብ ይመ።

15፥4 *እግዚአብሔርን የሚፈሩትን፤* እግዚአብሔርን የሚያከብሩና ሕይወታቸውንም እንደ ፈቃዱ የሚመሩ ማለት ነው (የዘፍ 20፥11 ግብ ይመ)፤ ይህንንም የሚያደርጉት ለእርሱ ካላቸው ከፍተኛ አክብሮት ነው።

15፥5 *በአራጣ፤* የዘፀ22፥25-27 ግብ ይመ። *አይናወጥም፤* የ10፥6 ግብ ይመ።

*መዝሙር 16፤* ለራስ ደኅንነት ሲባል የቀረበ ጸሎት ሲሆን (በጸሎት መዝሙሮች ውስጥ የሚገኙ ልመናዎች በአብዛኛው አጭር ናቸው፤ 3፥7፤ 22፥19-21፤ 44፥23-26 ይመ)፤ ጌታ ሕዝቡን ከሞት ዛቻ እንዲጠብቅ ልመናም የሚያቀርብ ጸሎት ነው፤ ይህ መዝሙር የመታመኛ መዝሙር ተብሎም ሊጠራ ይችላል።

16ርእስ *ቅኔ፤* በታላቅ አደጋ ጊዜ ዳዊት ባቀረባቸው ጸሎቶች (መዝ56-60 ይመ) መግቢያ ላይ ቢገኝም ቃሉ ግን ምስጢር እንደ ሆነ አለ።

## መዝሙር 16
### እግዚአብሔር ርስቴ

የዳዊት ቅኔ

[1]ስምዓኒ ሆይ፤ መጠጊያዬ ነህና፣
በከለላህ ሰውረኝ።
[2]*እግዚአብሔርን*፣ "አንተ ጌታዬ ነህ፤
ከአንተ በቀር በጎነት የለኝም" አልሁት።
[3]በምድር ያሉ ቅዱሳን፣
ሙሉ ደስታ የማገኝባቸው ክቡራን
ናቸው።[ሀ]
[4]ሌሎችን አማልክት የሚከተሉ፣
ሐዘናቸው ይበዛል፤
እኔ ግን የደም ቍርባናቸውን አላፈስም፤
ስማቸውንም በአፌ አልጠራም፤
[5]*እግዚአብሔር* የርስት ድርሻዬና ጽዋዬ
ነው፤
ዕጣዬም በእጅህ ናት።
[6]*መካለያ ገመድ ባማረ ስፍራ ተጥሎልኛል፤*
በእርግጥም የተዋበች ርስት አግኝቻለሁ።
[7]የሚመክረኝን *እግዚአብሔርን* እባርካለሁ፤
በሌሊት እንኳ ልቤ ቀናውን
ያመላክተኛል።
[8]*እግዚአብሔርን* ሁልጊዜ በፊቴ
አድርጌአለሁ፤
እርሱ በቀኜ ስላለ አልናወጥም።
[9]ስለዚህ ልቤ ደስ አለው፤ ነፍሴም
ሐሤት አደረገች፤
ሥጋዬም ያለ ሥጋት ዐርፎ ይቀመጣል፤
[10]በሲኦል[ለ] ውስጥ አትተወኝምና፤
ቅዱስህም[ሐ] መበስበስን እንዲያይ
አታደርግም።
[11]የሕይወትን መንገድ ታሳየኛለህ፤[መ]
በአንተ ዘንድ የደስታ ሙላት፣
በቀኝህም የዘላለም ፍሥሐ አለ።

## መዝሙር 17
### የንጹሕ ሰው አቤቱታ

የዳዊት ጸሎት

[1]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ በቅንነት የቀረበውን
አቤቱታዬን ስማ፤
ጩኸቴንም አድምጥ፤
ከአታላይ ከንፈር ያልወጣውን፣
ጸሎቴን አድምጥ።

16፥1 መዝ2፥12፤ 12፥7
16፥2 መዝ31፥14፤ 73፥25፤118፥28፤ 140፥6
16፥3 ዘዳ33፥3፤ መዝ30፥4፤85፥8፤101፥6፤ዳን7፥18፤ሐሥ9፥13፤ሮሜ1፥7
16፥4 ዘፀ18፥11፤ 20፥3፤23፥13፤ዘዳ 8፥19፤31፥20፤መዝ 32፥10፤ምሳ23፥29
16፥5 ዘሌ2፥2፤ኢዮ 31፥2፤መዝ23፥5፤75፥8፤116፥13፤ኢሳ51፥17፤ሰቆ4፥21፤ሕዝ23፥32-34፤ዕን2፥16
16፥6 ዘዳ19፥14፤ ኢዮ22፥26፤መዝ 104፥9፤ምሳ8፥29፤ ኤር5፥22
16፥7 ኢዮ35፥10፤ መዝ42፥8፤73፥24፤77፥6፤ምሳ15፥22፤ኢሳ 11፥2
16፥8 1ነገ2፥19፤ 1ዜና6፥39፤መዝ15፥5፤73፥23
16፥9 ዘዳ33፥28፤ መዝ4፥7፤13፥5፤28፥7፤30፥11
16፥10 ዘኍ16፥30፤2ነገ19፥22፤ኢዮ
17፥14፤መዝ30፥3፤31፥17፤86፥13፤ሆሴ13፥14፤ሐሥ2፥31፤13፥35
16፥11 መዝ21፥6፤ 80፥17፤139፥24፤ማቴ 7፥14፤ሐሥ2፥25-28
17፥1 መዝ5፥1፡2፤30፥10፤39፥12፤64፥1፤80፥1፤140፥6፤142፥6፤ 143፥1፤ኢሳ29፥13

[ሀ]3 *ወይም በምድሪቱ ላሉ አረማውያን፣ ካህናትና ደስ ለተሰኙ ባቸው መኳንንት ሁሉ ይህን እላለሁ*
[ለ]10 *ወይም በመቃብር*
[ሐ]10 *ወይም በአንተ የተታመነውን*
[መ]11 *ወይም ታሳውቀኛለህ*

*16፥1፤* ልመናንና ልመናው የቆመበትን መሠረት ይዞአል። ቀሪው የመዝሙሩ ክፍል የሚያብራራውና ግልጽ የሚያደርገው ልመናው የቆመበትን መሠረት አስመልክቶ ነው።

*16፥2-4፤* ዳዊት ያለው አንድ ብቸኛ መልካም ነገር እግዚአብሔር ብቻ ነው (73፥25፡28 ይመ)፤ ዳዊት ሌሎች ሰዎች የመጠጥ ቍርባን ከሚያወርዱላቸው ባእድ አማልክት ጋር በምንም መልኩ አይተባበርም።

16፥2 *ከአንተ በቀር በጎነት የለኝም፤* መዝሙረኛው ከእግዚአብሔር ውጪ ሕይወት ትርጕምና ጣዕም እንደሌላት ተመልክቶአል፤ ጌታም ከእርሱ ጋር ከሌለና በረከቱንም ካልሰጠው በሕይወቱ ውስጥ አንዳች በጎ ነገር የለም። ጳውሎስ ይህንኑ እውነታ እንዲህ በማለት አጠቃሎታል፣ "ለእኔ ሕይወት ማለት ክርስቶስ ነው" (ፊል1፥21 ከገላ2፥20 ጋር ያነጻጽሩ)።

*16፥3፤* መዝ101 ይመ።

16፥4 *ሐዘናቸው ይበዛል፤* ለዳዊት ታላቅ ሐሤትን ከሚያመጣለት (73፥18-20)፣ መልካም "ዕድል" (ቍ5፤ የ11፥6 ማብ ይመ) ጋር ተነጻጽሮ የቀረበ ነው። *የደም ቍርባናቸውን፤* በመሥዋዕት ማቅረቢያ ላይ የፈሰሰ የደም መሥዋዕት ማለት ነው። *ስማቸውንም በአፌ አልጠራም፤* ወደ እነርሱ አልመለከትም፣ እነርሱንም አላመልክም ማለት ነው (ኢያ 23፥7)።

*16፥5-6፤* ከጌታ በሆነና ከእርሱም በተገኘ ርስት መዝሙረኛው ሐሤት አደረገ፤ ዳዊት በዚህ ቦታ የሚጠቅሰው እግዚአብሔር በተስፋዪቱ ምድር ለሕዝቡ ስለ ሰጠው የዕርሻና የአትክልት ቦታ (ዘኍ 16፥14 ይመ) ወይም የካህናትና (ዘኍ 18፥20 ይመ) የሌዋውያን (ዘዳ10፥9) ርስት ስለ ሆነው ስለ ራሱ ስለ ጌታ ነው (ይኸውም በ73፥26፤ 119፥57፤ 142፥5፤ ሰቆ3፥24 ላይ እንደ ተጠቀሰው ማለት ነው)።

16፥5 *ጽዋዬ፤* እንግዳ ተቀባይ ለእንግዶቹ የሚያቀርበውን መጠጥ የሚያመለክት ተምሳሌት ወይም ዘይቤ ነው። ጌታ ለቅዱሳን የበረከት ጽዋን (23፥5) ወይም ድነትን (116፥13) ይሰጣቸዋል፤ ለክፉዎች ግን የቍጣውን ጽዋ እንዲጠጡ ያደርጋል (ኤር 25፥15፤ ራእ14፥10፤ 16፥19 ይመ)። *በእጅህ፤* በተስፋዪቱ ምድር የእያንዳንዱ እስራኤላዊ ቤተ ሰብ ርስት እንደሚጠበቀው ዐይነት ማለት ነው (ዘሌ 25፤ ዘኍ36፥7 ይመ)።

*16፥7-8፤* ጠባቂና መካሪ ለሆነው ጌታ የቀረበ ምስጋና ነው።

16፥7 *የሚመክረኝን፤* የሕይወት ጐዳናን የሚያሳየኝ ማለት ነው (ቍ11 ይመ)። *ልቤ፤* የዕብራይስጡ ቃል በቀጥታ ሲተረጐም "ኵላሊቴን" ማለት ነው (የ7፥9 ማብ ይመ)።

16፥8 *በቀኜ ስላለ፤* እያጸናኝ፣ እየተንከባከበኝና እየጠበቀኝ ሁልጊዜ ከአጠገቤ አለ ማለት ነው (73፥23፤ 109፥31፤ 110፥5፤ 121፥5 ይመ)፤ በቍ11 ላይ የጌታን ቀኝ እጅ በማመልከት ይበልጥ ጉልህ ሆኖአል። *አልናወጥም፤* የ10፥6 ማብ ይመ።

*16፥9-11፤* እስተማማኝ ዋስትና ማግኘት ምን ያህል እንደሚያስደስት ይገልጻል፤ ዳዊት በሌሎች መዝሙሮቹ ውስጥ እንደ ገለጸው ሁሉ፣ በዚህም መዝሙሩ ውስጥ እግዚአብሔር ከልግስናው ና ከጥበቃው የተነሣ ሁለንተናውን እንዴት በሐሤት እንዳጥለቀለቀው ይናገራል፤ መዝሙረኛው መጠጊያና አምባ ያደረገው ጌታ፣ አገልጋዩ በሕይወት እንዲኖር ፈቃዱ ሆኖአል (ከዚህም የተነሣ የሕይወትን መንገድ አሳይቶታል ቍ11)፤ ምንም እንኳ "አእምሮውና ጉልበቱ ቢደክሙም" (73፥26) ለመቃብር ግን አሳልፎ አይሰጠውም። በእነዚህ የዋስትና ቃላት ውስጥ (ግልጥልጥ ባለ መልኩ ባይሆንም) ጽኑ እምነት ያለ ይመስላል፤ ምክንያቱም ጌታ መጠጊያውና ዐምባው ከሆነ መቃብር ሕይወቱን ሊገፈው አይችልም (17፥15፤ 73፥24፤ እንዲሁም የ11፥7 ማብ ይመ)። ለዳዊት እንዲህ ተብሎ ከተነገረ፣ ለዳዊት የተስፋ ልጅማ እንዴት የበለጠ ይሆን! በመሆኑም ጴጥሮስ ቍ8-11 በመጥቀስ ዳዊት ስለ ክርስቶስና ስለ ትንሣኤው ትንቢት ተናገረ ይላል (ሐሥ 2፥25-28፤ እንዲሁም ጳውሎስ በሐሥ13፥35 ላይ ቍ10ን በተመሳሳይ ሁኔታ እንዴት እንደ ተጠቀመበት ይመ)። እንዲሁም የ6፥5 ማብ ይመ።

16፥9 *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *ነፍሴም፤* ቀጥታ ሲተረጐም "ሞገስ" ("ክብር") ማለት ነው (የ7፥5 ማብ ይመ)።

16፥10 *ቅዱስህም፤* በዕብራይስጥ ቋንቋ "ሃሲድ" ማለት ሲሆን ፍቺውም "የተወደደ ወይም የታመነ" ማለት ነው (የ4፥3 ማብ ይመ)፤ ይህ ቃል በመጀመሪያ የተነገረው ለዳዊት ነው (የ2፥2 ማብ ይመ)፤ ይሁን እንጂ በስተ መጨረሻ በክርስቶስ ተፈጽሞአል።

16፥11 *የሕይወት መንገድ፤* ምሳ15፥24 ይመ። *በቀኝህም፤* የቍ8 ማብ ይመ።

*መዝሙር 17፤* መዝሙረኛው ክፉ ጠላቶች በተነሡበት ጊዜ እግዚአብሔር በቅንነት እንዲፈርድለት አቤቱታውን ያቀርባል። ይህ መዝሙር በንጉሥ ፊት ትክክለኛውን ፍርድ ለማግኘት ዕብራውያን የሚጠቀሙበትን ዘዴ ወይም ይትበሀል የተከተለ ነው።

17ርእስ *ጸሎት፤* የመዝ86፤ 90፤ 102፤ 142 እንዲሁም 72፥20 ርእሶችን ይመ።

*17፥1-2፤* ፍትሕ ይታይ ዘንድ የቀረበ አቤቱታ ነው።

17፥1 *በቅንነት ... አቤቱታ፤* መዝሙረኛው ያቀረበው አቤቱታ ትክክለኛ ነው፤ አቤቱታው ከአታላይ ከንፈር የወጣ የብልጣ

2 ጽድቁ ከአንተ ዘንድ ይምጣ፤
ዐይኖችህም ፍትሕን ይዩ።
3 ልቤን መረመርኸው፣ በሌሊት ጠጋ
ብለህ ፈተንኸኝ፣
ፈተሸኸኝ አንዳች አላገኘህብኝም፤
አንደበቴም እላፊ አልሄደም።
4 ከሰዎች ተግባር፣
በከንፈርህ ቃል፣
ከዐመፀኞች መንገድ፣
ራሴን ጠብቄአለሁ።
5 አረማመዴ በመንገድህ ጸንቶአል፤
እግሮቼም አልተንሸራተቱም።
6 አምላክ ሆይ፤ ስለምትመልስልኝ አንተን
እጣራለሁ፤
ጆሮህን ወደ እኔ ጣል አድርገህ፣
ጸሎቴን ስማ።
7 ከጠላቶቻቸው መተገኛ ያደረጉህን፣
በቀኝ እጅህ የምትታደግ ሆይ፤
ጽኑ ፍቅርህን ድንቅ አድርገህ ግለጥ።
8 እንደ ዐይንህ ብሌን ጠብቀኝ፤
በክንፎችህም ጥላ ሰውረኝ፤
9 ከሚያስጨንቁኝ ከክፉዎች፣
ከሚከብቡኝ አደገኛ ባላንጣዎቼ
ጋርደኝ።
10 ደንዳና ልባቸውን ደፈኑት፤
በአፋቸውም ትዕቢት ይናገራሉ።
11 አሳደው ደረሱብኝ፤ ከበቡኝም፤
መሬት ላይ ሊዘርሩኝም አፈጠጡብኝ።
12 እነርሱ ለንጥቂያ እንደሚጓጓ አንበሳ፣
በስውርም እንደሚያደባ ደቦል አንበሳ
ናቸው።
13 እግዚአብሔር ሆይ፤ ተነሥተህ
ግጠማቸውና ጣላቸው፤
በሰይፍህም ከክፉዎች ታደገኝ።
14 እግዚአብሔር ሆይ፤ እንዲህ ካሉት
ሰዎች በክንድህ አድነኝ፤
ዕድል ፈንታቸው ይህችው ሕይወት
ብቻ ከሆነች፣ ከዚህ ዓለም ሰዎች
ታደገኝ።
ከመዝገብህ ሆዳቸውን ሞላህ፤
ልጆቻቸውም ተትረፍርፎላቸዋል፤
ለልጆቻቸውም ሀብት ያከማቻሉ።
15 እኔ ግን በጽድቅ ፊትህን አያለሁ፤
ስነቃም ክብርህን አይቼ እረካለሁ።

## መዝሙር 18

### የድል መዝሙር

18 ርእስ-50 ተጓ ምብ-2ሳሙ22፥1-51

*ለመዘምራን አለቃ፤ የእግዚአብሔር ባሪያ የዳዊት መዝ ሙር፤ ይህም እግዚአብሔር ከሳኦልና ከጠላቶቹ ሁሉ እጅ በታደገው ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲል የዘመረው ነው፦*

1 ጕልበቴ እግዚአብሔር ሆይ፤ እወድሃለሁ።

17፥2 መዝ24፥5፤ 26፥1፤99፥4፤ኢሳ46፥13፤50፥8-9፤54፥17
17፥3 ኢዮ7፥18፤ 23፥10፤መዝ39፥1፤139፥1፤ኤር12፥3፤ 50፥20
17፥5 ዘዳ32፥35፤ ኢዮ23፥11፤መዝ 44፥18፤73፥2፤119፥133፤121፥3
17፥6 መዝ4፥1፤86፥7፤116፥2
17፥7 መዝ2፥12፤10፥12፤31፥21፤69፥13፤106፥45፤107፥43፤117፥2
17፥8 ዘኍ6፥24፤ ዘዳ32፥10፤ሩት2፥12፤መዝ27፥5፤31፥20፤32፥7፤36፥7፤63፥7፤ምሳ 7፥2፤ኢሳ34፥15
17፥9 መዝ109፥3
17፥10 1ሳሙ2፥3፤መዝ73፥7፤119፥70፤ ኢሳ6፥10
17፥11 መዝ88፥17
17፥12 ዘፍ49፥9፤ መዝ7፥2፤ኤር5፥6፤12፥8፤ሰቆ3፥10
17፥13 ዘኍ10፥35፤ መዝ35፥8፤55፥23፤73፥18
17፥14 መዝ49፥17፤ኢሳ2፥7፤57፥17፤ ሉቃ16፥8:25
17፥15 ዘኍ12፥8፤ መዝ3፥5፤ማቴ5፥8፤
1ዮሐ3፥2 18፥1 ዘፀ15፥2፤ዘዳ33፥29፤1ሳሙ2፥10፤መዝ22፥19፤ 28፥7፤59፥9፤81፥1፤ኢሳ12፥2፤ 49፥5፤ኤር16፥19

ብልጦች ቃል አይደለም (ይህን ስለ መሰለው ሁኔታ 1ሳሙ 24፥15 ይመ)።

*17፥3-5፤* ዳዊት በእርግጥ ጻድቅ ሰው መሆኑን ለማረጋገጥ ንጽሕናውን አንድ በአንድ በመዘርዘር ይገልጻል፤ በእርሱ ላይ የተነሡ ጠላቶች በሄዱበት መንገድ አልሄደም፤ ለዚህም ሁለመናውን በርብሮ የሚያይ እግዚአብሔር ምስክሩ ነው (ከ139፥23-24 ጋር ያነጻጽሩ)።

17፥3 ***ልቤን፤*** የ4፥7 ማብ ይመ።

17፥4 ***በከንፈርህ ቃል፤*** እግዚአብሔር ፈቃዱን ያስታወቀው ሰዎች የእግዚአብሔርን መንገድ እንዲያውቁና (ቍ5) በዚያም መንገድ እንዲመላለሱ ነው።

*17፥6-9፤* በልበ ሙሉነት የቀረበ አቤቱታ ወይም ልመና ነው፤ ይህም ልመና በእግዚአብሔር ታማኝነትና ("ስለምትመልስልኝ" ቍ6)፣ በጽድቅም ላይ የተመሠረተ ነው (ቍ7)።

17፥7 ***ድንቅ፤*** የ9፥1 ማብ ይመ። ***ጽኑ ፍቅርህን፤*** የ6፥4 ማብ ይመ።

17፥8 ***እንደ ዐይንህ ብሌን፤*** የዘዳ32፥10 ማብ ይመ። ***ጥላ፤*** የዛፍ ወይም የአንድ ማንኛውም ነገር ጥላ ከሚያንገበግብ የፀሐይ ሐሩር እንደሚከልል ሁሉ እግዚአብሔርም ሕዝቡን ከክፉ ጨቋኞች የሚከላከል መሆኑን የሚያሳይ ተምሳሌት ነው፤ እንዲህ ያለው ተምሳሌት በዕብራውያን ዘንድ በጣም የተለመደ ነው። ነገሥታት ከበታቻቸው ለሚያስተዳድሯቸው ሕዝቦች እንደ "ጥላ" ይቈጠሩ ነበር (ይኸውም በዘኍ14፥9፤ ሰቆ4፥20፤ ዕዝ31፥6:12:17 ላይ እንደ ተጠቀሰው ዐይነት ነው)። ልክ እንዲሁ ጌታም ሕዝቡን የሚጠብቅ "ጥላ" ነው (91፥1፤ 121፥5፤ ኢሳ 25፥4፤ 49፥2፤ 51፥16 ይመ)። ***በክንፎችህም፤*** የእግዚአብሔርን ጽኑ ጥበቃ የሚያመለክት ተምሳሌት ነው (36፥7፤ 57፥1፤ 61፥4፤ 63፥7፤ 91፥4፤ ሩት2፥12 እንዲሁም 23፥37 ይመ)።

*17፥10-12፤* ክፉ በሆኑ ጠላቶች ላይ የቀረበ ክስ ነው (የ5፥9-10 ማብ ይመ)።

17፥10 ***በአፋቸውም፤*** የ5፥9 ማብ ይመ። ***በትዕቢት ይናገራሉ፤*** የ10፥11ማብ ይመ።

17፥12 ***አንበሳ፤*** የ7፥2 ማብ ይመ።

17፥13-14 ምልጃ ነው፤ እግዚአብሔር በጠብ ላይ የሚገኙ ሁለት ባላንጣዎችን እንዴት እንደሚዳኝ የሚጠይቅ ልመና ነው።

17፥13 ***ተነሥተህ፤*** የ3፥7 ማብ ይመ። ***ጣላቸው፤*** የ5፥10 ማብ ይመ።

17፥14 ***እንዲህ ካሉት ሰዎች፤*** 9፥19-20፤ 10፥18፤ 12፥1-4:8፤ 14፥1-3 ይመ።

*17፥14ለ-15፤* በእግዚአብሔር መታመንን የሚገልጽ የመዝጊያ ቃል ነው (የ3፥8 ማብ ይመ)።

17፥15 ***በጽድቅ፤*** ጻድቅ የሆነው ፈራጅ (የ4፥1 ማብ ይመ) ንጽሕናውን ተመልክቶ ከበደል ነጻ መሆኑን ይመሰክርለታል። ***ፊትህን አያለሁ፤*** የ11፥7 ማብ ይመ። ***ስነቃም፤*** ከሞት ጨለማ ማለት ነው (የ11፥7 ማብ ይመ)፤ ይህም "ከዚህ ዓለም ሰዎች" እጣ ፈንታ እጅግ ልዩ ነው (ቍ14፤ የ16፥9-11 ማብ ይመ)። ***ክብርህን አይቼ፤*** የጌታ አገልጋይ የነበረው ሙሴ እንደ አየው ዐይነት ማለት ነው (ዘኍ12፥8 ይመ)።

መዝ18 ይህ የዳዊት መዝሙር (አነስተኛ ለውጥ ይታይበት እንጂ) በ2ሳሙ22 ላይ ይገኛል (ማብ በዚያው ክፍል ይመ)። የዚህ መዝሙር አወቃቀር ከመግቢያውና ከመደምደሚያው (46-50) በስተቀር በሦስት ዐበይት ክፍሎች ሊመደብ ይችላል፤ (1) ጌታ ኃች ከሆኑ ጠላቶች ዳዊትን ስለ መታደጉ (ቍ4-19)፣ (2) የጌታ የማዳን ሥራ በምግባራዊ መሠረት ላይ ስለመቆሙ (ቍ20-29)፣ (3) የጌታ ርዳታ በግልጽ ስለመነገሩ (ቍ30-45)።

18ርእስ ***ለመዘምራን አለቃ፤*** የመዝሙር 4ርእስ ማብ ይመ። ***የእግዚአብሔር ባሪያ፤*** 78፥70፤ 89፥3:20:39፤ 132፥10፤ 144፥10 ይመ። ሙሴ (ዘዳ14፥31 እና ማብ ይመ)፣ ኢያሱ (ኢሱ 24፥29) እና ነቢያት (ኤልያስ 2ነገ9፥36፤ ዮናስ 2ነገ14፥25፤ ኢሳይያስ ኢሳ20፥3፤ ዳንኤል ዳን6፥20) እግዚአብሔር ራሱ በሚያስተዳድረው ሕዝብ ላይ ከእግዚአብሔር ባገኙት ውክልና ሹማምንት እንደ ነበሩ ሁሉ ይህም መዝሙር ዳዊት ንጉሣዊ ኀላፊነትን እንደ ተቀበለ ያሳያል (2ሳሙ7፥5 ይመ)። ***እግዚአብሔር ... በታደገው ጊዜ፤*** ዳዊት ይህን መዝሙር የጻፈው የውጭ ጠላቶቹን ድል ካደረገ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ሊሆን ይችላል (2ሳሙ 8፥1-14) ግን ደግሞ በመጨረሻው የሕይወት ዘመኑም ሊሆን ይችላል።

*18፥1-3፤* የምስጋና መቅደም ነው።

*18፥1፤* በ2ሳሙ22 ላይ አልተጠቀሰም። ***እወድሃለሁ፤*** በዕብራይስጥ ቋንቋ የተለመደ አባባል ባይሆንም የዳዊትን ፍቅር በአ

2 እግዚአብሔር ዐለቴ፣ መጠጊያዬና
ታዳጊዬ ነው፤
ስምባኤ የምሸሸግበት ዐለቴ፤
እርሱ ጋሻዬ፣ የደንንቴ ቀንድና[ሀ]
ዐምባዬ ነው።
3 ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን
እጠራለሁ፤
ከጠላቶቼም እድናለሁ።
4 የሞት ገመድ አነቀኝ፤
የጥፋት ጐርፍም አጥለቀለቀኝ።
5 የሲኦል[ለ] ገመድ ተጠመጠመብኝ፤
የሞት ወጥመድም ተጋረጠብኝ።
6 በተጨነቅሁ ጊዜ እግዚአብሔርን
ጠራሁት፤
እንዲረዳኝም ወደ ስምባኤ ጮኽሁ፤
እርሱም ከመቅደሱ ድምፄን ሰማ፤
ጩኸቴም ከፊቱ ደረሰ፤ ወደ ጆሮውም
ገባ።
7 ምድር ተንቀጠቀጠች፤ ተናወጠችም፤
የተራሮችም መሠረት ተናጋ፤
ጌታ ተቈጥቶአልና ተንቀጠቀጡ።
8 ከአፍንጫው ጢስ ወጣ፤
የሚባላ እሳት ከአፉ፤
የፍም ነበልባል ከእርሱ ፈለቀ።
9 ሰማያትን ሰንጥቆ ወረደ፤
ከእግሩም በታች ጥቍር ደመና ነበረ።
10 በኪሩቤል ላይ ተቀምጦ በረረ፤
በነፋስም ክንፍ መጠቀ።
11 ጨለማን መሰወሪያው፣ በዙሪያውም
አጐበሩ አደረገው፤
በዝናብ አዘል ጥቍር ደመናም ተሸፈነ።
12 በፊቱ ካለው ብርሃን የተነሣ፣
ደመናት፣ የበረዶ ድንጋይና መብረቅ
ወጡ።
13 እግዚአብሔር ከሰማያት አንጐደጐደ፤
ልዑልም ድምፁን አስተጋባ።[ሐ]
14 ፍላጻውን አስፈንጥሮ በተናቸው፤
መብረቅ አሽጐድጒዶ አሳደዳቸው።
15 እግዚአብሔር ሆይ፤ ከተግሣጽህ የተነሣ፣
ከአፍንጫህም እስትንፋስ የተነሣ፣
የባሕር ወለል ተገለጠ፤
የዓለምም መሠረት ራቍቱን ቀረ።
16 ከላይ እጁን ወደ ታች ዘርግቶ ያዘኝ፤
ከብዙ ጥልቅ ውሃም አወጣኝ፤
17 ከኀያላን ጠላቶቼ አዳነኝ፤
ከእኔ ከሚበረቱ ባላንጣዎቼም ታደገኝ።
18 እነርሱ በመከራዬ ቀን መጡብኝ፤
እግዚአብሔር ግን ድጋፍ ሆነኝ።
19 ወደ ሰፊ ስፍራ አወጣኝ፤
ደስ ተሰኝቶብኛልና አዳነኝ።

18፥2 ዘፍ15፥1፤ዘዐ 33፥22፤1ሳሙ2፥1፤ መዝ2፥12፤9፥9፤28፥7 ፥8፤31፥2፥3፤40፥17፤8 4፥9፤94፥22፤119፥ 114፤144፥2፤ኢሳ17፥ 10፤ኤር16፥19፤ሉቃ 1፥69
18፥3 1ዜና16፥25 ፤መዝ9፥13
18፥4 መዝ93፥4፤ 116፥3፤124፥4፤ኢሳ 5፥30፤17፥12፤ኤር6፥ 23፤51፥42፡55፤ሕዝ 43፥2
18፥5 ምሳ13፥14
18፥6 ዘዳ4፥30፤ኢዮ 16፥18፤መዝ30፥2፤66 ፥19፤99፥6፤102፥2፤1 16፥1፤120፥1
18፥7 መሳ5፥4፡5፤ ኢዮ9፥5፤መዝ97፥4 ፤ኢሳ5፥25፤64፥3፤ኤር 10፥10
18፥8 ዘዐ15፥7፤ 19፥18፤ኢዮ41፥20፡ 21፤መዝ50፥3፤97፥3፤ ምሳ25፥22፤ዳን7፥10፤ ሮሜ12፥20
18፥9 ዘፍ11፥5፤ዘዐ 20፥21፤ዘዳ33፥26፤ መዝ57፥3፤104፥3
18፥10 ዘፍ3፥24፤ዘዳ 33፥26፤መዝ104፥3፤ ሕዝ10፥18
18፥11 ዘዐ19፥9፤ዘዳ 4፥11፤ኢዮ22፥14፤ ኢሳ4፥5፤ኤር43፥10
18፥12 ኢሱ10፥11፤ ኢዮ36፥30፤መዝ 104፥2
18፥13 ዘዐ9፥23፤ 1ሳሙ2፥10 18፥14 ዘዳ32፥23፤ መሳ4፥15፤ኢዮ36፥ 30፤ራእ4፥5
18፥15 ዘዐ15፥8፤ መዝ 11፥3፤76፥6፤ 104፥7፤106፥9፤ኢሳ 50፥2
18፥16 ዘዐ15፥5፤መዝ69፥2፤ምሳ18፥4፤20፥5 18፥17 ቈላ48፤ምሳ 18፥26፤መዝ38፥19፤59፥1፤143፥9 18፥18 መዝ20፥2፤ምሳ1፥27፤ 16፥4፤ኢሳ 3፥1፤ኤር17፥17፤40፥2፤አብ1፥13
18፥19 ዘኍ14፥8፤ መዝ31፥8

[ሀ]2 *ቀንድ በዚህ ቦታ ብርታትን ያመለክታል*
[ለ]5 ወይም *የመቃብር*
[ሐ]13 አንዳንድ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆችና ሰብዓ ሊቃናት (በተጨማሪ 2ሳሙ22፥14 ይመ) እንዲሁ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ የዕብ ራይስጥ የጥንት ቅጆች ግን ... *አስተጋባ፤ በድንጋይ ዝናብ በድንገተኛ መብረቅ መካከል* የሚለውን ይጨምራሉ።

*ጽንዖት ያሳያል።*

18፥2 *ዐለቴ ... መጠጊያዬና፤* እግዚአብሔርን በ"ዐለት" መመሰል የተለመደ ዘይቤአዊ አገላለጽ ነው ("ዐለት" የሚለው ቃል ለባእድ አማልክትም ያገለግላል፤ ዘዳ32፥31፡37፤ ኢሳ44፥8)፤ ይህ ቃል እግዚአብሔር የዘላለም መጠጊያ አምባ (31፥46፤ 31፥2-3፤ 42፥9፤ 62፥7፤ 71፥3፤ 94፥22፤ ኢሳ17፥10) ወይም *ታዳጊና ቤዛ መሆኑን ያመለክታል* (19፥14፤ 62፥2፤ 78፥35፤ 89፥26፤ 95፥1፤ ዘዳ32፥15) *ቃሉ* ሁልጊዜ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ምንጊዜም የማይዝልና የማይታክት መሆኑን ነው። ጌታ የዳዊት እውነተኛ አምባ በመሆኑ የዳዊትን የሕይወት ልምድ (ገጠመኝ) (1ሳሙ23፥14፡25፤ 24፥2፡22፤ 26፥20 ይመ) ለመግለጽ ተገቢ የሆነ አባባል ነው። *መጠጊያዬ፤* የ2ሳሙ22፥2 ማብ ይመ። *ጋሻዬ፤* የ3፥3 ማብ ይመ። *ቀንድና፤* ዘዳ33፥17፤ ኤር 48፥25 ይመ።

*18፥4-5፤* ዳዊት ለሞት የሚያደርሰውን የሕይወት ገጠመኝ ቅኔያዊ በሆነ መልክ ይገልጻል።

18፥4 *ገመድ፤* 2ሳሙ22፥5 "ማዕበል" ይለዋል። *የጥፋት ጐርፍም፤* የ30፥1 ማብ ይመ።

18፥5 *የሲኦል ገመድ ... የሞት ወጥመድም፤* 116፥3 ይመ። መዝሙረኛው የሞት ወጥመድ እንደ ያዘውና የመቃብርም እስረኛ እንደ ሆነ ይናገራል፤ በዚህ ቦታ "ሞትና መቃብር" ሰውኛ ባሕሪን ተጐናጽፈዋል (ኢዮ36፥8 ይመ)።

18፥6 *ከመቅደሱ፤* እግዚአብሔር እጅግ ገዝፎና ተልቆ የሚገኝበት ሰማያዊ መንበሩ ነው (11፥4፤ 113፥5፤ ኢሳ6፥1፤ 40፥22 ይመ)።

*18፥7-15፤* እግዚአብሔር ባሪያውን ለመርዳት መጣ፤ አመጣጡ ግን እጅግ አስፈሪና አስደንጋጭ ከመሆኑም በላይ እንደ ሰማያዊ ጦረኛም ተመስሎአል (5፥4-5፤ 68፥1-8፤ 77፥16-19፤ ሚክ 1፥3-4፤ ናሆ1፥2-6፤ ዕን3፥3-15)። በዳዊትም ጠላቶች ላይ እንደ አስፈሪ መብረቅ ወረደ (ኢል10፥11፤ መሳ5፥20-22፤ 1ሳሙ2፥10፤ 7፥10፤ 2ሳሙ5፥24፤ ኢሳ29፥6 ይመ)።

*18፥8፤* አስፈሪ የሆነው የእግዚአብሔር ግርማ አስደንጋጭ በሆነው በሌዋታን አውሬ (ኢዮ41፥19-21) ተመስሎአል።

18፥9 *ሰማያትን ሰንጥቆ ወረደ፤* ኢሳ64፥1 እና ማብ ይመ።

18፥10 *በኪሩቤል፤* የግርማዊነትና የንጉሣዊነት ተምሳሌት ወይም ምልክት ነው (80፥1፤ 99፥1፤ እንዲሁም የዘፍ3፥24፤ የዘዐ 25፥18 ማብ ይመ)፤ በሕዝ1፥10 ላይ ኪሩቤል የእግዚአብሔር ዙፋን ሰረገላ ተሸካሚዎች ሆነው ተገልጸዋል።

18፥13 *ድምፁን፤* ነጐድጓድ የእግዚአብሔር ድምፅ ሆኖ ስለመገለጹ መዝ29፤ ኢዮ37፥2-5 ይመ። *ልዑልም፤* የዘፍ14፥19 ማብ ይመ።

18፥14 *ፍላጻውን፤* የመብረቅ በትር የእግዚአብሔር ፍላጻ ሆኖ ስለመገለጹ፣ 77፥17፤ 144፥6፤ ዕን3፥11 ይመ።

*18፥15፤* ሰማያዊ ተዋጊው በቀይ ባሕር ውስጥ የእስራኤልን ጠላቶች ባሸነፈ ጊዜ ያደረገውን ታላቅ ተጋድሎ የሚያስታውስ ይመስላል (ዘዐ 15፥1-12 ይመ)።

*18፥16-19፤* ለመዝሙረኛው የተደረገውን ድነት ያመለክታል።

18፥16 *ውሃም፤* የ32፥6 ማብ ይመ።

18፥19 *ሰፊ ስፍራ፤* 4፥1 እና ማብ ይመ፤ በፍርሀትና በአደጋ ሳይታሰር ነጻ ሆኖ የሚንቀሳቀስበት ቦታ ማለት ነው (ቈላ4-6፡16-18)። በችግር መመታት ወይም መጨቆን በእግር ብረት እንደ መታሰር ነው (ኢዮ36፥8፡13)። *ደስ ተሰኝቶብኛልና፤* እግዚአብሔር "እንደ ልቡ በሆነለት ሰው" በዳዊት ደስ ተሰኝቶአል (1ሳሙ13፥14፤ እንዲሁም 1ሳሙ15፥28፤ 1ነገ14፥8፤15፥5 ይመ)፤ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ሥርወ መንግሥቱ ሳይቋረጥ ለዘላለም የሚቀጥል ቃል ኪዳን ተጋብቶአል (2ሳሙ7)፤ ይህ ሐሳብ በቍ20-29 ላይ በይበልጥ ተብራርቶ ይገኛል።

*18፥20-24፤* ዳዊት ጻድቅ ሆኖ በመገኘቱ ብድራትን አገኘ ቶአል፤ ዳዊት ጻድቅ ሰው ስለ መሆኑ ሲናገር (እንደ ሳሙኤል 1ሳሙ12፥3፤ እንደ ሕዝቅያስ 2ነገ 20፥3፤ እንደ ኢዮብ ኢዮ 13፥23፤ 27፥6፤31 እንዲሁም መዝ17፥3-5፤26፤ 44፥17-18፤101 ይመ)፣ በደል የማይገኝብኝ ሰው ነኝ እያለ እየተከራከረ አይደለም (51፥5 ይመ)፤ ይልቁንም ከጠላቶቹ አኳያ ሲታይ፣ ልቡንና ሕይ

20 *እግዚአብሔር* እንደ ጽድቄ መለሰልኛል፤
እንደ እጄ ንጽሕናም ከፍሎኛል፤
21 *የእግዚአብሔርን* መንገድ ጠብቄአለሁና፤
አምላኬንም በመተው ክፉ አላደረግሁም።
22 ሕጎቹ ሁሉ በፊቴ ናቸው፤
ሥርዐቱን ከፊቴ አራቅሁም።
23 በፊቱ ነቀፋ አልነበረብኝም፤
ራሴንም ከኀጢአት ጠብቄአለሁ።
24 *እግዚአብሔር* እንደ ጽድቄ መጠን፣
በፊቱም እንደ እጄም ንጽሕና
ከፍሎኛል።

25 ከታማኙ ጋር ታማኝ ትሆናለህ፤
እንከን ከሌለበት ጋር ያለ እንከን
ትሆናለህ፤
26 ከንጹሑ ጋር ንጹሕ ሆነህ ትገኛለህ፤
ለጠማማው አንተ ትጠምበታለህ።
27 አንተ ትሑታንን ታድናለህ፤
ትዕቢተኛውን ዐይን ግን ታዋርዳለህ።
28 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ መብራቴን
ታበራለህ፤
አምላኬ ሆይ፤ ጨለማዬን ብርሃን
ታደርገዋለህ።
29 በአንተ ጕልበት በሰራዊት ላይ እረ
ማመዳለሁ፤[a]
በአምላኬም ኀይል ቅጥር እዘላለሁ።

30 የአምላክ መንገድ ፍጹም ነው፤
*የእግዚአብሔር* ቃል የነጠረ ነው።
መጠጊያ ለሚያደርጉት ሁሉ፣
እርሱ ጋሻ ነው።
31 *ከእግዚአብሔር* በቀር ማን አምላክ አለ?
ከአምላካችንስ በቀር ዐምባ ማን ነው?
32 ኀይልን የሚያስታጥቀኝ፣
መንገዴንም የሚያቃና እግዚአብሔር ነው።
33 እርሱ እግሮቼን እንደ ብሖር እግሮች
ያደርጋል፤
በከፍታዎችም ላይ ያቆመኛል።
34 እጆቼን ለጦርነት ያሠለጥናቸዋል፤
ክንዴም የናስ ቀስት መገተር ይችላል።
35 የድል ጋሻ ሰጥተኸኛል፤
ቀኝ እጅህም ደግፋ ይዛኛለች፤
ዝቅ ብለህም ከፍ አድረግኸኝ።
36 ከሥሬ ያለውን ስፍራ ለአረማመዴ
አሰፋህልኝ፤
እግሬም አልተንሸራተተም።

37 ጠላቶቼን አሳድጄ ያዝኋቸው፤
እስኪጠፉም ወደ ኋላዬ
አልተመለስሁም።
38 እንዳያንሰራሩ አድርጌ አደቀቅኋቸው፤
ከእግሬም ሥር ወደቁ።
39 አንተ ለጦርነት ኀይልን አስታጠቅኸኝ፤
ባላንጦቼ እግሬ ላይ እንዲደፉ
አደረግህ።
40 ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው እንዲሸሹ አደረግህ፤
እኔም የሚጠሉኝን አጠፋኋቸው።
41 ለርዳታ ጮኹ፤ የሚያስጥላቸው ግን
አላገኙም፤
ወደ *እግዚአብሔር* ጮኹ፤ እርሱም
አልመለሰላቸውም።
42 ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስደው ትቢያ
አደቀቅኋቸው፤
እንደ መንገድ ላይ ጭቃም አውጥቼ
ጣልኋቸው።

43 ከሕዝብ ግርግር አወጣኸኝ፤
የሕዝቦች መሪ አድርገህ አስቀመጥኸኝ፤
የማላውቀውም ሕዝብ ተገዛልኝ።
44 ትእዛዜን እንደ ሰሙ ይታዘዙልኛል፤
ባዕዳንም በፊቴ አንገት ደፉ።
45 ባዕዳን በፍርሃት ተዋጡ፤
ከምሽጋቸውም እየተንቀጠቀጡ ወጡ።

18፥20 ሩት2፥12 ፤1ሳሙ26፥23፤2ዜና1 5፥7፤ኢዮ22፥30 1መዝ24፥4፤1ቆሮ3፥8
18፥21 2ዜና34፥33 1መዝ37፥34፤119፥2: 102፤ምሳ8፥32፤ 23፥26
18፥22 መዝ119፥30
18፥23 ዘፍ6፥9
18፥24 1ሳሙ26፥23
18፥25 መዝ25፥10 ፤31፥23፤37፥28፤40፥ 11፤50፥5፤89፥24፤14 6፥6፤ምሳ2፥8
18፥26 ምሳ3፥34፤ 15፥26፤ማቴ5፥8፤10፥ 16፤ሉቃ16፥8፤ፊል1፥ 10፤1ጢሞ5፥22፤ቲቶ 1፥15፤1ዮሐ3፥3
18፥27 2ዜና33፥23 ኢዮ41፥34፤መዝ 10፥5፤ምሳ3፥33-34፤ ማቴ23፥12
18፥28 1ነገ11፥36 ፤ኢዮ29፥3፤መዝ97፥ 11፤112፥4፤132፥17፤ ዮሐ1፥5፤ሐሥ26፥18 ፤2ቆሮ4፥6፤2ጴጥ 1፥19
18፥29 ቍ32:39፤ ኢሳ45፥5፤ዕብ11፥34
18፥30 ዘዳ32፥4፤ መዝ2፥12፤3፥3፤12፥6 ፤ምሳ30፥5
18፥31 ዘፍ49፥24፤ ዘዳ4፥35፤32፥39፤መዝ 35፥10፤86፥8፤89፥6፤ ኢሳ44፥6:8፤45፥5:6 :14:18:21፤46፥9
18፥32 ቍ29፤መዝ 15፥2፤19፥13፤ዕብ 10፥14፤1ጴጥ5፥10፤ ያዕ3፥2
18፥33 ዘዳ32፥13፤ መዝ42፥1፤ምሳ5፥19፤ ኢሳ35፥6፤ዕን3፥19
18፥34 መዝ144፥1
18፥35 መዝ3፥5፤ 37፥5:17፤41፥3፤51፥1 2፤54፥4፤55፥22፤119 ፥116፤ኢሳ41፥4:10: 13፤43፥2:46፥4
18፥36 ኢዮ18፥7 ፤መዝ31፥8፤66፥9
18፥37 ዘሌ26፥7
18፥38 መዝ36፥12 ፤47፥3፤68፥21፤110፥6፤140፥10፤ኢሳ 26፥14
18፥39 ቍ32:47፤ መዝ47፥3፤144፥2፤ኢሳ 45፥5:24
18፥40 ቍ37፤ኢሱ 7፥12
18፥41 1ሳሙ8፥18 ፤14፥37፤2ነገ14፥26፤መዝ50፥22፤ኢር11፥11
18፥42 ዘዳ9፥21፤ኢሳ2፥22
18፥43 2ሳሙ8፥1-14፤ኢሳ55፥5
18፥44 መዝ54፥3 ፤144፥7:11፤ኢሳ25፥5
18፥45 1ሳሙ17፥ 32፤መዝ9፥9፤ኢሳ 66፥2፤ሆሴ3፥5፤11፥10፤ሚክ 7፥17፤2ቆሮ4፥1፤ዕብ12፥3

[a]29 ወይም ... *በመሰናክል ውስጥ መሮጥ እችላለሁ*

ወቱን ለጌታ አገልግሎት ሰጥቶአል፤ አረማመዱ ትክክለኛነትን ከመንፈሳዊነት ጋር ያጣመረ ነው፤ ይህ ትክክለኛ ወይም ቀና የሆነ ሕይወት እግዚአብሔር በቸርነቱ በልቡ ውስጥ ያከናወነው ተግባር ነው (51፥10-12 ይመ)።

18፥20፡24 *በጽድቄ፤* የ1፥5 ማብ ይመ። *ከፍሎኛል፤* አንድ ንጉሥ ቅን አገልጋዮቹን እንደሚሸልም ማለት ነው።

18፥21 *የእግዚአብሔርን መንገድ፤* 25፥4 እና ማብ ይመ።

*18፥25-29፤* እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደ ሥራው የሚ ክፍል በመሆኑ (ኢዮ43፥11 ምሳ3፥34)፣ እግዚአብሔር ያደረገለ ትን ቸርነት ዳዊት ከሕይወት ልምዱ ያውቀዋል።

18፥26 *ለጠማማው፤* ከእውነትና ቀናም ከሆነው ከጽድቅ መንገድ ያፈነገጠ ማለት ነው። *ትጠምበታለህ፤* አንድ ታጋይ ወይም ቡጢኛ ባላንጣውን እንደማይምር ሁሉ እግዚአብሔርም ለክፉዎች የእጃቸውን ይሰጣል።

*18፥27፤* የዚህ ቍጥር (ንባብ) ሐሳብ ከዳዊትና ከሳኦል የሥልጣን ግብግብ ጋር በሚገባ ይዛመዳል። ከዚህ በተጨማሪ የመጽሐፈ ሳሙኤል ጸሓፊ የሐናን መዝሙር ዋና ሐሳብ በትረካው ውስጥ እንዴት እንደ ተጠቀመበትም ወደኋላ ሄዶ የሚያስታውስ ነው። የመጽሐፈ ሳሙኤል ጸሓፊ ከሐና መዝሙር ውስጥ የወሰደውን ሐሳብ መሠረት በማድረግ እግዚአብሔር መን ግሥቱን እንዴት አድርጐ እውን እንደሚያደርግ ለማሳየት ሐሳ ቡን እንደ ማጉያ ተጠቅሞበታል።

18፥28 *መብራቴን ታበራለህ፤* የዳዊትን ሕይወት ወደ ሀል ውና ያመጣና የሚያለመልም እግዚአብሔር ነው (በተለይ ኢዮ 18፥5-6፤ 21፥17 ይመ)። *ብርሃን፤* የ27፥1 ማብ ይመ።

*18፥30-36፤* ከእግዚአብሔር በረከት የተነሣ ንጉሥ ዳዊት ተደላድሎ ለመቀመጥ በቅቶአል።

18፥30 *ፍጹም ነው፤* ከቶ አይሰነካከልም፤ በመሆኑም ከእግዚአብሔር በረከት የተነሣ የዳዊትም መንገድ ፈጽሞ አይሰነካከልም (ቍ32 ይመ)። *የእግዚአብሔርም ቃል፤* ይህ ሐረግ ጠቅለል ያለ አጠቃቀም ቢኖረውም በዚህ ቦታ ግን እግዚአብሔር ለዳዊት የገባለትን ቃል ነው የሚያሳየው (2ሳሙ7፥8-11)። *የነጠረ፤* የ12፥6 ማብ ይመ። *ጋሻ፤* የ3፥3 ማብ ይመ።

*18፥37-42፤* ዳዊት በእግዚአብሔር ርዳታ ጠላቶቹን ሁሉ ለማድቀቅ ችሎአል።

*18፥43-45፤* በሞት አፋፍ ላይ ያለና (ቍ4-5 ይመ)፣ ወደ አዘቅትም የሚወርድ የሚመስለውን (ቍ16 ይመ) ዳዊትን እግዚ አብሔር የሕዝብ መሪ አደረገው (2ሳሙ5፤8፤10 ይመ)።

18፥43 *ከሕዝብ ግርግር አወጣኸኝ፤* በሳኦል ዘመን ከገዛ ወገኖቹ የደረሰበትን ጥቃትና ምናልባትም በአቤሴሎም ዘመን የደረሰበትን ግፍ የሚያመለክት ነው። *የማላውቀውም ሕዝብ፤* ከዚህ በፊት ከእርሱ ጋር ምንም ዐይነት ግንኙነት የሌላቸው ወገ ኖች ማለት ነው።

*18፥46-50፤* የመደምደሚያ የውዳሴ ቃል ነው።

46 *እግዚአብሔር* ሕያው ነው! ዐምባዬ
ይባረክ፤
ያዳነኝ አምላክ ከፍ ከፍ ይበል።
47 እርሱ በቀሌን የሚመልስልኝ፣
ሕዝቦችንም የሚያስገዛልኝ አምላክ ነው፤
48 ከጠላቶቼም የሚታደገኝ እርሱ ነው።
አንተ ከባላንጦቼ በላይ ከፍ ከፍ
አደረግኸኝ፤
ከጨካኞች አዳንኸኝ።
49 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ስለዚህ በአሕዛብ
መካከል አመሰግንሃለሁ፤
ስምህንም በመዝሙር እወድሳለሁ።
50 እርሱ ላንገሠው ታላላቅ ድሎችን
ይሰጣል፤
ጽኑ ፍቅሩንም ለቀባው፣
ለዳዊትና ለዘሩ ለዘላለም ይገልጣል።

## መዝሙር 19

### እግዚአብሔር የጽድቅ ፀሓይ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1 ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤
የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ
ያውጃሉ።
2 ቀን ለሌላው ቀን ይናገራል፤
ሌሊትም ለሌሊት ዕውቀትን ይገልጣል፤
3 ንግግር የለም፤ ቃል የለም፤
ድምፃቸው በጆሮ የሚሰማ አይደለም።[*]
4 *ያም ሆኖ ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ፣
ቃላቸውም* እስከ ዓለም ዳርቻ ይወጣል።

እርሱ በሰማያት ለፀሓይ ድንኳን
ተክሎአል፤
5 ፀሓይም ከእልፍኙ እንደሚወጣ ሙሽራ
ይወጣል፤
ወደ ግቡም እንደሚሮጥ ብርቱ ሰው
ደስ ይለዋል።
6 *መውጫው* ከሰማያት ዳርቻ ነው፤
ዑደቱም እስከ ሌላኛው ዳርቻ ነው፤
ከትኩሳቱም የሚሰወር የለም።

7 *የእግዚአብሔር* ሕግ ፍጹም ነው፤
ነፍስንም መልሶ ያለመልማል፤
*የእግዚአብሔር* ሥርዐት የታመነ ነው፤
አላዋቂውን ጥበበኛ ያደርጋል።
8 *የእግዚአብሔር* ሕግጋት ትክክል ናቸው፤
ልብን ደስ ያሰኛሉ።
*የእግዚአብሔር* ትእዛዝ ብሩህ ነው፤
ዐይንን ያበራል።
9 *እግዚአብሔርን* መፍራት ንጹሕ ነው፤
ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
*የእግዚአብሔር* ፍርድ የታመነ፣
ሁለንተናውም ጻድቅ ነው፤
10 ከወርቅ ይልቅ የከበረ፣
እጅግ ከጠራ ወርቅም የተሻለ ነው፤
ከማር ይልቅ ይጣፍጣል፤
ከማር ወለላም ይበልጥ ይጥማል።
11 ደግሞም አገልጋይህ በእርሱ ጥንቃቄ
ያደርጋል፤
እርሱንም መጠበቅ ወሮታ አለው።

12 ስሕተቱን ማን ሊያስተውል ይችላል?
ከተሰወረ በደል አንጻኝ።

18፥46 ቍ31፤ዘፀ 33፥22፤ኢሱ3፥10፤ 1ሳሙ14፥39፤1ዜና16 ፥35፤መዝ21፥13፤35፥ 27፤40፥16፤108፥5፤ ሉቃ1፥47፤2ቆሮ13፥4
18፥47 ቍ39፤ዘኍ 4፥24፤መሳ4፥23
18፥48 ቍ17፤መዝ 7፥10፤37፥40፤140፥1 ፤ዳን3፥17
18፥49 መዝ7፥17፤ 9፥2፡11፤101፥1፤108፥ 1፤146፥2፤ሮሜ15፥9
18፥50 2ሳሙ23፥1 ፤መዝ89፥4፤144፥10
19፥1 ዘፍ1፥8፤መዝ 4፥2፤8፥1፡6፤50፥6፤89 ፥5፤97፥6፤103፥22፤1 48፥3፤ኢሳ6፥3፤40፥ 22፤ሮሜ1፥19
19፥2 መዝ74፥16
19፥4 መሳ5፥31፤ ኢዮ36፥29፤መዝ 104፥2፤ሮሜ10፥18
19፥5 1ሳሙ17፥4፤ ኢዮ36፥29፤ኢዩ2፥16
19፥6 ዘዳ30፥4፤ መዝ113፥3፤መክ1፥5
19፥7 ዘዳ4፥6፤መዝ 1፥2፤23፥3፤93፥5፤11 1፥7፤119፥130፡138፡1 42፡144፤ያዕ1፥25
19፥8 ዕዝ9፥8፤መዝ 33፥4፤38፥10፤119፥1 4፡128
19፥9 መዝ34፥11፤ 111፥10፤119፥138፤ ምሳ1፥7፤መክ12፥13፤ ኢሳ33፥6
19፥10 2ሳሙ14፥ 27፤ኢዮ22፥24፤መዝ 119፥72፡103፤ምሳ8፥ 10፤ማሕ4፥11፤ሕዝ 3፥3
19፥12 መዝ51፥2፤ 90፥8፤መክ12፥14

[*]3 ወይም *የሚናገሩት የላቸውም፤ ቃላት የለም፤ ከእርሱ ምንም ድምፅ አይሰማም*

[*]4 ሰብዓ ሊቃናት የሩምና ሱርስት እንዲሁ ሲሆኑ ዕብራይስጡ ግን ድንበራቸው ይላል።

18፥46 *እግዚአብሔር ሕያው ነው፤* እግዚአብሔር በዳዊት ሕይወት ውስጥ ጣልቃ እየገባ ዳዊትን በመባረኩ በእርግጥ ሕያው አምላክ መሆኑን በገሃድ አሳይቶአል (ዘዳ 5፥26 ይመ)።

18፥47 *በቀሌን የሚመልስልኝ፤* በእኔ ላይ የደረሰውን በደል አንተው ራስህ ተበቀልልኝ ማለት ነው (32፥41 ይመ)።

*18፥49፤* ዳዊት በሕዝቦች መካከል እግዚአብሔርን ለማሞገስ የገባውን ቃል ወይም መሐላ የሚያሳይ ነው (የ9፥1 ማብ ይመ)። *ስምህንም፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

18፥50 *ላነገሠው … ለቀባው፤* ዳዊት ራሱን የሚመለከተው በጌታ የተመረጠና የተቀባ ንጉሥ አድርጎ ነው (1ሳሙ 16፥13 እንዲሁም የ1ሳሙ10፥25፤ 12፥14-15 ማብ ይመ)። *ጽኑ ፍቅሩንም፤* ይህ የዳዊት የመደምደሚያ ቃል ከጌታ ከእርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ያስታውሳል (2ሳሙ 7፥18-16 ይመ)። ይህ መዝሙር መታየት ያለበት፣ ዳዊት በወቅቱ ካለው ሥልጣንና ጌታም ከእርሱ ጋር ከገባው ቃል ኪዳን አኳያ ነው። ዳዊት በዚህ ዐቢይ መደምደሚያ ላይ የሚናገረው ነገር ሁሉ ከዳዊት በሆነው ታላቅ ዘር ይኸውም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጽሞአል፤ እየተፈጸመም ነው።

*መዝሙር 19፤* የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጽ (ቍ1) መዝሙር ሲሆን የእግዚአብሔርም ክብር በሰማይ ጠፈሮችና (ቍ1-6 ይመ) ለእስራኤልም በተሰጠው "የእግዚአብሔር ሕግ" (ቍ7) አማካይነት ተገልጦአል። ይህ መዝሙር ከመዝሙር 18 ቀጥሎ በመገኘቱም የምስጋናና የውዳሴውን ዑደት ሙሉ ያደርገዋል፤ እግዚአብሔር ለክብሩ ሲል ያደረገው ማዳን በፍጥረቱና በሕጉ በኩል በግልጽ ታይቶአል።

19ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ 4 የርእስ ማብ ይመ።

*19፥1-4ሀ፤* ፀጥና ዝም ያለው ሰማይ ይናገራል፤ የፈጣሪውንም ክብር ለምድር ነዋሪዎች ሁሉ ያውጃል (148፥3 ይመ)። የሰማይ ብርሃናት የመለኮት ባሕርይ የላቸውም (ዘዳ4፥19፤ 17፥13 ይመ)፤ ደግሞም የሰውን ዕድል የመቈጣጠርና የወደፊት ሕይወቱንም የመተንበይ ችሎታ የላቸውም (ኢሳ47፥13፤ ኤር10፥2፤ ዳን4፥7 ይመ)፤ ሆኖም ግርማ ሞገሳቸው ግን የፈጣሪያቸውን ማለትም የጌታን ጽድቅና ታማኝነት ይመሰክራል (50፥6፤ 89፥5-8፤ 97፥6 እንዲሁም ሮሜ1፥19-20 ይመ)።

*19፥4፤* ጳውሎስ ይህንን ሰማያዊ አዋጅ ከክርስቶስ አኳያ በመተርጐም ይህን ጥቅስ (ንባብ) በእርሱ ዘመን ይሰበክ ከነበረው የወንጌል ትምህርት ጋር አዛምዶታል (ሮሜ10፥18 ይመ)። ስለዚህ እነዚህን ሁለት ዓለም አቀፍ አዋጆች እርስ በርስ አጓድኖአቸዋል።

*19፥4ለ-6፤* በጥንቱ መካከለኛው ምሥራቃውያን ዘንድ ብዙዎች ለሚያመልኳት ፀሓይ በመለኮት የተዘረጋ "ድንኳን" ተደርጐ ይወሰዳል (ከዘዳ4፥19፤ 17፥3፤ 2ነገ23፥5፡11፤ ከኤር8፥2፤ ከሕዝ 8፥16 ጋር ያነጻጽሩ)፤ በዚህ ቦታ ግን እንደ 136፥7-8 እና እንደ ዘፍ 1፥16 ሁሉ ተራ ፍጥረታት መሆናቸውን ነው የሚያመለክተው። ከፍጥረታት ሁሉ ፀሓይ የእግዚአብሔርን ክብር የምትወክል ከፍተኛዋ ተምሳሌት ናት።

*19፥7-9፤* እግዚአብሔር የሰጠው ሕግ ሕይወትን የሚያለመልም መሆኑን የሚገልጽና በዜማም መልክ የቀረበ ምስጋና ነው (መዝ119 ይመ)።

19፥7 *አላዋቂውን፤* እንደ ሕፃን ያሉትን፣ የማስተዋልና የማመዛዘን ችሎታቸው ገና ያልዳበረውን ማለት ነው (ምሳ1፥4 ይመ)፤ እንዲሁም 119፥98-100፤ 2ጢሞ3፥15 ይመ።

19፥8 *የልብ፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

19፥9 *እግዚአብሔርን መፍራት፤* ሕግ የሚጠይቀው ይኸንኑ ነው (የ15፥4 ማብ ይመ)

19፥10 *ከማር፤* ከዚህ በተቃራኒው ሕግን ችላ የሚሉ ፍትሕን ወደ እሬት ይለውጣሉ (አሞ5፥7፤ 6፥12 ይመ)።

*19፥11-13፤* ሕግ ወደ ሕይወት የሚወስደውን መንገድ ያመለክታል (ዘዳ5፥33 ይመ)፤ የሰው ምግባራዊ ግንዛቤ ግን የተጣመመና እንከን የማያጣው ሆኖ ይኖራል፤ በመሆኑም አንድ ሰው ሳይታወቀው ሊስትና ድብቅ ለሆነም በደሉ ይቅርታን መጠ

[13]ባሪያህን ከድፍረት ኀጢአት ጠብቅ፤
እንዳይሠለጥንብኝም ርዳኝ፤
ያን ጊዜ ያለ እንከን እሆናለሁ፤
ከታላቅ በደልም እነጻለሁ።

[14]መጠጊያዬና አዳኜ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
የአፌ ቃልና የልቤ ሐሳብ፣
በፊትህ ያማረ ይሁን።

## መዝሙር 20

### ጸሎት ለንጉሡ

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር

[1]*እግዚአብሔር* በጭንቅ ቀን ይስማህ፤
የያዕቆብም አምላክ ስም ይጠብቅህ።
[2]ከመቅደሱ ረድኤት ይላክልህ፤
ከጽዮንም ደግፎ ይያዝህ።
[3]ቍርባንህን ሁሉ ያስብልህ፤
የሚቃጠል መሥዋዕትህን ይቀበልልህ።
[4]የልብህን መሻት ይስጥህ፤
ዕቅድህን ሁሉ ያከናውንልህ።
[5]በአንተ ድል ደስ ይበለን፤
በአምላካችን ስም አርማችንን ከፍ
እናድርጋለን፤
*እግዚአብሔር* የለመንኸውን ሁሉ
ይፈጽምልህ።

[6]*እግዚአብሔር*፣ የቀባውን እንደሚያድን
አሁን አወቅሁ፤
የማዳን ኀይል ባለው ቀኝ እጁ፣
ከተቀደሰው ሰማይ ይመልስለታል።
[7]እነዚህ በሰረገላ፣ እነዚያ በፈረስ ይመካሉ፤
እኛ ግን ትምክህታችን የአምላካችን
*የእግዚአብሔር* ስም ነው።
[8]እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ፤
እኛ ግን ተነሣን፤ ጸንተንም ቆምን።

[9]እግዚአብሔር ሆይ፤ ንጉሥን አድን፤
እኛም በጠራንህ ቀን ስማን።[a]

## መዝሙር 21

### ምስጋና ስለ ንጉሡ

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር

[1]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ንጉሥ በኀይልህ
ደስ ይለዋል፤
በምትሰጠውም ድል እጅግ ሐሤት
ያደርጋል።
[2]የልቡን መሻት ሰጠኸው፤
የከንፈሮቹንም ልመና አልከለከልኸውም። ሴላ

[3]መልካም በረከት ይዘህ በመንገዱ ላይ
ጠብቀኸው፤
የንጹሕ ወርቅ ዘውድም በራሱ ላይ
ደፋህለት።
[4]ሕይወትን ለመነህ፤
ረዥም ዘመናትንም እስከ ዘላለም
ሰጠኸው።

19፥13 ዘፍ6፥9፤ ዘኍ15፥30፤ መዝ18፥32፤119፥133
19፥14 ዘዐ6፥6፤ ኢዮ19፥25፤ መዝ18፥31፤104፥34
20፥1 ዘፀ3፥6፤ መዝ4፥1፤46፥7:11፤59፥1፤69፥29፤91፥14
20፥2 ዘኍ3፥28፤ መዝ2፥6፤18፥18፤30፥10፤33፥20፤37፥40፤40፥17፤54፥4፤118፥7፤128፥5፤134፥3፤135፥21
20፥3 ዘጸ33፥11፤ ሐሥ10፥4
20፥4 መዝ21፥2፤37፥4፤140፥8፤145፥16:19፤ምሳ16፥3፤ኢሳ26፥8፤ሕዝ24፥25፤ዳን11፥17፤ሮሜ10፥1
20፥5 ዘኍ1፥52፤ 1ሳሙ1፥17፤ኢዮ3፥7፤መዝ60፥4፤ኢሳ5፥26፤ 11፥10:12፤13፥2፤30፥17፤49፥22፤62፥10፤ኤር50፥2፤51፥12:27
20፥6 2ሳሙ23፥1፤ኢዮ40፥14፤መዝ28፥8፤ዕን3፥13
20፥7 ዘጸ17፥16፤ 2ነገ19፥23፤2ዜና32፥8፤መዝ33፥17፤147፥10፤ምሳ21፥31፤ኢሳ31፥1፤36፥8:9
20፥8 ኢዮ11፥15፤ መዝ27፥2፤37፥23፤ ምሳ10፥25፤ኢሳ7፥9፤ 40፥30፤ኤር46፥6፤50፥32፤ሚክ7፥8 20፥9 መዝ17፥6
21፥1 1ሳሙ2፥10 ፤2ሳሙ22፥51
21፥2 መዝ20፥4 21፥3 2ሳሙ12፥30 ፤ዘካ6፥11፤ራእ14፥14
21፥4 መዝ10፥16፤ 45፥17፤48፥14፤133፥3

[a]9 ወይም *አድን! ንጉሥ ሆይ፤ ስማን*

የቅ የሚኖርበት ከዚህ የተነሣ ነው (ቍ12፤ ዘሌ5፥2-4 ይመ)። ሆን ተብሎ የሚሠራ ኀጢአት (ቍ13) ግን ይፋ የሆነ ዐመፅ ነው፤ እንዲህ ያለውም ታላቅ ኀጢአት (ቍ13) ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ለመወገድ ያበቃል (ዘኍ15:30-31 ይመ)።

19፥11:13 *አገልጋይህ፤* መዝሙረኛው ራሱ ነው።

*19፥14፤* መዝሙረኛው ይህንን መዝሙር የምስጋና መሥዋዕት አድርጎ ያቀርባል። *በልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *አምባ መጠጊያዬና አዳኜ፤* 78፥35 ይመ። *አምባ፤* የ18፥2፤ የዘፍ49፥24 ማብ ይመ። *አዳኜ፤* የዘዐ6፥6 ማብ ይመ።

*መዝሙር 20፤* ንጉሡ አስፈሪ የሆኑ ኀይሎችን ለመግጠም ከመውጣቱ በፊት (2ዜና20፥1-30) የሚቀርብ የቅዳሴ ጸሎት ነው።

20ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ 4 የርእስ ማብ ይመ።

*20፥1-5፤* ሕዝቡ (ምናልባትም በተጠንቀቅ ላይ የሚገኘው ሰራዊት) ለንጉሡ በጎ ምኞታቸውን ይገልጻሉ፤ ደግሞም ድል ያገኙ ዘንድ በንጉሡ ጸሎት ላይ የራሳቸውን ጸሎት ያክላሉ (ይደምራሉ)።

20፥1 *ይስማህ፤* እንዲህ ተጨንቀህ ሳለ ከመሥዋዕት ጋር (ቍ3) ያቀረብከውን ጸሎት ይስማህ፤ ቍ9 ይመ። *ስም፤* ቍ5:7 ይመ፤ እንዲሁም የ5፥11 ማብ ይመ። *ያዕቆብ፤* የ14፥7 ማብ ይመ። *ይጠብቅህ፤* በቀጥታ ሲተረጐም "አስተማማኝ በሆነና ከፍ ባለም ቦታ ላይ ያስቀመጥህ" ማለት ነው።

20፥2 *ከጽዮንም፤* የ9፥11 ማብ ይመ።

20፥4 *የልብህን፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

20፥5 *ደስ ይበለለን ... በአምላካችን ስም፤* የ7፥17 ማብ ይመ። *አርማችንን፤* የጦር ሰልፈኞች በአንድ ላይ ሆነው የሚሰለፉበት አርማ ሊሆን ይችላል።

*20፥6፤* ከቅዳሴው ተካፋዮች አንዱ (ምናልባትም አንድ ሌዋዊ ሊሆን ይችላል፤ 2ዜና 20፥14 ይመ)፣ የንጉሡ ጸሎት በእርግጥ የሚሰማ መሆኑን ይፋ አደረገ። *የቀባውን፤* ጌታ በስሙ እንዲያስተዳድር የሾመው ንጉሥ ማለት ነው (2፥2 እና ማብ ይመ።

*20፥7-8፤* ሰራዊቱ በጦር ሠረገላዎች ሳይሆን በእግዚአብሔር የሚታመኑ መሆናቸውን ገለጹ (ከ33፥16-17 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ጠላቶቻቸው ግን በሚያስደንቅ ጦረኞችና ፈረሰኞች ታጅበው ሳይመጡ አልቀረም። ዳዊት ጎልያድን በገጠመ ጊዜ የተናገረውን ተመሳሳይ የእምነት ቃል በዚህ ቦታ ከተነገረው የእምነት ቃል ጋር ያነጻጽሩ (1ሳሙ17፥45-47)።

*20፥9፤* የሰራዊቱ የመደምደሚያ ልመና ነው። *ስማን፤* የቍ1 ማብ ይመ። ይህ መዝሙር የሚያበቃው እንደ መጀመሪያው ወይም እንደ መነሻው ነው።

*መዝሙር 21፤* ለንጉሡ ስለተሰጠው ድል የቀረበ የምስጋና መዝሙር ነው፤ ከዚህም የተነሣ ከመዝሙር 20 ጋር የተያያዘ ነው። ሁለቱ መዝሙሮች ግን በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ስለመደረሳቸው የሚታወቅ ምንም ነገር የለም። እዚህ ላይ የሕዝቡ ምስጋና የቀረበው ንጉሡ ምስጋናውን ካቀረበ በኋላ ነው (ቍ1 ይመ)፤ በዚያኛው ላይ (መዝ20) ግን የሕዝቡ ጸሎት ከንጉሡ ጸሎት ጋር ተዳምሮአል። በአወቃቀር ረገድ ሲታይ መዝሙሩ በቍ1 እና 13 ("እግዚአብሔር ሆይ ... በኀይልህ" በሚለው በሁለቱ ቍጥሮች) አማካይነት ድንበርና ወሰን የተበጀለት ሲሆን፣ ንጉሡ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን መታመን በሚያመለክተውና ጌታም በጥበቃው የከለለው መሆኑን በሚገልጸው በቍጥር 7 የተማከለ ነው (በመግቢያው ላይ "ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርዎቱ" የሚለውን ይመ)።

21ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝሙር 4 የርእስ ማብ ይመ።

*21፥2-6፤* ሕዝቡ ጌታ ለንጉሡ ያደረገውን በጎ ነገር እያወሱና "የልቡን መሻት ሁሉ አከናወነለት" እያሉ አመሰገኑ (ቍ2)። ቍጥር 2 የመዝሙሩን ዐቢይ ሐሳብ ይፋ ሲያደርግ፣ ቍ3-5 ደግሞ የመዝሙሩን ዐቢይ ሐሳብ ያጕለብታል፤ በመጨረሻም ቍ6 እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ ዐቢይ ሐሳቡን ከመጨረሻው ደረጃ ላይ አድርሶ በማጠዝ ይደመድማል።

21፥2 *የልቡን፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

21፥3 *ጠበቅኸው፤* ከጦርነት ሲመለስ ማለት ነው። *ዘውድ ደፋህለት፤* በራስ ቍር ምትክ የማዕረግ አክሊል ደፋህለት ነው፤ ምናልባትም ድል የመታውን ንጉሥ ዘውድ ደፋህለት ማለት ሊሆን ይችላል (2ሳሙ12፥30 ይመ)።

*21፥4፤* የንጉሡ ሕይወት ከዘላለም እስከ ዘላለም ትኖር ዘንድ ከጥፋት ተረፈች (1ነገ1፥31፤ ዳን2፥4፤ 3፥9፤ እንዲሁም 1ሳሙ10፥24፤ 1ነገ1፥25:34:39 ይመ)።

5ባቀዳጀኸው ድል ክብሩ ታላቅ ሆነ፤
ክብርንና ሞገስን አጐናጸፍኸው።
6ዘላለማዊ በረከትን ሰጠኸው፤
ከአንተ ዘንድ በሚገኝ ፍስሐም ደስ
አሰኘኸው፤
7ንጉሡ *በእግዚአብሔር* ተማምኖአልና፤
ከልዑልም ጽኑ ፍቅር የተነሣ፣
ከቶመበት አይናወጥም።
8እጅህ ጠላቶችህን ሁሉ ታገኛቸዋለች፤
ቀኝ እጅህም የሚጠሉህን ፈልጋ
ትይዛለች።
9በምትገለጥበት ጊዜ፣
እሳት እንደሚንቀለቀልበት ምድጃ
ታደርጋቸዋለህ፤
*እግዚአብሔር* በመዓቱ እንዳልነበሩ
ያደርጋቸዋል፤
እሳቱም ሙጥጥ አድርጋ ትበላቸዋለች።
10ዘራቸውን ከምድር፣
ዘር ማንዘራቸውንም ከሰው ልጆች
መካከል ታጠፋለህ።
11ክፋት ቢያስቡብህ፣
ተንኰል ቢወጥኑብህም አይሳካላቸውም፤
12በመጡበት ትመልሳቸዋለህና፤
ቀስትህንም በፊታቸው ላይ
ታነጣጥራለህ።
13*እግዚአብሔር* ሆይ፤ በብርታትህ ከፍ
ከፍ በል፤
ኀይልህን እናወድሳለን፤ እንዘምራለንም።

## መዝሙር 22
## የጻድቅ ሰው መከራና ተስፋ

*ለመዘምራን አለቃ፤ በ"ንጋት አጋዘን" ዜማ የሚዜም፤ የዳዊት መዝሙር*

1አምላኬ፣ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?
እኔን ከማዳን፣
ከመቃተቴም ቃል ለምን ራቅህ?
2አምላኬ ሆይ፤ በቀን ወደ አንተ እጮኻለሁ፤
አንተ ግን አልመለስህልኝም፤
በሌሊት እንኳ አላረፍሁም።
3አንተ ግን ቅዱሱ ነጋሢ፤[T]
የእስራኤልም ምስጋና ነህ።
4አባቶቻችን በአንተ ታመኑ፤
ተማመኑብህ፤ አንተም ታደግሃቸው።
5ወደ አንተ ጮኹ፤ ዳኑም፤
በአንተም ታመኑ፤ አላፈሩም።
6እኔ ግን ትል እንጂ ሰው አይደለሁም፤
ሰው ያላገጠብኝ፣ ሕዝብም የናቀኝ ነኝ።
7የሚያዩኝ ሁሉ ይሣለቁብኛል፤
ራሳቸውንም እየነቀነቁ እንዲህ እያሉ
ይዘልፉኛል፤
8"*በእግዚአብሔር* ተማምኖአል፤
እንግዲህ እርሱ ያድነው፤
ደስ የተሰኘበትን፣
እስቲ ይታደገው።"
9አንተ ግን ከማሕፀን አወጣኸኝ፤

21፥5 ቍ1፤መዝ 8፥5፤18፥50፤44፥4፤45፥3፤93፥1፤96፥6፤104፥1
21፥6 1ዜና17፥27፤መዝ43፥4፤126፥3
21፥7 ዘፍ14፥18፤2ነገ18፥5፤መዝ6፥4፤15፥5፤55፥22
21፥8 ኢሳ10፥10
21፥9 ዘጸ32፥22፤መዝ50፥3፤ኤር15፥14
21፥10 ዘዳ28፥18
21፥11 ኢዮ10፥3፤መዝ2፥1፤10፥2፤26፥10፤37፥7
21፥12 ዘፀ23፥27
21፥13 መዝ18፥1፡46
22፥1 ኢዮ3፥24፤6፥15፤መዝ9፥10፤10፥1፤ማቴ27፥46፤ማር15፥34
22፥2 ኢዮ19፥7፤መዝ42፥3፤88፥1
22፥3 ዘፀ15፥2፤2ነገ19፥22፤መዝ71፥22፤148፥14፤ማር1፥24
22፥4 መዝ78፥53፤107፥6
22፥5 1ዜና5፥20፤2ዜና13፥18፤መዝ25፥3፤31፥17፤71፥1፤ኢሳ8፥17፤25፥9፤26፥3፤30፥18፤49፥23፤ሮሜ9፥33
22፥6 2ሳሙ12፥14፤ኢዮ4፥19፤መዝ31፥11፤64፥8፤69፥19፤109፥25፤119፥141፤ኢሳ49፥7፤53፥3፤60፥14፤ሚል2፥9፤ማቴ16፥21
22፥7 ኢዮ17፥2፤ መዝ35፥16፤69፥12፤74፥18፤ማቴ27፥39፡41፡44፤ማር15፥29፡31፡32፤ሉቃ23፥36፡39 22፥8 2ሳሙ22፥20፤መዝ3፥2፤91፥14፤ማቴ3፥17፤27፥43 22፥9 ኢዮ10፥18፤መዝ71፥6፤78፥7፤ናሆ1፥7

[T]3 *ወይም አንተ ግን ቅዱስ ነህ፤ በእስራኤል ምሥጋና ላይ በዙፋን ተቀምጠሃል*

21፥5 *ክብሩ ... ክብርንና ሞገስን፤* 45፥3 ይመ፤ እንደ ሰማያዊው ጌታ ማለት ነው (96፥3 ይመ)።

21፥6 *ዘላለማዊ በረከትን፤* (1) ዘላቂነት ያለውን በረከት ወይም (2) ከቶ የማይደርቅን የበረከት ምንጭ ሊያመለክት ይችላል። *ከአንተ ዘንድ በሚገኝ፤* ወዳጅነትህ የታላቅ ደስታዬ ምንጭ ነው፤ ምክንያቱም የሌሎች በረከቶች ሁሉ ምንጭ ነው።

*21፥7፤* የመዝሙሩ ማእከል ነው (የ6፥6 ማብ ይመ)። ከቅዳሴው ተካፋይ አንዱ (ምናልባትም ሌዋዊ ሊሆን ይችላል)፣ ንጉሡ አስተማማኝ ዋስትናን ያገኘው ከምን የተነሣ እንደ ሆነ ይፋ አደረገ። *በእግዚአብሔር ... ከልዑልም፤* ልዑል እግዚአብሔር ማለት ነው (7፥17፤ እንዲሁም የ3፥7 ማብ ይመ)። *ጽኑ ፍቅር፤* የ6፥4 ማብ ይመ። *ከልዑልም፤* የዘፍ14፥19 ማብ ይመ። *አይናወጥም፤* የ10፥6 ማብ ይመ።

*21፥8-12፤* ሕዝቡ ድል አድራጊው ንጉሥ ወደፊት ስለሚያገኘው ድል እያሰቡ ምስጋናና እልልታ አቀረቡ፤ ቍ8 ዐቢይ ሐሳቡን ይፋ ያደርጋል፤ ቍ9-11 ዐቢይ ሐሳቡን ያጐለብታል፤ ቍ12 ደግሞ ዐቢይ ሐሳቡን ጫፍ በማድረስ ይደመድማል።

21፥9 *እግዚአብሔር በመዓቱ፤* ንጉሡ ድልን ያገኘው ከእግዚአብሔር ቍጣ የተነሣ መሆኑን ያመለክታል (የ2፥5 ማብ ይመ)።

*21፥10፤* በንጉሡ ላይ ተነሥተው የነበሩት መንግሥታት፣ ዳግመኛ በእርሱ ላይ የሚነሣ ትውልድ አይኖራቸውም።

*21፥13፤* መደምደሚያ ሐሳብ ሲሆን፣ ወደ መነሻ ሐሳቡ በመመለስ ጌታ ሆይ፤ "ንጉሥ ደስ የሚሰኝበትን" (ቍ1፤ እንዲሁም ቍ7 ይመ) ኀይል ስጠው፣ እኛም ስለ አንተ ታላቅ ኀይልህ ለዘላለም እናመሰግንሃለን ይላል።

*መዝሙር 22፤* ዳዊት ይህን ጸሎት ያቀረበው በታላቅ ሐዘን ውስጥ እያለ ነው፤ ምንም ያላደረጋቸው ሰዎች አሳሩን አብዝተውበታል፤ ጌታም ከእነዚህ ሰዎች እጅ ገና አልታደገውም፤ ስለ ዚህ ሐዘን በተሞላበት ሁኔታ አቤቱታውን ያሰማል። ይህ መዝሙር ከመዝሙር 69 ጋር በብዙ መንገድ ይመሳሰላል፤ ሆኖም በ69፥22-28 ላይ እንደ ተመለከተው የበቀል አቤቱታ አያቀርብም (የ5፥10 ማብ ይመ)። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በዋለበት ጊዜ፣ ከሆነው ሁኔታ ጋር አብሮ የሚሄድ እንደዚህ ያለ ሌላ መዝሙር የለም። ስለዚህ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ በመዝሙሩ ውስጥ ያሉ ቃሎችን ቃል በቃል ተናግሮአቸዋል (ማቴ 27፥46 እና ተጓ ምብ ይመ)፤ እንዲሁም የወንጌል ጸሐፊዎች በተለይም ማቴዎስና ዮሐንስ የክርስቶስን ሥቃይና ሕማም በሚገልጸው ትረካ ውስጥ (እንደ መዝ69 ሁሉ) በተደጋጋሚ ጠቅሰውታል (ማቴ 27፥35፡39፡43፤ ዮሐ 19፥23-24፡28)። እነዚህ ጸሐፊዎች በኢየሱስ መከራና ሕማም ውስጥ የዚህን ጩኸት ፍጻሜና የጻድቅ ሰውን መከራ ተመልክተዋል። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ደግሞ በቍ22 ላይ የሰፈረውን ቃል ኢየሱስ እንደ ተናገረው አድርጎ አቅርቦአል (ዕብ2፥12 እና ማብ ይመ)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደዚህ መዝሙር ብዙ ጊዜ የተጠቀሰ አንድም መዝሙር የለም።

*22ርእስ፤* የመዝ 4 እና 9 የርእስ ማብ ይመ።

22፥1 *ለምን? ... ለምን?* የ6፥3 ማብ ይመ፤ እንዲሁም በመግቢያው ላይ "ትምህርተ መለኮት" የሚለውን ይመ።

*22፥1ሀ፤* ኢየሱስ ይህንን ክፍል በማቴ22፥46 እና በማር 15፥34 ላይ ጠቅሶታል።

*22፥3-5፤* ጌታ ለእስራኤል ሕዝቦች ያደረገውን መልካም ነገር የሚያስታውስ ነው (የቍ9-10 ማብ ይመ)።

22፥3 *ዙፋንህም ... ተንሰራፍቶአል፤* የ9፥11 ማብ ይመ። *በእስራኤል ምስጋና፤* ስለ ማዳን ሥራው እስራኤል የምታቀርበው ምስጋና ነው (148፥14፤ ዘዳ10፥21፤ ኤር17፥14 ይመ)።

22፥6 *ትል እንጂ ሰው አይደለሁም፤* ኢዮ25፥6፤ ኢሳ 41፥14 ይመ።

22፥7 *ራሳቸውንም በመነቅነቅ ... የስድብ ናዳ ያወርዱብኛል፤* ማቴ27፥39፤ ማር15፥29፤ እንዲሁም የ5፥9 ማብ ይመ።

*22፥8፤* በማቴ27፥43 ላይ በከፊል ተጠቅሶአል፤ የ3፥2 ማብ ይመ።

*22፥9-10፤* ጌታ በሕይወቱ ውስጥ እንዴት ያለ አምላክ እንደ ነበር የሚያስታውስ ነው (የቍ3-5 ማብ ይመ)።

በእናቴም ጡት ሳለሁ፣
መታመኛ ሆንኸኝ።
10ከማሕፀን ስወጣም በአንተ ላይ ተጣልሁ፤
ከእናቴ ሆድ ጀምሮም አንተ አምላኬ
ነህ።
11መከራ እየተቃረበ ነውና፣
የሚረዳኝም የለምና፣
ከእኔ አትራቅ።
12ብዙ ኮርማዎች ከበቡኝ፤
ኀይለኛ የባሳን በሬዎችም ዙሪያዬን
ቆሙ።
13እንደሚነጥቅና እንደሚያገሣ አንበሳ፣
አፋቸውን ከፈቱብኝ።
14እንደ ውሃ ፈሰስሁ፤
ዐጥንቶቼም ሁሉ ከመጋጠሚያቸው
ወለቁ፤
ልቤ እንደ ሰም ሆነ፤
በውስጤም ቀለጠ።
15ጕልበቴ እንደ ገል ደረቀ፤
ምላሴ ከላንቃዬ ጋር ተጣበቀ፤
ወደ ሞት ዐፈርም አወረድኸኝ።[ሀ]
16ውሾች ከበቡኝ፤
የክፉዎች ሸንጎ በዙሪያዬ ተሰልፎአል፤
እጆቼንና እግሮቼንም ቸነከሩኝ።[ለ]
17ዐጥንቶቼን ሁሉ አንድ በአንድ መቍጠር
እችላለሁ፤
እነርሱም አፍጥጠው ይመለከቱኛል።
18ልብሶቼን ተከፋፈሉ፤
በእጀ ጠባቤም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።
19አንተ ግን፣ እግዚአብሔር ሆይ፤ ከእኔ
አትራቅ፤
አጋዤ ሆይ፤ እኔን ለመርዳት ፍጠን።
20ነፍሴን ከሰይፍ ታደጋት፤
ውድ ሕይወቴንም ከውሾች ጡጫ
አድናት።
21ከአንበሶች አፍ አድነኝ፤
ከአውራሪስ ቀንድም ታደገኝ።[ሐ]
22ስምህን ለወንድሞቼ እነግራለሁ፤
በጉባኤም መካከል አመሰግንሃለሁ።
23እናንተ እግዚአብሔርን የምትፈሩ፤
አወድሱት፤
እናንተ የያቆብ ዘር ሁላችሁ፤ አክብሩት፤
የእስራኤልም ዘር ሁላችሁ፤ እርሱን
ፍሩት።
24እርሱ የተጨነቀውን ሰው ጭንቀት፣
አልናቀም፤ ቸልም አላለምና፤
ፊቱንም ከእርሱ አልሰወረም፤
ነገር ግን ድረስልኝ ብሎ ሲጮኽ
ሰማው።
25በታላቅ ጉባኤ የማቀርበው ምስጋናዬ
ከአንተ የመጣ ነው፤
እርሱን በሚፈሩት[መ] ፊት ስእለቴን
እፈጽማለሁ።
26ምስኪኖች በልተው ይጠግባሉ፤
እግዚአብሔርን የሚሹትም
ያመሰግኑታል፤

22፥10 መዝ71፥6 ፤ኢሳ46፥3፤49፥1
22፥11 ቍ19፤2ነገ 14፥26፤መዝ10፥1:14 ፤ኢሳ41፥28
22፥12 ዘዳ32፥14፤ መዝ17፥9፤27፥6፤49፥5፤68፥30፤109፥3፤140፥9፤ኢሳ2፥13፤ ሕዝ 27፥6፤39፥18 ፤አሞ4፥1
22፥13 ቍ24፤ዘፍ 49፥9፤ሰቆ3፥46፤ሕዝ 22፥25፤ሶፎ3፥3
22፥14 ኢሱ7፥5፤ ኢዮ23፥16፤መዝ6፥2፤ 68፥2፤97፥5፤መዝ107 ፥26፤ዳን5፥6፤ሚክ1፥4
22፥15 ኢዮ7፥21፤ መዝ104፥29፤137፥6፤ ኢሳ45፥9፤ሰቆ4፥4፤ ሕዝ3፥26፤ዮሐ19፥28
22፥16 ኢሳ51፥9፤ 53፥5፤ዘካ12፥10፤ዮሐ 20፥25፤ፊል3፥2
22፥17 መዝ25፥2፤ 30፥1፤35፥19፤38፥16 ፤ሰቆ2፥17፤ሚክ7፥8፤ ሉቃ23፥35
22፥18 ዘሌ16፥8፤ ማቴ27፥35፤ማር9፥12 ፤15፥24፤ሉቃ23፥34፤ ዮሐ19፥24
22፥19 ቍ11፤መዝ 18፥1፤38፥22፤40፥13 ፤70፥5፤141፥1
22፥20 ኢዮ5፥20፤ መዝ35፥17፤37፥14፤ ፊል3፥2
22፥21 ቍ12:13፤ ዘኍ23፥22፤ኢዮ4፥10
22፥22 መዝ26፥12 ፤35፥18፤40፥9:10 ፤68፥26፤ዕብ2፥12
22፥23 ዘዳ14፥23፤ መዝ33፥2:8፤50፥15፤ 66፥8፤86፥12፤103፥1፤106፥1፤113፥1፤117፥1፤135፥19፤ኢሳ 24፥15፤25፥3፤29፥23 ፤60፥9፤ኤር3፥17
22፥24 ኢዮ24፥12፤ 36፥5፤መዝ9፥12፤13፥1፤27፥9፤69፥17፤102፥2:17፤143፥7፤ዕብ 5፥7
22፥25 ዘኍ30፥2፤ መዝ26፥12፤35፥18፤ 40፥9፤82፥1
22፥26 መዝ40፥16 ፤107፥9

[ሀ]15 ወይም ... *ዐፈር ውስጥ ተኛኹኝ*
[ለ]16 አንዳንድ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች፣ ሰብዓ ሊቃናትና ሱርስት እንዲሁ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች *እንደ አንበሳ፣* ይላሉ።
[ሐ]21 ወይም *ሰምተኸኛል*
[መ]25 ዕብራይስጡ *እኔ በሚፈሩኝ* ይላል።

*22፥12-18፤* የመዝሙረኛው የልብ ስብራት ጥልቅ መሆኑን ያሳያል፤ በቍ12-13 እና 16-18 ላይ ጠላቶቹ ያደረሱበትን ጥቃት ለማሳየት ሲል አራት ዘይቤዎችን ተጠቅሞአል፤ በቍ14-15 ላይ ደግሞ ጠላቶቹ ክፉኛ ባጠቁት ጊዜ ምን ያህል ዐቅመ ቢስ እንደ ነበር ይገልጻል።

22፥12-13፡16 *በሬዎችም ... አንበሳ ... ውሾች፤* የጠላቶቹን ማንነት ለመግለጽ የተጠቀመባቸው ተለዋጭ ዘይቤዎች ናቸው (የ7፥2 ማብ ይመ)።

22፥12 *የባሳን፤* በልምላሜው የታወቀ በመሆኑ በዚያ የሚኖሩ እንስሳት ግዙፍና ጠንካራ ናቸው (ዘዳ32፥14፤ ሕዝ 39፥18 እና ማብ እንዲሁም አሞ4፥1 ይመ)።

22፥14 *ዐጥንቶቼም ... ልቤ፤* የ102፥4 ማብ ይመ። *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

*22፥15፤* ዮሐ 19፥28 እና ማብ ይመ። *ወደ ሞት ዐፈርም፤* ቍ29፤ እንዲሁም ኢዮ 7፥21 እና ማብ ይመ።

22፥16 *እጆቼንና እግሮቼንም ቸነከሩ፤* ውሾች እና ወይም ክፉ ሰዎች ከሚያደርሱበት ጥቃት ለመከላከል በሞከረ ጊዜ እጆቹንና እግሮቹን አቍስለውታል፤ ሆኖም ኢሳ53፥5፤ ዘካ12፥10፤ ዮሐ19፥34 ይመ።

22፥17 *ዐጥንቶቼን ... መቍጠር እችላለሁ፤* ምናልባት "ዐጥንቶቼን ሁሉ በአደባባይ እቈጥራለሁ" ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፤ ምሳሌው የሚያመለክተው መዝሙረኛው የለበሰውን መጐናጸፊያ ለመግፈፍ፣ የጐዳና ዘራፊዎች ወይም የጠላት ወታደሮች የተነሡበት መሆኑን ነው (ቍ18፤ እንዲሁም የቍ20-21 ማብ ይመ)።

*22፥18፤* የማቴ27፥35 አግራጭ ትርጕም ይመ።

*22፥20-21፤* መዝሙረኛው በቍ12-13 እና 16-18 ላይ "ሰይፍ"፣ "ውሾች"፣ "አንበሶች"፣ "አውራሪስ" በማለት ጠላቶቹን የመሰለባቸውን አራት ምሳሌዎች ቅደም ተከተል በመገልበጥ እንደ ገና በዚህ ቦታ ይጠቅሳል፤ በዚህ ቦታ "ሰይፍ" የሚለው ቃል በቍ16ለ-18 ላይ የተጠቀሰውን ድርጊት እንደ ገና መልሶ ሊያስታውስ ይችላል፤ በዚህም ምክንያት ብዙዎች ይህንን ክፍል (ንባብ) የሚተረጕሙት በዘራፊዎች ወይም በጠላት ወታደሮች የተፈጸመ ጥቃት እንደ ሆነ አድርገው ነው፤ ሆኖም "ሰይፍ" የሚለው ምሳሌ ማንኛውንም አሠቃቂ ሞት ሊያመለክት ይችላል።

22፥21 *አድነኝ፤* አንዳንድ ቅጆች እንዲሁም ትርጕሞች "አድነኝ" በሚለው ቃል ፈንታ "ጸሎቴን ሰምተሃል" የሚለውን ሐረግ እንደ አማራጭ አድርገው ይወስዱታል፤ ይህ የሚያመለክተው መዝሙረኛው ከዚህ ቀደም ተደጋጋሚ የጸሎት መልስ ያገኘ መሆኑን ነው። እንግዲህ መዝሙረኛው እንዲህ ማለቱ ነው፣ "ልመናዬን ሰምተሃል፣ ጠላቶቼም ካጠመዱብኝ የሞት ወጥመድ ታድነኛለህ፤ ለጸሎቴም መልስ ትሰጣለህ" (የ3፥8 ማብ ይመ)።

*22፥22-31፤* የጌታ ድነት በሚመጣበት ጊዜ ጌታን ለማመስገን የቀረበ ስእለት ነው (የ7፥17 ማብ ይመ)፤ የስእለቱ ቃል በቍ22 እና 25 ላይ ተጠቅሶአል። ቍ23-24 ከመዝሙረኛው ጋር በመሆን ምስጋናን የሚያቀርቡ ወገኖች እንዳሉ አሻግሮ ያያል፤ ቍ26-31 ደግሞ ምስጋናን የሚያቀርቡ ወገኖች እጅግ ብዙ መሆናቸውን ይገልጻል፤ እንዲያውም ነገሩን በጣም በማስፋት በዓለም ዙሪያ ያሉ ነገዶች ሁሉ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚቀጥል ምስጋናን የሚያቀርቡ መሆናቸውን ይገልጻል። እንደዚህ መዝሙር የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ አስመልክቶ ይህን ያህል ብዛት ያላቸው ወገኖች ምስጋናን ሲያቀርቡ የሚያሳይ አንድም መዝሙር ወይም ትንቢት ከቶ የለም።

*22፥22፤* ዕብ2፥12 እና ማብ ይመ። *ስምህ፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

22፥23 *እግዚአብሔርን የምትፈሩ፤* ቍ25 እንዲሁም የ15፥4 ማብ ይመ።

22፥25 *ጉባኤ፤* የ1፥5 ማብ ይመ።

22፥26 *በልተው ይጠግባሉ፤* የኅብረት መሥዋዕትና ምስጋና በሚያቀርቡበት ጊዜ ሁሉ ማለት ነው (ዘሌ7፥11-27 ይመ)።

ልባችሁም ለዘላለም ሕያው ይሁን!
27የምድር ዳርቻዎች ሁሉ ያስታውሳሉ፤
ወደ እግዚአብሔርም ይመለሳሉ፤
የሕዝቦች ነገዶች ሁሉ፣
በፊቱ ይሰግዳሉ።
28መንግሥት የእግዚአብሔር ናትና፤
ሕዝቦችንም የሚገዛ እርሱ ነው።
29የምድር ከበርቴዎች ይበላሉ፤
ይሰግዱለታልም፤
ነፍሱን በሕይወት ማቆየት የማይችለው፣
ወደ ዐፈር፣
ተመላሽ የሆነው ሁሉ በፊቱ
ይንበረከካል።
30የኋለኛው ትውልድ ያገለግለዋል፤
ለመጪው ትውልድ ስለ ጌታ
ይነገረዋል።
31ገና ላልተወለደ ሕዝብ፣
ጽድቁን ይነግራሉ፤
እርሱ ይህን አድርጎአልና።

22፥27 መዝ2፥8፤ 86፥9፤102፥22፤ዳን7፥27፤ሚክ4፥1
22፥28 መዝ47፥7፤ ዘካ14፥9
22፥29 መዝ45፥12፤89፥48፤95፥6፤96፥9፤ 99፥5፤ኢሳ26፥19፤ 27፥13፤49፥7፤66፥23፤ዘካ14፥16
22፥30 መዝ102፥18፤ኢሳ53፥10፤54፥3፤ 61፥9፤66፥22
22፥31 መዝ5፥8፤ 40፥9፤71፥18፤78፥6፤ 102፥18፤ሉቃ18፥31፤ 24፥44

23፥1 ዘፍ48፥15፤ መዝ28፥9፤34፥9:10፤ 84፥11፤107፥9፤ዮሐ 10፥11፤ፊል4፥19
23፥2 መዝ36፥8፤ 46፥4፤ራእ7፥17
23፥3 መዝ5፥8፤ 19፥7፤25፥9:11፤31፥3፤73፥24፤79፥9፤106፥8፤109፥21፤143፥11፤ ኢሳ42፥16

## መዝሙር 23

### መልካሙ እረኛ

የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤
አንዳች አይጐድልብኝም።
2በለመለመ መስክ ያሳርፈኛል፤
በዕረፍት ውሃ ዘንድ ይመራኛል፤
3ነፍሴንም ይመልሳታል።
ስለ ስሙም፣
በጽድቅ መንገድ ይመራኛል።
4በሞት ጥላ ሸለቆ ውስጥ፤[ሡ]
ብሄድ እንኳ፣
አንተ ከእኔ ጋር ስለ ሆንህ፣
ክፉን አልፈራም፤
በትርህና ምርኩዝህ፣
እነርሱ ያጽናኑኛል።
5ጠላቶቼ እያዩ፣
በፊቴ ማዕድ አዘጋጀህልኝ፤

23፥4 ኢዮ3፥5፤መዝ 3፥6፤16፥8፤27፥1፤107፥14፤ኢሳ43፥2
23፥5 ኢዮ36፥16፤ መዝ16፥5፤45፥7፤92፥10፤ሉቃ7፥46

ሡ4 ወይም *እጅግ ጨለማ በሆነው ሸለቆ ውስጥ*

22፥27 *የምድር ዳርቻዎች ሁሉ፤* ለእነርሱም የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ይነገራቸዋል (18፥49 እንዲሁም የ9፥1 ማብ ይመ)። የእስራኤል አምላክ የሕዝቡን ጸሎት እንደሚሰማና ሕዝቡንም እንደሚያድን የሚያረጋግጠው የምሥራች ሌሎች ሕዝቦች ጣዖቶቻቸውን ትተው ወደ እውነተኛው አምላክ እንዲመለሱ ይገፋፋቸዋል።

*22፥28፤* የእስራኤል አምላክ አገዛዝ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ይዘልቃል፤ የምድር ሕዝቦችም በሕዝቡ መካከል በሚያከናውናቸው ተግባራት አማካይነት የአገዛዙን ስፋት ያስተውላሉ (መዝ 47፤ ዘፍ12፥2-3፤ እንዲሁም ዘፀ32፥21፤ ሮሜ10፥19፤ 11፥13-14 ይመ)።

22፥29 *የምድር ከበርቴዎች ... ውደ ዐፈር ተመላሽ የሆነው ሁሉ፤* እጅግ ባለ ጸጋና በሞትም አፋፍ ላይ የሚገኙ ሰዎችን፣ እንዲሁም ከእነዚህ ሁለት አጽናፎች መካከል የሚገኙ ወገኖችን ሁሉ ያመለክታል። *ዐፈር፤* ቍ15፤ እንዲሁም ኢዮ7፥21 እና ማብ ይመ።

22፥31 *ጽድቁን፤* የ4፥1 ማብ ይመ።

*መዝሙር 23፤* ጌታ መልካም "እረኛና ንጉሥ" መሆኑን የሚገልጽ የደስታ ቃል ነው። ይህ መዝሙር እግዚአብሔር ሕዝቡን ከታደገ በኋላ "በእግዚአብሔር ቤት" (ቍ6) ውስጥ የምስጋና ክብረ በዓል ሲደረግ ከምስጋናው ጋር አብሮ የሚቀርብ ነው፤ ይህም በጥልቅ ምርመራና አስተውሎት በ22፥25-31 ላይ ተመልክቶአል (የ7፥17 ማብ ይመ)። መዝሙሩ እኩል ሁለት ቦታ ሊከፈል የሚችልና የመጀመሪያው አንድ ራሱን የቻለ አንጓ፣ ሁለተኛውም እንዲሁ አንድ ራሱን የቻለ አንጓ ሊወጣው ይችላል፤ እያንዳንዱም አንጓ አራት በሁለት በሁለት ቤት የተጻፉ ስንኞች አሉት (በዕብራይስጥ ግጥም ውስጥ አንድ የሁለት ቤት ስንኝ በአንድ መስመር ነው የሚጻፈው)፤ (1) አንጓ አንድ፤ ቍ1-2ሀ፣2ለ-3ሁ፥3ለ-ሐ 4ሁ-ሐ (ቍ4ሀ የአንድ ባለ ሁለት ቤት ስንኝ ግማሽ ክፍል ነው)፤ (2) አንጓ ሁለት፤ ቍ5ሀ-ለ፣5ሐ-መ፣6ሀ-ለ፣6ሐ-መ። በመካከል ላይ የሚገኘው በሦስት ቤት የተጻፈው ስንኝ (ቍ4 መ-ረ) ማእከላዊ መስመር ሲሆን (የ6፥6 ማብ ይመ) "እረኛና ንጉሥ" የሆነው ጌታ ከሕዝቡ ጋር እንደሚሆን ያረጋግጣል። ይህ ባለ ሦስት ቤት ስንኝ (ቍ4መ-ረ) በሁለቱ አንጓዎች መካከል እንደ መሸጋገሪያ በመሆን "እረኛና በግ" የሚለውን የመጀመሪያውን አንጓ ዐቢይ ሐሳብ ከፍጻሜና ከድምዳሜ በማድረስ ወደ ሁለተኛው አንጓ ዐቢይ ሐሳብ ይወስዳል። መዝሙሩ በመጀመሪያው ባለ ሁለት ቤት አንጓ መጀመሪያ ላይ በሚገኘውና በሁለተኛው ባለ ሁለት ቤት አንጓ መጨረሻ ላይ በሚገኘው "እግዚአብሔር" በሚለው ቃል የታጠረና ድንበርም የተበጀለት ነው።

23፥1 *እረኛዬ፤* በጥንቱ ቅርብ ምሥራቅና በእስራኤል ነዋሪዎች ዘንድ፣ የአንድን ንጉሥ ማንነት ለመግለጽ የሚያገለግል ተለዋጭ ዘይቤ ነው (78፥71-72፤ 2ሳሙ5፥2፤ ኢሳ44፥28፤ ኤር3፥15፤ 23፥1-4፤ ሚክ5፥4 ይመ)። ጌታ የእስራኤል እረኛ መሆኑን ለማየት 28፥9፤ 79፥13፤ 80፥1፤ 95፥7፤ 100፥3፤ ዘፍ48፥15፤ ኢሳ 40፥11፤ ኤር17፥16፤ 31፥10፤ 50፥19፤ ሕዝ34፥11-16 ይመ። በዚህ ቦታ ንጉሥ ዳዊት፣ ጌታ የእነርሱ "እረኛና ንጉሥ" መሆኑን ይገልጻል። ኢየሱስ የሕዝቡ እረኛ መሆኑን ዮሐ10፥11:14፤ ዕብ 13፥20፤ 1ጴጥ5፥4፤ ራእ 7፥17 ይመ። *አንዳች አይጐድልብኝም፤* ከዚህ በተቃራኒው በዕድሜው ዘመን ሁሉ "በጎነቱን" (ቍ6) ሲቈጥር ይኖራል።

23፥2 *ያሳርፈኛል፤* ከብቶች ርካታንና አስተማማኝ ጥበቃን አግኝተው ማረፍ እንዳለባቸው፤ ኢሳ14፥30፤ 17፥2፤ ኤር33፥12፤ ሕዝ34፥14-15፤ ሶፎ2፥7፤ 3፥13 ይመ። *በለመለመ መስክ፤* ሕይወትን የሰመረ ለሚያደርግ ማንኛውም ነገር ሁሉ የሚያገለግል ተለዋጭ ዘይቤ ነው (ሕዝ34፥14፤ ዮሐ 10፥9 ይመ)። *ይመራኛል፤* አንድ እረኛ መንጋውን እንደሚመራ ማለት ነው (ኢሳ 40፥11 ይመ)። *በዕረፍት ውሃ፤* በቀጥታ ሲተረጐም "በማረፊያ ቦታ ያሉ ውሆች" ማለትም ሕይወትን የሚያድሱና ለጤንነትም የሚስማሙ ያልታወኩ ውሆች ማለት ነው (ኢሳ49፥10 ይመ)።

23፥3 *ነፍሴን ይመልሳታል፤* መንፈሴንም ያድሳል ማለት ነው (19፥7፤ ሩት4፥15፤ምሳ25፥13፤ ሰቆ1፥16 ይመ)። *በጽድቅ መንገድ ይመራኛል፤* አንድ እረኛ በጎቹን መልካም በሆነና ዋስትናም ባለው መንገድ እንደሚመራ ሁሉ (77፥20፤ 78፥72 ይመ)፣ የዳዊትም "እረኛና ንጉሥ" መልካም ወደ ሆነውና ባለጸጋም ወደ ሚያደርገው መንገድ ይመራዋል። በዚህ ቦታ የተጠቀሰው "ጽድቅ" ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት ምሳ8፥18 ("ክብረት")፤ 21፥21 ("ብልጽግና")፤ ኢሳ48፥18፤ እንዲሁም ምሳ 8፥20-21 ይመ። በሌላ በኩል ደግሞ "በጽድቅ መንገድ" ሲባል፣ ከእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ጋር የሚስማማ መንገድ ማለትም ሊሆን ይችላል። *ስለ ስሙም፤* የእግዚአብሔር አገልጋይ መበልጸግ የጌታን ስም ያስከብራል (1ነገ8፥41-42፤ ኢሳ48፥9፤ ኤር 14፥21፤ ሕዝ 20፥9:14:22 ይመ)።

23፥4 *ያጽናኑኛል፤* የዚህ መዝሙር ዐቢይ ሐሳብ ነው፤ ከላይ የተመለከተውን የመግቢያ ማብ ይመ። *ከእኔ ጋር፤* 16፥8 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም ዘዳ31፥6:8፤ ማቴ28፥20 ይመ። *በትርህና፤* የሥልጣን ምልክትና መሣሪያ ነው (ይኸውም በ2፥9፤ 45፥6፤ ዘፀ21፥20፤ 2ሳሙ7፥14፤ ኢዮ9፥34 ላይ እንደ ተመለከተው ዐይነት ነው)፤ እንዲሁም እረኞች በጎችን ለመቍጠር፣ ለመምራት፣ ለማዳንና ለመንከባከብ ይገለገሉበታል (ዘሌ 27፥32፤ ሕዝ20፥37 ይመ)። *ከዘራህ፤* ድጋፍ የሚሰጥ መሣሪያ ነው (ይኸውም በዘዳ 21፥19፤ በመሳ 6፥21፤ በ2ነገ 4፥29፤ በዘካ 8፥4 ላይ እንደ ተመለከተው ዐይነት ነው)። *ያጽናኑኛል፤* ያበረታቱኛል፣ የጸናም ዋስትና ይሰጡኛል ማለት ነው (ይኸውም በ71፥21፤ 86፥17፤ ሩት2፥13፤ ኢሳ12፥1፤ 40፥1፤ 49፥13 ላይ እንደ ተመለከተው ዐይነት ነው)።

*23፥5፤* ሰማያዊው "እረኛና ንጉሥ" ዳዊትን እንደ ንጉሥ እንደራሴ አድርጎ በማእዱ ላይ እንዲገኝ ተቀበለው፤ በጥበቃውም ውስጥ እንዲሆን አደረገው። በጥንት የቅርብ ምሥራቅ አገሮች፣

ራሴን በዘይት ቀባህ፤
ጽዋዬም ሞልቶ ይፈስሳል::
6በሕይወቴ ዘመን ሁሉ፣
በጎነትና ምሕረት በእርግጥ ይከተሉኛል፤
እኔም በእግዚአብሔር ቤት፣
ለዘላለም እኖራለሁ::

## መዝሙር 24

## ወደ መቅደስ መግቢያ ጸሎት

### የዳዊት መዝሙር

1ምድርና በእርሷ ያለው ሁሉ፣
ዓለምና በውስጧ የሚኖር ሁሉ የእግዚ
አብሔር ነው፤
2እርሱ በባሕሮች ላይ መሥርቶአታልና፤
በውሆችም ላይ አጽንቶአታል::
3ወደ እግዚአብሔር ተራራ ማን ሊወጣ
ይችላል?
በተቀደሰ ስፍራውስ ማን ይቆማል?
4ንጹሕ እጅና ቅን ልብ ያለው፤
ነፍሱን ለሐሰት ነገር የማያስገዛ፤

23፥6 ነህ9፥25
24፥1 ዘፀ9፥29፤ኢዮ 41፥11፤1ቆሮ10፥26
24፥2 ዘፍ1፥6፤መዝ 104፥3፤2ጴጥ3፥5
24፥3 መዝ2፥6፤ 15፥1፤65፥4
24፥4 2ሳሙ22፥21 ፤መዝ51፥10፤73፥1፤ ሕዝ18፥15፤ማቴ5፥8
24፥5 ዘዳ11፥26፤ መዝ17፥2
24፥6 መዝ27፥8፤ 105፥4፤119፥58፤ሆሴ 5፥15
24፥7 መዝ29፥31 44፥4፤74፥12፤118፥1 9:20፤ኢሳ26፥2፤60፥ 11:18፤62፥10፤ ዘካ 9፥9፤ማቴ21፥5፤ሐሥ 7፥2፤ 1ቆሮ 2፥8
24፥8 ዘፀ15፥3:6፤ ዘዳ4፥34፤1ዜና29፥11 ፤መዝ89፥13፤ኤር50፥ 34፤ኤፌ6፥10

በውሸት የማይምል፤[ረ]
5እርሱ በረከትን ከእግዚአብሔር ዘንድ፣
ምሕረትንም ከአዳኝ አምላኩ ይቀበላል::
6እርሱን የሚፈልግ ትውልድ እንዲህ ነው፤
የያዕቆብ አምላክ ሆይ፤ ፊትህን[ሰ] የሚፈልግ
እንዲህ ያለ ነው:: ሴላ
7እናንተ ደጆች፤ ቀና በሉ፤
እናንተ የዘላለም በሮች፤
የክብር ንጉሥ እንዲገባ ብድግ በሉ!
8ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው?
እግዚአብሔር ነው ብርቱና ኀያል፤
እግዚአብሔር ነው በውጊያ ኀያል::
9እናንተ ደጆች፤ ቀና በሉ፤
እናንተ የዘላለም በሮች፤
የክብር ንጉሥ እንዲገባ ብድግ በሉ!

[ረ]4 ወይም *በሐሰትም ያልማለ*
[ሰ]6 ሁለት የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆችና ሱርስት (እንዲሁም ሰብዓ ሊቃናት ይመ) እንዲሁ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች ግን *ያዕቆብ፤ ፊትህን* ..

ቃል ኪዳን ከተደረገ በኋላ ትልቅ ግብዣ ይዘጋጃል፤ ግብዣው የሚ ያመለክተው ቃል ኪዳን በተጋቡት ወገኖች መካከል ያለው ወዳጅነት ጥብቅ መሆኑን ነው (41፥9፤ ዘፍ 31፥54፤ አብ7 ይመ):: በአንድ ንጉሥና ከንጉሡ በታች ባሉ አስተዳዳሪዎች መካከል ስምምነት ወይም ቃል ኪዳን ሲደረግ ግን አስተዳዳሪው በግብ ዣው ላይ ይገኛል (ዘፀ24፥8-12 ይመ):: *ራሴን በዘይት ቀባህ፤* አንድ የተከበረ እንግዳ በግብዣ ላይ በዚህ ዐይነት መልክ ማስተ ናገድ የተለመደ ወግና ባህል ነው (ሉቃ7፥46፤ እንዲሁም 2ሳሙ 12፥20፤ መክ 9፥8፤ ዳን 10፥3 ይመ):: *ጽዋዬም፤* የጌታ ግብዣ ነው፤ የ16፥5 ማብ ይመ::

23፥6 *በጎነትና ምሕረት፤* ሁለቱም ሁልጊዜ የሚያመለክ ቱት ኪዳኑ የሚያስገኘውን በረከትና ጥቅም ነው (የ6፥4 ማብ ይመ)፤ በዚህ ቦታ በሰውኛ ዘይቤ ቀርበዋል (25፥21፤ 43፥3፤ 79፥8፤ 89፥14 ይመ):: *ይከተሉኛል፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ዘወ ትር ካጠገቤ አሉ" እንደ ማለት ነው:: *በእግዚአብሔር ቤት ... እኖራለሁ፤* የ15፥1 ማብ ይመ:: *ለዘላለም፤* የዕብራይስጡ ቃል "ዓመ ታቱን ሁሉ ወይም ዘመናቱን ሁሉ" የሚል ይመስላል፤ ሆኖም የ11፥7፤ 16፥9-11 ማብ ይመ::

*መዝሙር 24፤* ጌታ በአሸናፊነት ወደ ጽዮን በመግባቱ ምክንያት የቀረበ የምስጋና ቃል ነው (መዝ47፤ 68፤ 118፤ 132 ይመ):: ይህ መዝሙር ዳዊት የቃል ኪዳኑን ታቦት ይዞ ወደ ኢየሩ ሳሌም በገባበት ወቅት (2ሳሙ6) ወይም ይህንን ሁኔታ ለማሰብ የተደረሰ መዝሙር ነው:: ከመዝሙር23 ቀጥሎ መቅረቡም ወደ ማደሪያው ድንኳን ማን መግባት እንዳለበት የሚገልጽ ነው (23፥6 ይመ):: ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ይህንን መዝሙር የጌታን ዕርገትና በእንዴት ያለ ክብርም ወደ ሰማ ያዊቷ ኢየሩሳሌም ወይም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንደ ገባ ለማሳ የት/ ለማክበር ስትጠቀምበት ቈይታለች (የመዝ47ን መግቢያ ይመ)::

*24፥1-2፤* ይህ መግቢያ እግዚአብሔር ፈጣሪና ሁሉን የሚመግብ፣ ደግሞም የዓለም ሁሉ ባለቤትና "የክብርም ንጉሥ" በመሆኑ (ቍ7-10፤ መዝ29፤ 33፥6-11፤ 89፥5-18፤ 93፤ 95፥3-5፤ 104 ይመ)፣ ሊመለክና ሊከበር የሚገባው መሆኑን የሚያውጅ መግቢያ ነው (ምናልባት ይህንን ቃል የተናገረው አንድ ሌዋዊ ሳይሆን አይቀርም)::

24፥1 *ምድርና በእርሷ ያለው ሁሉ፤* ጳውሎስ ይህንን አገላለጽ በእንዴት ያለ መንገድ እንደ ተጠቀመበት 1ቆሮ10፥25-26 ይመ::

*24፥2፤* የዘፍ1፥1-10 ቃል እንደ ገና መልሶ የሚያስተጋባ ነው:: *መሥርቶአታልና ... አጽንቶታል፤* ከከተማ መሠረት (ኢሱ 6፥26፤ 1ነገ16፥24፤ ኢሳ14፥32 ይመ) ወይም ከቤተ መቅደስ መሠ ረት (1ነገ5፥17፤ 6፥37፤ ዕዝ3፥6-12፤ ኢሳ44፥28፤ ሐጌ2፥18፤ ዘካ 4፥9፤ 8፥9 ይመ) ላይ የተወሰደ ተምሳሌት ወይም ዘይቤ ነው:: እንደ ቤተ መቅደስ ሁሉ መሬትም (ምድርም) መሠረትና (18፥15፤ 82፥5፤ 1ሳሙ2፥8፤ ምሳ8፥29፤ ኢሳ24፥18 ይመ) ምሰሶ ወይም ዐምድ (75፥3፤ ኢዮ9፥6 ይመ) አላት ተብሎ ይነገር ነበር:: በጥንት ቅርብ ምሥራቅ ነዋሪዎች ዘንድ ቤተ መቅደሶች የምድር ወይም የዓለም ነጸብራቆች ናቸው ተብሎ ይታመናል፤ በዚህም ምክንያት የአንድን ቤተ መቅደስ ምንነት ለመግለጽ የሚውለው ቋንቋ ዓለምንም ሁኔታ ለመግለጽ ያገለግል ነበር::

*24፥3-6፤* ወደ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ለሚገቡ ሰዎች የተ ሰጠ መመሪያ ነው (ምናልባት በካህኑ የተነገረ ሊሆን ይችላል)፤ መዝሙር 15 እና መግቢያውን ይመ::

24፥3 *ወደ እግዚአብሔር ተራራ፤* 2፥6 እና ማብ ይመ::

24፥4 *ንጹሕ እጅና፤* በደል የማይገኝበትን ተግባር የሚ ያሳይ ነው:: *ቅን ልብ፤* ቀና አመለካከትና ቅዱስ ተነሣሥቶት ማለት ነው፤ ኢየሱስ "ልበ-ንጹሐን እግዚአብሔርን ያዩታል" (ማቴ 5፥8) በማለት ተናግሮአል:: *ልብ፤* የ4፥7 ማብ ይመ:: *ነፍሱን ... ይማያስገዛ፤* ያላመለከ ወይም እምነቱን በዚያ ላይ ያልሰቀለ ማለት ነው (25፥1-2 ይመ):: *ነፍሱን፤* የ6፥3 ማብ ይመ:: *በሐ ሰትም፤* ወይም በውሸትም ማለት ነው፤ ይህ አባባል በሐሰት መመስከርን ያጠቃልላል (ተመሳሳይ አገላለጽን ለማግኘት ዘፀ 20፥16፤ ዘሌ19፥12፤ ኤር5፥2፤ 7፥9፤ ዘካ5፥4፤ ሚል3፥5 ይመ)::

24፥5 *ምሕረትንም፤* ይኸውም የምሕረትን ፍሬ፣ ለምሳሌ ታማኝ ከሆነው አምላክ መልካም እንክብካቤን ማግኘት ማለት ነው፤ በዚህም መሠረት "በረከትን" ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ትርጒም አለው (23፥3 እና ማብ ይመ)::

24፥6 *ትውልድ፤* የ78፥8 ማብ ይመ:: *ያዕቆብ፤* የ14፥7 ማብ ይመ::

*24፥7-10፤* የክብር ንጉሥ እየመጣ መሆኑን የሚያውጅ ክፍል ነው:: (ምናልባት ይህ ቃል የተነገረው በንጉሡ ሳይሆን አይቀርም፤ ንጉሡ በተሰበሰቡት እስራኤላውያን ፊት ሲናገር የበር ጠባቂዎች አጸፋውን ይመልሱ ነበር):: ጌታ በጽዮን ቤተ መቅደስ ውስጥ ተገኘ ማለት ከግብፅ የጀመረውን ዘመቻ አጠ ናቀቀ ማለት ነው:: "የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር" (ቍ10)፣ ወይም "ብርቱ ጦረኛ የሆነው እግዚአብሔር" (ቍ8፤ ዘፀ15፥1-18)፣ ጠላቶቹን ሁሉ ከሰባበረ በኋላ "ማረፊያ ቦታ" ወደ ሆነችው (132፥8:14፤ 68፥7-8፤ መሳ5፥4-5፤ ዕን3፥3-7 ይመ)፣ ወደ ራሱ ከተማ በድል አድራጊነት ገባ (መዝ46፤ 48፤ 76፤ 87 ይመ):: ከዚህ በኋላ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር መንግሥት ንጉሣዊ ከተማ ናት (የ9፥11 ማብ ይመ)::

24፥7 *እናንተ ደጆች ቀና በሉ፤* ድል አድራጊውን የክብር ንጉሥ ለመቀበል በታላቅ እልልታና ሆታ ተነሡ ማለት ነው (3፥3፤ 27፥6፤ 110፥7 ይመ):: *በሮች፤* የከተማን ወይም የቤተ መቅደስን በሮች የሚያመለክት ነው:: *ደጆች፤* "በሮች" ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ትርጒም ያለው ሲሆን በዚህ አገባቡ ግን የበሮች መዝጊያ የሚለውን አያመለክትም (ይኸውም በመሳ16፥3፤ 1ሳሙ21፥13 ላይ እንደ ተመለከተው ዐይነት ነው):: በኢሳ14፥31 ላይ እንደ ተመለከተው ሁሉ በዚህም ቦታ "በሮች" የሚለው ቃል መልእክትን ብርቱ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ሲባል ሥዕላዊ በሆነ ወይም ምስል ከሳች በሆነ ሰውኛ ዘይቤ ቀርቦአል::

10ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው?
የሰራዊት አምላክ፣
እርሱ የክብር ንጉሥ ነው። ሴላ

## መዝሙር 25[#]

## በአደጋ ጊዜ የቀረበ ጸሎት

የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ነፍሴን ወደ አንተ
አነሣለሁ፤
2ስምሳኬ ሆይ፣ በአንተ እታመናለሁ፤
እባክህ አታሳፍረኝ፤
ጠላቶቼም አይዘባነኑብኝ።
3አንተን ተስፋ የሚያደርጉ፣
ከቶ አያፍሩም፤
ነገር ግን እንዲያው ያለ ምክንያት፣
ተንኰለኞች የሆኑ ያፍራሉ።

4እግዚአብሔር ሆይ፤ አካሄድህን
እንዳውቅ አድርገኝ፤
መንገድህንም አስተምረኝ።
5አንተ አዳኜ፣ ስምሳኬም ነህና፣
በእውነትህ ምራኝ፤ አስተምረኝም፤
ቀኑን ሙሉ አንተን ተስፋ
አደርጌአለሁ።
6እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረትህንና
ፍቅርህን አስብ፤
እነዚህ ከጥንት የነበሩ ናቸውና።
7የልጅነቴን ኀጢአት፣
መተላለፌንም አታስብብኝ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ቸርነትህ
ብዛት፣
እንደ ምሕረትህም መጠን አስበኝ።
8እግዚአብሔር መልካምና ቅን ነው፤
ስለዚህ ኀጢአተኞችን በመንገድ
ይመራቸዋል።
9ዝቅ ያሉትን በፍትሕ ይመራቸዋል፤
ለትሑታንም መንገዱን
ያስተምራቸዋል።
10ኪዳኑንና ሥርዐቱን ለሚጠብቁ፣
የእግዚአብሔር መንገድ ሁሉ ቸርነትና
እውነት ናቸው።
11እግዚአብሔር ሆይ፤ ኀጢአቴ ታላቅ
ነውና፣
ስለ ስምህ ይቅር በለኝ።
12እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ማን ነው?
በተመረጠለት መንገድ ያስተምረዋል።
13ዘመኑን በተድላ ደስታ ያሳልፋል፤
ዘሩም ምድርን ይወርሳል።
14እግዚአብሔር ምስጢሩን ከሚፈሩት
ወዳጆቹ አይሰውርም፤
ኪዳኑንም ይገልጥላቸዋል።
15ዐይኖቼ ሁልጊዜ ወደ እግዚአብሔር
ናቸው፤

24፥10 1ሳሙ1፥11
25፥1 መዝ86፥4፤ 143፥8
25፥2 መዝ31፥6፤ 143፥8
25፥3 መዝ22፥5፤ ኢሳ24፥16፤29፥22፤ ዕን1፥13፤ሰቈ3፥4፤ 2ጢሞ3፥4
25፥4 ኢዮ34፥32
25፥5 ቍ3፤መዝ 24፥5፤31፥3፤33፥20፤ 39፥7፤42፥5፤43፥3፤7 1፥5፤130፥7፤131፥3፤ ዮሐ16፥13
25፥6 መዝ5፥7፤ 98፥3፤ኢሳ63፥7፡15፤ ኤር31፥20፤ሆሴ11፥8
25፥7 ዘፀ23፥21፤ 1ዜና16፥34፤ኢዮ 13፥26፤መዝ6፥4፤34፥ 8፤51፥1፤69፥16፤73፥ 1፤107፥17፤109፥26፤ 119፥124፤ኢሳ54፥4 ፤ኤር3፥25፤31፥19፤3 2፥30፤ሕዝ16፥22፡60 ፤23፥3፤2ጢሞ2፥22
25፥8 መዝ32፥8፤ 92፥15፤ኢሳ26፥7፤ 28፥26
25፥9 ቍ4፤መዝ 23፥3፤27፥11
25፥10መዝ18፥25፤ 103፥18፤132፥12
25፥11 ዘፀ9፥16፤ 32፥30፤34፥9፤መዝ31 ፥3፤78፥38፤79፥9፤ኤር 14፥7
25፥12 ቍ8፤ኢዮ 1፥8 25፥13 ዘኍ14፥24 ፤ዘዳ30፥15፤1ነገ3፥14፤ኢዮ8፥7፤ማቴ5፥5
25፥14 ዘፍ17፥2፤ ምሳ3፥32፤ዮሐ7፥17 25፥15 2ዜና20፥12 ፤ኢዮ34፥30፤መዝ 119፥110፤123፥2፤ዕብ 12፥2

[#]25 ይህ መዝሙር እያንዳንዱ ጥቅስ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆሄያት የሚጀምር፣ ጅማሬው ወይም ጅማሬውና መጨረሻው ትርጕም የሚሰጥ ግጥም ነው።

24፥10 *የሰራዊት አምላክ፤* የ1ሳሙ1፥3 ማብ ይመ። በዚህ ቦታ የቀረበው የነገሩ መደምደሚያ ወይም ማሳረጊያ ሆኖ ነው።

*መዝሙር 25፤* መዝሙረኛው በኀጢአት ምክንያት ከባድ መከራ ባገኘው ጊዜ፣ ጠላቶቹም ባገኙት አጋጣሚ ስሙን ለማጥፋት በሚራወጡበት ጊዜ እግዚአብሔር በኪዳናዊ ምሕረቱ እንዲያስበው ልመናውን ያቀርባል (የ5፥9 ማብ ይመ)። ከዚህም በቀር በጎ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳንና (ይኸውም ምሕረቱን፣ ፍቅሩን፣ ቸርነቱን፣ ቅንነቱን፣ ታማኝነቱንና ጸጋውን ነው፤ ቍ6-8፡10፡16 ይመ) እርሱም በበኩሉ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት መሠረት በማድረግ (ቍ1፡5፡15፡20-21 ይመ) እግዚአብሔር ከጠላቶቹ እንዲታደገውና (ቍ2፡19 ይመ) ፈቃዱንና መንገዱም እንዲያስታውቀው (ቍ4-5፡21 እና ቍ8-10፡12 ይመ)፣ እንዲሁም ኀጢአቱን ይቅር እንዲለውና (ቍ7፡11፡18 ይመ) ከደረሰበትም ከባድ መከራ እንዲያሳርፈው ጸሎት ያቀርባል (ቍ2፡16-18፡20 ይመ)። እነዚህ ነገሮች እርስ በርስ የተሳሰሩ ናቸው፤ ይኸውም መዝሙረኛው የደረሰበትን ከባድ መከራ አውልቆ የሚጥልለት የእግዚአብሔር ምሕረት ሲሆን ጠላቶቹም ከእንግዲህ በኋላ ስሙን የሚያጠፉበትና የሚሳለቁበት መንገድ አያገኙም። እንዲሁም እግዚአብሔር "በመንገዱ" (ቍ9) ማለትም "በቃል ኪዳኑ" መሠረት (ቍ10) ስለሚመራው "በዐመፃ መንገድ" (ቍ7) ላይ አይመላለስም። መዝሙረኛው በእግዚአብሔር በመታመን፣ "ነፍሴን ወደ አንተ አነሣለሁ" (ቍ1፤ 24፥4 ይመ) በማለቱ ይህ መዝሙር ከመዝሙር 24 ጋር የእርስ በርስ ተዛምዶ አለው።

*25፥1-3፤* ከጭንቀትና ከሕመም፣ እንዲሁም ጠላቶቹ ስሙን ለማጥፋት ከሚያደርጉት ሩጫ እንዲጠብቀው የቀረበ ጸሎት ነው።

25፥3 *ያለ ምክንያት፤* ዳዊት ጠላቶቹ በእርሱ ላይ በጥላቻ እንዲነሡ፣ ያደረገው አስተዋፅኦ የለም።

*25፥4-7፤* ቀናውን መንገድና ምሕረትን ለማግኘት የቀረበ ጸሎት ነው።

25፥4 *አካሄድህን ... መንገድህንም፤* ቃል ኪዳኑን የሚያሳዩ ተለዋጭ ዘይቤዎች ናቸው (ቍ10፤ ዘዳ8፥6፤ 10፥12-13፤ 26፥17፤ 30፥16፤ ኢሱ22፥5፤ እንዲሁም ቍ8-9፤ 18፥21፤ 51፥13፤ 81፥13፤ 95፥10፤ 119፥3፡15፤ 128፥1 ይመ)።

25፥5 *በእውነትህ፤* ለጌታ ታማኝ የሆነ ሕይወት ማለት ነው።

25፥6-7 *አስብ ...አታስብብኝ፤* ከድሮ ጀምሮ ጸንተው የነበሩትን ("ከጥንት የነበሩትን") "ምሕረትህንና ፍቅርህን" ተመልከት፤ ነገር ግን ገና ከሕፃንነቴ ጀምሮ ያለውን ("ከልጅነቴ") በደሌን አትመልከት ማለት ነው። *ፍቅርህን፤* ቍ10 እንዲሁም የ6፥4 ማብ ይመ።

*25፥8-15፤* የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሚያስገኘውን መልካም ነገር በማስተዋል የተነገረ የእምነት ቃል ነው። ዳዊት ምሕረትን በሚለምንበት በዚህ ዐውደ ንባብ ውስጥ ራሱን ከኀጢአተኞች (ቍ8) እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ከሚጠብቁና (ቍ10፡14 ይመ) እግዚአብሔርንም ከሚፈሩ (ቍ12፡14 ይመ) ትሑታን ጋር (ቍ8) አንድ አድርጎ አቅርቦአል። ኀጢአተኛ እንደ መሆኑ መጠን ይቅርታ ያስፈልገዋል፤ ደግሞም የጌታ ትሑት አገልጋይ እንደ መሆኑም መጠን፣ የእግዚአብሔርን ይቅርታና ምሪት ለቃል ኪዳኑ ታማኝ በመሆን በተስፋ ይጠባበቃል።

25፥9 *ትሑታንንም፤* አለኝታ የሌላቸው መሆናቸውን የተገነዘቡ ናቸው።

25፥10 *የእግዚአብሔር መንገድ፤* ለመንገዶቹ ታማኝ ለሆኑት (ቍ4 ማብ ይመ) በቸርነት ይገለጣል (103፥7፤ 138፥5 ይመ)።

25፥11 *ስለ ስምህ፤* የ23፥3 ማብ እንዲሁም 1ዮሐ 2፥12 ይመ። *ስም፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

25፥12 *መርጦ የሚሄድበትን፤* ወይም "ሊመርጠው የሚገባውን መንገድ" ማለት ነው።

25፥13 *ምድርን ይወርሳል፤* ለዘራቸው የተሰጠውን የተስፋ ምድር እንደያዙ ይቈያሉ (37፥9፡11፡18፡22፡29፡34፤ 69፥36፤ ኢሳ 60፥21 ይመ)።

25፥14 *አይሰውርም፤* የቅርብ ወዳጆች አድርጐ ወደ ኅብረቱ ያስገባቸዋል (ዘፍ18፥17-19፤ ኢዮ29፥4 ይመ)። *ከሚፈሩት፤* እግዚአብሔርን የበለጠ ለማወቅና እርሱም የሚጠላውንና የሚጸየፈውን ሁሉ የሚጠሉና የሚጸየፉ ማለት ነው (ከምሳ3፥5-7 ጋር ያነጻጽሩ)።

እግሮቼን ከወጥመድ የሚያላቅቃቸው
እርሱ ነውና::
16እኔ ብቸኛና የተጨነቅሁ እንደ መሆኔ፣
ወደ እኔ ተመለስ፤ ምሕረትም
አድርግልኝ::
17የልቤ መከራ በዝቶአል፤
ከጭንቀቴ ገላግለኝ::
18ጭንቀቴንና መከራዬን ተመልከት፤
ኀጢአቴንም ሁሉ ይቅር በለኝ::
19ጠላቶቼ እንዴት እንደ በዙ ተመልከት፤
እንዴት አምርረው እንደሚጠሉኝ እይ::
20ነፍሴን ጠብቃት፤ ታደገኝም፤
መጠጊያዬ ነህና አታሳፍረኝ::
21አንተን ተስፋ አድርጌአለሁና፣
ታማኝነትና ቅንነት ይጠብቁኝ::
22ስምባክ ሆይ፤ እስራኤልን፣
ከመከራው ሁሉ አድነው::

## መዝሙር 26

### የንጹሕ ሰው ጸሎት

የዳዊት መዝሙር

1*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ያለ ነቀፋ እንደ
መሆኔ፣
አንተው ፍረድልኝ::
ወዲያ ወዲህ ሳልል፣
በ*እግዚአብሔር* ታምኛለሁ::
2*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ፈትነኝ፤
መርምረኝም፤
ልቤንና ውስጤን መርምር፤
3ምሕረትህ ከፊቴ አልተለየምና፣
በእውነትህም ተመላለስሁ::
4ከማይረቡ ጋር አልተቀመጥሁም፤
ከግብዞችም ጋር አልተባበርሁም::
5የክፉዎችን ማኅበር ተጸየፍሁ፤
ከዐመፀኞችም ጋር አልቀመጥም::
6እጆቼን በየዋህነት እታጠባለሁ፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ መሠዊያህንም
እዞራለሁ፤
7የምስጋናን ድምፅ አሰማ ዘንድ፣
ታምራትህንም አወራ ዘንድ ነው::
8*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የምትኖርበትን ቤት፣
የክብርህን ማደሪያ ቦታ ወደድሁ::
9ነፍሴን ከኀጢአተኞች ጋር፣
ሕይወቴንም ከደም አፍሳሾች ጋር
አታስወግዳት::
10በእነርሱ እጅ የተንኰል ዕቅድ አለ፤
ቀኝ እጃቸውም ጉቦን ያጋብሳል::
11እኔ ግን በተአማኒ ሕይወት እኖራለሁ፤
አድነኝ፤ ምሕረትንም አድርግልኝ::

25፥16. ዘኍ6፥25፤ መዝ6፥4፤68፥6
25፥17 1ነገ1፥29፤ መዝ6፥3፤34፥6፡17፤39፥2፤40፥12፤54፥7፤116፥3
25፥18 2ሳሙ16፥12፤መዝ13፥3፤103፥3፤ሮሜ12፥12
25፥19 መዝ3፥1፤9፥13፤35፥19፤38፥19፤69፥4
25፥20 ቍ3፤መዝ2፥12፤17፥13፤22፥21፤43፥1፤71፥2፤86፥2፤116፥4፤140፥1፤142፥6፤144፥11
25፥21 ቍ3፤ዘፍ20፥5፤1ነገ9፥4፤መዝ85፥10፤111፥8፤ምሳ10፥9፤ኢሳ60፥17፤ሚል2፥6
25፥22 መዝ130፥8፤ሉቃ24፥21
26፥1 1ሳሙ24፥15፤2ነገ20፥3፤መዝ15፥2፤22፥4፤40፥4፤ምሳ20፥7፤ኢሳ12፥2፤25፥9፤ኤር17፥7፤ዳን3፥28፤ዕብ10፥23
26፥2 ዘጸ6፥6፤መዝ7፥9፤66፥10፤ኤር11፥20፤20፥12፤ሕዝ11፥5
26፥3 1ነገ2፥4፤መዝ6፥4፤40፥11፤43፥3፤86፥11፤119፥30
26፥4 መዝ1፥1፤28፥3፤ማቴ6፥2 26፥5 መዝ139፥21 26፥6 መዝ73፥13፤ማቴ27፥24 26፥7 ኢሱ3፥5፤መዝ9፥1፤ኢሳ42፥12፤60፥6 26፥8 ዘፀ29፥43፤2ዜና7፥1፤መዝ96፥6፤122፥6፤ኢሳ66፥10 26፥9 መዝ5፥6፤28፥3፤55፥23፤139፥19፤ምሳ29፥10 26፥10 ኢዮ36፥18፤መዝ21፥11፤ኢሳ 1፥23፤ሕዝ22፥12 26፥11 መዝ31፥5፤ 69፥18፤119፥134፤ቲቶ2፥14

*25፥16-21፤* ከጭንቀትና ከሕመም፣ እንዲሁም ከጠላቶች ጥቃት ለመዳን የቀረበ ጸሎት ነው::

25፥17 *የልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ::

25፥21 *ታማኝነትና ቅንነት፤* በሰውኛ አገላለጽ የቀረቡ በጎ ተግባራት ናቸው (23፥6 እና ማብ ይመ):: ይቅር መባል ብቻውን በቂ አይደለም፤ ዳዊት፣ እግዚአብሔር "ቸርና ቅን" (ቍ8፤ እንዲሁም 51፥10-12 ይመ) እንደ ሆነ ሁሉ እርሱም በአረማመዱ ሁሉ ንጹሕ ሰው እንዲሆን እግዚአብሔር እንዲረዳው ልመና አቀረበ::

*25፥22፤* በእግዚአብሔር ሕዝብ ስም የቀረበ የማሳረጊያ ጸሎት ነው (3፥8 እና ማብ ይመ):: *አድነው፤* "ተቤዠው" ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ትርጕም አለው::

*መዝሙር 26፤* እግዚአብሔር በምሕረት ዐይን እየተመለከተ እንዲመረምር ጥያቄ የሚያቀርብ ጸሎት ነው፤ ይኸውም ታማኝና ቅዱስ የሆነውን አገልጋዩን፣ ክፉዎችንና ከሓዲዎችን ጠራርጎ ከሚወስደው ሞት እንዲያድነው ነው:: መዝሙረኛው "ፍረድልኝ" (ቍ1) የሚል ጸሎት በማቅረቡ በ"ማይረቡና" (ቍ4) "በደም አፍሳሶች" (ቍ9) (በመዝ23፤25፤27-28 ላይ እንደ ተመለከተው) በጠላቶች መከበቡን ያመለክታል:: ይህ መዝሙር "የጌታ ቤት" በሚለው ዋና ሐሳብ ከመዝ27-28 (እንዲሁም መዝ23-24 ይመ) ጋር በጥብቅ ይዛመዳል:: እዚህ ላይ ዳዊት ለቤተ መቅደሱ (ወይም ለማደሪያው ድንኳን) ያለው "ፍቅር" (ቍ8)፣ እምነቱ ምን ያህል ከልብ እንደ ሆነ ያሳያል:: በመዝሙር 27 ላይ እንደ ተመለከተው የጌታ ቤተ መቅደስ፣ ዳዊት ከጠላቶቹ የሚደበቅበት ዐምባ ነው፤ በመዝሙር 28 ላይ እንደ ተጠቀሰው ደግሞ ዳዊት ጩኸቱን ወደ ጌታ ዙፋን ፊት (እጅግ ወደተቀ ደሰው ማደሪያው፤ 28፥2) ያሰማል::

*26፥1-8፤* እግዚአብሔር ዳዊት ያሳየውን ምግባራዊ ታማኝነት እንዲሁም እምነቱ የማይናወጥና በጌታም ያለው ርካታ ፍጹም መሆኑን እንዲቈጥርለት የሚያሳስብ ምልጃ ነው፤ ዳዊት ይህን ሁሉ የዘረዘረው እንደ ፈሪሳውያን በራሱ ጽድቅ ለመመካት አስቦ አይደለም (ሉቃ18፥9-14)::

26፥1 *ያለ ነቀፋ እንደ መሆኔ፤* ቍ11 እና ማብ ይመ፤ ይህ አባባል የሚያመለክተው ኀጢአት የሌለበት ፍጹም ሰው መሆኑን ሳይሆን (7፥8፤ 41፥12፤ 101፥2፤ በተለይም 1ነገ9፥4 ይመ)፣ በምግባሩ ሁሉ ታማኝ ሆኖ መገኘቱን ነው (ቍ2-5 ይመ):: *ታምኛለሁ፤* ከአብርሃም የሕይወት ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው (ዘፍ 12፥4) እና ማብ፤ 22፥12፤ እንዲሁም መዝ34፥8-14 እና ማብ ይመ)፣ ታዛዥነትና ታማኝነት የቅድስና ሕይወት ሁለት ገጽታዎች ናቸው::

26፥2 *ልቤንና ውስጤን፤* የ7፥9 ማብ ይመ::

26፥3 *ምሕረትህ... በእውነትህም፤* 40፥10 ይመ:: ዳዊት ልቡን የሰቀለው "ቃል ኪዳኑን ለሚጠብቁ" (25፥10) ሁሉ በተሰጠው ተስፋ በእግዚአብሔር ፍቅርና (የ6፥4 ማብ ይመ) እውነት (ታማኝነት፤ 25፥10 ይመ) ላይ ነው:: *ተመላለስሁ፤* ይኸውም የኪዳኑን በረከት ለማግኘት ነው::

26፥4-5 *አልተቀመጥሁም፤* ዳዊት ዙሪያውን ከከበቡት "ከአታላዮች"፣ "ከግብዞች"፣ "ከክፉ አድራጊዎች" እና "ከኀጢአተኞች" ጋር አብሮ ለመቀመጥና አባሪ ተባባሪም ለመሆን እምቢ አለ (1፥1 እና ማብ፤ እንዲሁም መዝ101 ይመ)::

26፥4 *ከግብዞችም፤* ዐውደ ንባቡ በማጭበርበር ጕዳያቸውን የሚያስፈጽሙትን ወይም በመሳ6፥12-14 ላይ የተጠቀሱትን ዐይነት ሰዎች ሊያመለክት ይችላል::

26፥6 *እጆቼን በየዋህነት እታጠባለሁ፤* ገርነትንና ንጽሕናን የሚያመለክት የተለመደ አባባል ነው:: ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ የሚፈልጉ ሁሉ ንጹሕ የሆነ እጅና ንጹሕ ልብ ሊኖራቸው ያስፈልጋል (24፥4 እና ማብ ይመ):: *መሠዊያህንም እዞራለሁ፤* የእግዚአብሔርን አዳኝነት እያወሱ በመሠዊያው ዙሪያ መዞር ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሕይወትን የሚያሳይ ሲሆን እንዲህ ያለው ምም አምልኮ ሌሎችን ለምስጋና ያነሣሳ ነበር (43፥4 ይመ)::

26፥7 *ምስጋናን፤* የ9፥1 ማብ ይመ::

26፥8 *የክብርህን ማደሪያ፤* የእግዚአብሔር ክብር በአንድ ቦታ መገኘት፣ እግዚአብሔር ራሱ በዚያ ቦታ መገኘቱን ያመለክታል (ዘፀ24፥16፤ 33፥22 ይመ):: በማደሪያው ድንኳን (ዘጸ40፥35) በኋላም በቤተ መቅደሱ ላይ የወረደው የእግዚአብሔር ክብር (1ነገ 8፥11 ይመ)፣ እግዚአብሔር በእስራኤል መካከል ሲያድር ቅዱስና ቸር መሆኑን ያረጋግጣል:: ዮሐ1፥14 "ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም አደረ፤" ሲል ይህንኑ የእግዚአብሔርን መገኘት መናገሩ ነው::

*26፥9-11፤* ክፉዎችን የሚጠብቃቸው ሞት በዳዊት ላይ እንዳይደርስ የቀረበ ምልጃ ነው::

26፥9 *ነፍሴን፤* የ6፥3 ማብ ይመ::

26፥11 *በተአማኒ ሕይወት እኖራለሁ፤* ዳዊት ወደ ተነሣበት ምልጃ ይመለሳል (ቍ1ይመ):: *አድነኝ፤* የ25፥22 ማብ ይመ::

12 እግሮቼ በደልዳላ ስፍራ ቆመዋል፤
በታላቅ ጉባኤ መካከልም እግዚአ
ብሔርን እባርከዋለሁ::

## መዝሙር 27

### ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ሰው ድፍረት

የዳዊት መዝሙር

1 እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኀኔ ነው፤
የሚያስፈራኝ ማን ነው?
እግዚአብሔር ለሕይወቴ ዐምባዋ ነው፤
ማንን እፈራለሁ?
2 ሥጋዬን ይበሉ ዘንድ፣[†]
ክፉዎች ገፍተው በመጡ ጊዜ፣
ጠላቶቼና ባላጋራዎቼ በተነሡብኝ ጊዜ፣
እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ::
3 ሰራዊት ቢከበኝ እንኳ፣
ልቤ አይፈራም፤
ጦርነት ቢነሣብኝ እንኳ፣
ልበ ሙሉ ነኝ::

4 እግዚአብሔርን አንዲት ነገር
እለምነዋለሁ፤
እርሷንም እሻለሁ፤
ይኸውም በሕይወቴ ዘመን ሁሉ፣
በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፣
የእግዚአብሔርን ክብር ውበት አይ
ዘንድ፣
በመቅደሱም ሆኜ አሰላስል ዘንድ ነው::
5 በመከራ ቀን፣
በድንኳኑ ውስጥ ይሰውረኛልና፤
በድንኳኑም ጓዳ ይሸሽገኛል፤
በዐለትም ላይ ያቆመኛል::
6 በዚህ ጊዜ በዙሪያዬ ባሉ ጠላቶቼ ላይ፣
ራሴ ከፍ ከፍ ይላል፤
በድንኳኑም ውስጥ የእልልታ መሥዋዕት
እሠዋለሁ፤
ለእግዚአብሔር እቀኛለሁ፤
እዘምርለታለሁም::

7 እግዚአብሔር ሆይ፤ ድምፄን ከፍ
አድርጌ ስጮኽ ስማኝ፤
ራራልኝ፤ ስማኝም::
8 "ፊቴን ፈልጉ" ባልህ ጊዜ፣[°]
ልቤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ፊትህን
እሻለሁ አለች::
9 ፊትህን ከእኔ አትሰውር፤
ተቈጥተህ አገልጋይህን አታርቀው፤
መቼም ረዳቴ ነህና::
አዳኝ አምላኬ ሆይ፤
አትጣለኝ፤ አትተወኝም::
10 አባቴና እናቴ ቢተዉኝ እንኳ፣
እግዚአብሔር ይቀበለኛል::
11 እግዚአብሔር ሆይ፤ መንገድህን
አስተምረኝ፤
ስለ ጠላቶቼም፣
በቀና መንገድ ምራኝ::
12 ለጠላቶቼ ፍላጎት አሳልፈህ አትስጠኝ፤
የሐሰት ምስክሮች ተነሥተውብኛልና፣
ዐመፃ የሚረጩ ናቸው::

13 የእግዚአብሔርን ቸርነት፣
በሕያዋን ምድር እንደማይ፣
ሙሉ እምነቴ ነው::

26፥12 መዝ22፥25፤27፥11፤40፥2፤143፥10፤ኢሳ26፥7፤40፥3-4፤45፥13፤ዘካ4፥7፤ሉቃ6፥17
27፥1 ዘፀ15፥2፤2ሳሙ22፥29፤ኢዮ13፥15፤መዝ3፥8፤9፥9፤56፥4፤11፤118፥6
27፥2 መዝ9፥3፤20፥8፤37፥24፤ዳን11፥19፤ሮሜ11፥11
27፥3 ዘፍ4፥7፤ኢዮ4፥6፤መዝ3፥6
27፥4 መዝ23፥6፤61፥4፤ሉቃ10፥42
27፥5 ኢዮ38፥23፤መዝ12፥7፤17፥8፤40፥2
27፥6 ዘፀ15፥1፤2ሳሙ22፥49፤ዕዝ3፥13፤ኢዮ22፥26፤መዝ3፥3፤18፥48፤22፥12፤33፥2፤50፥14፤54፥6፤92፥1፤107፥22፤116፥17፤147፥7፤ኤፌ5፥19
27፥7 መዝ4፥1፤5፥3፤18፥6፤55፥17፤119፥149፤130፥2፤ኢሳ28፥23
27፥8 1ዜና16፥11
27፥9 ዘፍ49፥25፤ዘዳ4፥31፤31፥17፤33፥29፤መዝ2፥5፤18፥46፤22፥24፤37፥28፤119፥8፤ኢሳ41፥17፤62፥12፤ኤር14፥9
27፥11 ዘፀ33፥13፤ዕዝ8፥21፤መዝ5፥8፤72፥4፤78፥42፤106፥10፤ኤር21፥12
27፥12 ዘዳ19፥16፤ማቴ26፥60፤ሐሥ6፥13፤1ቆሮ15፥15
27፥13 ዘፀ33፥19፤2ዜና6፥41፤ኢዮ28፥13፤መዝ23፥6፤31፥19፤145፥7

[†]2 ወይም ስሜን ሊያጠፉ
[°]8 ወይም ልቤ ሆይ፤ ለአንተ "ፊቴን ..." አለ

*26፥12፤* በመደምደሚያ ላይ የቀረበ የመታመኛ ቃልና (የ3፥8 ማብ ይመ) ምስጋና ለማቅረብ የተገባ ስእለት ነው (የ7፥17 ማብ ይመ):: *በደልዳላ ስፍራ፤* ቀና የሆነና የአደጋም ስጋት የሌለበት መንገድ ነው (143፥10፤ ኢሳ40፥4፤ 42፥16 ይመ):: *ጉባኤ፤* የ1፥5 ማብ ይመ:: *እባርከዋለሁ፤* የ9፥1 ማብ ይመ::

*መዝሙር 27፤* ዳዊት ከሥልጣን ሊያወርዱት ከሚያሴሩ ሰዎች እግዚአብሔር እንደሚታደገው በመተማመን በሙሉ ልብ ያቀረበው ጸሎት ነው:: ጸሎቱ ጌታ ከዳዊት ጋር የገባውን ቃል ኪዳን መሠረት ያደረገ ነው (2ሳሙ7 ይመ):: ከፍ ባለ ድምፅ የተነገረ የእምነት ቃል ሲሆን (ይኸውም በሁለት አንጓዎች ቍ1-3፤ 4-6) ንጉሡ በጌታ ላይ ያለውን ጽኑ እምነት በይፋ የሚመሰክርና በቍ7-12 ላይ የተገለጸውን ጸሎት ከወዲሁ የሚያስተዋውቅ ነው:: መደምደሚያው (ቍ13-14) በቍ1-6 ላይ የተነገረውን የእምነት ቃል መልሶ የሚያስተጋባና እምነት ከእምነት ጋር የምታደርገውን ውይይት ጨምሮም የሚያቀርብ ነው፤ እምነት እምነትን እያበረታታችሁ አሁን የማይታየውን ግን ደግሞ አንድ ቀን እውን የሚሆነውን ተስፋ በትዕግስት መጠባበቅ አስፈላጊ መሆኑን ታስተምራለች (መዝ42-43፤ ዕብ11፥1 ይመ):: ለተጨማሪ ማብራሪያ የመዝ26 መግቢያን ይመ::

*27፥1-3፤* ጠላቶቹ ምንም ያህል ብርቱ ቢሆኑም ንጉሡ ግን በጌታ ዘንድ ዋስትና አለው (መዝ2 ይመ)::

27፥1 *ብርሃኔና፤* አብዛኛውን ጊዜ ጤናማና ሰላማዊ ኑሮን (97፥11፤ ኢዮ18፥5-6፤ 22፥28፤ 29፥3፤ ምሳ13፥9፤ ሰቆ3፥2 ይመ) ወይም ሕይወትንና ድነትን የሚወክል ምሳሌ ነው (18፥28፤ ኢሳ9፥2፤ 49፥6፤ 58፥8፤ 59፥9፤ ኤር13፥16፤ አሞ5፥18-20 ይመ):: "እግዚአብሔር ብርሃኔ ነው" ማለት እግዚአብሔር የዚህ ሁሉ ነገር ምንጭ በመሆኑ በእርሱ እታመናለሁ ማለት ነው (ኢሳ10፥17፤ 60፥1-2፡19-20፤ ሚክ7፥8-9 ይመ):: *መድኀኔ፤* የእኔ አዳኝ ማለት ነው (ቍ9 ይመ)::

27፥2 *ሥጋዬን ይበሉ ዘንድ፤* 7፥2 እና ማብ ይመ::

27፥3 *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ::

*27፥4-6፤* የጌታ መቅደስ ወይም ማደሪያ የንጉሡ ምሽግ ነው፤ ምክንያቱም ጌታ ራሱ የእርሱ ምሽግ ነው (ቍ1፤ የ9፥11፤ የ8፥12 ማብ ይመ)::

27፥4 *እኖር ዘንድ፤* የ15፥1 ማብ ይመ:: *የእግዚአብሔርን ውበት፤* ጽኑ የሆነውን በጎነቱን ማለት ነው (90፥17 ላይ "የጌታ ፍቅር" የሚለውን ይመ)::

27፥5 *በድንኳኑ፤* 31፥20፤ 32፥7፤ 61፥4፤ 91፥1 ይመ::

27፥6 *እሠዋለሁ፤* የ7፥17 ማብ ይመ:: *እዘምርለታለሁም፤* የ9፥1 ማብ ይመ::

*27፥7-12፤* ከዳተኛ ከሆኑ ጠላቶች ለመዳን የቀረበ ጸሎት ነው:: እነዚህ ጠላቶች ከግዛቱ ውስጥ ወይም ከግዛቱ ውጪ ወይም ከሁለቱም አቅጣጫ ይሁኑ ከዚህ ላይ ግልጽ አይደለም:: ዋና መሣሪያ አድርገው የተቀመጡት የስም ማጥፋት ዘመቻ ነው (የ5፥9 ማብ ይመ)::

27፥9 *ፊትህን ከእኔ አትሰውር፤* የ13፥1 ማብ ይመ:: *ተቈጥተህ፤* የ2፥5 ማብ ይመ:: *ረዳቴ ነህና፤* ወይም "ረዳቴ ሁን" ማለት ነው::

27፥10 *እግዚአብሔር ይቀበለኛል፤* ወይም "እግዚአብሔር ይቀበለኝ" ማለት ነው::

27፥11 *መንገድህን አስተምረኝ፤* እግዚአብሔርን የሚያውቁና ፈቃዱንም የሚፈጽሙ ብቻ ናቸው ለጸሎታችን በጎ ምላሽ እናገኛለን በማለት በተስፋ መጠባበቅ ያለባቸው (መዝ24-26፤ እንዲሁም 2ሳሙ7፥14 ይመ):: *በቀና መንገድ ምራኝ፤* 5፥8 እና ማብ ይመ::

*27፥13-14፤* በመደምደሚያ ላይ የተነገረ የእምነት ቃል ነው (የ3፥8 ማብ ይመ)::

27፥13 *የእግዚአብሔርን ቸርነት፤* ጌታ ከዳዊት ጋር በገባው ቃል ኪዳን ውስጥ "ቸርነትን" እንደሚያደርግ ቃል ገብቶአል (2ሳሙ7፥28፤ እንዲሁም 31፥19 እና ማብ ይመ):: *በሕያዋን ምድር፤* የዚህ ዓለም ሕይወት ማለት ነው::

14 እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፤
አይዞህ፣ በርታ፤
እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ።

## መዝሙር 28

### ልመናና ምስጋና

የዳዊት መዝሙር

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ እጣራለሁ፤
ዐለቴ ሆይ፤ ስምተህ እንዳልሰማ
አትሁንብኝ፤
አንተ ዝም ካልኸኝ፤
ወደ ጕድጓድ እንደሚወርዱ እሆናለሁ።
2 ለርዳታ በጮኽሁ ጊዜ፣
ወደ ቅዱስ ማደሪያህ፣
እጆቼን በዘረጋሁ ጊዜ፣
የልመናዬን ቃል ስማ።
3 በልባቸው ተንኰል እያለ፣
ከባልንጀሮቻቸው ጋር በሰላም ከሚናገሩ፣
ከክፉ አድራጊዎችና፣
ከዐመፃ ሰዎች ጋር ጐትተህ
አትውሰደኝ።
4 እንደ ሥራቸው፣
እንደ ክፉ ተግባራቸው ክፈላቸው፤
እንደ እጃቸው ሥራ ስጣቸው፤
አጸፋውን መልስላቸው።
5 ለእግዚአብሔር ሥራ ግድ ስለሌላቸው፣
ለእጆቹም ተግባራት ስፍራ ስላልሰጡ፣
እርሱ ያፈርሳቸዋል፤
መልሶም አይገነባቸውም።
6 የልመናዬን ቃል ሰምቶአልና፣
እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን።
7 እግዚአብሔር ብርታቴና ጋሻዬ ነው፤
ልቤ በእርሱ ይታመናል፤ እርሱም
አግዞኛል፤
ልቤ ሐሤት አደረገ፤
በዝማሬም አመሰግነዋለሁ።
8 እግዚአብሔር ለሕዝቡ ብርታታቸው ነው፤
ለቀባውም የመዳን አምባ ነው።
9 ሕዝብህን አድን፤ ርስትህንም ባርክ፤
እረኛ ሁናቸው፤ ለዘላለሙም ዐቅፈህ
ያዛቸው።

27፥14 ዘዳ31፥21፤ መሳ5፥21፤መዝ33፥20፤130፥5፡6፤ኢሳ8፥17፤30፥18፤ዕን2፥3፤ሰፎ3፥8፤ሐሥ1፥4፤ኢፌ6፥10
28፥1 ዘጸ1፥45፤አስ4፥14፤ኢዮ33፥18
28፥2 ዕዝ9፥5፤መዝ5፥7፤11፥4፤17፥1፤61፥1፤63፥4፤116፥1፤130፥2፤141፥2፤142፥1፤143፥1፤ሰቆ2፥19፤1ጢሞ2፥8
28፥3 መዝ12፥2፤26፥4፤55፥21፤ኤር9፥
28፥4 መዝ62፥12፤ሰቆ3፥64፤2ጢሞ4፥14፤ራእ18፥6፤22፥12
28፥5 ኢሳ5፥12
28፥6 ቍ2፤ዘፍ24፥27፤2ቆሮ1፥3፤ኤፌ1፥3፤1ጴጥ1፥3
28፥7 ዘጸ16፥15፤መዝ13፥5፤16፥9፤18፥1፤33፥3፤40፥3፤69፥30፤112፥7፤144፥9፤149፥1፤ኢሳ26፥3
28፥8 ዘፀ15፥2፤መዝ18፥1፤20፥6፤27፥1፤ዕን 3፥13
28፥9 ዘፀ34፥9፤ዘዳ1፥31፤32፥11፤1ዜና11፥2፤16፥35፤መዝ23፥1፤78፥52፡71፤80፥1፤106፥47፤118፥25፤ኢሳ40፥11፤46፥3፤63፥9፤ኤር31፥10፤ሕዝ34፥12-16፡23፡31፤ሚክ7፥14

27፥14 *እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፤* እምነት እምነትን ታበረታታለች (42፥5፡11፤ 43፥5፤ 62፥5 ይመ)።

*መዝሙር 28፤* እግዚአብሔርን ከሚያዋርዱና ከመሰሪዎችም እጅ ለመዳን የቀረበ ጸሎት ነው። እንደ መዝሙር 25 ሁሉ ይህም መዝሙር የሚደመድመው የጌታ ለሆኑት ሁሉ ምልጃ በማቅረብ ነው (3፥8 እና ማብ ይመ)። በመጨረሻው ቍጥር ላይ ጌታ የሕዝቡ እረኛ መሆኑን የሚያመለክት ቃል በመያዙ ከመዝሙር 23 ጋር የሚያዛምደው ነገር ያለ ይመስላል፤ ምናልባትም ከመዝሙር 23-28 ያለውን ክፍል ለብቻው ለይቶ የሚያስቀምጥና አንድ በሆነ የጋራ ዐቢይ ሐሳብም አዛምዶ የሚያስቀምጥ ሳይሆን አይቀርም። የመዝሙር 26 እና 29ን መግቢያ ይመ።

*28፥1-2፤* እግዚአብሔር ጩኸቱን እንዲሰማ ገና ከመነሻው ላይ የቀረበ ምልጃ ነው።

28፥1 *ዐለቴ፤* የ18፥2 ማብ ይመ። *ዝም ካልኸኝ፤* ለእኔ በትን ካላደረግህ ማለት ነው፤ *ጕድጓድ* የመቃብር ተለዋጭ ዘይቤ ነው (የ30፥1 ማብ ይመ)።

28፥2 *እጆቼን በዘረጋሁ ጊዜ፤* በአምልኮና በጸሎት ማለት ነው (63፥4፤ 134፥2፤ 141፥2 ይመ)። *ወደ ቅዱስ ማደሪያህ፤* የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚገኝበት የቤተ መቅደሱ ቅድስተ ቅዱሳን ነው (1ነገ8፥6-8)፤ በዚህ ምድር የእግዚአብሔር ዙፋን ወይም መንበር የሚገኘው በዚህ ክፍል ውስጥ ነው።

*28፥3-5፤* በቤተ መቅደሱ ውስጥ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው አምላክ አገልጋዩን እንዲታደግና በንጉሡና በሕዝቡ ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ በሚያደርጉት እንዲሁም ራሱን እግዚአብሔርን በሚያዋርዱት ላይ ፍርዱን ይገልጥ ዘንድ የቀረበ ጸሎት ነው።

28፥3 *በልባቸው፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *ተንኰል እያለ፤* የ5፥9 ማብ ይመ።

28፥4 *አጸፋውን መልስላቸው፤* የ5፥10 ማብ እንዲሁም ማቴ16፥27፤ 2ጢሞ4፥14፤ ራእ20፥12-13፤ 22፥12 ይመ።

28፥5 *ለእግዚአብሔር ሥራ፤* ይኸውም እስራኤልን መቤዠቱ፣ እስራኤልንም የራሱ መንግሥት አድርጎ ማቆሙ (በቃል ኪዳኑ መሠረት፤ ዘፀ19-24)፣ የዳዊትንም ቤት በሕዝቡ ላይ ምድራዊ እንደራሴው አድርጎ መሾሙ (ይህም በቃል ኪዳኑ መሠረት የሆነ ነው፤ 2ሳሙ7) ናቸው። *ለእጆቹም ተግባራት፤* ክፉዎች (ቍ3) በእጃቸው የሚፈጽሙት ክፉ ሥራ (ቍ4) የሚያሳየው እስራኤልና ዳዊት የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት በእግዚአብሔር የተሾሙ መሆናቸውን ከቶ የማይቀበሉ መሆኑን ነው። *ያፈርሳቸዋል፤* ወይም ያፍርሳቸው እንደ ማለት ነው።

*28፥6-7፤* ጸሎቱን እንደሚሰማው በመተማመን በሐሤት ያቀረበው ምስጋና ነው (የ3፥8 ማብ ይመ)።

28፥7 *ጋሻዬ፤* የ3፥3 ማብ ይመ። *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *በዝማሬም አመሰግነዋለሁ፤* የ7፥17 ማብ ይመ።

*28፥8-9፤* ጌታንና ሕዝቡን የሚመለከት ክፍል ነው (የ3፥8 ማብ ይመ)።

28፥8 *ለሕዝቡ ... ለቀባውም፤* በሁለቱ መካከል ጽኑ ኅብረት ያለ መሆኑን ያመለክታል (የ2፥2 ማብ ይመ)።

28፥9 *አድን ...ባርክ፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ አዲስ ሕይወት በሚሰጥበት ጊዜ በቅድሚያ የሚያከናውናቸው ሁለት ድርጊቶች ናቸው፤ ሁኔታውም በሚጠይቀው መሠረት በየጊዜው ያድናቸዋል፤ ደግሞም ሕይወታቸውና ድካማቸው ሁሉ ፍሬያማ እንዲሆን ዕለት በዕለት ይባርካቸዋል። *ርስትህንም፤* ዘዳ9፥29 ይመ። *ጠባ እረኛ፤* መግቢያውን ይመ፤ እንዲሁም 80፥1፤ ኢሳ40፥11፤ ኤር 31፥10፤ ሕዝ34፤ ሚክ5፥4 ይመ። የዚህ ጸሎት መልስ ይኸውም ሙሉና ፍጹም የሆነው መልስ እውን የሆነው "በመልካሙ እረኛ" አገልግሎት ነው (ዮሐ10፥11፡14)።

*መዝሙር 29፤* ግርማ ሞገሱና ኀይሉ እንደ ነጐድጓድና እንደ ማዕበል የሚያስገመግመውን የፍጥረታትን ንጉሥ ለማመስገን የቀረበ መዝሙር ነው። ከሜድትራኒያን ባሕር ላይ እያገሳ የሚነሳው ማዕበል ("ኀያላን ውሆች" ቍ3) የሊባኖስን ዝግባዎች እንደሚሰባብርና (ቍ5-6 ይመ) የቃዴስንም በረሓ እንደሚያርበደብድ ሁሉ (የቃዴስ በረሓ በኦሮንቴስ ወንዝ የላይኛው ጫፍ በስተ ሰሜን የሚገኝ በረሓ ነው፤ ቍ8) የእግዚአብሔርም ግርማ ሞገስ እንዲሁ ያርበደብዳል። የእግዚአብሔር ክብር ጉልህ ሆኖ የሚታየው በፍጥረታት ብቻ ሳይሆን (19፥1-6፤ 104 እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች) ፍጥረታትም በሚያሰሙት አስፈሪ ድምፅ ጭምር ነው። ይህ ለያህዌ ("እግዚአብሔር") የቀረበው መዝሙር፣ በዐል የተባለው የከነዓናውያን አምላክ የሚኖረውም በነጐድጓድ ውስጥ ነው ተብሎ የሚታመነው ይህ መለኮታዊ ኀይል መመለክ እንደሌለበት ያስገነዝባል። የመዝሙሩ ድምድማት (ይኸውም "ሁሉም በቤተ መቅደሱ" 'ይከበር!' የሚለው) እንደ ሚያመለክተው ይህ መዝሙር አሁን ባለበት ቦታ ወይም አቀማመጥ የመዝ23-28 ማጠቃለያ ወይም መደምደሚያ በመሆን ያገለግላል (የመዝ26 እና 28 መግቢያን ይመ)። ባወቃቀር ረገድ ደግሞ በመዝሙሩ መግቢያ ላይ ያሉት ሁለት ስንኞችና በመደምደሚያው ላይ ያሉት ሁለት ስንኞች በውስጣቸው ሰባት ስንኞችን ዐቅፈዋል። በመግቢያውና በመደምደሚያው ላይ ብቻ ያህዌ ("እግዚአብሔር") የሚለው ቃል አራት ጊዜ ያህል የተጠቀሰ ሲሆን በመካከል ላይ ባሉት በሰባቱ ስንኞች ላይ ደግሞ ዐሥር ጊዜ ያህል ተጠቅሶአል። "የእግዚአብሔር ድምፅ" የሚለው ሐረግ ደግሞ ሰባት ጊዜ ያህል ተጠቅሶአል (በብሉይ ኪዳን ውስጥ አራት፣ ሰባትና ዐሥር ቍጥሮች ሙሉነትን ያመለክታሉ)።

*29፥1-2፤* በእግዚአብሔር ግዛት ውስጥ የሚገኙ ሁሉ (የቍ1 ማብ ይመ) ጌታን ያመሰግኑ ዘንድ የቀረበ ጥሪ ሲሆን በቤተ መቅደሱ ውስጥ ከሚደረገው የቅዳሴና የጥሪ ሥርዐት የተወረሰ ነው (96፥7-9፤ 1ዜና16፥28-29 ይመ)።

## መዝሙር 29

### ለግዕበሉ ጌታ የቀረበ ውዳሴ

የዳዊት መዝሙር

[1]እናንተ ኀያላን፣ ለእግዚአብሔር ስጡ፤
ክብርንና ብርታትን ለእግዚአብሔር
ስጡ።
[2]ለስሙ የሚገባ ክብር ለእግዚአብሔር
ስጡ፤
በቅድስናው ግርማ ለእግዚአብሔር
ስገዱ።

[3]የእግዚአብሔር ድምፅ በውሆች ላይ ነው፤
የክብር ስምላክ አንጐደጐደ፤
እግዚአብሔር በታላላቅ ውሆች ላይ
አንጐደጐደ።

[4]የእግዚአብሔር ድምፅ ኀያል ነው፤
የእግዚአብሔር ድምፅ ግርማዊ ነው።
[5]የእግዚአብሔር ድምፅ ዝግባን ይሰብራል፤
እግዚአብሔር የሊባኖስን ዝግባ
ይሰባብራል።
[6]ሊባኖስን እንደ ጥጃ፣
ስርዮንንም[+] እንደ አውራሪስ ግልገል
ያዘልላል።
[7]የእግዚአብሔር ድምፅ
የእሳት ነበልባል ይረጫል።
[8]የእግዚአብሔር ድምፅ ምድረ በዳውን
ያናውጣል፤
የእግዚአብሔር ድምፅ የቃዴስን
ምድረ በዳ ያናውጣል።
[9]የእግዚአብሔር ድምፅ ወርካዎችን
ይወዘውዛል፤[‡]
ጫካዎችንም ይመነጥራል፤
ሁሉም በእርሱ ቤተ መቅደስ ሆኖ
"ይክበር!" ይላል።

[10]እግዚአብሔር በጐርፍ ላይ ዙፋኑን
ዘርግቶ ተቀምጦአል፤[↑]
እግዚአብሔር በንጉሥነቱ ለዘላለም
በዙፋኑ ላይ ይቀመጣል።
[11]እግዚአብሔር ለሕዝቡ ብርታትን
ይሰጣል፤
እግዚአብሔር ሕዝቡን በሰላም ይባርካል።

## መዝሙር 30

### ከክፉ አደጋ የዳነ ሰው ምስጋና

ለቤተ መቅደሱ ምረቃ የተዘመረ፤ የዳዊት መዝሙር

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ ከታች
አንሥተኸኛልና፣
ጠላቶቼም በላዬ እንዳይደሰቱ
አድርገሃልና፣

+6 አርሞንዔም የተባለው ተራራ ነው።
‡9 ወይም እግዚአብሔር ሊጋዞን እንድትወልድ ያደርጋል
↑10 ወይም ይቀመጣል

29፥1 ቍ2፥2ሳሙ1፥19፤2ዜና16፥28፤መዝ8፥1፤103፥20፤ኢሳ10፥13
29፥2 1ዜና16፥29፤መዝ96፥7-9
29፥3 ዘፀ15፥10፤1ሳሙ2፥10፤ኢዮ37፥5፤መዝ18፥13፤24፥7፤46፥6፤68፥33፤77፥17፤ኤር10፥13፤25፥30፤ኢል2፥11፤አሞ1፥2፤ሐሥ7፥2
29፥4 መዝ68፥33
29፥5 መሳ9፥15
29፥6 ዘኍ23፥22፤ዘዳ3፥9፤ኢዮ39፥9፤መዝ92፥10፤114፥4
29፥7 ሕዝ1፥14፤ራእ8፥5
29፥8 ዘኍ13፥26፤20፥1
29፥9 ዘኍ13፥32፤መዝ26፥8፤ኢሳ2፥13፤ሕዝ27፥6፤አሞ2፥9
29፥10 ዘፍ6፥17፤ዘፀ15፥18
29፥11 ዘሌ26፥6፤ዘኍ6፥26፤መዝ18፥1፤28፥8፤68፥35
30፥1 ዘፀ15፥2፤ኢዮ11፥8፤መዝ22፥17፤63፥9፤107፥26፤ምሳ9፥18፤ኢሳ14፥15

29፥1 *እናንተ ኀያላን፤* ቃል በቃል ሲተረጉም፣ "የአማልክት ልጆች" ማለት ነው፤ ምናልባት የመላእክትን ሰራዊት (103፥20፤ 148፥2፤ ኢዮ1፥6፤ ኢሳ6፥2 ይመ) ሊያመለክት ይችላል፤ ወይም ደግሞ በመዝ97 ላይ እንደሚታየው እኛም አማልክት ነን (ቍ7) የሚሉትን ሊያመለክት ይችላል፤ መዝ 97 ከዚህ መዝሙር ዐቢይ ሐሳብ ጋር በብዙ መንገድ ይመሳሰላል። እግዚአብሔር ብቻ መለኮታዊ ንጉሥ እንደ ሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል።

29፥2 *ለስሙ፤* የ5፥11 ማብ ይመ። *በቅድስናው ግርማ፤* ከአንድ አስቸጋሪ የዕብራይስጥ ሐረግ ቃል በቃል የተተረጐመ ሐረግ ነው፤ ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ራሱን እግዚአብሔርን ወይም ቤተ መቅደሱን ወይም ለአምልኮ የሚመጡት ምእመናን ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡ የሚለብሱትን የተለየ ልብስ ለመሆኑ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። በመዝ110፥3 ላይ የሚነበበው ተመሳሳይ የዕብራይስጥ ሐረግ የመጨረሻውን ትርጒም የሚደግፍ ይመስላል።

*29፥3-9፤* ድምፁ እንደሚያነካከት ነጐድጓድ ለሆነው ጌታ የቀረበ ምስጋና ነው (68፥4፡33 ይመ)። ከፍጥረታት ውስጥ እያስገመገመ የሚወጣው ኀይልና አስፈሪ ድምፅ የእስራኤልን አምላክ ክብር ያውጃል።

29፥5 *የሊባኖስን ዝግባ፤* ከዛፎች ሁሉ እጅግ ኀያላን ዛፎች ናቸው (ኢሳ2፥13 እና ማብ ይመ)።

29፥6 *ያዘልላል፤* 114 እና ማብ ይመ።

29፥9 *በእርሱ ቤተ መቅደስ፤* ይህ ቃል መዝ23-28 ያለውን ክፍል በጥብቅ የሚያስተሳስር ዐቢይ ቃል ነው። ቃሉም በኢየሩሳሌም ያለው ቤተ መቅደስ ወይም የፍጥረታት ሁሉ ጌታ የሆነው እግዚአብሔር በክብር የተቀመጠበትን ሰማያዊ ቤተ መቅደሱን ሊያመለክት ይችላል (2፥4፤ 11፥4፤ 113፥5፤ ኢሳ6፥1፤ 40፥22 ይመ)። ምናልባት ግን በዚህ ቦታ ቤተ መቅደስ ሲባል ተፈጥሮን ራሷን ማለት ሊሆን ይችላል (የ24፥2 ማብ ይመ)። ከዚህ በኋላ "ሁሉም" ("ክብር" እያሉ የሚጮኹት) ማለትም ፍጥረታት ሁሉ ከፍ ባለ ድምፅ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ። *ይክበር፤* የ26፥8 ማብ ይመ።

*29፥10-11፤* ፍጹምና ዘላለማዊ የሆነው የጌታ አገዛዝ፣ የእርሱ ለሆኑት ሕዝቦች ድነትንና ፍጹም በረከትን ለመስጠት የቆመ ነው። ይህም ያሸብር ሞገድና ማዕበል ሁሉን ነገር በሚያንቀጠቅጥበት ዓለም ውስጥ ወደር የማይገኝለት ማጽናኛ ነው።

29፥10 *በጐርፍ፤* "ጥልቅ" ከሆነውና ቅርጽም ከሌለው ነገር (ዘፍ1፥2፡6-10) ውስጥ በቃሉ ሥርዐት ያለውን ዓለም ያጸናውን ጌታ ወይም በኖኅ ዘመን የነበረውን የጥፋት ውሃ ሊያመለክት ይችላል።

*መዝሙር 30፤* ጌታ ከሞት ፍርሃት ሕዝቡን ስላዳነ ለስሙ የቀረበ የምስጋና ዝማሬ ነው፤ ምናልባት ይህ የሞት ፍርሃት የመጣው በሕመም ምክንያት ሊሆን ይችላል (በቍ7 ላይ "አንተም ፈወስከኝ" ይላልና፤ የቍ7፥17 ማብ ይመ)። ይህ መዝሙር በምስጋና ተስፋ የተቀነበበ ወይም የተከበበ ነው (መዝ1፥12 ይመ)።

30ርእስ *ዝማሬ፤* የመዝ18፤ 45-46፤ 48፤ 65-68፤ 75-76፤ 83፤ 87-88፤ 92፤ 108 ርእስን ይመ። ከመዝ 83 እና 88 በስተቀር ሁሉም የምስጋና መዝሙሮች ናቸው። በተጨማሪም "ከክፉ ነገር ውስጥ ለመውጣት" የሚቀርቡ መዝሙሮችም አሉ (መዝ 120-134)። *ለቤተ መቅደሱ ምረቃ የተዘመረ፤ የዳዊት መዝሙር፤* "የዳዊት" የሚለው ቃል የዚህ መዝሙር ጸሓፊ ዳዊት መሆኑን የሚያመለክት ከሆነ መዝሙሩ መቼ እንደ ተጻፈ ፍንጭ ሊሰጠን የሚችል ሐሳብ በ1ዜና21፥1-22፥6 ላይ ተጽፎ ይገኛል። በ1ዜና22፥1-6 ላይ ዳዊት ለቤተ መቅደሱ መሥሪያ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ዕቃዎችን እንዳዘጋጀ ተመልክቶአል፤ ስለዚህ መዝሙር 30 ቤተ መቅደሱ በሚመረቅበት ወቅት እንዲዘመር የታሰበ ሳይሆን አይቀርም። ይህ ከሆነ ደግሞ፣ ቍ2-3 ዳዊት ያለበትን አስከፊ ሁናቴና በ1ዜና21፥17-30 ላይም የተገለጸውን ሁናቴ ሊያመለክት ይችላል። በቍ5 ላይ "ቸርነቱ" የሚለው ቃል በ1ዜና21፥13 ላይ የተጠቀሰውን "ምሕረት" የሚለው ቃል ሐሳብ እንደ ገና መልሶ ያስተጋባል፤ ከጊዜ በኋላ ይህ መዝሙር የእስራኤልን የግዞት ተመክሮ (ልምድ) ለመግለጽ ያገለግል ጀመር። መዝሙሩ ከታልሙድ ዘመን ጀምሮ በአይሁዶች የቅዳሴ ሥርዐት ውስጥና ሃኑካ በተባለው ክብረ በዓል ላይ ማኀሌት በሚቆምበት ወቅት የሚዘመር ነው፤ የሃኑካ ክብረ በዓል መከበር የጀመረው አንጥያኮስ ኤጲፋኔዎስ (168) ቤተ መቅደሱን ካረከሰውና ይሁዳ መቃቢስ ደግሞ (168 ዓ.ቅ.ክ.) ቤተ መቅደሱን እንደ ገና አስተካክሎና መርቆ ከከፈተ በኋላ ነው። በዚህ መዝሙር ላይ "እኔ" የሚለው አንደኛ መደብ ተውላጠ ስም የሚያመለክተው አጠቃላዩን የእስራኤልን ሕዝብ ሲሆን እንዲህ ያለው አባባል በብሉይ ኪዳን ዘመን የተለመደ አገላለጽ ነው።

*30፥1-3፤* በምስጋና ጊዜ የቀረበ የመግቢያ አዋጅ ነው።

30፥1 *ከታች፤* አሳዛኝ ሁናቴን "ከጥልቁ" ጋር አያይዞ ማቅረብ በብሉይ ኪዳን ሥነ ግጥም ውስጥ በጣም የተለመደ ነው፤ እንዲህ ያለው አገላለጽ የሰው ልጆችን አስከፊ ኑሮ ምስላዊ

ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ።
2 *እግዚአብሔር* ስምላኬ ሆይ፤ ትረዳኝ
ዘንድ ወደ አንተ ጮኽሁ፤
አንተም ፈወስኸኝ።
3 *እግዚአብሔር* ሆይ ነፍሴን ከሲኦል[ነ]
አወጣሃት፤
ወደ ጒድጓድ ከመውረድም መልሰህ
ሕያው አደረግኸኝ።

4 እናንተ ቅዱሳኑ፤ ለ*እግዚአብሔር* ዘምሩ፤
ቅዱስ ስሙንም አወድሱ።
5 ቍጣው ለአጭር ጊዜ ነው፤
ቸርነቱ ግን እስከ ዕድሜ ልክ ነውና፤
ሌሊቱን በልቅሶ ቢታደርም፣
በማለዳ ደስታ ይመጣል።

6 እኔም በተረጋጋሁ ጊዜ፣
"ከቶ አልናወጥም" አልሁ።
7 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ በአንተ ሞገስ፣
ተራሮቼ[ጎ] ጸኑ፣
ፊትህን በሰወርህ ጊዜ ግን፣
ውስጤ ታወከ።

8 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ወደ አንተ ተጣራሁ፤
ወደ ጌታም እንዲህ ብዬ ጮኽሁ፤
9 "በእኔ ወደ ጒድጓድ መውረድ፣
በመሞቴ ምን ጥቅም ይገኛል?[ኦ]
ዐፈር ያመሰግንሃልን?
ታማኝነትህንስ ይናገራልን?
10 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ስማ፤ ማረኝም፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ረዳት ሁነኝ።"
11 ዋይታዬን ወደ ሽብሸባ ለወጥህልኝ፤
ማቄን አውልቀህ፣ ፍስሓን አለበስኸኝ፤
12 እንግዲህ፣ ነፍሴ ታመሰግንህ፤ ዝምም
አትበል፤
*እግዚአብሔር* ስምላኬ ሆይ፤ ለዘላለም
አመሰግንሃለሁ።

## መዝሙር 31

### የመከራ ጊዜ ጸሎት

31፥1-4 ተጓ ምብ-መዝ71፥1-3

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ በአንተ ተተግኛለሁ፤
እንግዲህ እፍረት ከቶ አይድረስብኝ፤
በጽድቅህም ታደገኝ።
2 ጆሮህን ወደ እኔ መልሰህ ስማኝ፤
ፈጥነህ አድነኝ፤
መጠጊያ ዐለት ሁነኝ፤
ታድነኝም ዘንድ ምሽግ ሁነኝ።
3 አንተ ዐለቴና መጠጊያዬ ነህና፣
ስለ ስምህ ስትል ምራኝ፤

[ነ]3 ወይም *ከመቃብር* [ጎ]7 ወይም *ኰረብታማ የሆነች አገሬ*
[ኦ]9 ወይም *ዝም ብል ... ይገኛል?*

30፥2 ዘኍ12፥13፤ መዝ5፥2፤88፥13
30፥3 መዝ16፥10፤ 28፥1፤55፥23፤56፥13፤69፥15፤86፥13፤143፥7፤ምሳ1፥12፤ኢሳ 38፥17፤ዮና2፥6
30፥4 ዘፀ3፥15፤መዝ 16፥3፤33፥1፡21፤47፥7፤68፥4፤103፥1፤145፥21
30፥5 2ሳሙ15፥30፤ዕዝ3፥11፤ኢዮ14፥13፤መዝ6፥6፤103፥9፤12 6፥6፤ኤር31፥16፤2 ቆሮ 4፥17
30፥6 ኢዮ29፥18
30፥7 ዘዳ31፥17
30፥9 ኢዮ33፥18፤ መዝ6፥5፤88፥11፤ኢሳ 38፥18
30፥10 መዝ4፥1፤17፥1፤20፥2
30፥11 ዘፀ15፥20፤ ዘዳ16፥15፤2ሳሙ3፥3 1፤አስ4፥1፤መዝ16፥9፤ 35፥13
30፥12 መዝ35፥18፤ 44፥8፤52፥9፤75፥1፤1 18፥21፤ራእ11፥17
31፥1 መዝ5፥8፤7፥1
31፥2 ዘፀ2፥17፤2ሳሙ 22፥3፤መዝ6፥4፤18፥2
31፥3 መዝ18፥2፤ 23፥3

በሆነ መንገድ የሚያቀርብ ነው (69፥2፡15፤ 71፥20፤ 88፥6፤ 130፥1፤ ሰቆ3፥55፤ ዮና2፥2 ይመ)። በዚህ ቦታ እንደሚታየው ሁሉ ከጥልቁ የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ ከሲኦልና ("መቃብር" ቍ3) "ከጒድጓድ" (ቍ3)፣ እንዲሁም ከዚሁ ሐሳብ ጋር ትስስር ካላቸው ከሌሎች ቃላት ጋር የተያያዘ ነው፤ ለምሳሌ ይህ ቃል ከዝምታ (31፥17፤94፥17፤ 115፥17፤ 1ሳሙ2፥9 ይመ)፣ ከጨለማ (88፥6፡12፤ 143፥3፤ ኢዮ10፥21-22፤ 17፥13፤ መክ6፥4፤ ሰቆ3፥6 ይመ)፣ ከጥፋት (ቍ9፤ 18፥4፤ 55፥23፤ "ከብስባሴ" ወይም "ከብልሹነት" 88፥11፤ ኢሳ38፥17፤ ሆሴ13፥14 ይመ)፣ ከትቢያ (ቍ9፤ 7፥5፤ 22፥15፥29፤ ኢዮ17፥16፤ 40፥13፤ ኢሳ26፥19፤ 29፥1 ይመ)፣ ከጒድጓድ (40፥2፤ 69፥2፡14 ይመ)፣ ከረግረግና (40፥2 ይመ)፣ ከጭቃ (40፥2፤ ኢዮ30፥19 ይመ) ተዛማጅ ትርጒም አለው፤ እንዲሁም የ49፥14 ማብ ይመ። *ጠላቶቼም በላዬ እንዳይደሰቱ፤* የመዝ6 ማብ ይመ።

30፥3 *ከሲኦል፤* "በሞት አፋፍ" ለሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ወይም ዘይቤአዊ አገላለጽ ነው፤ ይኸውም በ18፥5 እና በዮና 2፥2 ላይ እንደ ተመለከተው ዐይነት ነው። *ጒድጓድ፤* የ28፥1 ማብ ይመ።

*30፥4-5፤* ለአምልኮ የተሰበሰቡት ምእመናን እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ዘንድ የቀረበ ማሳሰቢያ ነው (የ9፥11 ማብ ይመ)።

30፥4 *ቅዱሳኑ፤* የ4፥3 ማብ ይመ። *ስሙንም፤* ቃል በቃል ሲተረጐም መታሰቢያውን ማለት ነው (ኢሳ26፥8፤ ሆሴ12፥5 ይመ)።

30፥5 *ቍጣው፤* የ2፥5 ማብ ይመ። *ለአጭር ጊዜ፤* ኢሳ 54፥7 ይመ። *ሌሊቱን፤* በቀጥታ ሲተረጐም፣ "አንድ ሌሊት ለማደር መጣ" ማለት ሲሆን ምሳሌውም አንድ ሌሊትን ለማሳለፍ የመጣ እንግዳን ያመለክታል።

*30፥6-10፤* የጌታን ታዳጊነት ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚያሳስብ ነው።

*30፥6-7፤* ምንም እንደማይሆን ባወቀ ጊዜ "እንደ ተራራ ያጸናው" ማን እንደ ሆነ ረሳ፤ ጌታ ግን ለዚህ ያበቃው ማን እንደ ሆነ አስታወሰው።

30፥6 *ከቶ አልናወጥም፤* ክፉዎች እንደሚናገሩት እርሱም ተናገረ (10፥6 ይመ)፤ ከዚህም የተነሣ የጻድቅን በረከት ሳያገኝ ቀረ (15፥5 ይመ)። *አልናወጥም፤* የ10፥6 ማብ ይመ።

30፥7 *ተራሮቼ ጸኑ፤* ይህ አባባል የሚያመለክተው ዳዊት እንደ ምሽግ ያደረገውን የጽዮንን ተራራ ወይም ደግሞ በዚህ ቦታ ዳዊት እንደ ምሽግ ያደረገው ተራራ ብርቱና ድል አድራጊ ንጉሥ መሆኑን ተምሳሌታዊ በሆነ መንገድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። *ፊትህን በሰወርህ ጊዜ፤* የ13፥1 ማብ ይመ።

*30፥8-10፤* እንኩትኩት ያለ አቅም በራስ የመተማመንን ስሜት ሁሉ እንዳልነበረ ያደርጋል፤ በመሆኑም በሞት አፋፍ ላይ ሲደርስ የእግዚአብሔር ምሕረት ከወደቀበት ማጥ ሊያወጣው ተገለጠ።

*30፥9፤* የ6፥5 ማብ ይመ። *ታማኝነትህንስ፤* ቃል ኪዳንህን ማለት ነው።

*30፥11-12፤* እግዚአብሔር ጩኸቱን ስለሰማና ጸሎቱንም ስለመለሰለት፣ ዳዊት እስከ ዘላለም ድረስ ምስጋናን ለማቅረብ ቃል ገባ (የ7፥17 ማብ ይመ)፤ *ዋይታዬን ... ለወጥህልኝ፤* ይህም የሆነው የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ዝምታ ሳይሆን የምስጋና መዝሙር እንዲያጅበው ነው።

30፥11 *ማቄን፤* የሐዘን ምልክት ነው (35፥13፤ ዘፍ37፥34 ይመ)።

30፥12 *ነፍሴ፤* በቀጥታ ሲተረጐም "ክብሬ" እንደ ማለት ነው (የ7፥5 ማብ ይመ)።

*መዝሙር31፤* ብዙዎች ሴራ በመቱበትና በዶለቱበት ጊዜ፣ እንዲሁም አሉኝ የሚላቸው ወዳጆቹ ሁሉ የት እንዳለ እንኳ በረሱት ጊዜ እግዚአብሔር ከዚህ ሁሉ እንዲታደገው መዝሙረኛው ያቀረበው ጸሎት ነው። ከሉቃ 23፥46 እንደምንረዳው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በነበረበት ጊዜ መዝ31፥5 ከእርሱ ሁኔታ ጋር አዛምዶ ተናግሮታል። ስለዚህ ከክርስትና እምነት ተቃዋሚ ኀይሎች እጅ መከራን የሚቀበሉና የኢየሱስም መከራ ተካፋይ የሚሆኑ ሁሉ በዚህ መዝሙር ሊጽናኑና መዝሙሩንም በአዲስ እይታ ሊመለከቱት ይገባል (ሐሥ7፥59፤ 1ጴጥ4፥19 ይመ)። ክፉና አስጨናቂ ኀይሎች በተነሡ ጊዜ በጌታ ላይ በጽኑ መታመን አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳስብ እንደዚህም መዝሙር አይገኝም። የጸሎቱ ጭብጥ ወይም ፍሬ ነገር የሚገኘው በቍ9-18 ላይ ሲሆን ከላይና ከታች ባሉ ስምንት የዕብራይስጥ ስንኞችም ተከብበዋል (ተካበው ተቀምቅመዋል)። እነዚህ ስንኞች ደጋግመው የሚያወሡት በጌታ መታመን ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን ነው (ቍ14)። ቍ13 በመካከል ላይ ሆኖ፣ ጸሎቱ የቀረበበትን ሁኔታ በግልጽ ይጠቁማል።

31ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 የርእስ ማብ ይመ።

*31፥1-5፤* ታማኝ መጠጊያ ለሆነው ለጌታ ገና ከመግቢያው ላይ የቀረበ ምልጃ ነው።

31፥1 *በጽድቅህም፤* የ4፥1 ማብ ይመ።

31፥2 *መጠጊያ ዐለት፤* የ18፥2 ማብ ይመ።

31፥3 *ስለ ስምህ ስትል፤* የአገልጋዩ ሕይወት በአሥጊ ሁኔታ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የእግዚአብሔር ክብር በሰው ዘንድ

መንገዱንም ጠቍመኝ፡፡
4አንተ መጠጊያዬ ነህና፤
በስውር ከተዘረጋብኝ ወጥመድ
አውጣኝ፡፡
5መንፈሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ፤
እግዚአብሔር የእውነት ስምላክ ሆይ፤
አንተ ተቤዠኝ፡፡
6ለከንቱ ጣዖታት ስፍራ የሚሰጡትን
ጠላሁ፤
ነገር ግን በእግዚአብሔር ታመንሁ፡፡
7በምሕረትህ ደስ እሰኛለሁ፤ ሐሤትም
አደርጋለሁ፤
መከራዬን አይተሃልና፤
የነፍሴንም ጭንቀት ዐውቀሃል፡፡
8ለጠላት አሳልፈህ አልሰጠኸኝም፤
ነገር ግን እግሮቼን ሰፊ ቦታ ላይ
አቆምሃቸው፡፡

9እግዚአብሔር ሆይ፤ በመከራ ውስጥ ነኝና
ማረኝ፤
ዐይኖቼ በሐዘን ደክመዋል፤
ነፍስና ሥጋዬም ዝለዋል፡፡
10ሕይወቴ በመጨነቅ፤
ዕድሜዬም በመቃተት አለቀ፤
ከመከራዬ[ሀ] የተነሣ ጕልበት ከዳኝ፤
ዐጥንቴም በውስጤ ሟሟ፡፡
11ከጠላቶቼ ሁሉ የተነሣ፤
ለጎረቤቶቼ መዘባበቻ፤
ለወዳጆቼ መሳለቂያ ሆኛለሁ፤
መንገድ ላይ የሚያገኙኝም ይሸሹኛል፡፡
12እንደ ሞተ ሰው ተረሳሁ፤
እንደ ተሰበረ የሸክላ ዕቃም ተቈጠርሁ፡፡
13የብዙ ሰዎችን ሹክሹክታ እሰማለሁና፤
ዙሪያው ሁሉ ሽብር አለ፤
በእኔ ላይ ባሤሩ ጊዜ፤
ሕይወቴን ለማጥፋት ዶለቱ፡፡

14እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔ ግን በአንተ
እታመናለሁ፤
"አንተ ስምላኬ ነህ" እልሃለሁም፡፡
15ዘመኔ ያለው በእጅህ ነው፤
ከጠላቶቼ እጅ ታደገኝ፤
ከሚያሳድዱኝም አድነኝ፡፡
16ፊትህን በአገልጋይህ ላይ አብራ፤
በምሕረትህም አድነኝ፡፡
17እግዚአብሔር ሆይ፤
ወደ አንተ እጮኻለሁና አልፈር፤
ክፉዎች ግን ይፈሩ፤
ሲኦል[ለ] ገብተውም ጸጥ ይበሉ፡፡
18በጻድቁ ላይ በእብሪት የሚናገሩ፤
ትዕቢትንና ንቀትን የተሞሉ፤
ዋሾ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ፡፡

19በሰዎች ልጆች ፊት፤
ለሚፈሩህ ያስቀመጥሃት፤
መጠጊያ ላደረጉህም ያዘጋጀሃት፤
በጎነትህ ምንኛ በዛች!
20ከሰዎች ሤራ፤
በማደሪያህ ውስጥ ትሸሽጋቸዋለህ፤
ከአንደበት ጭቅጭቅም፤
በድንኳንህ ውስጥ ትከልላቸዋለህ፡፡

31፥4 1ሳሙ28፥9፤ኢዮ18፥10፤መዝ9፥9
31፥5 ኢሳ45፥19፤65፥16፤ሉቃ23፥46፤ሐሥ7፥59
31፥6 ዘዳ32፥21፤መዝ4፥5
31፥7 መዝ13፥3፤25፥17፤ሉቃ22፥44
31፥8 ዘዳ32፥30፤2ሳሙ22፥20
31፥9 መዝ4፥1፤6፥7፤63፥1
31፥10 ቍ7፤መዝ6፥2፡6፤22፥15፤25፥18፤32፥4፤38፥10፤73፥6
31፥11 ዘዳ30፥7፤መዝ3፥7፤22፥6፤25፥19፤38፥11፤102፥8
31፥12 መዝ28፥1፤88፥4
31፥13 ዘፍ37፥18፤ዘሌ19፥16፤ኢዮ18፥11፤መዝ41፥7፤50፥20፤56፥6፤71፥10፤83፥3፤ኢሳ13፥8፤ኤር6፥25፤20፥3፡10፤46፥5፤49፥5፤ሰቆ2፥22፤ማቴ12፥14
31፥14 መዝ4፥5
31፥15 ኢዮ14፥5
31፥16 ዘኍ6፥25፤መዝ6፥4
31፥17 1ሳሙ2፥9፤መዝ22፥5፤94፥17፤115፥17
31፥18 1ሳሙ2፥3፤መዝ120፥2፤ምሳ10፥18፤26፥24፤ይሁ1፥15
31፥19 መዝ2፥12፤23፥5፤27፥13፤ሮሜ11፥22
31፥20 ዘፍ37፥18፤መዝ17፥8፤55፥8

[ሀ]10 ወይም *ከበደሌ* [ለ]17 ወይም *መቃብር*

እየደበዘዘ ነው (የ23፥2 ማብ ይመ)፡፡ *ስም፤* የ5፥11 ማብ ይመ፡፡ *መንገዱን ጠቍመኝ፤* መልካም የበግ እረኛ በጎቹን እንደሚንከባከበው ዐይነት ማለት ነው (23፥2-3 እና ማብ ይመ)፡፡

31፥4 *ከተዘረጋብኝ ወጥመድ አውጣኝ፤* ይህን ያደረጉበት ጠላቶቹ ናቸው (ቍ11 ይመ)፡፡

31፥5 *መንፈሴን በእጅህ ዐደራ እሰጣለሁ፤* በእግዚአብሔር ላይ በጽኑ መታመንን የሚገልጽ የመጨረሻ ትልቅ አባባል ነው፤ በሉቃ23፥46 ላይ ኢየሱስ ይህንን ቃል ጠቅሶታል፡፡ *እሰጣለሁ፤* በቀጥታ ሲተረጕም "እኖራለሁ" ማለት ሲሆን (ይኸውም በኤር36፥20 ላይ "አኑረውት" ነበር እንደ ተባለው ዐይነት ነው)፤ በዚህ ቦታ ይህ አባባል የሚያመለክተው ሁለንተናን በእግዚአብሔር እጅ ላይ ማኖርንና ለእርሱም አደራን መስጠትን ነው (ዘሌ6፥4፤ 1ነገ14፥27 ይመ)፡፡ *መንፈሴን፤* ነፍሱን ማለት ነው፡፡ *ተቤዠኝ፤* የ25፥22 ማብ ይመ፡፡ *የእውነት አምላክ፤* ታማኝ (ይከዳል ተብሎ የማይጠረጠር) አምላክ ማለት ነው (የ30፥9 ማብ ይመ)፡፡

*31፥6-8፤* ዳዊት የጠላቶቹ ዛቻ ባስጨነቀው ጊዜ እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ያደረገለትን ምሕረት በማስታወስ አሁንም በእግዚአብሔር የሚታመን መሆኑን በሐሤት ይናገራል፡፡

31፥6 *ጠላሁ፤* ከሌሎች ጋር መተባበርን አልፈለገም፡፡

31፥7 *በምሕረትህ፤* ቍ16፥21፤ እንዲሁም የ6፥4 ማብ ይመ፡፡ *የነፍሴንም፤* የ6፥3 ማብ ይመ፡፡

31፥8 *ሰፊ ቦታ፤* የ18፥19 ማብ ይመ፡፡

*31፥9-13፤* ምን ያህል እንደ ተጨነቀ የሚያሳይ ክፍል ነው፤ ከመከራው ብዛት የተነሣም በአካልና በመንፈስ ክፉኛ ላሽቆአል (ቍ9-10፤ እንዲሁም 22፥14-15 ይመ)፤ ወዳጆቹ ሁሉ ተሰባብሮ እንደደቀቀ የሸክላ ዕቃ ጥለውታል (ቍ11-12 ይመ)፤ ይህም ሁሉ የሆነው በእርሱ ላይ የተጠነሰሰው ሤራ ጠንካራ በመሆኑ ነው (ቍ13)፡፡

31፥9 *ዐይኖቼ በሐዘን ደክመዋል፤* የ13፥3 ማብ ይመ፡፡ *ነፍስ፤* የ6፥3 ማብ ይመ፡፡

31፥10 *ዐጥንቴም፤* የ6፥2 ማብ ይመ፡፡

*31፥11-12፤* እግዚአብሔር ፊቱን ያዞረ በሚመስልበት ጊዜ በወዳጆች መረሳትና መጣል ያለና የተለመደ ነው (38፥11፤ 41፥9፤ 69፥8፤ 88፥8፡18፤ ኢዮ19፥13-19፤ ኤር12፥6፤ 15፥17 ይመ)፡፡

31፥13 *ስድብ፤* የ5፥9 ማብ ይመ፡፡ *ዙሪያውን ሁሉ ሽብር፤* የኤር6፥25 እና 20፥3 ማብ ይመ፡፡

*31፥14-18፤* በጌታ ላይ ያለው እምነት የሚናወጥ አይደለም፤ ብርቱና ኀያል የሆነ ጠላቶቹን መቋቋም የቻለው እግዚአብሔር ታማኝና ቅን ፈራጅ በመሆኑ ነው፡፡

*31፥14፤* ከቍ22 ጋር ያነጻጽሩ፡፡

31፥15 *ዘመኔ ያለው በእጅህ ነው፤* በሕይወቴ ዘመን የሚገጥሙኝ ነገሮችና ሁኔታዎች ሁሉ "በአምላኬ" (ቍ14) እጅ ናቸው ማለት ነው፤ እንደ መዝሙረኛው አባባል ከአምላኩ ፈቃድ ውጪ የሚደርስበት ምንም ነገር የለም፡፡

31፥16 *ፊትህን ... አብራ፤* የ13፥1 ማብ ይመ፡፡

31፥17-18 *ክፉዎች ... ጸጥ ይበሉ፤* የ5፥10 ማብ ይመ፡፡

31፥18 *ዋሾ ከንፈሮች፤* የ5፥9 ማብ ይመ፡፡ *በጻድቁ፤* የ1፥5 ማብ ይመ፡፡

*31፥19-20፤* እግዚአብሔር ያዘጋጀውን በረከት እንደሚያገኝ ምንም ጥርጥር የለውም (የ3፥8 ማብ ይመ)፡፡

31፥19 *በሰዎች ልጆች ፊት፤* ከጠላቶቻቸው ክስ በተቃራኒው (86፥17 ይመ)፤ እግዚአብሔር በባሪያዎቹ አካሄድ የተደሰተና ጠበቃም ሆኖ የቆመላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ *ለሚፈሩህ፤* የ15፥4 ማብ ይመ፡፡ *ያስቀመጥሃት፤* ዳዊት፤ እግዚአብሔር ለታማኝ ባሪያዎቹ ያከማቸውን የኪዳኑን በረከት ለመካፈል ሕይወቱን በእግዚአብሔር እጅ ላይ አኖረ ("ቸርነትህ" ዘፀ18፥9፤ ዘኍ10፥29፡32፤ ዘዳ26፥11፤ ኢሱ21፥45፤ 23፥14-15፤ 2ዜና6፥41፤ ነህ9፥25፡35፤ ኢሳ63፥7፤ ኤር33፥9፤ እንዲሁም ኤር31፥12፡14 "በረከት" የሚለውን ይመ)፡፡

31፥20 *በማደሪያህ፤* የ27፥5 ማብ ይመ፡፡ *ከአንደበት ጭቅጭቅም፤* በቍ13 ላይ "ስድብ" እንዲሁም በቍ18 ላይ ደግሞ "የሚዋሹ ከንፈሮቻቸው" የሚለውን ይመ፡፡

21በተከበበች ከተማ ውስጥ፣
የሚያስደንቅ ምሕረቱን ያሳየኝ፣
እግዚአብሔር ይባረክ።
22እኔ በደነገጥሁ ጊዜ፣
"ከዐይንህ ፊት ተወግጃለሁ" አልሁ፤
አንተ ግን ወደ አንተ ስጮኽ፣
የልመናዬን ቃል ሰማህ።
23እናንተ ቅዱሳኑ ሁሉ፣ እግዚአብሔርን
ውደዱት!
እግዚአብሔር ታማኞችን ይጠብቃል፤
ትዕቢተኞችን ግን ፈጽሞ ይበቀላቸዋል።
24እግዚአብሔርን ተስፋ የምታደርጉ ሁሉ፤
በርቱ፤ ልባችሁም ይጽና።

## መዝሙር 32

**ግልጥ ኑዛዜ**

የዳዊት ትምህርት

1መተላለፉ ይቅር የተባለለት፣
ኀጢአቱም የተሸፈነለት፣
እንዴት ቡሩክ ነው!
2እግዚአብሔር ኀጢአቱን የማይቈጥርበት፣
በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው፣
እርሱ ቡሩክ ነው።
3ቀኑን ሙሉ ከመቃተቴ የተነሣ፣
ዝም ባልሁ ጊዜ፣
አጥንቶቼ ተበላሹ፤
4በቀንና በሌሊት፣
እጅህ ከብዳብኛለችና፤
ኀይሌም የበጋ ትኵሳት እንደሚያደርቀው ነገር፣
ከውስጤ ተሟጠጠ። ሴላ
5ኀጢአቴን ለአንተ አስታወቅሁ፤
በደሌንም አልሸሸግሁም፤
ደግሞም "መተላለፌን
ለእግዚአብሔር እናዘዛለሁ" አልሁ፤
አንተም የኀጢአቴን በደል፣
ይቅር አልህ። ሴላ
6ስለዚህ ጻድቅ ሁሉ፣
በጭንቅ ጊዜ ወደ አንተ ይጸልይ፤
ኀይለኛ ጐርፍ አካባቢውን ቢያጥለቀልቅም፣
እርሱ አጠገብ አይደርስም።

31፥21· 1ሳሙ23፥7 ፤መዝ17፥7፤28፥6
31፥22 ኢዮ6፥9፤ 17፥11፤መዝ6፥9፤37፥9 ፤66፥19፤88፥5፤116፥ 1:11፤145፥19፤ኢሳ 38፥12
31፥23 ዘጻ32፥41፤ መዝ4፥3፤18፥25፤94፥ 2፤ራእ2፥10
31፥24 መዝ27፥14
32፥1 መዝ85፥2 ፤103፥3
32፥2 ዮሐ1፥47 ፤ሮሜ4፥7-8፤ራእ 14፥5
32፥3 ኢዮ3፥24፤ 31፥34፤መዝ6፥6፤ 31፥10
32፥4 1ሳሙ5፥6፤ ኢዮ9፥34፤መዝ22፥15 ፤38፥2፤39፥10
32፥5 ዘሌ26፥40፤ ኢዮ31፥33፤መዝ103 ፥12፤ምሳ28፥13፤1 ዮሐ1፥9
32፥6 ዘፀ15፥10፤ መዝ69፥1:13፤ኢሳ 43፥2፤55፥6

*31፥21-22፤* የእግዚአብሔርን ትድግና ተስፋ በማድረግ የቀረበ ምስጋና ነው (የ12፥5-6 ማብ ይመ)።

31፥21 *በተከበበች ከተማ፤* የደረሰበትን አስጨናቂ ገጠመኝ የሚያሳይ ተምሳሌት ወይም ዘይቤአዊ አገላለጽ ነው።

31፥22 *ከ ... ፊት ተወግጃለሁ፤* የ13፥1 ማብ ይመ።

*31፥23-24፤* ምስጋና ቅዱሳንን ያጠነክራል፣ ያበረታታልም (62፥8 ይመ)።

31፥23 *ቅዱሳኑ፤* የ4፥3 ማብ ይመ። *ታማኞችን፤* በቅንነት ወይም በበጎ ምግባር ጸንተው የሚኖሩትን ማለት ነው። *ትዕቢተኞችን፤* በትሕትናና ራሳቸውንም ዝቅ ዝቅ በማድረግ በእግዚአብሔር ላይ ለመታመን እሻፈረኝ ያሉትን ማለት ነው፤ ንቀትና ትዕቢት የተሞላውን ልባቸውን የሕይወታቸው መመሪያ ለማድረግ የተነሡ (ለምሳሌም ቍ18፤ 10፥2-11፤ 73፥6፤ 94፥2-7፤ ዘዳ8፥14፤ ኢሳ2፥17፤ ሕዝ28፥25፤ ሆሴ13፥6 ይመ)፤ ወይም በባዕዳን አማልክት ላይ ለመታመን የሞከሩ ናቸው (ኤር13፥9-10 ይመ)፤ ከዚህም የተነሣ "ትዕቢተኞች" ሁልጊዜ "ከክፉዎች" ጋር አንድ ተደርገው ተቈጥረዋል።

*መዝሙር 32፤* ኀጢአታቸውን ከልብ የተናዘዙና የእግዚአብሔርንም ሕግና ሥርዐት ከልብ የተቀበሉ ሰዎች ለእግዚአብሔር የኀጢአት ይቅርታ ስጦታ ያቀረቡት ምስክርነት ነው። ይህ መዝሙር እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደ ቤተ መቅደስ በመጡ ሰዎች ፊት እግዚአብሔርና ዳዊት በቃል የተመላለሱትን የሚያስታውስ የቅዳሴ ሥርዐት ይመስላል። በቍ1-2 እንዲሁም በቍ 11 ላይ ዳዊት ለጉባኤው ይናገራል፤ በቍ3-7 ላይ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር (ጉባኤው ሁሉ እየሰማው) ይጸልያል፤ በቍ8-10 ላይ ከጌታ ካህናት አንዱ ሲናገረው ይታያል (የቍ8-10 ማብ ይመ)። ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ክርስቲያኖች ይህንን መዝሙር የሚመድቡት በችግርና በመከራ ጊዜ ከሚቀርቡ የልመና መዝሙሮች ተርታ ነው (የመዝ6 መግቢያን ይመ)።

32ርእስ *የዳዊት ትምህርት፤* በመዝ42፤ 44-45፤ 52-55፤ 74፤ 78፤ 88-89፤ 142 ርእሶችም ላይ የሚገኝ ቃል ነው። የዕብራይስጡ ቃል እንደሚያመለክተው እነዚህ መዝሙሮች በመልካም አኗኗር መዝለቅ አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳስቡ ሳይሆን አይቀርም (በ14፥2 እና በ53፥2 ላይ "የሚያስተውል" ወይም "የሚያስተውሉ" እንዲሁም በ41፥1 ላይ "የሚያስብ" የሚለውን ይመ)።

*32፥1-2፤* የእግዚአብሔርን ይቅርታ ወይም ምሕረት ያገኙ ሰዎች ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ያሰሙት ቃል ነው። *ቡርክ ነው.... ቡሩክ ነው፤* የ1፥1 ማብ ይመ፤ ድግግሞሹ አጽንኦት ለመስጠት ነው። *ይቅር የተባለለት ... የተሸፈነለት ... ኀጢአቱ የማይቈጠርበት፤* ተመሳሳይ ትርጕም ባላቸው ልዩ ልዩ ቃላት ሐሳብን መግለጽ ለነገሩ አጽንኦት ከመስጠቱም በላይ ሊባል የተፈለገውን ነገር ፈካ አድርጎ ያሳያል። ጳውሎስ ይህን ኀባብ በእንዴት ያለ መንገድ እንደ ተጠቀመበት ለማየት ሮሜ4፥6-8 ይመ።

32፥2 *በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት፤* ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ብቻ ናቸው ከእግዚአብሔር ይቅርታን ማግኘት የሚችሉት።

32፥3-4 *ዝም ባልሁ ጊዜ ዐጥንቶቼ ተበላሹ፤* እነዚህ ጥቅሶች የተደበቀ ኀጢአት የሚያደርሰውን ሥቃይና የሚያስከትለውንም ቅጣት ያመለክታሉ፤ ዳዊት ኀጢአቱን ለመደበቅና ለእግዚአብሔርም ለማሳየት ባልፈለገ ጊዜ፣ ለሕይወት እጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ማለትም ጤናን፣ የሕሊናንም ሰላም፣ ደስታንና በእግዚአብሔርም ፊት ያለውን ሞገስ ሁሉ አጣ። በዚህ ፈንታ ግን የእግዚአብሔር ቅጣት የሕሊና ወቀሳና የመንፈስ ጭንቀት አመጣበት።

32፥4 *ኀይሌ ... ትሟጠጠ፤* በእግዚአብሔር ከባድ እጅ ሥር ስለወደቀ፣ የበጋ ሐሩር እንዳደረቀው ተክል ሆነ።

32፥5 *ኀጢአቴን ... አስታወቅሁ፤* ኀጢአትን እውነተኛና ቅን በሆነ ልብ መናዘዝ ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ምሕረት ያስገኛል፤ እግዚአብሔርም በእንዲህ ዐይነት ልብ የሚቀርቡ ሰዎችን ኀጢአት ያስወግዳል፤ የእርሱም ማደሪያ ያደርጋቸዋል።

*32፥6-7፤* ሕይወት ዋስትና ያላት ከእግዚአብሔር የተነሣ ብቻ እንደ ሆነ የሚያሳስብ ነው።

*32፥6፤* ለእግዚአብሔር የቀረበ የኀጢአት ኑዛዜ ቢሆንም በኅብረት ለማምለክ የሚመጡ ሰዎችም እንዲሰሙት የታሰበ ነው። "እግዚአብሔርን በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፤ ቀርቦም ሳለ ጥሩት" (ኢሳ55፥6) እንደ ተባለ ልብን ወደ እግዚአብሔር መመለስ አስፈላጊ መሆኑን ያሳስባል፤ በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔር እጅ እንዳይከብድባቸው እንደ ዳዊት እግዚአብሔርን እንዳያስቈጡ ይመክራቸዋል። ኀጢአትን ይቅር ላለና ምሕረትንም ላደረገ አምላክ ሕይወትን ሁሉ መስጠት ተገቢ ነው (130፥4 ይመ)። *ጻድቅ፤* የ4፥3 ማብ ይመ። *ኀይለኛ ጐርፍ፤* አስፈሪ ኀይልን ወይም ሁኔታን የሚያሳይ ጠንካራ የአገላለጽ ዘይቤ ነው። ይህ እና ሌሎችም ተዛማጅ የአገላለጽ ዘይቤዎች ከጥንት ቅርብ ምሥራቅ የሥነ ፍጥረት አፈ-ታሪክ ላይ የተቀዱ ናቸው። በእነዚህ ጥንታዊ ታሪኮች ወይም አፈ-ታሪኮች ውስጥ እንደሚታየው ማዕበል ውሃ (ፈረሰኛና ጉግሰኛ ባሕር) አማልክት ዓለምን ከመፍጠራቸው እና/ወይም ምድርንም እንደ መለኮታዊ ንጉሥ ከመግዛታቸው በፊት መረታትና በቍጥጥርም ሥር መዋል አለበት (ማዕበሉ ውሃ አብዛኛውን ጊዜ የሚታወቀው በአስፈሪነቱና በአጥፊነቱ በመሆኑ ብዙ ራሶች ባሉት የባሕር ውስጥ ዘንዶ ወይም አውሬ ይመስላል፤ መዝ 74፥13-14 እና ማብ ይመ)። በአፈ-ታሪኩ ውስጥ እንደተገለጸው ይህ የአሁኑ ዓለም በሚፈጠርበት ጊዜ ማዕበሉ ውሃው የተረታ ቢሆንም አሁንም ግን አሁን ካለው የምድር ሥርዐትና ህልውና አሥጊ መሆኑ አልቀረም። በዚህም ምክንያት ማዕበሉ ውሃ የሰዎችን ሕይወት አስጊ ሁኔታ ላይ ከሚጥሉ ማናቸው ክፉ ነገሮች ጋር ተዛምዶ ቀርቦአል። ከዚህም በተጨማሪ ማዕበሉ ውሃ አንዳንድ ጊዜ ምድርን ሁሉ ለመሸፈን ቈርጦ የተነሣ ከሚመስለው ሞገደኛ ባሕር ጋር ተዛምዶ ታይቶአል። በከነዓናውያን አፈ-ታሪክ ውስጥ ባሕርና ሞት የበዓል (የምድር

[7]አንተ መሸሸጊያዬ ነህ፤
ከመከራ ትጠብቀኛለህ፤
በድል ዝማሬም ትከብበኛለህ። ሴላ
[8]አስተምርሃለሁ፤ በምትሄድበትም
መንገድ እመራሃለሁ፤
እመክርሃለሁ፤ በዐይኔም እከታተልሃለሁ።
[9]በልባብና በልጓም ካልተገሩ በቀር፣
ወደ አንተ እንደማይቀርቡት፣
ማስተዋል እንደሌላቸው፣
እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ።
[10]የክፉዎች ዋይታ ብዙ ነው፤
*በእግዚአብሔር* የሚታመን ግን፣
ምሕረት ይከብበዋል።
[11]ጻድቃን ሆይ፤ *በእግዚአብሔር* ደስ
ይበላችሁ፤ ሐሤትም አድርጉ፤
ቅን ልብ ያላችሁም ሁሉ፣ እልል በሉ።

## መዝሙር 33

### ውዳሴ ለቸር አምላክ

[1]ጻድቃን ሆይ፤ *በእግዚአብሔር* ደስ
ይበላችሁ፤
ቅኖች ሊወድሱት ይገባቸዋል።

32፥7 መሳ5፥1፤ 9፥35፤መዝ9፥9
32፥8 መዝ25፥8፤ 33፥18፤34፥11
32፥9 ኢዮ30፥11፤ 39፥10፤ያዕ3፥3
32፥10 መዝ4፥5፤ ምሳ16፥20፤ሮሜ2፥9
32፥11 መዝ64፥10
33፥1 መዝ5፥11፤ 11፥7፤101፥1፤147፥1
33፥2 ዘፍ4፥21፤ መዝ92፥3፤144፥9፤1 ቆሮ14፥7፤ራእ5፥8
33፥3 ኢዮ3፥7፤መዝ 35፥27፤40፥3፤47፥1፤ ኢሳ42፥10፤ራእ5፥9
33፥4 መዝ18፥25፤ 19፥8፤25፥10፤119፥1 42፤ራእ19፥9፤22፥6
33፥5 መዝ6፥4፤ 11፥7
33፥6 ዘፍ1፥3፡16 ፤ዘፀ8፥19፤2ዜና2፥12 ፤ዕብ11፥3
33፥7 ዘፍ1፥10፤ኢሱ 3፥16
33፥8 ዘዳ6፥13፡4፥ 23 ፤መዝ2፥11፤49፥1 ፤ኢሳ18፥3፤ሚክ1፥2

[2]*እግዚአብሔርን* በመሰንቆ አመስግኑት፤
ዐሥር አውታር ባለውም በገና
ዘምሩለት።
[3]አዲስ መዝሙር ዘምሩለት፤
በገናውን ባማረ ቅኝት ደርድሩ፤
እልልም በሉ።
[4]*የእግዚአብሔር* ቃል እውነት ነውና፤
የሚሠራውም ሁሉ የታመነ ነው።
[5]እርሱ ጽድቅንና ፍትሕን ይወዳል፤
ምድርም በምሕረቱ የተሞላች ናት።
[6]*በእግዚአብሔር* ቃል ሰማያት ተሠሩ፤
በአፉም እስትንፋስ የከዋክብት
ሰራዊት።
[7]የባሕርን ውሃ በአንድ ዕቃ ይሰበስባል፤[a]
ቀላዩንም በአንድ ስፍራ ያከማቻል።
[8]ምድር ሁሉ *እግዚአብሔርን* ትፍራው፤
በዓለም የሚኖር ሕዝብ ሁሉ በፊቱ
ይንቀጥቀጥ።
[9]እርሱ ተናግሮአልና፣ ሆኑ፤
አዞአልና፣ ጸኑም።

33፥9 መዝ148፥5

*[a]7 ወይም የባሕርን ውሃ ይሰበስባል*

"ጌታ" ተብሎ የሚታወቀው አምላክ) ዐቢይ ጠላቶች ተደርገው የሚታዩ በመሆናቸው የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች አስፈሪ ሁኔታዎችን ለመግለጽ ሲሉ አንዳንድ ምስላዊ አገላለጾችን ተውሰዋል። (18፥4-5፡16፤ 42፥7፤ 65፥7፤ 74፥12-14፤ 77፥16፡19፤ 89፥9-10፤ 93፥3-4፤ 124፥4-5፤ 144፥7-8፤ ኢዮ7፥12፤ 26፥12፤ 38፥8-11፤ ኢሳ5፥30፤ 8፥7-8፤ 17፥12-14፤ 51፥9-10፤ ኤር5፥22፤ 47፥2፤ 51፥55፤ ዕን3፥8-10፤ እንዲሁም የማሕ8፥7 ማብ ይመ)። ከሞት ዓለም ጋር የተዛመደ ምስላዊ አገላለጽ ለማስተዋል የ30፥1፤ የ49፥14 ማብ ይመ።

32፥7 *በድል ዝማሬም ትከበኛለህ፤* የምስጋና መሥዋዕቴን ወደ አንተ ሳቀርብ ሳለሁ ከአንተ ርዳታ የተነሣ የአንተን የማዳን ሥራ በሚያከብሩ ሰዎች እከበባለሁ (የ7፥17 እና የ9፥1 ማብ እንዲሁም 35፥27፤ 51፥8 ይመ)።

32፥8 *እከታተልሃለሁ፤* እግዚአብሔር ኀጢአት ይቅር የተባለለትንና ከእርሱም ለመማር ዝግጁ የሆነውን ሰው እንደሚያስተምረውና እንደሚመራው ቃል ገብቶአል፤ እግዚአብሔርን መሸሸጊያ የሚያደርጉ (ቍ7)፣ በእርሱ የሚታመኑ (ቍ10)፣ በእርሱ ሐሤት የሚያደርጉና (ቍ11) በቅንም ልቦና በፊቱ የሚመላለሱትን (ቍ11) ሰዎች ኀጢአት ይቅር እንደሚል ተስፋ ሰጥቶአል።

*32፥9፤* የእግዚአብሔር አገልጋይ ከእንስሳት ይልቅ ብልህ መሆን አለበት፤ ፈረሶችና በቅሎዎች ጌቶቻቸውን ከሚያውቁት ይልቅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ አለበት።

32፥10 *ምሕረት፤* የ6፥4 ማብ ይመ።

*32፥11፤* ለተሰበሰቡት ምእመናን የተነገረ የመጨረሻ ቃል ነው፤ ቃሉ ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ምስጋና እጥፍ ድርብ እንዲሆን ያሳስባል (የ1፥5 ማብ ይመ)። *ቅን ልብ፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

*መዝሙር 33፤* የእስራኤልን ልዑል አምላክ ለማመስገን የቀረበ ውዳሴ ነው። በመዝሙሩ ውስጥ፣ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳስበው ክፍልና (ቍ1-3) ከምን የተነሣም ምስጋና ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን የሚያስረዳው ክፍል (ቍ4-19) በምስጋና ቋንቋ ውስጥ የሚመደቡ ናቸው (የ9፥1 ማብ ይመ)። በዚህ መዝሙር ውስጥ የመዘምራኑ የሌዋውያን ድምፅ ሳይሰማ አይቀርም (1ዜና16፥7-36፤ 25፥1 ይመ)። ምናልባት በቍ1-3 ላይ ያለውን የተናገረው የመዘምራኑ መሪ ሳይሆንና በቍ 4-19 ላይ ያለውን መዘምራኑ፣ በቍ20-22 ላይ ያለውን ደግሞ ሕዝቡ ሳይናገሩት አይቀርም። ይህ መዝሙር በምን ወቅት እንደ ተዘመረ አይታወቅም፤ ይሁን እንጂ "አዲስ መዝሙር" የሚለው ሐሳብ (የቍ3 ማብ ይመ)፣ ይሁዳ በኢዮሳፍጥ (2ዜና20) ወይም በሕዝቅያስ ዘመን (2ነገ19) ቍ10-11፡16-17 ያገኘችውን ድልና ሰላም የሚያመለክት ነው። ከመዝሙር 1እና 2 እንዲሁም 10 ጋር (የመዝ 9 መግቢያን ግን ይመ) ይህ መዝሙር በመጀመሪያው መጽሐፍ ውስጥ ንዑስ ርእስ ከሌላቸው አራት መዝሙሮች ውስጥ አንዱ ነው። ምንም እንኳን ባወቃቀሩ እንደተከታዩ መዝሙር (መዝ34) በፊደል ገበታ መልክ የተቀናጀ ባይሆንም የመዝሙሩ ርዝመት ግን (22ቍጥሮች አሉት) በዕብራይስጡ ቋንቋ የፊደል ገበታ ልክ የተወሰነ ነው (የዕብራይስጥ ቋንቋ 22 ፊደላት አሉት)፤ መዝ38፤ 103፤ ሰቆ 5 ይመ። የመዝሙሩ ፍሬ ሐሳብ በመግቢያው ላይ ባሉ ሦስት ቍጥሮች (የምስጋና ጥሪ) እና በመደምደሚያው ላይ ባሉ ሦስት ቍጥሮች (ለቀረበው የምስጋና ጥሪ የተሰጠ መልስ) የተቀነበበ ነው።

*33፥1-3፤* ምስጋና ይቀርብ ዘንድ የቀረበ ጥሪ ነው፤ ከኤፌ 5፥19 ጋር ያነጻጽሩ።

33፥1 *ጻድቃን፤* የምእመናን ጉባኤ ማለት ነው (የ1፥5 ማብ ይመ)።

33፥3 *አዲስ መዝሙር፤* የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ የሚያወድስ መዝሙር ነው፤ ይህም በ40፥3፤ 96፥1፤ 98፥1፤ 144፥9፤ 149፥1 ላይ እንዳለው ዐይነት ነው፤ ኢሳ42፥10፤ ራእ 5፥9፤ 14፥3፤ እንዲሁም የ7፥17 ማብ ይመ።

*33፥4-19፤* በሁለት አንጓዎች የቀረበ ምስጋና ሲሆን፣ እያንዳንዱ አንጓ ስምንት ስንኞች አሉት።

*33፥4-11፤* የዚህ ዓለም መገኛ እግዚአብሔር በመሆኑ እርሱ በፈጠረው ዓለም ላይ ሥርዐቱንና ሕጉን የማጽናት መብት አለው (ዘፍ1 ይመ)፤ በመሆኑም ሕዝቡን ለማዳን ያለውን ዓላማ የሚያደናቅፍ አንድም ኀይል የለም (ስለዚህ የተመረጠው ሕዝቡ የተባረከ ሕዝብ ነው፤ ቍ12-19 ይመ)።

33፥4 *ቃል፤* ሁሉን ነገር የሚገዛበትንና የሚያስተዳድርበትን (107፥20፤ 147፥15፡18) ክቡር ቃሉን የሚያሳይ ነው (107፥20፤ 147፥15፡18 ይመ)። *እውነት፤* ከመስመር የወጣና ጥጥያጣ ያልሆነ እንዲሁም የሚያስትና የሚያጠፋ ያልሆነ ማለት ነው፤ እግዚአብሔር በሚያስተዳድረው ዓለም ውስጥ መልካምና ሥርዐት ያለውን ነገር እንጂ ጤና ያጣን ነገር አናይም፤ የእርሱም አስተዳደር ፍጹም የታመነ ነው።

33፥5 *ይወዳል፤* በጎ የሆነውን ነገር ማድረግ ደስ ያሰኛል ማለት ነው። *ጽድቅንና ፍትሕን፤* የ4፥1 ማብ ይመ። *በምሕረቱ፤* በዚህ በታ አባባሉ ለፍጥረቱ ሁሉ የሚያደርገው ቸርነት የሚያመለክት ነው (36፥5-9፤ 104፥27-28፤ እንዲሁም የ6፥4 ማብ ይመ)።

33፥6 *ቃል፤* ዓለምንና በውስጧም ያሉትን ፍጥረቶች ሁሉ ወደ ህልውና ያመጣበትን ቃሉን ማለት ነው (ቍ9፤ 104፥7፤ 119፥89፤ ዘፍ1፤ ኢዮ38፥8-11፤ ዕብ11፥3 ይመ)።

33፥7 *በአንድ ዕቃ ... በአንድ ስፍራ፤* እህሉንና የወይራ ዘይቱን እንደሚያከማች የቤት መጋዘ (የቤት ጎተራ) ማለት ነው (104፥9፤ ዘፍ1፥9-10፤ ኢዮ38፥8-11፤ ምሳ8፥29፤ ኤር5፥22 ይመ)።

33፥8 *ምድር ሁሉ ... ሕዝቦች ሁሉ፤* እስራኤል ብቻ

10 እግዚአብሔር የሕዝቦችን ምክክር
ከንቱ ያደርጋል፤
የሕዝብንም ዕቅድ ያጨናግፋል።
11 የእግዚአብሔር ሐሳብ ግን ለዘላለም
ይጸናል፤
የልቡም ሐሳብ ለትውልድ ሁሉ ነው።
12 እግዚአብሔር አምላኩ የሆነው ሕዝብ፣
ለርስቱ የመረጠውም ወገን የተባረከ
ነው።
13 እግዚአብሔር ከሰማይ ይመለከታል፤
የሰውንም ልጆች ሁሉ ያያል፤
14 ከማደሪያው ቦታ ሆኖ፣
በምድር ወደሚኖሩት ሁሉ
ይመለከታል፤
15 እርሱ የሁሉን ልብ የሠራ፣
የሚያደርጉትን ሁሉ የሚያስተውል
ነው።
16 ንጉሥ በሰራዊቱ ታላቅነት አይድንም፤
ጀግናም በኀይሉ ብርታት አያመልጥም።
17 በፈረስ ድል አደርጋለሁ ማለት ከንቱ
ተስፋ ነው፤
በብርቱ ጒልበቱም ማንም አያድንም።
18 እነሆ፤ የእግዚአብሔር ዐይኖች በሚፈሩት
ላይ ናቸው፤
ምሕረቱንም በሚጠባበቁት ላይ
አትኵረዋል።
19 በዚህም ነፍሳቸውን ከሞት ያድናል፤
በራብ ዘመንም በሕይወት ያኖራቸዋል።
20 ነፍሳችን እግዚአብሔርን ተስፋ
ታደርጋለች፤
እርሱ ረዳታችንና መጠጊያችን ነው።
21 ልባችን በእርሱ ደስ ይለዋል፤

33፥10 ኢዮ5፥12፤ መዝ2፥1፤ኢሳ44፥25
33፥11 ዘኍ23፥19፤ ኤር51፥12፡29
33፥12 ዘፀ8፥22፤ 34፥9፤ዘዳ7፥6፤መዝ4፥3፤65፥4፤84፥4፤144፥15
33፥13 ኢዮ28፥24 1መዝ11፥4፤14፥2፤53፥2፤102፥19፤ዕብ4፥13
33፥14 ዘሌ15፥31፤ 1ነገ8፥39
33፥15 ኢዮ10፥4፡8 1መዝ119፥73፤ኤር32፥19
33፥16 1ሳሙ14፥6
33፥17 መዝ20፥7
33፥18 ዘፀ3፥16፤ መዝ6፥4፤11፥4፤1ጴጥ3፥12
33፥19 ኢዮ5፥20፤ መዝ56፥13፤ሐሥ12፥11
33፥20 መዝ27፥14
33፥21 1ሳሙ2፥1፤ መዝ30፥4፤99፥3፤ ኢል2፥23
33፥22 መዝ6፥4
34 ርዕስ 1ሳሙ21፥13
34፥1 መዝ71፥6፤ ኤፌ5፥20፤1ተሰ5፥18
34፥2 መዝ44፥8፤ 69፥32፤107፥42፤119፥74፤ኤር9፥24፤1ቆሮ1፥31
34፥3 ዘፀ15፥2፤መዝ63፥3፤86፥12፤ዳን4፥37፤ዮሐ17፥1፤ሮሜ15፥6
34፥4 ቍ17፤ዘፀ32፥11፤መዝ18፥4፡12፥4፤56፥13፤77፥2፡18፥6፥13

በቅዱስ ስሙ ታምነናልና።
22 እግዚአብሔር ሆይ፤ ተስፋ ባደረግንህ፣
በእኛ ላይ ምሕረትህ ትሁን።

## መዝሙር 34[o]

## የእግዚአብሔር ፍትሕ ውዳሴ

እንደ እብድ ሆኖ አቤሜሌክ ፊት በመቅረቡ ተባርሮ
በወጣ ጊዜ የዘመረው፤ የዳዊት መዝሙር

1 እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ፤
ምስጋናውም ዘወትር ከአፌ አይለይም።
2 ነፍሴ በእግዚአብሔር ተመካች፤
ትሑታንም ይህን ሰምተው ሐሤት
ያደርጋሉ።
3 ኑና ከእኔ ጋር እግዚአብሔርን አክብሩት፤
ስሙንም በአንድነት ከፍ ከፍ
እናድርግ።
4 እግዚአብሔርን ፈለግሁት፤ እርሱም
መለሰልኝ፤
ከፍርሀቴም ሁሉ አዳነኝ።
5 ወደ እርሱ የሚመለከቱ ያበራሉ፤
ፊታቸውም ከቶ አያፍርም።
6 ይህ ችግረኛ ጮኸ፤ እግዚአብሔርም
ሰማው፤
ከመከራውም ሁሉ አዳነው።
7 እግዚአብሔርን በሚፈሩት ዙሪያ
የእግዚአብሔር መልአክ ይሰፍራል፤
ያድናቸዋልም።

34፥5 ዘፀ34፥29፤ መዝ25፥3፤44፥15፤69፥7፤83፥16
34፥6 መዝ25፥17 34፥7 ዘፍ32፥1፤መዝ22፥4፤37፥40፤41፥1፤97፥10፤ኢሳ31፥5፤ዳን3፥28፤ማቴ18፥10፤ሐሥ12፥11

[o]34 እያንዳንዱ የዚህ መዝሙር ጥቅስ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆሄያት የሚጀመር ሲሆን ጅማሬው ወይም ጅማሬውና መጨረሻው ትርጒም የሚሰጥ ግጥም ነው።

ሳትሆን የምድር ሕዝቦችም ሁሉ የእግዚአብሔርን መልካምነትና ሉዓላዊነት ያውቃሉ፤ በተጨባጭ አይተዋልና (የ9፥1 ማብ ይመ)፤ ነገር ግን ተቃራኒ ሐሳቦቻቸውን ሁሉ ከንቱ ያደርግባቸዋል (ቍ10-11 ይመ)። *እግዚአብሔርን ትፍራው፤* ቍ18፤ እንዲሁም የ15፥4 ማብ ይመ)።

33፥11 *የልቡም፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

*33፥12-19፤* እስራኤል በሰላም መኖር የምትችለውና ለህልውናዋም ዋስትናን ማግኘት የምትችለው በእግዚአብሔር አመራር ጥበቃ ሥር ስትሆን ብቻ ነው።

33፥12 *የተባረከ፤* የ1፥1 ማብ ይመ። *ለርስቱ የመረጠውም፤* እስራኤልን ማለት ነው (ዘዳ9፥29 ይመ)።

33፥16 *ንጉሥ፤* ሕዝብና (ቍ12) መሪ (ንጉሥ) አንድ ማኅበራዊ አካል ናቸው (የ28፥8 ማብ ይመ)።

33፥18-19 *በሚፈሩት፤* የእግዚአብሔር "ዐይን" በምድር ላይ ያሉትን ሁሉ የሚያይ ቢሆንም (ቍ13-14) "በሚፈሩት" ላይ ግን በተለየ ሁኔታ ያርፋል (34፥15 ይመ)። የእግዚአብሔር "ዐይን" የሚለው አነጋገር እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ፍቅርና ክብካቤ የሚያሳይ ነው።

33፥18፡22 *ምሕረትህ፤* በዚህ ቦታ ይህ አባባል የሚያሳየው ኪዳኑ ለእስራኤል የሚሰጠውን በረከት ነው (የ6፥4 ማብ ይመ)።

*33፥20-22፤* የሕዝቡ መልስ ነው፤ ሕዝቡ እምነቱን የሚገልጸው ንስሓ በመግባትና (ቍ20-21) ልመናም በማቅረብ (ቍ22) ነው።

33፥20 *መጠጊያችን፤* የ3፥3 ማብ ይመ።

33፥21 *ልባችን፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *ስሙ፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

*መዝሙር 34፤* እግዚአብሔር የሕዝቡን ጸሎት ሰምቶ ሕዝቡን በመታደጉ ለስሙ የቀረበ ምስጋና ነው፤ መዝሙሩ እግዚአብሔርን እየመሰሉ መኖር አስፈላጊ መሆኑን መመሪያ ይሰጣል። በቍ3 ላይ እንደሚታየው ሁሉ (የ9፥1 ማብ ይመ) ምስጋና ሁልጊዜ ወደ ምስጋና ይመራል፤ በዳዊት መዝሙር ውስጥ ይህን እውነታ ማግኘት የተለመደ ነው። በዚህ ቦታ ልዩ በሆነ መንገድ እንደሚስተዋለው (መዝ 92 ይመ) ምስጋና (ቍ1-7) እግዚአብሔርን እየመሰሉ ወደ መኖር ይመራል (ቍ8-22)፤ ይህም የጥበብ መምህራን እንደሚያደርጉት ዐይነት ነው (በመጽሐፈ ምሳሌ መግቢያ ላይ የጥበብ ጽሑፍ የሚለውን ይመ)።

*34ርእስ፤* የዚህ ምዕራፍ ርእስ እንደሚያመለክተው ይህ መዝሙር በ1ሳሙ21፥10-15 ላይ ለዳዊት ከተነገረው ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት አለው (የመዝ3 ርእስ ማብ ይመ)፤ ሆኖም አንኩስ ሳይሆን አቤሜሌክ መባሉን ግን አስተውል (ምናልባት "አቤሜሌክ" የሚለው መጠሪያ የፍልስጥኤም ነገሥታት የሚጠሩበት ቤተ ሰባዊ ስም ወይም ማዕረግ ሳይሆን አይቀርም፤ ዘፍ20፤ 21፡22-34፤ 26 ይመ)።

34፥1-7 እግዚአብሔር የሕዝቡን ጸሎት ሰምቶ ሕዝቡን ስለታደገ ለስሙ የቀረበ ምስጋና ነው።

34፥2 *ነፍሴ፤* የ6፥3 ማብ ይመ።

34፥3 *ስሙንም፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

*34፥4-7፤* ይህ መዝሙር የተደረሰው እግዚአብሔር የሕዝቡን ጸሎት ሰምቶ ሕዝቡን ባዳነበት ወቅት ነው።

34፥5 *ያበራሉ፤* በደስታ ይፈካሉ ማለት ነው (ኢሳ60፥5 ይመ)።

34፥6 *ችግረኛ፤* በዳዊት መዝሙር ውስጥ ብዙውን ጊዜ እንደ ተመለከተውና በዚህም ቦታ እንደ ተጠቀሰው "ችግረኛ" ሲባል ሀብትና ንብረት የሌለው ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ራሱን ለማዳን የሚችልበት ምንም ነገር የሌለው በመሆኑ በእግዚአብሔር ላይ የሚታመን ማለት ነው።

34፥7 *የእግዚአብሔር ... መልአክ ይሰፍራል፤* "የእግዚአብሔር መልአክ" የሚለው ሐረግ የሰማይ መላእክት ሰራዊትን

8 *እግዚአብሔር* ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ
 እዩ፤
 እርሱን መጠጊያ የሚያደርግ ምንኛ
 ብሩክ ነው!
9 እናንተ ቅዱሳኑ፤ *እግዚአብሔርን* ፍሩት፤
 እርሱን የሚፈሩት አንዳች አያጡምና።
10 አንበሶች ሊያጡ፣ ሊራቡም ይችላሉ፤
 *እግዚአብሔርን* የሚሹ ግን መልካም
 ነገር አይጐድልባቸውም።
11 ልጆቼ ሆይ፣ ኑ፤ ስሙኝ፤
 *እግዚአብሔርን* መፍራት
 አስተምራችኋለሁ።
12 ሕይወትን የሚወድ፣
 በጎውንም ያይ ዘንድ ዕድሜን የሚመኝ
 ማን ነው?
13 አንደበትህን ከክፉ ነገር ከልክል፤
 ከንፈርህንም ከሽንገላ ጠብቅ።
14 ከክፉ ሽሽ፤ መልካሙንም አድርግ፤
 ሰላምን ፈልጋት፤ ተከተላትም።
15 *የእግዚአብሔር* ዐይኖች ወደ ጻድቃን
 ናቸው፤
 ጆሮዎቹም ለጩኸታቸው ክፍት
 ናቸው።
16 *መ*ታሰቢያቸውን ከምድር ለማጥፋት፣
 *የእግዚአብሔር* ፊት በክፉ አድራጊዎች
 ላይ ነው።
17 ጻድቃን ሲጮኹ፣ *እግዚአብሔር*
 ይሰማቸዋል፤
 ከመከራቸውም ሁሉ ያድናቸዋል።
18 *እግዚአብሔር* ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ
 ነው፤
 መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል።
19 የጻድቅ መከራው ብዙ ነው፤
 *እግዚአብሔር* ግን ከሁሉም ያድነዋል።
20 ዐጥንቶቹን ሁሉ ይጠብቃል፤
 ከእነርሱም አንድ አይሰበርም።
21 ኀጢአተኞችን ክፋት ይገድላቸዋል፤
 ጻድቃንን የሚጠሉ ይፈረድባቸዋል።
22 *እግዚአብሔር* የባሪያዎቹን ነፍስ
 ይቤዣል፤
 እርሱንም መጠጊያ ያደረገ
 አይፈረድበትም።

34፥8 መዝ2፥12፤ ዕብ6፥5፤1ጴጥ2፥3
34፥9 ዘዳ6፥13፤ መዝ23፥1፤ራእ14፥7
34፥10 መዝ23፥1
34፥11 መዝ19፥9፤ 32፥8፤66፥16
34፥12 መክ3፥13
34፥13 መዝ12፥2፤ 39፥1፤141፥3፤ምሳ13፥3፤21፥23፤ያዕ1፥26፤ 1ጴጥ2፥22
34፥14 መዝ37፥27፤ኢሳ1፥17፤ሮሜ 14፥19፤3ዮሐ1፥11
34፥15 ኢዮ23፥10፤ 36፥7፤መዝ33፥18፤ ሚል3፥16፤ዮሐ9፥31
34፥16 ዘፀ17፥14፤ ዘሌ17፥10፤መዝ9፥6፤ ኤር23፥30፤1ጴጥ 3፥10-12
34፥17 መዝ145፥19
34፥18 ዘዳ4፥7፤ መዝ51፥17፤109፥16፤ 119፥151፤145፥18፤1 47፥3፤ኢሳ50፥8፤ 61፥1
34፥19 ቍ17፤ኢዮ 5፥19፤መዝ25፥17፤2 ጢሞ3፥11
34፥20 ዮሐ19፥36
34፥21 መዝ7፥9፤ 9፥16፤11፥5፤37፥20፤ 73፥27፤94፥23፤106፥ 43፤112፥10፤140፥11 ፤ምሳ14፥32፤24፥16
34፥22 ዘዳ6፥6፤ 15፥13፤መዝ2፥12፤ ሉቃ1፥68፤ራእ14፥3

## መዝሙር 35

## የተጨቈነ ሰው ጸሎት

የዳዊት መዝሙር

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ የሚታገሉኝን
 ታገላቸው፤
 የሚዋጉኝንም ተዋጋቸው።
2 ትልቁንና ትንሹን ጋሻ ያዝ፤
 እኔንም ለመርዳት ተነሥ።
3 በሚያሳድዱኝ ላይ፣
 ጦርና ጭሬ ምዘዝ፤[a]

35፥1 ዘፀ14፥14፤1ሳሙ24፥15
35፥2 ዘዳ50፥24፤ኢዮ17፥3፤መዝ3፥3፡7

[a]3 ወይም ... መንገድ ዝጋ

የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም፤ እነዚህም መላእክት "የሚድኑትን ለማገልገል የሚላኩ አገልጋይ መናፍስት ናቸው" (ዕብ1፥14 ይመ፤ ደግሞም ከዘፍ32፥1-2፤ 2ነገ6፥17 ጋር ያነጻጽሩ)፤ እግዚአብሔር ቅዱሳኑን ከሥጋዊና ከመንፈሳዊ ጉዳት ለመጠበቅና ለማዳን መላእክቱን ሾሞአል።

*34፥8-14፤* "እግዚአብሔርን መፍራት" ተገቢ መሆኑን የሚያስተምር ክፍል ነው። የዕብራይስጥ ጸሐፊዎች ብዙውን ጊዜ ቁልፍ የሆነውን ሐሳብ የሚያስፍሩት በመካከል ላይ ነው (የ6፥6 ማብ ይመ)። ለምሳሌ በትእዛዝ አንቀጽ የሰፈሩትን ቃላት "ቅመሱ" (ቍ8)፤ "ፍሩ" (ቍ9)፤ "ኑ" (ቍ11)፤ "ጠብቅ" (ቍ13)፤ "ተለይ" (ቍ14) ልብ ብሎ መመልከት ይቻላል። በአንጻሩም ላይ ጐልቶ የሚታየው "ቸር" የሚለው ሐሳብ ነው፤ ጌታ ቸር በመሆኑ (ቍ8) በእርሱ የሚታመኑት ሁሉ የሚያጡት አንዳች በጎ ነገር የለም (ቍ10)፤ ነገር ግን በጎ ዘመናትን ለማየት (ቍ12) ከክፉ መራቅና መልካምም ነገር ማድረግ ይኖርባቸዋል (ቍ14)፤ ማመንና መታዘዝ ማለት "እግዚአብሔርን" መፍራት ማለት ነው። የዚህን አንጓ ትምህርት ለማጤን መዝ37 ይመ፤ ሐዋርያው ጴጥሮስ በቍ12-16 ያለውን ሐሳብ በመልእክቱ ውስጥ እንዴት እንደ ተጠቀመበት ለማስተዋል 1ጴጥ3፥8-12 ይመ።

34፥8 *ብሩክ፤* የ1፥1 ማብ ይመ።

34፥9 *ቅዱሳኑ፤* የ4፥3 ማብ ይመ። *እግዚአብሔርን ፍሩ፤* ቍ11 እንዲሁም የ15፥4 ማብ ይመ።

34፥11 *ልጆቼ ሆይ፤ ኑ፤* በጥበብ መምህራን ዘንድ የተለመደ አባባል ነው (ከመጽሐፈ ምሳሌ መግቢያ "ዐላማውና ትምህርቱ" የሚለውን ይመ)።

*34፥13፤* 15፥2-3፤ ያዕ3፥5-10 ይመ። ምላስ መሣሪያ ስለመሆኑ የ5፥9 ማብ ይመ።

34፥14 *ሰላምን ፈልጋት፤* 37፥37፤ 120፥7፤ ምሳ12፥20፤ ዘካ8፥19 (እንዲሁም ዘካ8፥16-17 ይመ)፤ ማቴ5፥9፤ ሮሜ12፥18፤ 1ቆሮ7፥15፤ 2ቆሮ13፥11፤ 1ተሰ5፥13፤ ዕብ12፥14፤ ያዕ3፥17-18 ይመ።

*34፥15-18፤* እግዚአብሔር የጻድቃንን ጸሎት እንደሚሰማ የሚያረጋግጥ ነው። ክፉዎችን ግን ጨርሶ እስኪረሱ ድረስ ድራሻቸውን ያጠፋል (ቍ16)።

34፥15 *ጻድቃን፤* ቍ8-14፤ እንዲሁም የ1፥5 ማብ ይመ።

34፥16 *የእግዚአብሔር ፊት፤* የ13፥1 ማብ ይመ።

*34፥17-18፤* በተለይ 51፥17ን ይመ።

*34፥19-22፤* እግዚአብሔር የጻድቃን የዘላለም ታዳጊ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፤ በጻድቃን ላይ የሚነሱ ክፉዎችን ግን እየተከታተለ (እያሳደደ) ያጠፋቸዋል (ቍ21 ይመ)።

34፥20 *ዐጥንቶቹን ሁሉ፤* ሁለንተናውን ማለት ነው (የ6፥2 ማብ ይመ)። *ከእነርሱም አንድ አይሰበርም፤* ከሁሉ በላይ "ጻድቅ የሆነውን" ጌታ ለማመልከት ምናልባት የዮሐንስ ወንጌል ጸሐፊ ይህን አገላለጽ ሳይጠቀምበት አይቀርም።

34፥21-22 *ይፈረድባቸዋል፤* በበደላቸው ፍርድን ይቀበላሉ ማለት ነው።

34፥22 *ይቤዣል፤* የ25፥22 ማብ ይመ።

*መዝሙር 35፤* ሰማያዊ ንጉሥ መለኮታዊ ጠረኛና ዳኛ በመሆኑ "የአገልጋዩን" (ቍ27) ስም ፍቅሩንና ወዳጅነቱን የገለጠላቸው ሰዎች እያጠፉት ስለሆነ ከዚህ ሁሉ ክፋት ተሟግቶ እንዲታደገው የቀረበ አቤቱታ ነው። ጠላቶች ያደረሱበት ጥቃትም በንጉሡ ላይ (ቍ15፡19፡21፡25 ይመ) ጭንቀት (ቍ26) ሳያመጣበት አልቀረም፤ ምናልባትም ሕመም አምጥቶበት ሊሆን ይችላል (ቍ13፤ እንዲሁም የመዝ6 መግቢያን ይመ)። በመዝ34፥15-22 ላይ መዝሙረኛው ንጹሕ መሆኑን እንዳመለከተው ሁሉ በዚህም ቦታ ከበደል ነጻ መሆኑንና ጌታም ይህንን ንጽሕናውን ያስታውቅለት ዘንድ ጩኸቱን ሲያሰማ ይታያል፤ በሁለቱ ምዕራፎች መካከል ልዩነት ቢኖር በዚህ ቦታ መዝሙረኛው ራሱን "ጻድቅ" ብሎ አለመጥራቱ ነው (34፥21)። ወደ መዝሙሩ አወቃቀር ስንመጣ፣ መዝሙረኛው አቤቱታውን ለመለኮታዊው ጠረኛ ካሰማ በኋላ (ቍ1-3) ለመለኮታዊው ዳኛ ያቀረበውን አቤቱታ በሦስት እጅ እያሰረና እያብራራ ያቀርባል፤ እያንዳንዱም ክፍል የሚያበቃው የምስጋና መሥዋዕት ለማቅረብ ቃል በመግባት ነው (ቍ4-10፡11-18፡19-28)፤ እንዲሁም የ7፥17 ማብ ይመ።

*35፥1-3፤* ጠረኛና ንጉሥ ለሆነው ጌታ የቀረበ አቤቱታ ነው (ዘፀ15፥1-8 ይመ) ምክንያቱም ዳዊት ያለ አግባብ እየተበደለና እየተጨቈነ ነው።

35፥2 *ተነሥ፤* የ3፥7 ማብ ይመ።

ነፍሴንም፣ “የማድንሽ እኔ ነኝ” በላት።

4ሕይወቴን የሚፈልጓት፣
ይቅለሉ፣ ይዋረዱ፤
እኔን ለማጥፋት የሚያሤሩ፣
አፍረው ወደ ኋላቸው ይመለሱ።

5በነፋስ ፊት እንዳለ እብቅ ይሁኑ፤
*የእግዚአብሔር* መልአክ ያሳዳቸው።
6መንገዳቸው ጨለማና ድጥ ይሁን፤
*የእግዚአብሔር* መልአክ ያባርራቸው።
7ያለ ምክንያት ወጥመዳቸውን በስውር
አስቀምጠውብኛልና፤
ያለ ምክንያት ለነፍሴ ጕድጓድ
ቈፍረውላታል።
8ያልታሰበ ጥፋት ይምጣባቸው፤
የሰወሩት ወጥመድ ይያዛቸው፤
ይጠፉም ዘንድ ወደ ጕድጓዱ ይውደቁ።
9ነፍሴም *በእግዚአብሔር* ደስ ይላታል፤
በማዳኑም ሐሤት ታደርጋለች።
10የሥራ አካላቴ እንዲህ ይልሃል፤
“*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እንደ አንተ
ማን አለ?
ድኻውን ከእርሱ ከሚበረቱ፣
ችግረኛውንና ምስኪኑን ከቀማኞች
ታድናለህ”።

11ጨካኝ ምስክሮች ተነሡ፤
ስለማላውቀውም ነገር ጠየቁኝ።
12በበጎ ፈንታ ክፉ መለሱልኝ፤
ነፍሴንም ብቸኛ አደረጓት።
13እኔ ግን እነርሱ በታመሙ ጊዜ
ማቅ ለበስሁ፤
ነፍሴንም በጾም አደከምኋት፤
ጸሎቴም መልስ አጥቶ ወደ ጕያዬ
ተመለሰ።

14ለወዳጄ ወይም ለወንድሜ እንደማደርግ፣
እየተንቈራጠጥሁ አለቀስሁ፤
ለእናቴም እንደማለቅስ፣
በሐዘን አንገቴን ደፋሁ።
15እነርሱ ግን እኔ ስሰናከል በእልልታ

35፥3 ዘኍ25፥7፤ ኢሳ8፥18፤መዝ27፥1
35፥4 መዝ25፥3፤ 38፥12፤40፥14፤69፥6፡ 19፤70፥2፤83፥17፤12 9፥5፤ኢሳ45፥16፤ኤር 4፥30፤ሚል2፥9
35፥5 ኢዮ13፥25፤ መዝ1፥4፤34፥7
35፥7 ኢዮ9፥31፤ 18፥8፤መዝ7፥4፡15፤5 5፥23
35፥8 መዝ7፥15፤ ኢሳ47፥11፤1ተሰ5፥3
35፥9 መዝ2፥11፤ 9፥14፤13፥5፤27፥1፤ ሉቃ1፥47
35፥10 ዘፀ9፥14፤ መዝ12፥5፤18፥17፡31 ፤37፥14፤74፥21፤86፥ 1፤109፥16፤113፥5፤ 140፥12፤ኢሳ41፥17
35፥11 ዘፀ23፥1፤ ማቴ26፥60
35፥12 መዝ38፥20 ፤ 109፥5፤ምሳ17፥13 ፤ኤር18፥20
35፥13 2ሳሙ3፥31 ፤1ነገ20፥31፤ኢዮ30፥ 25፤መዝ30፥11፤69፥ 10፡11፤109፥24
35፥14 መዝ38፥6፤ 42፥9፤43፥2
35፥15 ኢዮ16፥10፤ 31፥29
35፥16 ኢዮ16፥9፤ መዝ22፥7፤ማር9፥18፤ 10፥34፤ሐሥ7፥54
35፥17 መዝ6፥3፤ 22፥20፤22፥21፤57፥4 ፤58፥6
35፥18 መዝ22፥22 ፡25፤42፥4፤109፥30
35፥19 ቍ7፤መዝ 9፥13፤38፥19፤69፥4፤ ምሳ6፥13፤10፥10፤ ዮሐ15፥25
35፥20 መዝ38፥12 ፤55፥21፤ኤር9፥8፤ ሚክ6፥12
35፥21 ኢዮ16፥10፤ መዝ40፥15፤70፥3፤ ሕዝ25፥3
35፥22 ዘፀ3፥7፤

ተሰበሰቡ፤
ግፈኞች በድንገት ተሰበሰቡብኝ፤
ያለ ዕረፍትም ቦጫጨቁኝ።
16እንደ ምናምንቴዎች አፌዙብኝ፤[ᵂ]
ጥርሳቸውንም አፋጩብኝ።
17ጌታ ሆይ፤ እስከ መቼ ዝም ብለህ
ታያለህ?
ነፍሴን ከክፉ ሥራቸው፣
ብርቅ ሕይወቴን ከአንበሶች ታደጋት።
18በታላቅ ጉባኤ መካከል አመሰግንሃለሁ፤
ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበትም
አወድስሃለሁ።

19ከምድር ተነሥተው ጠላቶቼ የሆኑት፣
በላዬ ደስ አይበላቸው፤
እንዲያው የሚጠሉኝ፣
በዐይናቸው አይጣቀሱብኝ።
20የሰላም ንግግር ከአፋቸው አይወጣም፤
ዳሩ ግን በምድሪቱ በጸጥታ በሚኖሩት
ላይ፣
ነገር ይሸርባሉ።
21አፋቸውን አስፍተው ከፈቱብኝ፤
“እሰይ! እሰይ! በዐይናችን አየነው” አሉ።

22*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ይህን አይተሃልና
ዝም አትበል፤
ጌታ ሆይ፤ ከእኔ አትራቅ።
23አምላኬ፣ ጌታዬ፤ ለእኔ ለመሟገት ተነሥ!
ልትከራከርልኝም ተንቀሳቀስ።
24*እግዚአብሔር* አምላኬ ሆይ፤ በጽድቅህ
ፍረድልኝ፤
በእኔም ላይ ደስ አይበላቸው።
25በልባቸው፣ “እሰይ! ያሰብነው ተሳካ!
ዋጥ አደረግነውም” አይበሉ።
26በጭንቀቴ ደስ የሚላቸው፣

መዝ10፥1፡14 35፥23 1ሳሙ24፥15፤መዝ7፥6፤17፥13፤80፥2
35፥24 መዝ22፥17 35፥25 ቍ21፤መዝ124፥3፤ምሳ1፥12፤ሰቆ 2፥16 35፥26 ኢዮ8፥22፤19፥5፤መዝ4፥1፤22፥17፤38፥16፤109፥29፤ ሚክ7፥10

ᵂ16 ሰብዓ ሊቃናት እንዲሁ ሲሆን በዕብራይስጥ ግን *ምናምንቴ ፌዘኞች* ማለት ሊሆን ይችላል።

35፥3 *ነፍሴንም፤* የ6፥3 ማብ ይመ።

*35፥4-10፤* ጌታ የመዝሙረኛውን ጠላቶች እንዲሟገትና የእጃቸውንም እንዲከፍላቸው (የ5፥10 ማብ ይመ) የሚያሳስብ አቤቱታ ነው።

35፥4 *ለማጥፋት የሚያሤሩ፤* የ5፥9 ማብ ይመ።

35፥5-6 *የእግዚአብሔር መልአክ፤* 34፥7 እና ማብ ይመ።

35፥5 *እንዳለ እብቅ፤* የ1፥4 ማብ ይመ።

*35፥9-10፤* የ7፥17 ማብ ይመ።

35፥9 *ነፍሴ፤* የ6፥3 ማብ ይመ።

35፥10 *ድኻውን ... ችግረኛውን፤* 34፥6 እና ማብ ይመ።

*35፥11-18፤* በአዲስ መልክ የቀረበ አቤቱታ ሲሆን (ቍ 17) አቤቱታው ከተሰማለት ምስጋና የሚያቀርብ መሆኑን ቃል ይገባል (ቍ 18)፤ ፍቅሩንና ወዳጅነቱን ያሳያቸው ሰዎች ግን በመልካም ፈንታ ክፉ መልሰውለታል።

35፥12 *ነፍሴንም፤* የ6፥3 ማብ ይመ።

35፥13 *ማቅ፤* የሐዘን ምልክት ነው (30፥11፤ ዘፍ37፥34 ይመ)። *በጾም፤* ከልብ ንስሓ መግባትን ያሳያል (69፥10 ይመ)።

35፥15 *ስሰናከል፤* የተሰናከለው በምግባራዊ ጉዳዮች አይደለም፤ ሁኔታዎች ግን ክፉኛ ደቍሰውታል (9፥3፤27፥2፤ 37፥24፤ 56፥13፤ 119፥165 ይመ)።

35፥16 *ጥርሳቸውንም አፏጩብኝ፤* በመረረ ጥላቻ ተነሡብኝ ማለት ነው (37፥12፤ ሰቆ2፥16 ይመ)።

35፥17 *እስከ መቼ?* የ6፥3 ማብ ይመ (እንዲሁም በመግቢያው ላይ “ትምህርተ መለኮት” የሚለውን ይመ)። *ከአንበሶች፤* የ7፥12 ማብ ይመ።

35፥18 *ጉባኤ፤* የ1፥5 ማብ ይመ።

*35፥18-19፤* ፍርድ ይሰጥ ዘንድ በአዲስ መልክ የቀረበ አቤቱታ ሲሆን፣ ነገሩን ከመጨረሱ በፊት ምስጋና ለማቅረብ ቃል ይገባል (ቍ 28)።

35፥19 *ከምድር ተነሥተው ጠላቶቼ የሆኑት፤* ቍ 11-17 ይመ። በዳዊት መዝሙር ውስጥ በተደጋጋሚ የሚንጸባረቅ ገጠመኝ ነው (38፥19፤ 69፥4፤109፥3፤ 119፥78፡86፡161 ይመ)፤ እንዲሁም ሰቆ 3፥52 ይመ። *እንዲያው የሚጠሉኝ፤* 69፥4 ይመ። በዮሐ 15፥25 ላይ የትኛው ክፍል እንደ ተጠቀሰ በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም። ሁለቱም መዝሙሮች ግን ጌታ ኢየሱስ የነበረበትን ሁኔታ ያንጸባርቃሉ (የሆነ ሆኖ የመዝ69 መግቢያን ይመ)።

35፥21 *እሰይ! እሰይ!* ቍ 25፤ የ3፥2 ማብ ይመ።

35፥22 *ዝም አትበል፤* አይተህ እንዳላየህ ችላ አትበል ማለት ነው (28፥1 እና የ83፥1፤ የ109፥1 ማብ ይመ)።

35፥23 *ተነሥ፤* የ3፥7 ማብ ይመ። *ተንቀሳቀስ፤* የ7፥6 ማብ ይመ።

35፥24 *በጽድቅህ፤* የ4፥1 ማብ ይመ።

35፥25 *ዋጥ አደረግነውም፤* 124፥3 ይመ።

*35፥26፤* ለክፉ ሐሳባቸው የሚሰጠው ፍርድ ተመጣጣኝ እንዲሆን በድጋሚ የቀረበ ጥያቄ ነው (4-10 ይመ)።

ይፈሩ፤ ግራም ይጋቡ፤
በእኔ ላይ ራሳቸውን ከፍ ከፍ የሚያደርጉ፣
እፍረትንና ውርደትን ይከናነቡ።
27 ፍትሕ ማግኘቴን የሚወዱ፣
እልል ይበሉ፤ ሐሤትም ያድርጉ፤
ዘወትርም፣ "የባርያው ሰላም ደስ የሚለው፣
*እግዚአብሔር* ከፍ ከፍ ይበል!" ይበሉ።
28 አንደበቴ ጽድቅህን፣
ምስጋናህንም ቀኑን ሙሉ ይናገራል።

## መዝሙር 36

## የኀጥኡ ክፋት፣ የእግዚአብሔር በጎነት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የእግዚአብሔር ባሪያ የዳዊት መዝሙር*

1 ክፉውን ሰው፣
በደል በልቡ ታናግረዋለች፤[a]
እግዚአብሔርን መፍራት፣
በፊቱ የለም፤
2 በደሉ ግልጽ ወጥቶ እንዳይጠላ፣
ራሱን በራሱ እጅግ ይሸነግላልና።
3 ከአንደበቱ የሚወጣው የክፋትና የተንኰል
ቃል ነው፤
ማስተዋልንና በጎ ማድረግን ትቶአል።
4 በመኝታው ላይ ክፋትን ያውጠነጥናል፤
ራሱን በጎ ባልሆነ መንገድ ይመራል፤
ክፋትንም አያርቅም።
5 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረትህ እስከ
ሰማያት ይደርሳል፤
ታማኝነትህም እስከ ጠፈር ይመጥቃል።
6 ጽድቅህ እንደ ታላላቅ ተራሮች፣
ፍርድህም እጅግ ጥልቅ ነው፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ሰውንም
እንስሳንም ታድናለህ።
7 አምላክ ሆይ፤ ምሕረትህ እንዴት ክቡር
ነው!
የሰዎች ልጆች ሁሉ፣
በክንፎችህ ጥላ ሥር መጠጊያ ያገኛሉ።
8 ከቤትህ ሲሳይ ይመገባሉ፤
ከበረከትህም ወንዝ ይጠጣሉ።
9 የሕይወት ምንጭ ከአንተ ዘንድ ነውና፤
በብርሃንህም ብርሃን እናያለን።

35፥26 ኢዮ8፥22፤ 19፥5፤መዝ4፥1፤22፥17፤38፥16፤109፥29፤ ሚክ7፥10
35፥27 ኢዮ17፥3፤ መዝ9፥4፤20፥5፤33፥3፤መዝ147፥11፤149፥4
35፥28 መዝ5፥8፤ 51፥14፤71፥15፡24፤72፥15
36፥1 ኢዮ21፥6፤ 23፥15፤ኤር2፥19፤36፥16፡24፤ሮሜ3፥18
36፥2 ዘዳ29፥19
36፥3 ኢዮ5፥13፤ መዝ5፥6፡9፤10፥7፤43፥1፤94፥8፤144፥8፡11፤ ኢሳ44፥20፤ኤር4፥22፤13፥23፤አሞ3፥10
36፥4 መዝ52፥3፤ ምሳ4፥16፤ኢሳ65፥2፤ ሮሜ12፥9
36፥5 መዝ57፥10፤ 71፥19፤89፥1፡2፤103፥11፤108፥4፤119፥90
36፥6 ዘፍ1፥2፤7፥11፤ነህ9፥6፤መዝ5፥8፤ 68፥15፤104፥14፤ 145፥16
36፥7 ሩት2፥12፤ መዝ6፥4፤17፥8፤57፥1፤91፥4 36፥8 ኢዮ20፥17፤ መዝ23፥2፤63፥5፤65፥4፤ኢሳ25፥6፤ ኤር31፥12፡14፤ራእ22፥1 36፥9 መዝ4፥6፤ 27፥1፤76፥4፤87፥7፤ 104፥2፤ምሳ10፥11፤ 16፥22፤ኢሳ2፥5፤9፥2፤60፥1፡19፤ኤር2፥13፤ ዮሐ1፥4፤1ጴጥ 2፥9

[a]1 *ወይም ... ኀጢአት ከኀጥእ ይመነጫል*

*35፥27፤* የእግዚአብሔር "አገልጋይ" (እዚህ ላይ "አገልጋይ" ሲባል "የተቀባው" ማለት ነው፤ የ2፥2 ማብ ይመ) አጋር የሆኑ ሁሉ ጌታን የሚያመሰግኑበትና በእርሱም ደስ የሚሰኙበት በቂ ምክንያት አላቸው።

35፥28 *ጽድቅህን፤* የ4፥1 ማብ ይመ።

*መዝሙር 36፤* መዝሙረኛው ስለ እምነተ ቢሶች ክፋትና ስለ እግዚአብሔር ቸርነት በሚያሰላስልበት ወቅት እግዚአብሔር በዘላለማዊ ፍቅሩ ጥበቃውን እንዲያበዛለት ያቀረበው ጸሎት ነው። ቍ7-10 በአይሁድ የሃይማኖት ሥርዐት ውስጥ ከንግሀ ጸሎት ውስጥ የሚመደብ ነው።

36ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 የርእስ ማብ ይመ። *የእግዚአብሔር ባሪያ፤* የመንግሥቱ አገልጋይ ማለት ነው (የመዝ 18 ርእስ እና የ35፥27 ማብ እንዲሁም 2ሳሙ7፥20 ይመ)።

*36፥1-4፤* የክፉዎችን ቂልነት፣ እምነተ ቢስነትና ትዕቢት የሚያመለክት ክፍል ነው።

36፥1 *ታናግረዋለች፤* ይህ ቃል ሁልጊዜ የተያያዘው እግዚአብሔር በነቢያቱ አፍ ከሚናገረው ቃል ጋር ነው (ለምሳሌ ዘኍ23፥7፤ ኢሳ 13፥1፤ ኤር23፥33-38፤ ሕዝ12፥10 እንዲሁም የዘኍ23፥7 ማብ ይመ)። በዚህ ቦታ ቃሉ የተዛመደው የክፉዎችን ባሕርይ ከሚያሳይ ሁኔታ ጋር ሲሆን ምናልባት በቅጽበት ብልጭ ያለ ነገር ሳይሆን አይቀርም። *ልቡ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *እግዚአብሔርን መፍራት ... የለም፤* 55፥19 ይመ፤ የእግዚአብሔር ዐይኖች ሁሉንም ነገር እንደሚመለከቱ፣ ፍርዱም ቅን እንደ ሆነና የእጃቸውንም ለመክፈል ብርቱና ኀያል እንደ ሆነ አያስተውሉም (የ10፥11 ማብ ይመ)። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ምንባብ እንዴት እንዳ ገናዘበው ሮሜ3፥18 ይመ።

36፥2 *በራሱ ይሸነግላል፤* ራሱን ከመጠን በላይ ከማግነኑ የተነሣ በኀጢአቱ እንደሚቀጣና ተጠያቂም እንደሚሆን አያስብም።

36፥3 *ከአንደበቱ የሚወጣው፤* የ5፥9 ማብ ይመ። *ማስተዋልን ... ትቶአል፤* 94፥8-11፤ ምሳ2፥9-11 ይመ። *በጎ ማድረግን፤* 34፥8-14 እና ማብ ይመ።

36፥4 *በመኝታው ላይ፤* ሐሳቡ ነጻ በሚሆንበትና በማግስቱ የሚሠራውን ነገር ሲያወጣ ሲያወርድ ማለት ነው፤ ክፉዎች የእግዚአብሔርን ሕግ ቀንና ማታ አያሰላስሉም (1፥2፤ 119፥55 ይመ)፤ ወይም እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እንዲያስተምራቸው አያደርጉም (16፥7 ይመ)፤ ወይም በሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት አይነጋገሩም (42፥8 ይመ)፤ ስለ እርሱም አያስቡም (63፥6)፣ ተስፋውንም አያሰላስሉም (119፥148 ይመ)። *ክፋትንም አያርቅም፤* ክፉዎች ኀጢአትን አይጠሉም፤ (1) ኀጢአትን መጥላት የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው (ምሳ6፥16፤ ኤር 44፥4፤ ዕን 1፥13) ደግሞም የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት መሠረት ነው (45፥7)፤ (2) ሰዎች ሌሎችን የሚወዱ፣ ለሌሎች የሚያስቡና ድኾችንም የሚረዱ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ሆኖም ከኀጢአት የማይርቁ፣ ከዓለም ክፉ ሐሳብ ጋር የማይተባበሩ፣ ለፍትህ የማይቆረቆሩ ወይም ክፉን የማይጠሉ ከሆነ በእግዚአብሔር ፊት ሊቆሙና መንፈስ ቅዱስንም ሊከተሉ አይችሉም (ከገላ5፥16-24 ጋር ያነጻጽሩ)። "እግዚአብሔርን የሚወዱ ክፋትን ይጥሉ" (97፥10)።

*36፥5-9፤* የእግዚአብሔር ቸርነት፣ ይኸውም ለፍጥረቱ ሁሉ የሚያደርገው በጎነት በዚህ ክፍል ተመልክቶአል (33፥4-5 ይመ)።

36፥5 *ምሕረትህ ... ታማኝነትህም፤* ፍቅርህና ታማኝነትህ ማለት ነው (ይኸውም በ57፥3፤ 61፥7፤ 85፥10፤ 86፥15፤ 89፥14፤ 115፥1፤ 138፥2፤ በምሳ3፥3፤ 14፥22፤ 16፥6፤ 20፥28 ላይ እንደ ተገለጠው ዐይነት ማለት ነው (የ3፥7 ማብ ይመ)። *እስከ ጠፈር ይመጥቃል፤* ፍጥረት ሁሉ በሚኖርበት ስፍራ ሰፍኖ ይገኛል ማለት ነው (57፥10፤ 108፥4 ይመ)።

36፥6 *ጽድቅህ ... ፍርድህም፤* ጽድቅህና ፍርድህ ማለት ነው (ይኸውም በ33፥5፤ 89፥14፤ 97፥2፤ በሆሴ2፥19 ላይ እንደ ተገለጠው ዐይነት ማለት ነው፤ እንዲሁም ኢሳ9፥7፤ 33፥5፤ ኤር 9፥24 ይመ)። *ጽድቅህ፤* የ4፥1 ማብ ይመ። *ታላላቅ ተራሮች ... ጥልቅ፤* ከፍታው እንደተራራ፣ ጥልቀቱም እንደ ባሕር የሆነ ማለት ነው።

36፥7 *ምሕረትህ፤* ቍ5፤ እንዲሁም የ6፥4 ማብ ይመ። *የሰው ልጆች ሁሉ፤* በማንኛውም የኑሮ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ማለት ነው። *በክንፎችህ ጥላ ሥር፤* 17፥8 እና ማብ ይመ።

36፥8 *ይመገባሉ ... ይጠጣሉ፤* ሕይወትን የሚሰጥ ምግብና መጠጥ ማለት ነው። *በቤትህ፤* በዚህ ቦታ ይህ አባባል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ የሚሆን ምግብ ያከማቸበትን ቦታ ነው (24፥2 ይመ)። *ወንዝ፤* እግዚአብሔር ዝናብን ከላይኛው ማንደልዶያ "ከግምጃ ቤቱ" (ከዕቃ ቤቱ) የሚያወርድበት ነው (33፥7፤ ኢዮ38፥8-11፡22፡37፤ ኤር 10፥13 ይመ)፤ ይህ ግልጽ ምስላዊ አነጋገር እግዚአብሔር ከሰማይ የሚፈልቀውን ውሃና በሚፈስበት አቅጣጫ ሁሉ የምድር ወንዞችንና ምንጮችን እየመገበ ሕይወትንና ሰላምን የሚሰጠውን ውሃ የሚቆጣጠር መሆኑን ያሳያል፤ ይህ ውሃ ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለሚወጣው "የሕይወት ውሃ ወንዝ" ምንጭ ምልክት ነው (ራእ22፥1 እንዲሁም ሕዝ47፥1-12 ይመ)። *ከበረከትህም፤* አያሌ የደስታ ምንጭ ከሚያስገኝልን ማለት ነው።

*36፥9፤* በቍ5-9 ያለውን ሐሳብ የሚያጠቃልልና ከፍጻሜው ላይ የሚያደርስ ነው። *የሕይወት ምንጭ፤* ኤር2፥13፤ 17፥13 ይመ። በመጨረሻ እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት ለኀጢአተኞች የሕይወትን ውሃ አዘጋጀ (ዮሐ4፥10፡14)። *በብርሃንህ፤* 27፥1 እና ማብ ይመ። *እናያለን፤* እውን ሆኖ እንመለከታለን፤ እናገኛለን፤ ደስታንም እንመለከታለን ማለት ነው፤ ይኸውም

10ለሚያውቁህ ምሕረትህ፣
ልባቸውም ለቀና ጽድቅህ ዘወትር
አይቋረጥባቸው::
11የትዕቢተኛ እግር በላዬ አይምጣ፤
የክፉውም ሰው እጅ አያሳደኝ::
12ክፉ አድራጊዎች እንዴት እንደ ወደቁና
እንደ ተጋደሙ፣
ቀ·ልቀ·ልም እንደ ተወረወሩና መነሣት
እንደማይችሉ ተመልከት!

## መዝሙር 37[ፊ]

## የጻድቁና የክፉው ዕጣ ፈንታ

የዳዊት መዝሙር

1ዐመፀኞችን በማየት አትሸበር፤
በክፉ አድራጊዎችም አትቅና፤
2እንደ ሣር ፈጥነው ይደርቃሉና፤
እንደ ለምለም ቅጠልም ይጠወልጋሉ::
3*በእግዚአብሔር ታመን*፤ መልካምንም
አድርግ፤
በምድሪቱ ተቀመጥ፤ ዘና ብለህ ተሰማራ::
4*በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ*፤
የልብህንም መሻት ይሰጥሃል::
5*መንገድህን ለእግዚአብሔር ዐደራ ስጥ*፤
በእርሱ ታመን፤ እርሱም ያከናውንልሃል፤
6ጽድቅህን እንደ ብርሃን፣
ያንተን ፍትሕ እንደ ቀትር ፀሓይ
ያበራዋል::
7*በእግዚአብሔር ፊት ጸጥ በል*፤
በትዕግሥትም ተጠባበቀው፤
*መንገዱ በተቃናለት*፣
ክፉትንም በሚሸርብ ሰው ልብህ
አይሸበር::
8ከንዴት ተቈጠብ፤ ቍጣንም ተው፤
ወደ እኵይ ተግባር እንዳይመራህ
አትከፋ::
9ክፉ ሰዎች ይጠፋሉና፤
*እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን*
ምድርን ይወርሳሉ::

36፥10 መዝ7፥10፤ 11፥2፤94፥15፤125፥4 ፤ኤር9፥24፤22፥16፤ 31፥3
36፥11 መዝ71፥4፤ 140፥4
36፥12 መዝ18፥38
37፥1 መዝ73፥3፤ ምሳ3፥31፤23፥17-18፤24፥19
37፥2 ቍ38፤2ነገ 19፥26፤ኢዮ14፥2፤ መዝ90፥6፤92፥7፤102 ፥4፤ኢሳ40፥7፤ያዕ 1፥10
37፥3 ዘዳ30፥20፤ ሕዝ34፥14፤ዮሐ10፥9
37፥4 ኢዮ7፥6፤ 27፥10፤መዝ21፥2፤14 5፥19፤ማቴ6፥33
37፥5 መዝ4፥5
37፥6 ኢዮ11፥17 ፤መዝ18፥24፤103፥17 ፤112፥3
37፥7 ቍ1፤ ዘፀ14፥ 14፤መዝ21፥11፤26፥ 10፤27፥14፤40፥1፤ 119፥150፤130፥5፤ ኢሳ38፥13፤41፥1፤ ኤር 12፥1፤ዕን3፥16፤ ሮሜ8፥25 37፥8 ቍ1፤ኤፌ 4፥31፤ቈላ3፥8
37፥9 ቍ22፤መዝ 25፥13፤31፥22፤101፥8፤118፥10፤ምሳ2፥22፤ኢሳ 25፥9፤26፥8፤40፥ 31፤49፥8:23፤51፥5፤57፥13፤ ማቴ5፥5

[ፊ]ም37 የዚህ መዝሙር እያንዳንዱ ጥቅስ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆሄያት የሚጀምር ሲሆን ጅማሬው ወይም ጅማሬውና መጨረሻው ትርጉም የሚሰጥ ግጥም ነው::

በ16፥10፤ 27፥13፤ 34፥8:12፤49፥9:19፤ 89፥48፤ 90፥15፤ 106፥5 ላይ እንደ ተመለከተው እንዲሁም ("ደስ ይለን ዘንድ") ኢዮ9፥25 ("በጨረፍታ አያይም") 42፥2፤ ማሕ1፥16 ("ጨመርሁ") 3፥13 ("ይለው ዘንድ") 6፥6 ("መልካምን ቢያዩ") 8፥16፤ ኢሳ53፥10፤ ሰቆ3፥1:: *ብርሃን፤* ከመጀመሪያም ሲፈጠር የተትረፈረፈ እንዲ ሆን ነው:: ብርሃን፣ ከሕይወት ጋር ያለውን ትስስር ለማስተዋል 49፥19፤ 56፥13፤ ኢዮ3፥20፤ 33፥30፤ ኢሳ53፥11 ይመ::

*36፥10-11፤* ጸሎት ነው፤ በፍጥረትህ ሁሉ ላይ ያሳየኸው "ፍቅርህ" (ቍ5) እና "ጽድቅህ" (ቍ6) ለሚገዙልህና በቅንነትም በፊት ለሚመላለሱ ሁሉ ግልጽ ሆኖ ይታያል፤ ክፉዎች ግን በእኔ ላይ እንዳይነሱ "እግራቸውንና እጃቸውን" እሰርልኝ ማለት ነው (*ንጉሡ፤* የ33፥16 ማብ ይመ)::

36፥10 *ምሕረትህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ:: *ጽድቅህ፤* የ4፥1 ማብ ይመ::

36፥11 *የትዕቢተኛ፤* የ31፥23 ማብ ይመ::

*36፥12፤* ልበ ሙሉነትን ያመለክታል (የ3፥8 ማብ ይመ):: *መነሣትም እንደማይችሉ፤* ሞት አሸንፎት ሊሆን ይችላል (የ13፥4 ማብ ይመ)::

*መዝሙር 37፤* እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ መሆኑን የሚያስገነዝብ ትምህርት ነው፤ ("የጥበብ መዝሙር" በመባል የሚታወቁ ሌሎች መዝሙሮች እንዳሉ በ34፥8-22፤ 49፤ 112 ላይ ይመ፤ ከዚህ መዝሙር ጋር የጠበቀ ትስስር ያላቸው ሌሎች መዝሙሮችም የሚከተሉት ናቸው፤ መዝ73፤91፤92፥6-9:12-15፤ 111፤119፤127-128፤133፤ በመጽሐፈ ምሳሌ መግቢያ ላይ "የጥ በብ መጻሕፍት" የሚለውን ይመ):: የዚህ መዝሙር ዐቢይ ሐሳብ በመዝሙር 36 ላይ በክፉዎችና በጻድቃን መካከል ተነጻጽሮ ከቀ ረበው ሐሳብ ጋር በብዙ ይዛመዳል:: በመዝሙሩ ላይ ገኖ የምና ገኘው ሐሳብ "ምድሪቱን የሚወርስ" ማን ነው (ቍ9:11:22:29)? የሚለው ነው፤ በሌላ አነጋገር በተስፋዪቱ ምድር የእግዚአብሔ ርን በረከት የሚያገኝ ማን ነው? የሚል ነው:: የተስፋዪቱን ምድር የሚወርሱት ሤራን የሚያውጠነጥኑ (ቍ12)፣ ነገር የሚሸ ርቡ (ቍ7:32)፣ የተበደሩትን የማይከፍሉ (ቍ21)፣ ጥቅምን ለማ ግኘት የሚያደቡና (ቍ14) ከዚህም የተነሣ ነገር ሁሉ የተከና ወነላቸው መስለው የሚታዩ ክፉዎች ናቸውን (ቍ7:16:35)? ወይስ በጌታ የሚታመኑ (ቍ3:5:7:34)፣ ከዚህም የተነሣ ገሮች (ቍ11)፣ ነቀፋ የሌለባቸው (ቍ18:37)፣ ለጋሶች (ቍ21:26)፣ ትክክለኞች (ቍ37)፣ ሰላም ወዳዶች (ቍ37)፣ ከአንደበታቸው የሚወጣው ቃል በልባቸው የሚያሰላስሉትን የእግዚአብሔርን ሕግ የሚያንጸባርቅ ጻድቃን (ቍ30-31)? የክፉዎች ባሕርይ ምን እንደሚመስል ለማየት 10፥2-11፤ 73፥4-12 ይመ:: እንዲሁም የጻድቃን ባሕርይ ምን እንደሚመስል ለማየት መዝ112 ይመ:: የክፉዎች ዘመን አጭር መሆኑን ለማየት መዝ49፤ 73፥18-20 ይመ:: የዚህ መዝሙር ዐቢይ ሐሳብ አድጎ የሚታየው በቍ1-11 ላይ ሲሆን በይበልጥ ደግሞ ቀጥሎ ባሉት ቍጥሮች ላይ የመዝ ሙሩ ዐቢይ ሐሳብ በሰፊው አድጎ ይታያል:: የመዝሙሩ ጠቅላላ ሐሳብ የተቀነበበው የክፉዎች ዘመን አጭር መሆኑን በሚያመለክተው ሐሳ ብና (ቍ1-2) ጌታ ግን ጻድቃንን እስከ መጨረሻው አቅፎና ደግፎ እንደሚይዛቸው በሚያመለክተው ሐሳብ ነው (ቍ39-40)::

*37፥1-2፤* ቍ7፤ መዝ 73 ይመ::

*37፥2፤* የቍ20 ማብ ይመ::

*37፥3፤* 34፥8-14 እና ማብ ይመ::

37፥4 *በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፤* በጌታ ደስ ይበላችሁ ሲባል የጌታን ባጠገባችሁ መሆንና የቃሉንም እውነትና ጽድቅ ባጠገባችሁ መሆን ከልብ ናፍቁ ማለት ነው (ከኢዮ 22፥26፤ 27፥10፤ ከኢሳ58፥14 ጋር ያነጻጽሩ):: በጌታ ደስ ለሚሰኙት፣ እግዚአብሔር የልባቸውን መሻት ይሰጣቸዋል፤ (1) ፍላጎታችንና ጥያቄአችን እንደ ፈቃዱ ከሆነ እግዚአብሔር ከልብ የጠየቅነውን ነገር ሁሉ ይመልስልናል (ዮሐ15፥7 ይመ):: (2) በእግዚአብሔርና በፈቃዱም ደስ የሚለን ከሆነ፣ እግዚአብሔር ራሱ የራሱን ሐሳብ በልባችን ውስጥ ያስቀምጣል (ፊል2፥13 ይመ)::

37፥5 *ዐደራ ስጥ፤* 1ጴጥ5፥7 ይመ::

37፥6 *ጽድቅህን እንደ ብርሃን ... ያበራዋል፤* በኀጢአት ምክንያት በደል የደረሰባቸው ጻድቃን፣ ከዚህ የሚከተሉትን በጎ ነገሮች እንደሚያገኙ ተስፋ ተገብቶላቸዋል፤ (1) ለጸሎታቸው መልስ ያገኛሉ (ቍ4-5)፤ (2) የጽድቅ መንገዳቸው ይባረክላቸዋል (ቍ6) (3) ሰማያዊ ርስትን ያገኛሉ (ቍ9:11:34)፤ (4) የጌታ እርዳታ ዘወትር ከእነርሱ ጋር ይሆናል (ቍ17-19:39)፤ (5) የጌታ ምሪትና ጥበቃም ከእነርሱ ጋር ይሆናል (ቍ23-25:28)፤ (6) ድነትም የእነርሱ ነው (ቍ6)::

37፥7 *በትዕግሥትም ተጠባበቀው፤* ይህ መዝሙር ክፉዎች በመንገዳቸው ሁሉ ኀጢአተኛና ጠማማ ሆነው ሳለ ቢበለጽጉና ነገርም ሁሉ ቢሳካላቸው ጻድቃን ይህንን ሁኔታ እንዴት መመል ከት እንዳለባቸው ማሳሰቢያ ይሰጣል፤ እግዚአብሔር ቅን ፍርዱን እስኪያሳይና ነጻም እስኪያወጣን ድረስ በእምነት መጽናት ይኖርብናል (ከቍ1፥73፤ ከምሳ3፥31፤ 23፥17፤ 24፥1፤ ከኤር12 ጋር ያነጻጽሩ):: በችግርና በሥቃይ ውስጥ ጸንቶ ማለፍ የሚቻ ለው መንፈስ ቅዱስ ሲረዳንና ሲያግዘን ብቻ ነው (ገላ5፥22፤ ሮሜ8፥3-4 ይመ፤ ከኤፌ4፥1-2፤ ከቈላ1፥11፤3፥12 ጋር ያነጻጽሩ)፤ መንፈስ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር ክፉዎችን እንደሚቀጣና ለእኛም ሽልማትን እንደሚያዘጋጅ አስቀድሞ አረጋግጦልናል (ከሮሜ 8፥28፤ ከዕብ12፥1-2:5-13 ጋር ያነጻጽሩ)::

37፥8 *ከንዴት ... ቍጣንም፤* በጻድቃን ላይ እየተረማመዱ ያግበሰበሱት ሀብት ዋስትና እንደሌለው አንዱ ማስረጃ ነው::

37፥9 *ምድርን ይወርሳሉ፤* ከእግዚአብሔር ዋስትና ያለውን የርስት መያዣ (እነርሱና ልጆቻቸው) ይቀበላሉ፤ ይህች ምድር ለእግዚአብሔር ሕዝቦች መኖሪያ ትሆን ዘንድ የተበጀችና የተቤ

10 ለአፍታ እንጂ፣ ክፉ ሰው አይዘልቅም፤
ስፍራውንም ብታስስ አታገኘውም።
11 ገሮች ግን ምድርን ይወርሳሉ፤
በታላቅ ሰላምም ሐሤት ያደርጋሉ።

12 ክፉዎች በጻድቃን ላይ ያሤራሉ፤
ጥርሳቸውንም ያፋጩባቸዋል።
13 እግዚአብሔር ግን ይሥቅባቸዋል፤
ቀናቸው እንደ ደረሰ ያውቃልና።

14 ድኾችንና ችግረኞችን ለመጣል፣
አካሄዳቸው ቀና የሆነውንም ለመግደል፣
ክፉዎች ሰይፋቸውን መዘዙ፤
ቀስታቸውንም ገተሩ።
15 ሰይፋቸው የገዛ ልባቸውን ይወጋል፤
ቀስታቸውም ይሰበራል።

16 የጻድቅ ጥቂት ሀብት፣
ከክፉዎች ብዙ ጥሪት ይበልጣል።
17 የክፉዎች ክንድ ይሰበራልና፤
ጻድቃንን ግን *እግዚአብሔር* ደግፎ
ይይዛቸዋል።

18 *እግዚአብሔር* የንጹሐንን የሕይወት
ዘመን ያውቃል፤
ርስታቸውም ለዘላለም ይኖራል።
19 በክፉ ጊዜ ዐንገት አይደፉም፤
በራብ ዘመንም ይጠግባሉ።
20 ክፉዎች ግን ይጠፋሉ፤
የ*እግዚአብሔር* ጠላቶች እንደ መስክ
ውበት ይሆናሉ፤
ይጠፋሉ፤ እንደ ጢስም ተነው ይጠፋሉ።

21 ኀጢአተኛ ይበደራል፤ መልሶም
አይከፍልም፤
ጻድቅ ግን ይቸራል።
22 *እግዚአብሔር* የባረካቸው ምድርን
ይወርሳሉ፤
እርሱ የሚረግማቸው ግን ይጠፋሉ።

23 የሰው አካሄድ *በእግዚአብሔር* ይጸናል፤
በመንገዱ ደስ ይለዋል።
24 ቢሰናከልም አይወድቅም፤
*እግዚአብሔር* በእጁ ደግፎ ይይዘዋልና።

25 ጐልማሳ ነበርሁ፤ አሁን አርጅቻለሁ፤
ነገር ግን ጻድቅ ሲጣል፣
ዘሩም እንጀራ ሲለምን አላየሁም።

26 ሁልጊዜ ቸር ነው፤ ያበድራልም፤
ልጆቹም የተባረኩ ይሆናሉ።

27 ከክፉ ራቅ፤ መልካሙንም አድርግ፤
ለዘላለምም ትኖራለህ።
28 *እግዚአብሔር* ፍትሕን ይወዳልና፤
ታማኞቹንም አይጥልም፤

ለዘላለምም ይጠብቃቸዋል፤
የኀጢአተኛው ዘር ግን ይጠፋል።
29 ጻድቃን ምድርን ይወርሳሉ፤
በእርሷም ለዘላለም ይኖራሉ።

30 የጻድቅ አፍ ጥበብን ይናገራል፤
አንደበቱም ፍትሓዊ ነገር ያወራል።
31 የአምላኩ ሕግ በልቡ አለ፤
አካሄዱም አይወላገድም።

32 ክፉዎች ጻድቁን ይከታተሉታል፤
ሊገድሉትም ይሻሉ።
33 *እግዚአብሔር* ግን በእጃቸው
አይጥለውም፤
ፍርድ ፊት ሲቀርብም አሳልፎ
አይሰጠውም።
34 *እግዚአብሔርን* ደጅ ጥና፤
መንገዱንም ጠብቅ፤
ምድሪቱን ትወርስ ዘንድ ከፍ ከፍ
ያደርግሃል፤
ክፉዎችም ሲጠፉ ታያለህ።

37፥10 ኢዮ7፥10፤ ሕዝ27፥36
37፥11 ዘሌ26፥6፤ ዘኍ6፥26፤14፥24፤ ማቴ5፥5
37፥12 ኢዮ16፥9፤ መዝ2፥1፤31፥12፤ 35፥16፤112፥10
37፥13 1ሳሙ26፥10፤ሕዝ12፥23
37፥14 መዝ11፥2፤ 22፥20፤35፥10
37፥15 1ሳሙ2፥4፤ መዝ9፥16፤46፥9፤ኤር 49፥35
37፥16 ምሳ15፥16፤ 16፥8
37፥17 ኢዮ38፥15፤ መዝ10፥15፤41፥12፤1 40፥12፤145፥14፤ 146፥7
37፥18 ቍ27:29፤ ኢዮ23፥10፤መዝ 44፥21
37፥20 መዝ34፥21 ፤68፥2፤102፥3፤ኢሳ 51፥6
37፥21 ዘሌ25፥35፤ መዝ112፥5
37፥22 ቍ9፤ኢዮ 5፥3
37፥23 ዘኍ14፥8፤ ኢዮ11፥15፤መዝ 7፥9፤66፥9፤147፥11
37፥24 2ዜና9፥8፤ መዝ 13፥4፤27፥2፤ 38፥17፤41፥12፤55፥2 2፤119፥165፤145፥14 ፤ምሳ3፥23፤10፥9
37፥25 ቍ28፤ዘፍ 51፥1፤መዝ111፥5፤14 5፥15፤ማር10፥46፤ዕብ 13፥5
37፥26 ዘሌ25፥35፤ ዘዳ28፥4፤መዝ112፥2
37፥27 ዘኍ24፥21 ፤መዝ34፥14፤3ዮሐ 1፥11
37፥28 ዘፍ17፥14፤ ዘዳ7፥6፤32፥26፤መዝ 18፥25፤97፥10፤ምሳ2፥22 37፥29 ቍ9፤ምሳ 2፥21፤ኢሳ34፥17
37፥30 መዝ49፥3፤ ምሳ10፥13 37፥31 ዘዳ6፥6፤ 32፥35፤ኢዮ 22፥22 37፥32 መዝ10፥8፤ 11፥5 37፥33 ኢዮ32፥3፤ መዝ 34፥22፤79፥11፤2ጴጥ2፥9 37፥34 ቍ9፤መዝ18፥21፤27፥14፤52፥6

ዦች፣ የተትረፈረፈም ሀብት ምንጭ እንድትሆን የተደረገች ናት። በጌታ ተስፋ የሚያደርጉ ማለትም ሕይወትንና በረከትን የሚሰጥ ጌታ መሆኑን በጽኑ የሚያምኑ የተስፋዪቱን ምድር ይወርሳሉ፤ ከእግዚአብሔር ተለይተውና ክፉ መንገዳቸውንም ተጠቅመው ምድሪቷን ለመውረስና ሀብቷንም ለመብላት ደፋ ቀና የሚሉ ግን አያገኟትም (ቍ11:22:29 ይመ፤ ከያዕ7 ጋር ያነጻጽሩ)።

37፥10 *ለአፍታ፤* በዚህ ቦታ የጊዜው አጭርነት የሚያሳየው ሊመጣ ያለው ሁኔታ አይቀሬ መሆኑን ነው (58፥9፤ ኢዮ 20፥5-11፤ ሐጌ2፥6 ይመ)።

*37፥11፤* ማቴ5፥5 ይመ። *ገሮች፤* በእግዚአብሔር ቸርነትና ጸጋ የሚተማመኑ እንዲሁም ወንድሞቻቸውን ያልገፉ ማለት ነው፤ *በታላቅ ሰላም፤* ያልተቀየጠ በረከት ማለት ነው።

37፥12 *በጻድቃን፤* የ1፥5 ማብ ይመ። *ጥርሳቸውንም ያፋጩባቸዋል፤* 35፥16 እና ማብ ይመ።

37፥13 *እግዚአብሔር ግን ይሥቅባቸዋል፤* 2፥4 ይመ። *ቀናቸው እንደ ደረሰ ያውቃልና፤* በጣም የሚገርመው መዝሙረኛው በቍ22 ላይ ነገሩን በመጠኑ ያወሣው ቢሆንም እግዚአብሔር ክፉዎችን ድምጥማጣቸውን ለማጥፋት ከቶ የማይተኛ መሆኑን በቀጥታ የገለጸበት ሁኔታ የለም፤ የክፉዎች ሕይወት በእርግጥ "የሚጠፋ" መሆኑን በተመለከተ በተደጋጋሚ ተናግሮአል (ቍ9:22:28:34:38፤ ከቍ2:8:10:15:17:20:36:38 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የክፉዎች ሕይወት አጭር እንደ ሆነ ጌታ ያውቃል፤ ለጻድቃን ግን ጥበቃውንና እንክብካቤውን ያበዛላቸዋል። *ቀናቸው፤* በ1ሳሙ26፥10 ላይ እንደ ተገለጸው ሁሉ ይህ አባባል ክፉዎች "የሚጠፉበትን" ዕለት ያመለክታል ("ጊዜው" በቀጥታ ሲተረጐም "ቀኑ" እንደ ማለት ነው)፤ ኢዮ18፥20 ("ዕጣ ፋንታው")።

37፥14 *ድኾችንና ችግረኞችን፤* 34፥6 እና ማብ ይመ።

37፥15 *ልባቸውን ይወጋል፤* 45፥5 ይመ።

37፥16-17 *ጻድቃን፤* የ1፥5 ማብ ይመ።

37፥18 *ንጹሓን፤* ቍ37፤ 15፥2፤ እንዲሁም የ26፥1 ማብ ይመ።

37፥20 *ውበት፤* ሣሩና አበባው ነው (ከቍ2፤ 90፥5-6፤ 102፥11፤ 103፥5-16፤ ከኢዮ14፥2፤ ከኢሳ40፥6-8 ጋር ያነጻጽሩ፤ ያዕ 1፥10-11 ይመ)።

*37፥21፤* "ክፉዎች ይበደሩ ዘንድ ግድ ነው፤ ዕዳቸውን መክፈል ግን አይችሉም፤ ጻድቃን ግን በልግስና መስጠት ይችላሉ" (ዘዳ15፥6፤ 28፥12:44 ይመ)።

*37፥24፤* ምሳ24፥16 ይመ።

*37፥26፤* የቍ21 ማብ ይመ።

37፥28 *ታማኞቹንም፤* የ4፥3 ማብ ይመ።

37፥29 *ለዘላለም፤* ከክፉዎች በተቃራኒው (ቍ28)፣ ጻድቃንና ልጆቻቸው፣ የልጅ ልጆቻቸውም ቃል በተገባላቸው ምድር ለዘላለም እንደሚኖሩ ያመለክታል።

37፥30 *ጥበብን፤* 119፥98:130፤ ዘዳ4፥6 ይመ።

37፥31 *በልቡ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *አይወላገድም፤* ቀና ከሆነው ጎዳና ማለት ነው (17፥5 ይመ)።

37፥32 *ይከታተሉታል፤* 10፥8-9፤ እንዲሁም የ7፥2 ማብ ይመ። *ሊገድሉትም ይሻሉ፤* የሐሰት ክስ በማቅረብ (ቍ33) ሕይወታቸውን ለማጥፋት ይሯሯጣሉ።

[35]ክፉና ጨካኙን ሰው፣
እንደ ሊባኖስ ዝግባ ለምልሞ አየሁት፤
[36]ዳግመኛ በዚያ ሳልፍ፣ እነሆ፣ በቦታው
አልነበረም፤
ብፈልገውም አልተገኘም።

[37]ንጹሐንን ልብ በል፤ ቅኑንም አስተውል፤
የሰላም ሰው ተስፋ አለውና።[ጀ]
[38]ኀጢአተኞች ግን በአንድነት ይጠፋሉ፤
የክፉዎችም ዘር[ገ] ይወገዳል።

[39]የጻድቃን ድነት *ከእግዚአብሔር* ዘንድ
ነው፤
በመከራ ጊዜም መጠጊያቸው እርሱ
ነው።
[40]*እግዚአብሔር* ይረዳቸዋል፤
ይታደጋቸዋልም፤
ከክፉዎች እጅ ነጥቆ ያወጣቸዋል፤
እርሱን መጠጊያ አድርገዋልና
ያድናቸዋል።

## መዝሙር 38

## የጭንቅ ሰዓት ጸሎት

የዳዊት መዝሙር፤ ለመታሰቢያ

[1]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ በቍጣህ አትገሥጸኝ፤
በመዓትህም አትቅጣኝ።
[2]ፍላጻዎችህ ወግተውኛልና፤
እጅህም ተጭናኛለች።
[3]ከቍጣህ የተነሣ ሰውነቴ ጤና አጥቶአል፤
ከኀጢአቴም የተነሣ ዐጥንቶቼ ሰላም
የላቸውም።
[4]በደሌ ውጦኛል፤
እንደ ከባድ ሸክምም ተጭኖኛል።

[5]ከንዝህላልነቴ የተነሣ፣
ቍስሌ ሸተተ፤ መገለም፤
[6]ዐንገቴን ደፋሁ፤ ጕበጥሁም፤
ቀኑንም ሙሉ በትካዜ ተመላለስሁ።
[7]ወገቤ እንደ እሳት ነዶአል፤
ሰውነቴም ጤና የለውም።
[8]እጅግ ዝያለሁ፤ ፈጽሞም ደቅቄአለሁ፤
ከልቤም መታወክ የተነሣ እጮኻለሁ።

[9]ጌታ ሆይ፤ ምኞቴ ሁሉ በፊትህ
ግልጽ ነው፤
ጭንቀቴም ከአንተ የተሰወረ አይደለም።
[10]ልቤ በኀይል ይመታል፤ ጕልበት
ከድቶኛል፤
የዐይኔም ብርሃን ጠፍቶአል።
[11]ከቍስሌ የተነሣ ወዳጆቼም-ባልንጀሮቼም
ሸሹኝ፤
ጎረቤቶቼም ርቀው ቆሙ።
[12]ሕይወቴን ለማጥፋት የሚሹ ወጥመድ
ዘረጉብኝ፤
ሊጐዱኝ የሚፈልጉ ሊያጠፉኝ ዛቱ፤
ቀኑንም ሙሉ ተንኰል ይሸርባሉ።

[13]እኔ ግን እንደማይሰማ ደንቈሮ፣
አፉንም መክፈት እንደማይችል ዲዳ
ሆንሁ።
[14]በእርግጥም ጆሮው እንደማይሰማ፣
አንደበቱም መልስ መስጠት እንደ
ማይችል ሰው ሆንሁ።
[15]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ በተስፋ
እጠብቅሃለሁ፤
ጌታ አምላኬ ሆይ፤ አንተ መልስ
ትሰጠኛለህ።
[16]እኔ፣ "ጠላቶቼ በእኔ ላይ ደስ
አይበላቸው፤
እግሬም ሲንሸራተት፣ በላዬ
አይኵራሩብኝ" ብያለሁና።

37፥35 ኢዮ5፥3
37፥36 ቍ10፤ምሳ 12፥7፤ኢሳ41፥12፤ዳን 11፥9
37፥37 ቍ18፤ዘፍ 6፥9፤መዝ11፥7፤18፥25፤ኢሳ57፥1-2
37፥38 ቍ2:9፤መዝ 1፥1፤73፥19
37፥39 መዝ3፥8፤ 9፥9
37፥40 1ዜና5፥20፤ መዝ2፥12፤18፥48፤ 20፥2፤34፥7
38፥1 መዝ6፥1
38፥2 ኢዮ6፥4
38፥3 ኢዮ33፥19፤ ምሳ3፥8፤ኢሳ4፥22፤ 66፥14
38፥4 ዘኍ11፥14፤ ዕዝ9፥6፤መዝ40፥12 ፤65፥3፤ሉቃ11፥46
38፥5 ቍ11፤ኢዮ 19፥17፤መዝ69፥5፤14 7፥3፤ምሳ5፥23፤12፥2 3፤13፥16፤መክ10፥3
38፥6 መዝ35፥14፤ 57፥6፤145፥14፤146፥8
38፥7 ቍ3፤ኢዮ 14፥22
38፥8 መዝ6፥3:6፤ 22፥1፤34፥18፤ምሳ 5፥11፤17፥22
38፥9 ኢዮ3፥24፤ መዝ119፥20፤143፥7
38፥10 ኢዮ37፥1፤ መዝ6፥7፤19፥8፤31፥ 10፤88፥9
38፥11 ቍ5
38፥12 መዝ31፥4፤ 35፥4:20፤41፥5፤ 140፥5፤141፥9
38፥13 መዝ115፥6 ፤135፥17፤ኢሳ43፥8፤ ማር7፥37
38፥15 መዝ17፥6፤ 27፥14
38፥16 ዘዳ32፥35፤ መዝ22፥17

[ጀ]37 ወይም *ዘር ይወጣለታል* [ገ]38 ወይም *ትውልድ*

*37፥35-36፤* ከቍ25-26 ጋር ያነጻጽሩ።

37፥37 *ንጹሐንን፤* የቍ18 ማብ ይመ።

*37፥37-39፤* አንዱ ተስፋ ያለው ሲሆን፣ ሌላው ተስፋ ቢስ መሆኑን የሚያሳይ ታላቅ ንጽጽር ነው።

37፥39-40 *የጻድቃን ... ይረዳቸዋል፤* ዕጣ ፈንታቸው በክፉዎች እጅ አይደለም፤ *መጠጊያቸው እርሱ ነው፤* ክፉዎች የሚያደርጉትን ቢያደርጉ ጌታ ግን ርስታቸውን ጠብቆ ያቈይላቸዋል።

*መዝሙር 38፤* ዳዊት በሠራው ኀጢአት እግዚአብሔር "ስለ ገሠጸውና" በዚህም ምክንያት ከባድ የሕመም ሥቃይ ስለ ደረሰበት ከዚህ ሁሉ ሥቃይ በፍጥነት ይገላገል ዘንድ ያቀረበው ልመና ነው። ይህ መዝሙር መቼ እንደ ተደረሰና በመዝሙረኛውም ላይ የደረሰው ሕመም ምን ዐይነት እንደ ሆነ በትክክል ለይቶ ማወቅ አይቻልም። የዳዊት ሥቃይ የተባባሰው ወዳጆቹ ሁሉ ጥለውት ስለሸሹና (ቍ11)፣ ይህንንም አጋጣሚ በመጠቀም ጠላቶቹ ሊጥሉት በማሤራቸው ነው (ቍ 12:16:19-20)፤ የመዝ 39-41 መግቢያ ይመ። በጥንቲቱ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ውስጥ ይህ መዝሙር ከሰባቱ የጭንቅ ጊዜ ወይም የችግር ጊዜ መዝሙሮች ውስጥ የሚመደብ ነው (የመዝ6ን መግቢያ ይመ)። እንደ መዝ33 ሁሉ (የመዝ33 አወቃቀር ለመመልከት የመዝሙሩን የመግቢያ ማብ ይመ) የዚህም መዝሙር ርዝመት (22 ቍጥሮች አሉት) የዕብራይስጡን የፊደል ገበታ ቍጥር የተከተለ ነው። መዝሙሩ እያንዳንዳቸው አራት ስንኞች ባሏቸው አምስት አንጓዎች የተዋቀረ ሲሆን፣ እያንዳንዱም አንጓ በሁለት በሁለት ስንኞች የተቋጠረ ነው።

38ርእስ *ልመና፤* ይህ ሐረግ በሌላ ቦታ የሚገኘው በመዝ 70 ርእስ ላይ ብቻ ነው።

*38፥1-4፤* ጌታ ተግሣጹን ያቀልለትና ያነሳለት ዘንድ ያቀረበው ልመና ነው።

38፥1 *አትገሥጸኝ ...አትቅጣኝ፤* (39፥11፤ እንዲሁም የ3፥7 ማብ ይመ)። *በቍጣህ ... በመዓትህም፤* የ2፥5 ማብ ይመ።

38፥2 *ፍላጻዎችህ፤* የእግዚአብሔርን በትር በግልጽ የሚያሳይ ተለዋጭ ዘይቤ ነው (ኢዮ6፥4፤ 34፥6፤ ሰቆ3፥12፤ ሕዝ5፥16 ይመ)። *እጅህም ተጭናኛለች፤* 32፥4 እና የ32፥3-5 ማብ ይመ።

38፥3 *ዐጥንቶቼ፤* የ6፥2 ማብ ይመ።

38፥4 *ሸክምም፤* በደሉ ያደረሰበትን የሥነ ልቡና ውድቀት ብቻ ሳይሆን በቍ5-8 ላይ እንደ ተገለጸው ከባድ ሥቃይ እንደ ተጫነውም ያሳያል።

*38፥5-8፤* ሕመሙ ያስከተለበትን አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ቀውስ ያመለክታል።

38፥8 *ከልቤም፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

*38፥9-12፤* የሕመሙ ሥቃይ (ቍ10)፣ የወዳጆቹ ከእርሱ መራቅና (ቍ11) የጠላቶቹም ክፋት (ቍ12)፣ ክፉኛ የጐዳው መሆኑን በድጋሚ በማስታወቅ አቤቱታውን የሚያቀርብበት ክፍል ነው።

38፥10 *የዐይኔም ብርሃን ጠፍቶአል፤* የ13፥3 ማብ ይመ።

38፥11 *ከቍስሌ፤* ይህ ቃል ለምጽ ያለበትን ሰው ለማመልከት ይውላል፤ ይህ የሚያሳየው የዳዊት ወዳጆች ዳዊትን ለምጽ እንዳለበት ሰው ያገለሉት መሆኑን ነው።

*38፥12፤* የ5፥9 ማብ ይመ።

*38፥13-16፤* ጌታ ለጠላቶቹ መልስ ይስጥ ማለቱ ነው (ቍ15)፤ መስማትና መናገር እንደማይችል ሰው፣ ዳዊት ለጠላቶቹ መልስ መስጠት አቃተው (ቍ13-14)፤ ስለዚህም በእርሱ ስም እግዚአብሔር እንዲናገርለት መጠባበቅ ጀመረ (ቍ15-16)፤ 1ሳሙ 25፥32-39፤ 2ሳሙ16፥10:12 ይመ።

38፥16 *እግሬም ሲንሸራተት ጊዜ፤* በዚህ ቦታ ይህ አባባል የሚያሳየው መዝሙረኛው የደረሰበትን ሕመም ነው (66፥9፤